# አብዱል-ባሃ

---

## የባሃኡላህ የቃል-ኪዳን ማዕከል

ከ ኤች.ኤም. ባልዩዚ (Abdu’l Baha’, Baha‘u’llah king of glory)
ከ ሾጌ-ኤፌንዲ (God passes by)
ከ አናማሪያ ሆኖልድ(Vignettes from the Life of Abdu’l-Baha)
መጽሐፎች የተወሰደ

በኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ የሕትመት ቦርድ
ታተመ::
2014 ዓ.ም

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

ምዕራፍ 1 የአብዱል-ባሃ ማንነት ........................................ 1
ምዕራፍ 2 አባቱ በሕይወት በነበረባቸው ቀናት ..................... 9
ምዕራፍ 3 የባሃኡላህ እርገት ................................................ 49
ምዕራፍ 4 የቃል ኪዳኑ ማዕከል ........................................ 53
ምዕራፍ 5 የለየለት የክህደት አመጽ .................................... 59
ምዕራፍ 6 የምዕራቡ ዓለም ደቀ-መዛሙርት ........................ 63
ምዕራፍ 7 የስቃይ ዓመታት ................................................... 87
ምዕራፍ 8 የአምላክን ቤተ-መቅደስ ማነጽ ........................ 121

## ክፍል ሁለት

ምዕራፍ 9 በአውሮፓና በአሜሪካ የአብዱል-ባሃ ጉዞ.......127

## ክፍል ሦስት

ምዕራፍ 10 ወደ ግብፅ ከዚያም ወደ ቅድስት አገር........155
ምዕራፍ 11 የጦርነቱ ዓመታት.............................................165
ምዕራፍ 12 የአገልግሎቱ የመጨረሻ ዓመታት...................185
ምዕራፍ 13 የአብዱል-ባሃ እልፈት.....................................209

## ክፍል አራት

የአብዱል-ባሃ የሕይወት ገጽታ ............................................243

# ክፍል አንድ

# ወጣትነት፣ እስራት እና ነፃነት

አብዱል ባሃ ከሚለው የኤች.ኤም. ባልዩዚ መጽሐፍ የተወሰደ

## ምዕራፍ 1
## የአብዱል-ባሃ ማንነት

የተትረፈረፈው፣ ሰፊው፣ ወደር የሌለው፣ የሕይወት ታሪክ ይኸውላችሁ፡፡ ተጠቃሎ ሊቀርብም የሚሞከር አይደለም፣ ከግምትም በላይ ነው፣ ምክንያቱም የባሃኡላህ ልጅ እያንዳንዱ ሁነት፣ ዋናውን ታሪክ ያጎላዋል፡፡ ወደ ቴህራን ጨለማ እስር ቤት አባቱን ለማየት ሲሄድ ገና ስምንት ዓመቱ ነበር፣ተወዳጅ አባቱን በሠንሠሎቶቹ ክብደት ጎብጦ አየው፡፡ ከዚያ ለጋ ዕድሜው ጀምሮ እስከ ሰባ ሰባት ዓመቱ፣ ካገለገለ በኋላ፣ አብዱል-ባሃ ሙሉ ለሙሉ ሰውነቱን ንቆ፣ ሳይሰበር እንደፀና፣ ለአምላክ እና ለሰው ተወዳዳሪ የሌለውን አገልግሎት ሰጥቶ፣ ከዚህ ዓለም አለፈ፡፡ በዚህ መስክ ራሱን ከድካም ወይም ከህመም ለማትረፍ አልሞከረም፡፡ ባሃኡላህ "ታላቁ ቅርንጫፍ"፣ "የአምላክ ምስጢር"፣ "ጌታው" (The Master) በማለት ሰይሞታል፡፡ ነገር ግን የስልጣን ካባ በእርሱ ጫንቃ ላይ ሲያርፍ፣ አብዱል-ባሃ፣ የባሃ አገልጋይ በሚል እንዲጠራ መረጠ፡፡

አብዱል-ባሃ፣ በጥልቅ ርህራሄ ካዘነው ጋር አዝኖ ከተሰቃየውም ጋር ተሰቃይቷል፡፡ ሺህዎች እፎይታን ለመሻት በእርሱ በር ደጃፍ ላይ ይጎርፉ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ዓለማዊ ቁሳቁሶችን የሚፈልጉ ሲሆኑ፣ ነገር ግን ብዙዎች

መንፈሳዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ፈላጊዎች ነበሩ። ለሁሉም፣ አብዱል-ባሃ በነፃ አትረፍርፎ ይሰጣቸው ነበር። ለአንዳቸውም የእርሱ በር በፊታቸው ላይ አልተዘጋም። እርሱ ጋር ቀርቦ ባዶ እጁን የተመለሰ የለም። የተጨቆኑት፣ ግራ የተጋቡት እና የወደቁት ወደ እርሱ እስኪመጡ ድረስ ዝም ብሎ አይጠብቅም። እነርሱን ለማገልገል ፍለጋ ይወጣል። ደግሞም የተማሩትና ጥበበኞቹ ከእርሱ የዕውቀት ምንጭ እስኪረኩ ለመጠጣት ወደ እርሱ ይመጣሉ። መሪ ዎችና አገረ-ገዢዎች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ የጦር አዛዦች፣ ኃይል ያላቸውና ታላላቆች ወደ እርሱ በመምጣት የማያዳላ ምክሩንና ልግስናውን አግኝተዋል።

በዚህ መጽሐፍ የአብዱል-ባሃን ሙሉ ገፅታ፣ አጠቃለን እናገኛለን ብለን ካሰብን በእርግጥ ስህተት ነው። እያንዳንዱን እንቅፋት በምልዓት የተሻገረውን የሕይወት ገፅታ ምንም ዓይነት ልኬት ሊገልፀው አይችልም። አንድ አስተዋይ እንዳለው “አብዱል-ባሃ መንፈሳዊ ረቂቅ ሚስጥሮችን (mystic) በተግባራዊ እግሮች እንዲራመዱ ያደረገ ነው” ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል። ዝነኛው የመፅሐፍ ቅዱስ ሊቅ እና ከፍተኛ ሐያሲ፣ ዶክተር ቲ.ኬ.ቺኒ፣ “የሰው ልጅ አምባሳደር” በማለት ገልፆታል።

የካምብሪጅ ኮሌጅ፣ታዋቂው ተመራማሪ ምሑር፣ ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን፣ በ1890 ኤፕሪል ወር ላይ አካን ሲጎበኝ ከአብዱል-ባሃ ጋር ከተገናኘ በኋላ እንዲህ ሲል ፅፎ ነበር:–

> ተክለ ሰውነታቸው ግርምት የሚፈጥሩብኝን ሰዎች የማየው አንዳንዴ ነው። ተክለ-ሰውነቱ ደልደል ብሎ እንደ ቀስት ቀጥ ያለ ነው፣ ነጭ ጥምጥም

የጠመጠመ ሲሆን፣ እስከ ትከሻው የሚደርስ ረዥም ሉጫ ፀጉር አለው፣ ጠንካራነቱን፣ አዋቂነቱንና ሳያወላውል የመተግበር ችሎታን የሚያመለክተው ሰፊና ግርማ የተሞላው ግምባሩ፣ እንደንስር አትኩረው የሚያዩት ዓይኖቹ ጠንካራ ገጽታዎቹ ሲሆኑ፣ ደስ የሚያሰኝ መልክም አለው፡፡ ተወዳዳሪ የለሽ በማ ለት የሚጠሩት አባስ ኤፌንዲን (‘ጌታው’)፣ በእኔ ላይ ያሳደረው የመጀመሪያው ስሜት ይህ ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር በቀጣይነት ካደረግኳቸው ንግግሮች የመጀመሪያው ያነቃቃኝ ሲሆን የእሱን ማንነት ያጠ ነከሩልኝና የእኔንም አክብሮት የሚጨምሩ ነበሩ፡፡ እነዚህ መለያዎቹ፣ ከግርማ ሞገስና ከተጫዋችነት ጋር አንድ ላይ ተደባልቀው፣ አክብሮትና አድናቆት እንዲያድርብኝ አድርገዋል፡፡ ስለዚህ የእርሱን ታላ ቅነትና ኃያልነት ለመመስከር ማንኛውም እርሱን ያየ ሰው ጥርጣሬ አይገባውም፡፡

የአሜሪካ አህጉር የመጀመሪያው ባሃኢ ቶርንቶን ቼዝ፣ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር ፦

ዝናው ዓለምን ሁሉ አዳርሷል፡፡ እዚህ አገር፣ ብዙ ዎች ጎብኝተውታል፡፡ ያለ ልዩነት ሁሉም በምድር ላይ እጅግ ኃያሉን ሰው እንዳዩ ሲናገሩ ሰምተናቸዋል፡፡ የተለያዩ ግምቶችን፣ የማወቅ ፍላጎትንና ተስፋዎችን ይዘው ወደ እርሱ እንደቀረቡ ከዚያም እንደየራሳቸው የተለያዩ ስሜቶች በአግራሞት፣ በአክብሮት፣ በፍቅር እንደተጥለቀለቁ ያወሳሉ፡፡ በእርሱ እግር ሥር በመውደቅ ሌላው

ቀርቶ የተራመደበትን አቧራ እንኳን ለመሳም እንደጓጉ ይናገራሉ……

አይበገሬ ሰዎች በጉንጮቻቸው ላይ እንባ እየጎረፈና ከስሜቶቻቸው የተነሳ ድምፃቸው እየተሰባበረ፣ ስለእዚያ ተራ ስለሚመስለው፣ ቀጠን ብሎ ደልደል ያለና መካከለኛ ቁመት ስላለው ሰው አንጸባራቂነት፣ ሊነገር ስለማይቻለው ጨዋነት፣ ግርማ ሞገስ እና ኃያልነት፣ ተናግረዋል …

ትናንሽ ልጆች እንደሚወዱት፣ በልቦቻቸው ውስጥ ጣፋጭነትን እንደሚያሰርፅባቸው፣ እንዴት ድኾችና ችግረኞች በየእርምጃዎቹ እንደሚከተሉትና ከቁሳዊና ከመንፈሳዊ ስጦታዎቹ እንደሚመገቡ፣ እርሱን ለአጭር ጊዜ በመጎብኘት ሁሉንም ነገሮችና ሁሉንም ፈተናዎች ለመቋቋም እንደሚያስችላቸው፣ ጠላቶቹ በእርሱ የጨዋነት ይቅርታ አድራጊነት ፊት እንዴት እንደቅጠል እንደሚረግፉ፣ አንዲት ነፍስ ወደ እርሱ ቅርበት ደርሳ ሳትለወጥ መውጣት እንደማትችል ሁሉ ነግረውናል፡፡

በእምነቱ ሞግዚት እደ-ሃይማኖት በመባል የተሰየሙት የተከበሩ ባሃኢ ሆራስ ሆሊ፣ አሜሪካን አገር ሌማን ሐይቅ ዳርቻ ኦገስት 1911 አብዱል-ባሃን አግኝተውት ነበር፡፡ የእርሳቸው ምስክርነት ይህ ነው:-

የሚያስከብር ውበቱ፣ አለባበሱና አኳኋኑ የማያጠራጥር ውህደት አላብሰውታል፡፡ ገና ጌታውን ከማየቴ፣ እርሱ እንደሆነ አውቂ ነበር፡፡ ጠቅላላው ሰውነቴ ተንዘፈዘፈ፡፡ ልቤ ዘለለ፣ ጉልበቶቼ ሰነፉ፣ ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ፣ በጣም አጣዳፊ

እርሱን የመቀበል ስሜት ፈሰሰብኝ፡፡ ወደ አንድ እጅግ ስስ ወደ ሆነ የስሜት ህዋስ የተቀየርኩ መሰለኝ፡፡ ለዚህ እጅግ ከፍተኛ ተፅዕኖ ዓይኖቼና ጆሮዎቼ በቂዎች አልመስልህ አሉኝ፡፡ በእያንዳንዱ ማንነቴ የአብዱል-ባሃን መኖር ማወቄን ተረዳሁ፡፡ ከጥልቅ ደስታዬ የተነሳ ስሜቴን የመግለጫው መንገድ  ስለመሰለኝ አልቅስ አልቅስ አለኝ፡፡ የእኔ ማንነት ጠፋ፤ የእኔ ያልሆነ አዲስ ማንነት በቦታው ተተካ፡፡ ከሰው ተፈጥሮ ከፍታዎች በላይ አንድ ዓይነት ክብር በላዬ ላይ ፈሰሰብኝ፣ ይህንን አጅግ የጋለ ስሜት ያለውን ግፊት ለማድነቅ ንቁ ነበርኩ፡፡ በአብዱል-ባሃ ውስጥ የባሃኡላህ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለ ተሰማኝ፡፡ አስተሳሰቤ ወደ ነባራዊው ሁኔታ ሲመለስ፣ ፍፁም መን ፈስና ፍፁም ህላዌ ወደ ሆነ ሰው ቀርቤ እንደነበር መረዳት ቻልኩ ...

በሁለቱ ቀን ጉብኝታችን፣ ጌታውን ለማግኘት ልዩ ዕድል ገጥሞን ነበር፡፡ ከአዋቂነት ወይም ከግብረ-ገባዊ መፍትሄዎች በላይ ወደ አክብሮት ስሜቴ አዘነበልኩ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት አስገራሚ ሰው፣ ከእርሱ አጠገብ በመሆን ለሚገኘው ለዛ፣ እጄን ሰጠሁ ይህ ደግሞ የማይቋረጥ ደስታን አመጣልኝ፡፡ እኔ ሳል ለወጥ እንዳለሁ እቀራለሁ ለሚለው ጉዳይ ፍርሃት አልነበረኝም... አባታዊነቱ፣ ግርማ ሞገሱ፣ ጥንካሬው፣ ወሰን የሌለው ደግነቱ የሆነ ዓይነት ንጉስ ከዙፋኑ ወርዶ ለእርሱ ከተጉት ሰዎች ጋር የሚቀላቀል ዓይነት ይመስላል ...

አብዱል-ባሃ ሰሜን አሜሪካን ሲጎበኝ ሃዋርድ ኮልቢ ኢቬስ በኒው ጀርሲ ከተማ ዩኒታሪያን ቤተ-ክርስቲያን ቄስ ነበር፡፡

አብዱል-ባሃም ኒውዮርክ ሲደርስ ኮልቢ ኢቪስ ባሃኢ ወዳጆቹ የነገሩትን ይህን ብፁዕ ሰው ለማየት ሄደ:-

> በጣም የጓጉትና እርሱን ቶሎ ለማግኘት የተመኙት ወዳጆች ግፊያና ግርግር ከባድ ስለነበር ወደ ውስጥ ለመግባት እጅግ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ፣ የቻልኩት እርሱን በጨልቅታ የማየት ዕድል ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የማስታውሰው በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዝምታ መስፈኑን ነው... በስተመጨረሻ ተጋፍቼ ወደፊት ለመጠጋት ቻልኩ፣ ከዚያም በየሰዉ ትከሻ ላይ ተንጠራርቼ ለመጀመሪያ ጊዜ የአብዱል-ባሃን ገጽታ ለቅፅበት ተመለከትኩ። ቁጭ ብሎ ነበር፣ በራሱ ላይ የሽሮ መልክ ያለው ቆብ አድርጓል፣ ነጭ ፀጉሩ እስከ ትከሻው ወርዶ ይታያል። የለበሰው ካባ፣ ምስራቃዊና ሙሉ ለሙሉ ነጭ ነው፤ ግርም የሚለውና ልረሳው የማልችለው ግን፣ ይህ ነው ለማለት የሚያዳግተኝ ግርማ ሞገሱና የሚ ደንቅ ትህትናው የተደባለቁበት ምስጢር ነው። ጨዋነት፣ ሊያፈልቅ የሚችለውን እንዲህ ዓይነት ፍቅር በፍፁም አይቼ አላውቅም። በዙሪያዬ ያሉት ሰዎች ለዓይኖቻቸው እንዲህ ዓይነት አብርሆት፣ ለልቦቻ ቸው ደስታን፣ የሰጣቸው ይሄ ይሆን? ከአንደበታቸው ለሚወጣው በተደጋጋሚ ለሚጠሩት 'አስገራሚ' የሚለው ቃል ትርጉሙ ይህ ይሆን? ከዚህ በፊት ፈልጌ በማላውቀው መልኩ አሁን ግን የማወቅ ፍላጎት አደረብኝ።

ከወራት በኋላ ኮልቢ ኢቭስ ከአብዱል-ባሃ ጋር ወዳጅነትን መሠረተ:–

> እዚህ አሁን አንድ ሰው አየሁ፣ ከውጪ ሲታይ፣ እንደኔው፣ በዚህ ውጥንቅጥ ዓለም ውስጥ ይኖራል፣ በጥልቀት ግን፣ ያለምንም ጥርጥር፣ በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ለከፍተኛው ዓለም እየኖረና እየሠራ ይገኛል፡፡ ሁሉም ፅንሰ ሐሳቦቹ፣ ሁሉም እሾቶቹ፣ ሁሉም ድርጊቶቹ፣ መነሻቸው 'ከብርሃን ዓለም' ነው፡፡ ለእኔም እጅግ አነቃቂዬና የሚያበረታታኝ እውነታ ይህ ነው፣…

የታወቀው ሃንጋሪያዊ የምስራቅ ሃገራት ተመራማሪ ምሁር፣ አርሚኒየስ ቫምብሪ፣ እ.ኤ.አ በ1913 በቡዳፔስት አብዱል-ባሃን አግኝቶት ነበር፡፡ እንዲህ በማለት ደብዳቤ ጽፎለታል:-

> ይህቺን ትንሽ አቤቱታ በተቀደሰው፣ በብፁኡ፣ የዕውቀት ማዕከል በሆነው፣ በዓለም ሁሉ ታዋቂ እና በሁሉም የሰው ዘር ዘንድ ተወዳጅ በሆነው፣ በአብ ዱል-ባሃ ፊት ሳቀርብ በታላቅ ትህትና ነው፡፡ ለሰው ልጅ መመሪያን ሰጪው የተከበርከው ወዳጄ ሆይ! ህይወቴ ለአንተ ቤዛ ይሁን …
>
> የእርስዎን የክቡርነትዎን አባት(ባሃኡላህን) ከሩቅ ማስተዋል ችያለሁ፡፡ ራስን የመሰዋት ክብርንና ፅናትንም አስተውያለሁ፣ እናም በአድናቆት ተሞልቻለሁ፡፡
>
> ስለክቡርነትዎ መርህና ዓላማዎች፣ አክብሮቴንና ፅናቴን መግለፅ እወዳለሁ፣ እጅግ ከፍተኛው፣ አምላክ፣ ረዥም ዕድሜ ከፈቀደልኝ፣ በሁሉም ሁኔታዎች እርስዎን ለማገልገል ዝግጁ ነኝ፡፡ ይህ እንዲሆን ከልቤ እጸልያለሁ እማፀናለሁ፡፡

በአንድ ወቅት የቦምቤይ አገረ-ገዢ የነበሩት ሎርድ ላሚን ግቶን፣ ለአብዱል-ባሃ እንዲህ ሲሉ ፅፈው ነበር:–

ለሰው ዘር መለኮታዊ መለዮዎች እውቅና በመስጠት በሰላም፣ በመልካም ምኞት፣ ለሌሎች ፍቅርን በማሳየት እንዲኖር ከመፈለግ በላይ እጅግ አስገራሚ ነገር የለም፡፡

በሐይፋ በ1919፣ ከመንገድ ዳር ተቀምጦ ያየሁትን ሰው ደህና አድርጌ አስታውሰዋለሁ፤ ብድግ ብሎ ተነስቶ ሲራመድ እውነተኛ ቅዱስ የተባረከ ተፅዕኖውን በእኔ ላይ አሳረፈ፡፡ በዚያ ጊዜ ነበር ቀለበቱን ከጣቶቹ አውልቆ ለእኔ የሰጠኝ፡፡

## ምዕራፍ 2

## አባቱ በሕይወት በነበረባቸው ቀናት

የባሃኡላህ የመጀመሪያ ልጅ፣ አብዱል-ባሃ፣ሜይ 23 1844 ባብ በሺራዝ ተልዕኮውን በገለፀበት ምሽት እኩለ ሌሊት ላይ በቴህራን ተወለደ። በአያቱ ስም 'አባስ' ተብሎ ተሰየመ፣ ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው፣ ባሃኡላህ ከአረገ በኋላ አብዱል-ባሃ የሚለውን ስም ወሰደ። ሁለት ተስፋ የቆረጡ ሰዎች በናስረዲን ሻህ ላይ አሳዛኝና ያልተሳካ የመግደል ሙከራ በመፈጸማቸው ባሃኡላህ ለእሥራት ሲዳረግ ገና የስምንት ዓመት ልጅ ነበር። ከዚያም ባቢዎች(የባብ ተከታዮች) በጭካኔ ተጨፈጨፉ። የባሃኡላህ ቤት ተዘረፈ፣ መሬቱና ንብረቱ ሁሉ ተወረሱ። ቤተሰቡ ከከፍተኛ ድሎት ወደ ድኽነት ወረደ። አብዱል-ባሃ አውሮፓን እየጎበኘ ሳለ፣ አንድ ቀን፣ እነዚያን የስቃይ አስከፊ ቀናት እንዲህ ሲል ገልጿቸዋል፡–

> ቴህራን ሳለን፣ ሁሉም ነገር ነበረን፣ አንድ ቀን ጠዋት ግን ሌላው ቀርቶ የምንበላው ምግብ እስክናጣ ድረስ ሁሉንም ነገር አጣን። እርቦኝ ነበር፣ ነገር ግን የምበላው ዳቦ እንኳን አልነበረም። እናቴ ጥቂት ዱቄት የእጆቼ መዳፍ ላይ ነሰነሰችልኝ በዳቦ ፋንታ እሱን ላስኩ። ነገር ግን በቂያችን ነበር። መላቀቅ የሚገለፀው በልብ ነፃነት ላይ ነውና።

እንደገናም ሲቀጥል፡–

> በሚጠሉን ሰዎች አደገኛ ውርጅብኝና ጥቃት በደረሰብን ወቅት፣ ዕድሜዬ ገና ዘጠኝ ዓመት ነበር። በቤታችን ላይ ብዙ ድንጋዮች ከመወርወራቸው የተነሳ ከጓሮዋችን ድንጋዩ ተከምሮ ነበር፣ እናቴ

ለደህንነታችን ስትል ወደ ሌላ ሠፈር ወስዳን ቤት ተከራይታ አኖረችን። ነገር ግን በቤት ውስጥ ያለው ምግብ በቂ አልነበረም። አንድ ቀን  እናቴ ወደ አክስቴ ቤት እን ድሄድና ጥቂት ብር እንድጠይቃት አዘዘችኝ። ሄድ ኩኝ አክስቴም የምትችለውን ሁሉ አደረገችልን። ሣንቲሞች በመሃረቧ ጠቅልላ ሰጠችኝ። ወደ ቤት እየሄድኩ ሳለ አንዱ አወቀኝና ‘ባቢ ይኸውላችሁ’ ብሎ ሲጮህ፤ በመንገድ ላይ ያሉት ልጆች አሳደ ዱኝ፣ የአንድ ቤት ጥግ መሸሸጊያ አግኝቼ ተደበቅሁ፤ እስኪመሽ ድረስ በዚያ ቆየሁ። ከዚያም ስወጣ እንደገና ልጆቹ አወቁኝና እየጮሁብኝ የድንጋይ መዓት አዘነቡብኝ። እቤት ስደርስ በጣም ደከመኝ። እናቴ ምን እንደደረሰብኝ ልታውቅ ፈልጋ ነበር፣ እኔ ግን አንዲት ቃል መተንፈስ አልቻልኩም ተዝለፍልፌ ወደቅሁ።

የባሃኡላህ እስራት በዚያ ጨለማና፣ ተባይ በበዛበት የጉድጓድ ወህኒ ውስጥ ለአራት ወራት ዘለቀ። የታሰረው ከሽፍቶችና ከዘራፊዎች ጋር ነበር። እርሱን የሚወዱና የሚያከብሩ ብዙ ባቢዎችም አብረውት ታስረው ነበር። ከእርሱ አጠገብ በመሆናቸውና ስቃዩን በመካፈላቸው እጅግ ደስተኞች ነበሩ። የባቢዎቹ መከራ እጅግ ከባድ ነበር፣ ሞት ወደ እነርሱ ሲመጣ ምንም እንኳ ለማመን በሚከብድ ስቃይ የታጀበ ቢሆንም የፊታቸው ፀዳል እያበራ ነበር። ለመሞት ከእስር ቤቱ ሲወስዷቸው፣ በእርሱ ስላላቸው ፅናት ሽልማት አመስግነው፣ የባሃኡላህን ልብስ ጫፍ ተንበርክከው ይስሙ ነበር።

ባሃኡላህ እራሱ እነዚያን ቀናት፣ የሃይማኖት ታሪክ ጸሐፊ ለነበረው ለናቢል-ኢ-አዛም እንዲህ ሲል ነግሮታል፦

በዚያ ማዕበሉ በተጧጧፈበት የማይረሳ ዓመት በቴህራን በሲያህ-ቻል አብረን የታሰረን የእኛ ቢጤ እስረኞች ነበሩ፡፡ ሁላችንም በአንዲት ክፍል ውስጥ ታጉረን ነበር፣ እግሮቻችን በጣውላ አንድ ላይ ታስረዋል፤ በአንገታችን ዙሪያ ክብደታቸው ከፍተኛ በሆኑ ሠንሠለቶች ተጣምረዋል፡፡ የምንተነፍሰው አየር በመጥፎ ጠረን የተበከለ ሲሆን፣ የተቀመጥን በት ወለል በቆሻሻ የተሸፈነና ተባይ የሚርመሰመስበት ነበር፡፡ ያ በተባይ የተበከለ፣ እንደበረዶ የቀዘ ቀዘ የጉድጓድ እስር ቤት ምንም ዓይነት የፀሐይ ብርሃን የሚገባበት ቀዳዳ አልነበረውም፡፡ አንዳችን ከአንዳችን በምንተያይበት ሁኔታ በሁለት መደዳ ረድፍ ተቀምጠናል፡፡ በእያንዳንዱ ምሽት፣ የተወሰኑ ጥቅሶችን እንድንደግም አስተማርናቸው፡፡ ‘አምላክ አርኪዬ ነው፣ እርሱ በእውነቱ ሁሉንም ያረካል!’ ሲሉ እጅግ በጋለ ስሜት ያዜማሉ፣ አንዱ ረድፍ አዚሞ ሲጨርስ ሌላው ይቀበላል፡፡ የእነዚህ በደስታ የተሞሉት ድምፆች ዜማ እስከ ንጋት ድረስ እየተደጋገመ ይቀጥ ላል፡፡ የገደል ማሚቶው የጉድጓድ እስር ቤቱን አስተጋብቶ፣ ከታሰርንበት እስር ቤት ብዙም ከማይርቀው ቤተ-መንግሥት ነስረዲን ሻህ ጆሮ ይደርሳል፡፡ “ይህ ድምፅ ምንድነው?” ሲል ጠየቀ ናስረዲን ሻህ፣ ‘ባቢዎች የሚያዜሙት መዝሙር ነው’ በማለት መለሱለት፡፡ ምንም እንኳን የእስራቱ ስቃይ እንደቀጠለ ቢሆንም፣ ሻሁ ምንም አልተናገረም፡፡ እስራቱን ለማላላት ሀዘኔታም አላሳየም፡፡

አንድ ቀን አብዱል-ባሃ አባቱን ለማየት በጣም ስለጓጓ፣ ወደ ጉድጓድ እስር ቤቱ ተወሰደ፡፡ ስለዚያ አሳዛኝ ጉብኝት ያለው ይህን ነበር:–

> የእርሱን(የባሃኡላህን) የተባረከ ቅርበት ለማግኘት ከአንድ ከቤታችን ሠራተኛ ጋር አብረው ላኩኝ፡፡ ጠባቂዎቹ ክፍሉን አሳዩን፣ ሠራተኛችን በትከሻዎቹ ላይ ተሸክሞ ወሰደኝ፡፡ ጨለማውን ጥቁር ጉድጓድ ወደ ውስጥ ቁልቁል አየሁ፡፡ በትንሽ ጠባብ መግቢያ ሁለት ደረጃዎችን ወረድን፣ ከዚህ በኋላ ግን ምንም ማየት አይቻልም ነበር፡፡ ድንገት “ወደ እዚህ አታምጣው” የሚል የተባረከውን ውበት ድምፅ ሰማን፣ ከዚያም መለሱኝ፡፡ እስረኞቹ ከጉድጓዱ እስኪወጡ ድረስ፣ ከውጪ ተቀመጥን፡፡ ድንገት የተባረከውን ውበት ከጉድጓድ እስር ቤቱ ውስጥ አውጥተው አመጡት፡፡ ከብዙዎች እስረኞች ጋር በሠንሠለት ተቆራኝቷል፡፡ አቤት ሠንሠለቱ! እጅግ ከባድ ነበር፡፡ እስረኞቹ ሠንሠለቱን ሊያንቀሳቅሱት የሚሞክሩት በከፍተኛ ችግር ነው፡፡ የሚያሳዝንና ልብን የሚሰብር ትዕይንት ነበር፡፡

በመጨረሻ ከእስር መለቀቅ ሲመጣ፣ ግዞት ደግሞ ተከተለ፡፡ ባሃኡላህና ቤተሰቡ ከትውልድ አገራቸው ተባረሩ፡፡ በዝርፊያ ያላቸውን ሁሉ የተቀሙትና የተዘረፉት እሱና ቤተሰቡ በክረምቱ ወራት በበረዶ በተሸፈኑት ተራሮች ከኢራን እንዲጋዙ ተደረገ፡፡ ለዚህ አድካሚ ጉዞ በደንብ ስላል ተዘጋጁ፣ ስቃያቸው እጅግ አስመራሪ ነበር፡፡ የባሃኡላህ ሴት ልጅ ታላቋ ቅዱስ ቅጠል በመባል የተሰየመችው ባሃዬህ ካህኑም ከሰባ ዓመት በኋላ፣ ለአንዲት በባሃኡላህ ሃይማኖት ፅኑ ለነበረችው

እንግሊዛዊት ሌዲ ብሎም ፊልድ፣ የእነዚያን የሩቅ ጊዜያት ትውስታ ነገረቻት። ዓይኖቿ እንባ አቀረሩ። እንዲህም አለቻት፣ "ስለእነዚያ ቀናት የበለጠ ብነግርሽ እጅግ በጣም ታዝኚያለሽ" ። ሌዲ ብሎም ፊልድም እንዲህ አለች "ውድ ካህኑም በሁሉም ሐዘንሽ ውስጥ በልቤ ካንቺ ጋር መሆን እፈልጋለሁ።" ባሃዬህ ካህኑምም ስትመልስ "ሁሉም ሐዘን ነበር፣ ነገር ግን በአምላክ መንገድ የሚሰቃዩት ስቃይ፣ በእውነት ሐዘኑ ደስታ ነው" አለች። አብዱል-ባሃ ገና በለጋ እድሜው የሳንባ በሽታ ተጠቂ ነበር። ከስድሳ ዓመት በኋላ፣ ስለእዚያን ጊዜ ህመሙ በፈረንሳይ ዋና ከተማ በፓሪስ ሲናገር:-

> …ቴህራን ልጅ እያለሁ፣ በሰባት ዓመቴ የሳንባ ምች በሽታ ያዘኝ። የመዳን ተስፋ አልነበረኝም። ከጊዜ በኋላ ለዚህ ጥበቡና ምክንያቱ ግልፅ ሆነ። ማዚንዳራን (የባሃኡላህ ቅድመ አያቶች የትውልድ መንደር) መሄድ ነበረብኝ። ነገር ግን በመታመሜ እዚያው ቴህራን እንድቆይ ተደረገ። የተባረከው ውበት በሚታሰርበት ወቅት እዚያው ነበርኩ። ስለዚህ አብሬ ወደ ኢራቅ እንድጋዝ ተደረገ። ምንም እንኳ እንዳገግም ሐኪሞች ቢረባረቡም፣ ጊዜው ሲደርስ ግን በድንገት ተፈወስኩ።

ተጋዥዎቹ እ.ኤ.አ በ1853 ባግዳድ ደረሱ። የእስራቱ ከባድነትና የጉዞው አድካሚነት በባሃኡላህ ጤንነት መጓደል ላይ የራሳቸውን አሻራ አኑረዋል። የቤተሰቡ አባላት በድካም ዝለዋል። ጠላቶቻቸው በደስታ ፈንጥዘዋል። የተደሰቱት በአንድ ወቅት የሀገሪቱ ራዕይ የነበረው እየጨለመ በመምጣቱ ነበር።

ባሃኡላህ ተልዕኮውንና ግቡን ያውቃል፡፡ በቴህራን የጉድጓድ እስር ቤት ደንገዝገዝ ባለው ብርሐን የፀሐይዋን ድምቀት ንጋት በእርሱ ሰብእና ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ባብ ያበ ሠረው የእርሱ ምፅዓቱ እና ሁሉም የሰው ዘር ቅዱሳን መፃህፍት የተነበዩለት የዓለም አዳኝ መሆኑን በእዚያው እስር ቤት ውስጥ ምልክቱን አይቷል፡፡ ነገር ግን እምነቱን የማወጅ ጊዜው ገና ነበር፡፡ ሆኖም በወቅቱ አብዱል-ባሃ የአባቱን ደረጃ ጠንቅቆ ያውቅ እንደነበር ተነግሮናል፡፡ ለባሃኡላህ ያለው አመለካከት ልጅ ለአባት የሚያሳየው ዓይነት አልነበረም፡፡ ከፍተኛ መሰጠትንና መታዘዝን የሚገልጽ ነበር፡፡ ባብ እንዳስቀመጠው በአምላክ ክስተት ለማመን የመጀመሪያው ሰው የቀጣዩ ግልፀት የውጤት ምንጭ እንደሆነ ተነግሯል፤ ስለዚህም በአባቱ ተልዕኮ በሁለመናው የመጀመሪያው አማኝ በመሆኑ፣ በባብ ለተሰነዘሩት እሴቶች ሁሉ የላቀው ተወካይ እንደሆነና 'የባሃኢነት ተምሳሌ አርአያ እና የእንዳንዱ የባሃኢ እሴት ዳግም መወለድ ነው …'

ልክ ባግዳድ ከደረሱ ከዓመት በኋላ፣ ባሃኡላህ ብቸኝነትን በመሻት ወደ ተራሮች ለመሄድ ወሰነ፡፡

በዚህ መለያየት ምክንያት አብዱል-ባሃ በሐዘን ተቆራመደ፣ ምንም እንኳ ገና በዕድሜ ከአሥር ዓመት ያልበለጠ ቢሆንም፣ ገፅታውና አቋሙ ልበ ሙሉና የተረጋጋ ነበር፡፡ የወጣትነት ትከሻው የበሰሉ ሰዎች እንኳ ወደ ጎን የተውትን ኃላፊነቶች ተሸክሞ ተወጥቷል፡፡ በባብ ፅሑፎች ውስጥ ሊያገኝ የቻለውን ሁሉ በጉጉት አንብቧል፡፡ የትኛውም ትምህርት ቤት አእምሮውን አልቀረፀውም፡፡ ያረቀውና የቀረጸው የባሃኡላህ ፍቅራዊ እንክብካቤ ነው፡፡ በለጋ የወጣትነቱ ዘመኑ፣ "እኔ የተደበቅሁ ነበርሁ እናም

ልታወቅ ወደድሁ፣ ስለዚህ የሚያውቁ ህላዌዎችን ፈጠርሁ" በሚለው በነብዩ ሙሐመድ በተነገረው በአንድ የታወቀ ትውፊት ላይ ግልፅና ብርሐን የሚፈነጥቅ ሐተታ ፅፎ ነበር፡፡ የአብዱል-ባሃ ሐተታ እጅግ ጥልቅ እውቀቱን የሚ ገልጽ ብቻ ሳይሆን፣ ታላቅ የቋንቋ ችሎታውን፣ እንደልብ የማይገኝ ብርቅ የአእምሮ ምጡቅነትንና፣ ከዚህም በላይ ከፍተኛ የመረዳት ችሎታውን አሳይቷል፡፡

አብዱል-ባሃ አብዛኛውን ጊዜ ከተማሩት በዕድሜ አማካይነት ጥበብ ካካበቱትና በተሞክሮ ከፍተኛ የመወዳደር ችሎታ ካላቸው ጋር አብሮ ሲሆን፣ እነሱ በሚያነሷቸው ጭብጦችና አርዕስቶች ላይ ይወያይ ነበር፡፡ የበሰለና አብርኾት ሰጪ በመሆኑ ሲናገር ትሁትና ደስ የሚል ስለነበር፣ የዚህን ወጣት ልጅ ንግግር ሁሉም ያከብሩ ነበር፡፡ አንድ የሚፈራ የባሃኡላህ ተቃዋሚ ሲናገር፣ "እንደ አባስ ኤፌንዲ የመሰለ ልጅ ማሳደጉ በራሱ በቂ ነው" ብሏል፡፡

በኢራቅ ሰሜን ተራሮች ላይ የሚገኝ የሚያስደንቅ የተለየ እሴቶች ያሉት፣ የአንድ ደርቪሽ (ባሕታዊ) ዜና ባግዳድ ደረሰ፡፡ አብዱል ባሃ ይህ የብስራት ዜና የአባቱ እንደሆነ አወቀ፡፡ የባሃኡላህ ታማኝ ወንድም፣ ሚርዛ ሙሳም እንደዚሁ አወቀ፡፡ ባሃኡላህን ለመፈለግና እንዲመለስ ለማሳመን መንገድ ፈለጉ፡፡ በመመለሱም ደስታና ፈንጠዝያ ሆነ፡፡ ባሃኡላህ ለባቢዎች አጥተውት የነበሩትን ራዕይ፣ ተስፋና የመንፈስ ጠንካራነትን ሰጣቸው፡፡ የአብዱል-ባሃ አእምሮ የአባቱ ደረጃ ምን እንደሆነ የበለጠ መረዳት ቻለ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ባሃኡላህ ለልጁ "ሲሩላህ" ማለትም የአምላክ ምስጢር የሚለውን ማዕረግ የሰጠው፡፡ እነዚያ የባሃኡላህን ቅርበት የሚሹቱ በእርሱ ልጅ ላይ

ከፍተኛ ውዳሴና አስገራሚ አድናቆት የሚያሰጠውን ባህርይና መለያዎችን መመልከት ቻሉ፡፡

ጠላቶች እንደገና ተንቀሳቀሱ፡፡ የባሃኡላህ ዝና በርቀትና በስፋት እየተሰራጨ ሲመጣ፣ ለሌላ ጥቃት ኃይላቸውን ማሰባሰብ ጀመሩ፡፡ ድምፃቸው በየትኛውም አቅጣጫ መሰማት ጀመረ፣ ናስረዲን ሻህም ጉዳዩ አሳሳቢ ሆነበት፡፡ ለኢራኑ አምባሳደር ተማፅንዎ ምላሽ ለመስጠት ሲል፣ የኦቶማን መንግሥት ባሃኡላህን ወደ ቱርክ ቁስጥንጢኒያ እንዲጋዝ ወሰነ፡፡ ከመሄዱ በፊት አስቀድሞ፣ ባሃኡላህ በኋላ ላይ በባሃኢዎች የሪዝቫን የአትክልት ስፍራ በመባል ወደሚያውቁት ከባግዳድ ከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው የናጂብ ፓሻ የአትክልት ስፍራ ለአሥራሁለት ቀን ቆየ፡፡ በዚያ ደረጃውንና ተልዕኮውን ገለፀ፡፡

ሜይ 3 ቀን 1863፣ ወደ ኦቶማን ግዛት ዋና ከተማ ቁስጥንጥኒያ ረዥሙን ጉዟቸውን ተያያዙት፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት እንደነበሩት ጥቂት ብቸኛ ተጓዦች ሳይሆን፣ አሁን ግን የእውነት ገነታቸው የባሃኡላህ ቅርበት በሆኑ ቁጥራቸው በበዛ ፅኑ አማኞች ታጅበው ነበር፡፡ የድል አድራጊነት ጉዞም ሆነ፡፡ በደረሱበት ቦታ ሁሉ ባሃኡላህ መኳንንቶች በክብር ይቀበሉት ጀመር፡፡ በዚያን ጊዜ አብዱል-ባሃ ቅድስና የተመላው፣ ንቁ፣ እምነቱን ለማገልገል ቀናኢና ለጋስ የሆነ የአሥራ ዘጠኝ ዓመት መልከ-መልካም ወጣት ነበር፡፡ ለሌሎች የዚህን ረዥም ጉዞ ድካም ለማቅለል በከፍተኛ ሁኔታ ይጥር ነበር፡፡ የተጓዥዎቹን ምቾት ለማረጋገጥ፣ ከሚጥሩት መካከል አንዱ ነበር፡፡ ሥንቃቸው አስተማማኝ ካልሆነ፣ ሌሊቱን ሙሉ ምግብ በመፈለግ ያሳልፋ ነበር፡፡ ተጓዦቹን ለቀጣዩ ቀን ጉዞ ለማዘጋጀት፣ ንጋት ላይ ቀድሞ ይነሳል፡፡ ከዚያም

ቀኑን ሙሉ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ለመታዘዝ፣ ከአባቱ ጎን ይሆናል፡፡ ኦገስት 16 1863፣ የኦቶማን መንግሥት ዋና ከተማ ቁስጥንጥኒያ ደረሱ፡፡

በቁስጥንጥኒያ ባሃኡላህን ምንም ዓይነት ውለታ አልፈለገም፣ ችሮታም አልጠየቀም፡፡ ባለስልጣናቱንና የዋና ከተማዋ ታዋቂ ሰዎች እንዲጎበኙት ላቀረቡትም ጥያቄ መልስ አልሰጠም፡፡ በተረጋጋ መንፈስ የኦቶማን ገዢውን ውሳኔ መጠበቁን ቀጠለ፡፡ ከአራት ወራት በኋላም፣ ሱልጣን አብዱል-አዚዝ ባሃኡላህንና ቤተሰቡን ወደ አድሪያኖፕል እንዲጋዙ ትእዛዝ አወጣ፡፡ በባሃኡላህ ላይ የተላለፈውን የሱልጣኑን ትዕዛዝ ይዞ የመጣውን ሰው የተቀበሉት አብዱል-ባሃና አጎቱ ሚርዛ ሙሳ ነበሩ፡፡

የባሃኡላህ ሦስተኛው ግዞት አሁንም በክረምት ወራት ነበር፡፡ ተጋዥዎቹ ለአስቸጋሪው ለክረምቱ መንገድ ብቁ ዝግጅት አልነበራቸውም፡፡

ሱልጣን አብዱል-አዚዝን አስመልክቶ ባሃኡላህ ሲፅፍ :- “ምንም ዓይነት ውርደት ሊስተካከለው በማይችል ሁኔታ ከከተማው በውርደት አባረውናል፡፡ ቤተሰቤም ሆነ ከእኔ ጋር ያሉት፣ ከዚያ የበረዶ አየር ንብረት ቅዝቃዜ የሚከላከልላቸው አስፈላጊ ልብስ እንኳ አልነበራቸውም… ተቃዋሚዎቻችንን ጨምሮ አርቆ ማስተዋል የሚችል ሰው ሁሉ ስለእኛ አዝነው አልቅሰዋል፡፡”

አብዱል-ባሃ ከቀናተኞችና ከእምነተ-ቢሶች አባቱን እንደ ጋሻ ሆኖ መከላከሉን ጀምሯል፡፡ የባሃኡላህ ሐዘን ግን ገና አልተደመደመም፡፡ በእራሱ በአባቱ ልጅ፣ የመጨረሻ የመሰሪነት ድርጊት ከፍተኛ አደጋ ደርሶበት ነበር፡፡

ባሃኡላህ አድሪያኖፕል ሳለም በዓለም ላይ ላሉ የሉዓላዊ ሀገር መሪዎች ምፅዓቱን አወጀ፡፡ ‘እጅግ ታላቁ ብዕር’ ማስጠንቀቂያና ምክርም ሰጠ፡፡ ሱቢህ-ኢ-አዛል (የዘለዓለም ጠዋት) የሚል ስያሜ ያዘለው፣ ያባቱ ልጅ ሚርዛ ያህያ፣ የባሃኡላህን ስልጣን በገሃድ ተቃውሞ የኋላ ኋላ በራሱ ላይ ጥፋትን ያስከተለውም እዚሁ ነበር፡፡

የሚርዛ ያህያ እና የግብረ አበሮቹ ተንኮል ባሃኡላህን ለአራተኛውና ለመጨረሻው ግዞት ዳረጉት፡፡

የሱልጣን አብዱል-አዚዝ ንጉሣዊ ትዕዛዝ በቆጵሮስ ደሴቶች የሚገኘው ቦታ ደግሞ የሚርዛ ያህያ የግዞት አካባቢ እንዲሆን ወሰነ፡፡ የኦቶማን መሪ ውሳኔ ዋነኛውን የክህደት ተዋናይ የሆነውንም ሰው እንኳ ያገለለ አልነበረም፡፡

ያለ ማስጠንቀቂያ፣ በዚያ አሰጨናቂ የበጋ ወር አንድ ቀን ጠዋት፣ ወታደሮች፣ ባሃኡላህ የሚኖርበትን፣ የኢዛት አቃን ቤት ወረሩት፣ ተከታዮቹ ተከበቡ፣ በከተማው ውስጥ ያሉት ሁሉ ለቀው እንዲሄዱ ተነገራቸው፡፡ ከእነርሱ መካከል አንዱ፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ጠንካራና ፅኑ አማኝ የነበረ አቃ ሪዳ፣ እንዲህ ሲል በፅሑፍ አስቀምጦታል:– ‘አብዛኞቹ ንብረቶቻችን በሐራጅ መሸጥ ከሚ ገባቸው ዋጋ በታች በግማሽ ተሸጡ፡፡ በከተማው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤም ተከስቶ ነበር፡፡ የአውሮፓ ሀገሮች ቆንስላዎች ለባሃኡላህ ድጋፍ ለመስጠት ጠየቁ ነገር ግን ድጋፋቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ፡፡ ባሃኡላህ እራሱ ለአሊ ፓሻ በላከው ፅላት እንዲህ ሲል ጠቅሶት ነበር :–

> የአምላክ ተወዳጆችና የእርሱ ልጆች ያለ ምንም ምግብ በመጀመሪያው ሌሊት ለቀው እንዲወጡ ሆነ …ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ለእኛ አለቀሱ፤ የክርስቲያን ህዝቦች ለቅሶ ግን ከሌሎቹ ሁሉ ለቅሶ ሁሉ የበለጠ ነበር።

ባሃኡላህ ከአድሪያኖፐል ወደ ጋሊፖሊ በነበረው ጉዞ ላይ በገለጸው ፅላት የኩራተኛው ሱልጣን ግዛት በጠላቶቹ እንደሚቀማ ተንብዮ ነበር፡-

> የምስጢራዊው ምድር (አድሪያኖፐል) ቀን እየቀረበ ነው፣ በአጠገቡ ያለው ነገር ሁሉ ይለወጣል፣ ከንጉሡም እጆች ወደ ሌላ ይተላለፋል፣ ነውጥ ይታያል፣ የሐዘን ድምፅም ይሰማሉ፣ በሁሉም በኩል የክህደት ማስረጃዎች ይገለፃሉ፣ የጭቆና ሠራዊት እጆች በእነዚህ ምርኮኞች ባደረሱት ምክንያት ግራመጋባት ይናኛል። የነገሮች አቅጣጫ ይቀየራል፣ ሁኔታዎችም ወደ ከፍተኛ ሐዘን ደረጃ ይደርሳሉ፣ የምድረ-በዳ ኮረብታዎች አሸዋዎች ያቃስታሉ፣ በተራሮች ላይ ያሉት ዛፎች ያነባሉ፣ ከሁሉም ነገሮች ውስጥ ደም ይፈሳል፣ ከዚያም ህዝቦች በሐዘንና በጭንቀት ውስጥ ሆነው ትመለከታቸዋላችሁ።

ከዚያም በኋላ፣ ለዋናው አገረ-ገዢ ከአካ በፃፈው ሁለተኛው ደብዳቤው :–

> በቅርቡ በእርሱ ቁጣ ንዴት ይይዝሃል፣ በመካከልህ ብጥብጥ ይነሳል፣ ግዛትህም ይፋለሳል፣ ከዚያም

ታዝናለህ ታለቅሳለህ፣ እናም የሚረዳህና የሚደግፍህ ማንም አይኖርም፡፡

በጋሊፖሊ፣ ግዞተኞቹን ከዚያ ከተማ ለማዛወር አንድ ባለሥልጣን ተመድቦ ነበር፣ ባሃኡላህን ተሰናብቶ ሲሄድ፡– ‘ይህ ግዛት ከንጉሡ እጅ እንደሚወጣና፣ ጉዳዮቹ ሁሉ ወደ ግራመጋባት እንደሚገቡ ለንጉሡ ንገረው’፣ ብሎት ነበር፡፡

በእነዚህ ዓመታት ነበር እጅግ ታላቁ ቅርንጫፍ አብዱልባሃ፣ ወደር የሌለው መሆኑንና ወደ ሙሉ አቋም አንፀባራቂነት መድረሱን ያስመሰከረው፡፡ ባሃኡላህና ቤተ ሰቡ የእስልምና መሪዎች መቀመጫ ከሆነችው፣ ቁስጥንጥንያ እንዲወጡና በአውሮፓ አህጉር ጥግ ወደ ምትገኘው የቱርክ ግዛት እንዲሄዱ ሲታዘዙ ገና አሥራዘጠኝ ዓመቱ ነበር፡፡ አሁን ሃያ አራት ሞልቶታል፣ በአባቱ ተከ ታዮች አጀብ መካከል ብቻ ሳይሆን በሌላውም በከፍተኛ ሁኔታ ተከባሪነትንና ተሰሚነትን አግኝቷል፡፡

የአድሪያኖፐል፣ ገዢ የሆነው ክሁርሺድ ፓሻ፣ በአብዱል-ባሃ ላይ ያስተዋለው የተለየ ሰብዕና፣ የሚያሳየውን ክብርና አድናቆት እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ነው፡፡ ክሁርሺድ ፓሻ ከባሃኡላህና ከልጁ ጋር በጣም ከመጎዳኘቱ የተነሳ፣ የሱልጣኑ ትዕዛዝ ሲመጣበት፣ ይዘቱን ለባሃኡላህ በአካል ለመንገር አልፈቀደም ነበር፡፡ ይህን አሳዛኝ ጉዳይ የበታቾቹ እንዲሠሩለት ይወክል ነበር፡፡ ሌላው የታወቀው የኦቶማን ባለሥልጣን፣ አዚዝ ፓሻ የጠቅላይ ገዢነት ማዕረግ ሲሾም፣ ለባሃኡላህ ያለውን አክብሮት ለመግለፅና ከአብዱል-ባሃ ጋር ለመነጋገር ሁለት ጊዜ ወደ እነሱ ሄዷል፡፡

ባሃኡላህ ጠቀሜታው ችላ ሊባል የማይቻለውን ፅላት የገለፀው በአድሪያኖፕል ነበር። ፅላቱም በምስራቅ ፋርስ ጠቅላይ ግዛት ለክሁራሳን ባሃኢዎች የተጻፈ ሲሆን ሱሪ-ኢ-ግሁስን (የቅርንጫፉ ጽላት) ይባላል። በባቢ ግልፀት ዘመን የባሃኡላህ ትንቢቶች በግልፅ ተግባራዊ ሆነው ስለተፈፀሙበት የተገለፀ ፅላት ነበር።

በሱሪይ-ኢ-ግሁስን፣ ባሃኡላህ የእርሱን የመጀመሪያ ልጅ አብዱል-ባሃን እንዲህ ሲል አወድሶታል ፡–

"ከሳድራቱል ሙንተሃ ይህየተቀደሰና የተከበረ ህላዌ፣ ይህ የቅድስና ቅርንጫፍ፣ አቆጥቁጦ ወጥቷል፣ እርሱ መጠጊያውን የፈለገና በእርሱ ጥላ ስር የተጠለለ እርሱ የበጀው ነው። እውነት እውነት እላችኋለሁ የአምላክ ህግ እጅና እግር፣ አምላክ በእርሱ ፈቃድ መሬት ላይ በጥብቅ ቅርፅ አበጅቶ ቅርንጫፉም ጠቅላላውን ፍጥረት በማቀፍ ከፍ እንዲል፣ ያቆጠቆጠው ከዚህ ስር ነው። ስለዚህ፣ ለዚህ ታላቅ፣ ለዚህ ለተባረከ፣ ለዚህ እጅግ ከፍ ለተደረገው የእጁ ሥራ፣ …ስሙ የገነነ ይሁን፤ ከእጅግ ታላቁ ፅላት እንደ ፈለቀ እንደፀጋ ስጦታችን፣ አንድ ቃል አምላክ በእራሱ ማንነት ጌጥ ያስጌጠው ቃል፣ በምድር ላይ እና በውስጧም ባሉት ላይ ሁሉ ሉዓላዊ እንዲሆን፣ በህዝቦች መካከልም የእርሱ ታላቅነትና ኃይል ምልክት ይሆን ዘንድ አስችሎታል …ህዝብ ሆይ፣ ስለመከሰቱ፣ ለአምላክ ምስጋና አቅርቡ፤ በእውነት እርሱ ለእናንተ የተሰጠ ታላቅ ውለታ ነው፣ ለእናንተ የተቸረ እጅግ ፍፁም ፀጋ ነው፤ በእርሱም አማካኝነት እያንዳንዱ የተልፈሰፈሰ አጥንት ተቀስቅሷል። ወደ እርሱ ፊቱን የመለሰ

> ሁሉ ወደ አምላክ ፊቱን መልሷል፣ እናም ከእርሱ ፊቱን ያዞረ ሁሉ እርሱ ከእኔ ውበት ፊቱን አዙሯል፣ ማስረ ጃዎቼን ክዷል፣ ከእኔም ተላልፏል። እርሱ በእናንተ መካከል የአምላክ ዋስትና ነው፣ በእናንተ ላይ ኃላፊ ነው፣ ለእናንተ የእርሱ ክስተት እና በውለታ በተ ቸራቸው አገልጋዮቹ መካከል የእርሱ መታየት ነው፣ ... የሰውነት መቅደስ ቅርፅ አልብሰን ወደ እናንተ አውርደንላችኋል። እርሱ የፈቀደውን ሁሉ ማንኛውንም ነገር በማይናወጠውና በማይሳሳተው ትዕዛዝ የፈጠረው አምላክ የተባረከ ይሁን። እነዚያ ከቅርንጫፉ ጠለላ ራሳቸውን የነፈጉት፣ በስህተት ዱር ውስጥ እየባዘኑ፣ በዓለማዊ ፍላጎቶች እሳት ውስጥ እየነደዱ ያሉት፣ ያለጥርጥር እነዚያ የሚ ጠፉት ናቸው።

ያለምንም ጥርጥር የእርሱን ተወዳጅ ልጅ ደረጃውን ከፍ ያደረገበት የባሃኡላህ ጽሑፍ፣ በእነዚህ እጅግ ቀስቃሽ ቃላት ተገልፀዋል። የእርሱ ልጅ የባሃኢዎች ዋና ትኩረት መሆን እንዳለበት ባሃኡላህ በትዕዛዙ በአትኩሮትና በስሜት ገልጿል። ከዚህ ታላቅ ቅርንጫፍ ፊቱን ላዞረው እርግማኑ ማንንም የማይምር ነው።

በኦገስት 21 1868፣ የኦስትሪያን መርከብ ከጋሊፖሊ ተነስታ ወደ አሌክዛንደሪያ ግብፅ አመራች። በውስጧ ባሃኡላህ፣ ቤተሰቡና ቁጥራቸው ወደ ሰባ የሚጠጉ የእርሱ ተከታዮች ነበሩባት። መርከቧ በአሌክዛንደሪያ ወደብ በኩል አልፋ፣ ፖርት ሰዒድና ጃፋን ላይ የአጭር ጊዜ ቆይታ ካደረገች በኋላ ወደ እስራኤል ሐይፋ አመራች፣ እዚያም ግዞተኞቹን አራገፈች። ከዚያም፣ ግዞተኞቹ ወደ አካ ለመጓዝ፣ ጀልባ መሣፈር ነበረባቸው፣ በእርግጥ ከባድ

ነበር፡፡ ባሃኡላህ የአካን መሬት ሲረግጥ የ1868 ኦገስት የመጨረሻው ቀን ነበር፡፡

የእስር ከተማው የተወናበዱ ነዋሪዎች በብዛት ሆነው ይጠባበቃሉ፡፡ 'የፋርሶች እግዚአብሔር' ተብሎ የተነገራ ቸውን በጨሉቅታ ለማየት አሰፍስፈዋል፡፡ በእውር መሪዎቻቸው የተወናበዱት፣ ምክንያት የለሽ መንጋ የከተማው ነዋሪዎች ለማፌዝ ከባህሩ ዳር ቆመዋል፡፡

ባሃኡላህ ሲፅፍ "በዚህ ቦታ ላይ ስንደርስ፣ 'እጅግ ታላቁ ወህኒ ቤት' በማለት ሰይመነዋል፡፡ ምንም እንኳ ከዚህ በፊት በሌላው መሬት (ቴህራን) ከዚህ ቀደም ለሠንሠለት ቁራኛ ብንዳረግም፣ ነገር ግን በዚህ ስም ልንጠራው አልፈቀድንም ነበር፡፡ "በሉ እናንተ በመረዳት የታደላችሁ፣ እዚህ ላይ አሰላስሉ!"

ይህ እንግዲህ ባሃኡላህና የእርሱ ተከታዮች የተመደቡበት የጀብደኞችና የህገ-ወጦች እስርቤት ነው፡፡ አካ በረጅም ታሪኳ ከአንድ ጊዜ በላይ ዝናን የተጎናፀፈች ነበረች፡፡ ለእጅግ ታላላቅ ቅኝ ገዢዎች ሳታጎበድድ ኖራለች፡፡ ከዚህም የተነሳ የእስራዔል ነቢያት እንዲሁም የአረቡ ነቢይ ከሌሎቹ ከተሞችና አውራ ከተሞች በተለየ ስለ አብረቅራቂነቷና ስለአንፀባራቂነቷ አወድሰዋታል፡፡ ሆሴዕ 'አካ የተስፋ በር' ሲል ጠርቷታል፡፡ ህዝቅዔል 'ወደ ምሥራቅ የምትመለከተው በር' ፣ 'የእስራዔል የአምላክ ክብር ከምሥራቅ በኩል የሚመጣበት' በማለት ጠርቷታል፡፡ ነብዩ ሙሐመድ :– 'አካን የጎበኘ ሰው እርሱ የተ ባረከ ነው፣ የአካን ጎብኚንም የጎበኘ እርሱ የተባረከ ነው፤ ...አካ ውስጥ አንድ ወር መቆየት በሌላ ቦታ አንድ ሺህ ዓመት ከመቆየት የላቀ ነው፡፡' ብለዋል፡፡

ነገር ግን በወቅቱ በአካ ለብቻው እንዲኖር ለተተወ ሰው፣ መከራው ዘርፈ ብዙ ነው። አየሩ የሚተነፍግ ፣ ውሃው የማይጠጣ ቆሻሻ ፣ ጎዳናዎቹና ሠፈሮቹ እጅግ የቆሻሹና የተበላሹ ናቸው። ነዋሪው ህዝብ በድንቁርና የተጋረደ፤ በጭለማ የተዋጠ፣ አታላይና አጭበርባሪ ነው። ወደር የሌላቸው የአካ ክብሮች ጠፍተዋል። ሆኖም ግን የአምላክ ክብር ወደ እዚህ መጥቷል።

ባሃኡላህ ለቱርክ ዋናው ገዢ በፃፈው ሁለተኛው ደብዳቤ የመጀመሪያው ሌሊት ሁሉም ከምግብና ከመጠጥ ተከልክለው እንደነበረና፤ ሌላው ቀርቶ ውኃም እንኳን ተከልክለው እንደነበር ጠቅሷል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ መጥፎ ጠረን ያለው የአካ አየርና የቅጥር ምሽጉ ያልተሟላ የመፀዳጃ አገልግሎት ጉዳቱን አከፋት። ከሁለት ሰው በስተቀር ሁሉም ግዞተኞች ታመሙ። ወባ፣ ተቅማጥና ታይፎይድ ወረራቸው። ሦስት ሰዎችም ሞቱ። አብዱል-ባሃ በሽተኞችን ይንከባከባል፣ ለአባቱ ከለላ ይሰጣል፣ የአካ ነዋሪዎችን ሽሙጥና የንዴት ግልምጫን፣ ርህራሄ ከሌላቸው የእስር ቤቱ ጠባቂዎች፣ ጨካኝ የወህኒው ዘበኞች እና በጥላቻ ከተሞሉት ሹማምንት ጋር ይጋፈጣል። በፍፁም አይወላውልም፣ ጥበቃው ለአፍታ አይላላም፣ ከዓመታት በኋላ ሚርዛ ሃይዳር-ዓሊ የተባሉ ጽኑ ምዕመን በግለ-ታሪካቸው ጸሐፍ ውስጥ እንዳጋሩን፣ ባሃኡላህ የእርሱን ልጅ ጥረትና ትጋት ሲያስታውስ እንዲህ ብሎ ነበር ይሉናል:-

> ወዳጆች እና የምናውቃቸው ሰዎች፣ እንግዶችና ስለእምነቱ ጠያቂዎችን ለማግኘት፣ በባግዳድ እኛ ራሳችን ወደ ሻይ ቤቶች እንሄድና መቀመጫ ይዘን

እንቀመጣለን፡፡ እነዚያ ርቀው የነበሩትን ወደ እምነቱ አቀረብናቸው፣ ብዙ ነፍሶችን ወደ እምነቱ መራና ቸው፡፡ ስለዚህም የአምላክን እምነት አገለገልን፣ የእርሱን ቃላቶች ለድል አበቃን፣ እናም ታላቁን ስሙንም ከፍ አደረግን፡፡ እጅግ ታላቁ ቅርንጫፍም (አብዱል-ባሃ) በአድሪያኖፕል፣ በተሻለ ሁኔታ፣ ተመሳሳይ ተግባር ያከናውን ነበር፡፡ በአካ ግን፣ እጅግ በላቀ ስፋት፣ ጥልቀትና ቅልጥፍና ኃላፊነቱን ይወጣ ጀመር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት፣ እኛ ላይ የሚወድቁ መከራዎችና ችግሮች ይደርሱበት ነበር፡፡ በባግዳድ እስረኞች አልነበርንም፣..በዚያን ጊዜ የተቃዋሚዎች፣ ባላጋራዎችና ክፉ ተመኚዎች ቁጥር ከዛ ሬው ጋር ሲነፃፀር እጅግ ሲበዛ አነስተኛ ነበር፡፡ በሚስጥራዊው ምድር (አድሪያኖፕል) ላይ ከአንዳንዶች ጋር እንገናኛለን ፣ ወደ እኛ ቅርበት እንዲመጡ እንፈቅድላቸዋለን፡፡ ነገር ግን በእጅግ ታላቁ እስር ቤት (አካ) ከእኛ እምነት ውስጥ ካልሆኑት ውጪ ማንንም አንገናኝም፡፡ የማህበራዊ መስተ ጋብር በሮች ሁሉ ተዘጉብን፡፡ እያንዳንዱን ችግር የሚወስደው ወደ ጌታው (አብዱል ባሃ) ነበር፡፡ ለእኛ ሲል፣ ኑሯችን እንዲቀልና ምቾት እንዲኖረን፣ ዓለምንንና ህዝቦቿን ተጋፍጧል፡፡ ለእኛ እርሱ ታላቅ ምሽግ፣ ኃይለኛ ጋሻ ሆኗል፡፡ በመጀመሪያ በማዝራይ [ከአካ ከተማ ወጣ ያለ ቦታ] ሰፊ ግቢ ያለው ቤት ተከራየ፡፡ በዚያም ለጥቂት ጊዜ ኖርን፡፡ ከዚያም የባህጂን እልፍኝና የተንጣለለ ግቢ ያለው ቤት ለእኛ ገዛ፡፡ እምነቱን ለማገልገል በሙሉ ኃይሉ ተነሳ፣ ጥረቱንም የማስተማመኛ ዘውድ አክሊል ደፋለት፡፡ ይህ ሥራ ቀኑንና ሌሊቱን ይወስድበታል

በመሆኑም በባህጂ መኖሪያችን ለሣምንታት እንዳይገኝ አድርጎ ታል፡፡

መራር የሆነው የአካ ምሽግ እስር ቤት ሕይወት የታሳሪዎቹን ጥንካሬ በእጅጉ የፈተነ ነበር፡፡ ዘበኞቹ ሲበዛ ጨካኞች፣ ንፉጎችና ክፉዎች ነበሩ፡፡

ስቃይ ከአፍ እስከገደፉ ሞልቶ ነበር፡፡ ነገር ግን እጅግ ስሜታቸውን የጎዳው የአብዱል-ባሃ ወንድም፣ በቅፅል ስሙ ንፁሁ ቅርንጫፍ የሚባለው፣ የሚርዛ ምሂዲ አሟሟት ነበር፡፡ ከሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜ ያልበለጠና አባቱን እንደ ፀሐፊ ሆኖ ሲያገለግል ነበር፡፡ አንድ ምሽት፣ በማሰላሰል ተውጦ በጣሪያ ላይ ሲዘዋወር፣ በቀዳዳ ሾልኮ ወደታች ወደቀ፡፡ ምንም እንኳ አወዳደቁ፣ ከፍተኛ የውስጥ ጉዳት ቢያደርስበትም፣ ወዲያውኑ ሊገድለው አልቻለም ነበር፡፡ አባቱን የእርሱ ሕይወት ጌታቸውን ለመገናኘት ወደዚህ ታላቁ የእስር ቦታ ለመምጣት ላልቻሉት ባሃኢዎች እንደ ቤዛ እንዲቀበልለት ለመነው፡፡ የዚህን የዓለም ስቃይዎች በከባድ ሁኔታ የተሸከመው አባቱ ምኞቱንና ፍላጎቱን ተቀበለው፡፡ በጁን 23 1870 ንፁሁ ቅርንጫፍ አረፈ፡፡ ከዚያም በአራት ወራት ጊዜያት ውስጥ፣ የምሽግ ቤቱ እስር አበቃ፡፡

ባሃኡላህ የእስረኛ ማጎሪያ ወደሆነችው አካ ሲላክ ተከታዮቹ የእርሱን ዕጣ ፈንታና ስለግዞቱ ቦታ የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡ …ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የእስር መቅጫ ከተማ በሆነችው በአካ ታስሮ እንደሚገኝ ለባሃኢዎቹ ዜናው ደረሳቸው፡፡ በወቅቱ የባሃኢዎቹ አንገብጋቢ እሾት፣ በየትም ቦታ ቢኖሩ፣ ወደ ባሃኡላህ ቅርበት መገናኘት ነበር፡፡ ነገር ግን ተቃዋሚዎች በጥንቃቄ ይከታተሏቸ ዋል፣ ወደ አካ ለሚሄድ ርቀቱም አዳጋች

ነበር፡፡ የሚደ ርሰው አደጋም ይህ ነው አይባልም፡፡ እንቅፋቶቹ ሊታለፉ የማይቻሉ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጀግኖች ተራራዎቹንና በረ ሃዎቹን አቋርጠው አካ መግባት ችለዋል፡፡ የአሥራ ሰባት ዓመቱ ባዲ አንዱ ነበር፡፡ የባሃኡላህን ፅላት ለናሲሪድ-ዲን ሻህ የሚያደርስ ለመሆን በቅቷል፡፡ በድል አድራጊነትም ሰማዕት ሆኗል፡፡ ባሃኡላህ ባዲን "እርሱ ልዩ የሆነው፣ አቻ የማይገኝለት" ሲል ሰይሞታል፡፡

ወደ እስር ከተማው፣ ከዚያም ወደ ምሽግ እስር ቤቱ የገቡት ጥቂቶች ናቸው፡፡ ሌሎቹ በከተማ ዙሪያ በተቆፈረው ጉድባ እንዲወሰኑ የተገደዱ፣ በሩቁ የባሃኡላህን ንጉሣዊ ግርማ፣ ከእስር ቤቱ ፍርግርግ ብረት ጀርባ ወደ እነርሱ አቅጣጫ የሚውለበለበውን እጁን አይተው በመመለስ ብቻ በቂያቸው አድርገው ወስደዋል፡፡ ነገር ግን ያቺ አንድ የጨልቅታ ምልክታ ተስፋቸውን አለምልማ ልቦቻቸውንም በደስታ አጥለቅልቃለች፡፡

ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በኋላ፣ አብዱል-ባሃ ከእነዚያ ለመጎብኘት ከመጡትና ታግደው ከቀሩት ውስጥ በዕድሜ የገፋውን በኢራን ይኖር የነበረውን ግንበኛ ሰውዬ ስሜት ቀስቃሽ ታሪክ እንዲህ በማለት ይተርከዋል :-

> ከከተማው ወጣ ብሎ ከሚገኘው ዋሻ መኖሪያውን አበጀ፣ ጥቂት ርካሽ የሆኑ ቀለበቶችን፣ የመስፊያ ዕቃዎችንና እስፒሎችን የሚሸጥበት ዝርግ ገበታ ሠራ፡፡ እነዚህን ዕቃዎች ይዞ ከማለዳ እስከ ቀትር በየመንገዶቹ ይዘዋወራል፡፡ የጆሮ ጉትቻዎቹ ከሃያ እስከ ሠላሳ የመዳብ ሣንቲም ያወጡለታል፡፡ በጣም ጥሩ ሽጠ ከተባለ እስከ አርባ የመዳብ ሣንቲም ይሸጣል፡፡ ከዚያም አነስተኛ የሆነ ምግብ ከተመገበ

> በኋላ የጌታውን ስም ለማሞገስና ለማጉላት ወደ ዋሻ ቤቱ ይሄዳል፡፡ ሁልጊዜም አመስጋኝ ነው፡፡ እንዲህ በማለትም ይፀልያል:- ለዚህ ታላቅ ፀጋ በመብቃቴ አምላክ ይመስገን፡፡ ወዳጆቼን ትቼ፣ በዚህ ዋሻ ውስጥ መኖሪያዬን አግኝቻለሁ፡፡ በመለኮታዊ ፊት ገፅታዬን አስውቤያለሁ፡፡ ከዚህ በላይ ታላቅ ቡራኬ የት አለ?

በ1870 በኦቶማን ግዛቶች ውስጥ ብጥብጦች በመብዛታቸው የቱርክ ወታደሮች አስፈላጊነት አስገዳጅ ነበር፡፡ ስለሆነም የአካ ምሽግ እስር ቤትም ለወታደራዊ ዓላማ ተፈላጊ ሆነ፡፡ ባሃኡላህና ተከታዮቹ ከእስር ቤቱ እንዲወጡ ተደረገ፡፡ ነገር ግን ከእስር አልተፈቱም፡፡ በከተማው ቅጥር ውስጥ መኖር ነበረባቸው፡፡ በቀጣዮቹ ወራት፣ ባሃኡላህና የእርሱ ቤተሰቦች ማሊክ የሚባለው ሰው ቤት ከዚያም ደግሞ ክሃዋም ቤት፣ ከዚያም ራቢይህ ቤት፣ በመጨረሻም፣ በጣም ጠባብ ወደሆነው ወደ ኡዲ ካማር ቤት እየተዘዋወሩ ኖሩ፡፡ ኡዲ ካማር ቤት አጠገብ ያለውን የአቡድ ቤት አጠቃለው በመያዝ ለረጅም ጊዜ ኖሩ፡፡ እዚህ ቤት እያሉም የአብዱል-ባሃ ጋብቻ ተከናወነ፡-

## የአብዱል-ባሃ ጋብቻ

በኤች.ኤም. ባልዩዚ ከተጻፈው "Baha'u'llah king of glory" ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ

> "የኢስፋሃን አገረ ገዥ ማኑቺህር ካሃን ፣ የከተማው ኢማም የሆነውን ሚር ሲኢይድ ሙሐመድን ባብን ተቀብሎ እንዲያስተናግደው ይጠይቀዋል፡፡ ኢማሙም የንብረቶቹ አስተዳደሪ የሆነውን ሚርዛ ኢብራሂምን ባብን እንዲያስተናግድ ያደርገዋል፡፡ ሚርዛ ኢብራሂም፣ የባብ ተከታይ የሆነ ሙሐመድ-

ዓሊ-ናህሪ የሚባል ወንድም ነበረው፡፡ አንድ ምሽት ብዙ ሰዎች ከባብ ጋር እራት እንዲበሉ ተጋበዙ፣ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ ከእንግዶቹ አንዱ ነበር፡፡ ባብም ልጆች እንዳሉት ጠየቀው ፣ እሱም ሁለት ጊዜ ቢያገ ባም ልጅ ሳይኖረው እንደቀረ ይናገራል ፣ ባብም ለሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ ከሚበላው ጣፋጭ ምግብ ላይ በማንኪያ ሰጠው ፣ እሱም ጥቂት በልቶ ቀሪ ውን ለሚስቱ አስቀመጠ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ሚስቱ ልጅ ጸነሰች፡፡

ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ፣ ኢስፋሃን ውስጥ ካሉ ሃያ አምስት ባቢዎች ጋር ወደ ኩራሳን ተጓዙ፣ በየቦታው ያሉ ሌሎች ብዙ የባቢ ተከታዮች እንዲሁ ተጓዙ፣ ከዚያም በአንድነት ለመማከር ኩራሳን ውስጥ ባለ በባድሽት መንደር ውስጥ ተሰባሰቡ፡፡ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ ከመሄዱ በፊት ባለቤቱን፣ ሴት ልጅ ከወለደች ፋጢሚ እንድትላት ነገራት፡፡ ሴት ልጅም ተወለደች ስሟም ፋጢሚ ሆነ፡፡ ይህች የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ የመጀመሪያ ልጅ፣ የባሃኡላህ የበኩር ልጅ የታላቁ ቅርንጫፍ ሚስት ለመሆን በቃች፡፡

እንደተለመደው፣ ታላቁ ቅርንጫፍ ማንን ሊያገባ እንደሚችል መላምት ነበር፡፡ ባሃኡላህ አንድ ቀን ያየውን ሕልም ሰይድ ሚህዲይ ለተባለ ባሃኢ እንደነገረው ተዘግቧል፡፡ ስለ ሕልሙ ሲናገርም “ከታላቁ ቅርንጫፍ ጋር ትዳር እንድትመሰርት የጠየቅነውን የወንድማችንን የሚርዛ ሐሰን ልጅ መልከ-መልካም ፊት አየን፡፡ ሆኖም ግን ቀስ በቀስ መልኳ እየጨለመ መጣና ጠፋ፡፡ ከዛም ፊቷና ልቧ

ብሩህ የሆነች ሌላ ልጅ ታየችን፤እኛም እሷን ለታላቁ ቅርንጫፍ ሚስት መረጥናት::”

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በኢስፋሃን ውስጥ፣ የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ ልጅ ፋጢማ ከአጎቷ ልጅ ጋር ተጋባች። ፋጢማ ግን በዚህ ጋብቻ አልተስማማ ችም ነበር። በሚገርም ሁኔታ በሠርጋቸው ምሽት ሙራው ከሙሽሪት እና ከዘመዶቹ ተለይቶ ሄደ ብዙም ሳይቆይ ወጣቱ በድንገት ሞተ። ከዚያም በኋላ የሰማዕታት ንጉሥ ለተባለው ለፋጢማ ሌላ አጎት ባሃኡላህ ጽላት ላከ። እንዲህም አለው “ ከእኛ ጋር እንደተዛመድክ አድርገን ቆጥረንሃል”። ይህም ከዘመዶቹ አንዱ ወደ ባሃኡላህ ልመና ልኳል ብሎ እንዲጠራጠር አደረገው:: ዘመዶችንም ጠየቆ ማንም ልመና እንዳላደረገ አረጋገጠ:: እሱም ለማንም አንድ ቃል እንዳይተነፍሱ ነገራቸው ፣ ይህ የተባረከ ጽላት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ተጠባበቀ። የባሃኡላህ መልዕክት አድራሽ ሸይኽ ሰልማን ወደ ኢስፋሃን እስኪመጣ ድረስ ጥቂት ወራት አለፉ። ሲመጣም እንዲህ አለ “ድንቅ የሆነ ብስራት አምጥቼልሃለሁ። የአጎትህን የሚች ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ-ናህሪ ሴት ልጅን መካ ከሐጅ ተጓዦች ጋር በማድረግ ወደ ቅድስት ምድር አካ እንድወስድ ተልእኮ ተሰጥቶኛል። የሐጅ ተጓዦች በመሄዱበት ጊዜ ወደ ሺራዝ ከዛም ቡሺህር ለመጓዝ እንድንችል ዝግጅት ማድረግ አለብህ። ይህ ዝግጅት ማንም ሳይሰማ በፀጥታ መከ ናወን አለበት፣ ከመሄዳችን ጥቂት ቀናት በፊት ስለ ጉዞአችን ማንም ማወቅ የለበትም” አለው። ጊዜው ሲደርስ ፋጢማ እና ወንድሟ ከሸይኽ ሰልማን እና ከአንድ አገልጋያቸው ጋር

በመሆን ወደ ሺራዝ ተጓዙ። ሺራዝ እንደደረሱም በመጀመሪያ በካራቫን ሴራይ (ሆስቴል) ውስጥ ቆዩ። ከዚያም የባብ ዘመድ የሆነ ሰው መጣና የባብ አጎት ሐጂ ሚርዛ ሰይድ ሙሐመድ ቤት ወሰዳቸው። ይህ የሆነው እ.ኤ.አ. 1872 ነበር።

በማግስቱ ደግሞ የባብ ሚስት ከዲጃህ-ባጉም ፋጢሚን ሰማዕት ወደሆነው ሌላኛው የባብ አጎት ቤት ወሰዳቻት። ያንን ሁኔታ ራሷ ፋጢሚ በአጭሩ የሕይወት ታሪኳ ውስጥ ጽፈዋለች፡-

ሰማዕት የሆነው የባብ አጎት ሚስት እሷ ሁል ጊዜ በአምልኮ የተጠመደች ታላቅ የሆነች እመቤት ነበረች፣ ሆኖም ግን ይህን አስደናቂ እምነት አልተቀበለችም ነበር። እሷ እንዲህ ትል ነበር "ይህ የእኛ ሚርዛ ዓሊ ሙሐመድ በዚህ ዓለም ውስጥ ምን ዓይነት ሁከት ፈጠረ!ስንት ደም ፈሰሰ!" በጽሞና እንዲህ አልኳት " ውድ እመቤቴ፣ ይህ የነብዩ መሐመድ ዘር የሆነው የእናንተ ሚርዛ ዓሊ መሐመድ (ባብ) በቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ ቃል የተገባለት ቃኢም (መልዕክተኛ) ነው። በእያንዳንዱ ጊዜ እና በእያንዳንዱ ዘመን የእግዚአብሔር ጥሪ በተስተጋባበት ወቅት፣ በዚህ ዓለም ውስጥ ተመሳሳይ ሁከት ይከሰታል፣ የሰማዕትነት የደም ጅረትም ይፈሳል" አልኳት።... ከቁርዓንና ከማቲናቪ በማንበብ ብዙ ጊዜ አሳልፍን። ... ከሺራዝ ከሄድን በኋላ እምነቱን ተቀበለች።

ፋጢሚ ሺራዝ በመቆየት ከባብ ሚስት ጋር በመገና ኘቷ በጣም ተደስታለች። ግን ብዙም ሳይቆዩ፣ ጉዞዎ ቸውን የሚቀጥሉበት ጊዜ መጣ። በወቅቱ በተፈጠረ

ችግር ምክንያት፣ አካ ያሉ ወዳጆች እንደገና ቅጣት ተጥሎባቸው የነበረ ሲሆን፣ ወደ አካ ከተማም ማንም መግባት አይችልም ነበር። ነገር ግን ሸይኽ ሰልማን የባሃኡላህ ፍላጎት ስለሆነ ወደ አካ የሚገቡበት መንገድ እንደሚያገኙ እርግጠኛ ነበር። በጅዳህ በኩል ስለ ሆነ የሄዱት እዚያ ሲደርሱ ከባሃኡላህ ጸሐፊ ከሚርዛ አቃ ጃን ደብዳቤ ይጠብቃቸው ነበር። ከመካ የሚመለሱት መንፈሳዊ ተጓዦች ወደአገራቸው እስኪመለሱ ድረስ በዚያ ባህር ዳራቻ ከተማ ውስጥ እንዲቆዩና ከዚያም ወደ አሌክ ዛንድርያ እንዲሄዱና ከቅድስት አገር የሚላክ ቴሌግራም እንዲጠብቁ አዘዛቸው። በአሌክዛንድርያ ከእነሱ ጋር አሥራ ሰባት ባሃኢዎችም ነበሩ።

በመጨረሻ ከባሃኡላህ ቴሌግራም መጣ። ከአራት ሰዎች በስተቀር ሁሉም እንዲበታተኑ አዘዘ። ፋጢሚ፣ ወንድሟ፣ ሸይኽ ሰልማን እና አገልጋያቸው ብቻ አነስተኛ መርከብ ተሳፍረው ወደ አካሄዱ። እዚያም አብዱል አሃድ የተባለ ሰው እንዲቀ በላቸው ተደረገ። ሆኖም ግን መርከቧ አካ ስትደረስ አብዱል አሃድ ሊገኝ አልቻለም። ከመርከቧ ላይ ሁሉም ተሳፋሪዎች ወረዱ፣ ቀኑም እየመሸ መጣ፣ ከመርከብ መውረጃው መተላለፊያም ተነሳ። ሸይኽ ሰልማን ከመርከብ ላይ ሆኖ ጮቅ ብሎ መጣራት ጀመረ፣ መጨረሻ ላይ አብዱል አሃድ መጣ መተላለፊያው ተዘረጋላቸው እነሱም ከመርከብ ላይ ወረዱ።

ፋጢሚ እንደጻፈችው ከመርከብ ወርደው ወደ ወደቡ ሲሄዱ በጣም ጨለማ ነበር፣ እዚያም

የባሃኡላህ ወንድም አቃ-ቃሊም እና ኢሊያስ አቡድን አገኙ። ሆኖም ግን በኋላ ታላቋ ቅድስት ቅጠል እንደነገረቻት አብዱል-ባሃ፣ ባሃኡላህ እዚያ እንዲሄድ ነግሮት ስለነበር ወደቡ ጋር ነበር ፋጢሚ ግን አላየችውም። ከዚያም አቃ-ካሊም እሱና ቤተሰቡ ወዳረፉበት ወሰዳቸው። በሚቀጥለው ቀን የባሃኡላህ ቤተሰብ አባላት አዲስ የመጡትን እንግዶች ወደ እርሱ ፊት ለመውሰድ ጠሯቸው።

ፋጢሚ ባሃኡላህ ፊት ስትቀርብ የነበረውን ሁኔታ ስትጽፍ፣ የመጀመሪያ ቃሉ "የእስር ቤት ከተማ በሮች ማንም እንዳይገባ በተዘጉበት ጊዜ ወደ እስር ቤቱ ከተማ አመጣናችሁ፣ በዚህም የአምላክን ኃያልነት ለሁሉም ግልፅና የተረጋገጠ ለማድረግ ነው" አለ። ፋጢሚ በአቃ-ካሊም ቤት ለአምስት ወራት ኖረች። በየጊዜውም ባሃኡላህ ዘንድ ትሄድ ነበር፣ አቃ-ቃሊምም ባሃኡላህ ጋር በሄደ ቁጥር ከእርሱ ዘንድ ስጦታ ያመጣላት ነበር። ስለዚህ ስትጽፍ:-

አንድ ቀን አቃ-ካሊም እንዲህ አለኝ "ከተባረከው ውበት (ባሃኡላህ) ድንቅ ስጦታ አምጥቼልሻለሁ። አዲስ ስም ሰጥቶሻል ሙኒሪህ (አንጸባራቂዋ) ብሎሻል። ይህን ስትሰማ፣ የተባረከው ውበት ለአቃ ሰይድ ሚህዲ የተናገረውንና እኛም የሰማነውን ሕልም ወዲያውኑ አስታወስኩ። ሕልሙም:- "ከታላቁ ቅርንጫፍ ጋር ትዳር እንድትመሰርት የጠየቅነውን የወንድማችንን የሚርዛ ሐሰን ልጅ መልከ-መልካም ፊት አየን። ሆኖም ግን ቀስ በቀስ መልኳ እየጨለመ መጣና ጠፋ። ከዚያም ፊቷ

አንጸባራቂ እና ልቧ ብሩህ የሆነች ሌላ ልጅ ታየችን፤ እኛም እሷን ለታላቁ ቅርንጫፍ ሚስት መረጥናት።” ቤት ባለመኖሩ በአቃ-ካሊም ቤት ውስጥ እኖር ነበር፣ ለባሃኡላህ ቤተሰብ ቤቱን አከራይቶ የነበረው ሃጂ አቡድ ምክንያቱን በጠየቀ ቁጥር አጥጋቢ መልስ አያገኝም ነበር፣ በኋላም የቦታ እጥረት መሆኑን እራሱ ተገነዘበ። ወዲያውኑ የባሃኡላህ ቤተሰብ አባላት ከሚኖሩበት አጠገብ ያለውን አንድ ክፍል ከፍቶ ካገናኘው በኋላ በሚያምር ሁኔታ አስጌጠው።

ሃጂ አቡድም ለባሃኡላህ “ይህን ክፍል ለአብዱል-ባሃ አዘጋጅቻለሁ” አለ። ባሃኡላህም ተቀበለው። ለእጅግ ታላቁ ቅርንጫፍ ሠርግ እንቅፋቱ ተወገደ። የባሃኡላህ ልጅ ታላቋ ቅዱስ ቅጠል፣ ለሙኒራህ ካኑም (ፋጢሚ) የምትለብሰው ነጭ ልብስ ሰጠቻት። ፀሐይ ከጠለቀች ከሦስት ሰዓታት በኋላ ባሃኡላህ ፊት ቀረበች። ሙኒራህ ካኑም ስትጽፍ፣ ታላቁ አንደበት (ባሃኡላህ) እንዲህ አለ፡-

ቅጠሌ እና አገልጋይት ሆይ፣ እኛ በእርግጥ እጅግ ታላቁን ቅርንጫፌን ታገለግይ ዘንድ ተቀብለን መርጠንሻል፣ ይህ የምድር እና የሰማይ ሀብቶች ሁሉ የማይስተካከሉት ጸጋዬ ነው። በባግዳድ፣ በኤድሪያንና በዚህ እጅግ ታላቅ እስር ቤት ያሉ ሴት አገልጋዮች፣ ይህንን ጸጋ ተስፋ አድርገው ነበር ሆኖም ግን ለእነሱ አልተሰጠም። ለዚህ ታላቅ ጸጋ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብሽ፣ ይህ የተሰጠሽ ከፍ ያለ ስጦታ ነው። አምላክ ከአንቺ ጋር ይሁን።

ባሃኡላህና ተከታዮቹ ልባቸው በተመረዘውና፣ አእምሯቸው በከንቱ ጥላቻ በተሸፈነው፣ የከተማው ሰዎች መካከል ራሳቸውን አገኙ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን ታጋሽነት የሚሰጥ እምነት ብቻ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር ትክክለኛው የአብዱል-ባሃ ማንነት ግልፅ እየሆነ መምጣት የጀመረው፡፡

በአካ አንድ ክርስቲያን ነጋዴ፣ ባሃኢዎችን በንቀት ያያቸው ነበር፡፡ ባሃኢዎች ከአካ ውጪ ከሰል እንዲገዙ ይፈቀድላቸው ነበር፡፡ ነጋዴው፣ ከሰሉ ጥሩ ዓይነት ጥራት ያለው መሆኑን ሲያውቅ፣ ነጥቆ ይወስድባቸዋል፡፡ ለእርሱ ባሃኢዎች እዚህ ግቡ የሚባሉ ሰዎች አይደሉም፣ ስለዚህ የእነርሱን ሸቀጥ መውረስ እንደመብቱ ይቆጥረዋል፡፡ ሁኔታውን አብዱል-ባሃ ሲሰማ፣ የወሰደውን ከሰል እንዲመልስ ወደ ነጋዴው ይሄዳል፡፡ ሱቁም ውስጥ ብዙ ሰዎችም ነበሩ፣ ሁሉም በየንግዳቸው ላይ አቀርቅረዋል፣ አብዱል-ባሃን አላስተዋሉትም፡፡ ቁጭ ብሎ ጠበቀ፡፡ ነጋዴው ወደ እርሱ አስኪዞር ድረስ ሦስት ሰዓት አለፈ፣ ከዚያም :– 'በዚህ ከተማ ከሚገኙት እስረኞች አንዱ አይደለህምን?' ሲል ጠየቀው፣ አብዱል-ባሃም አዎ አለ፣ በመቀጠል ነጋዴው ጠየቀ፡- 'የታሰርክበት ወንጀል ምን ነበር አለው?' አብዱል-ባሃም ሲመልስ፡- 'ክርስቶስ ተወንጅሎበት በነበረው ተመሳሳይ ወንጀል' አለ፡፡ ነጋዴው ደነገጠ፡፡ ክርስቲያን ስለሆነ የእርሱ ተግባርና የክርስቶስ ተግባር ተመሳሳይ እንደሆነ የሚናገር ሰው ገጠመው፡፡ 'ስለ ክርስቶስ ምን ታውቃለህ?' በማለት በንዴት መለሰ፡፡ አብዱል-ባሃ በእርጋታ ያናግረው ጀመር፡፡ የነጋዴው እብሪት በአብዱል-ባሃ ትዕግስት ከሰመ፡፡ አብዱል-ባሃ

ለመሄድ ሲነሣ፣ አክብሮት በማሳየት ነጋዴው ተነስቶ እስከ መንገድ ድረስ ሸኘው፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ፣ ከወዳጅነትም በላይ የእምነቱ ጥብቅ ደጋፊ ሆነ፡፡

በአካ ሼይክ ማሐሙድ የሚባል ባሃኢዎችን አጥብቆ የሚጠላ ሰው ይኖር ነበር፡፡ ምንም እንኳ የእርሱ ከተማ ሰዎች ቀስ በቀስ እንዴት በጣም ተሳስተው እንደነበር እያደር እየተረዱ መጥተው እስረኞቹን እያወደሱና እያመሰገኑ ቢሆንም፣ ሼክ ማሐሙድ ግን ከጥላቻው ንቅንቅ አላለም፡፡ አንድ የሆነ ቀን ሰዎች አብዱል-ባሃ እንዴት ዓይነት ጥሩና ቁምነገረኛ ሰው እንደሆነ በሚነጋገሩበት ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ ሼይሁ ሊቋቋመው ስላልቻለ፣ ከስብሰባው በንዴት ተነስቶ፣ አባስ ኤፌንዲ (አብዱል-ባሃ) እንዴት ዓይነት ሰው እንደሆነ አሳያችኋለሁ ብሎ ጥሎ ሄደ፡፡ በጦፈ ንዴት ተሞልቶ፣ አብዱል-ባሃ በዚያን ሰዓት የት እንደሚገኝ ስለሚያውቅ፣ በጥድፊያ ወደ መስጊዱ ሄደ፣ ከዚያም የጠበኝነት እጁን እላዩ ላይ አሳረፈበት፡፡ አብዱል-ባሃ ሼሁን ተመልክቶ በእርጋታና በከበሬታ፣ ነቢዩ ሙሐመድ የተናገሩትን አስታወሰው፡- 'ከሃዲ እንኳ ቢሆን፣ ለእንግዳህ ለጋስ ሁን፡፡'

ሼይሁ መለስ አለ፣ ቁጣውና ጥላቻውም በረደ፡፡ ጥልቅ የሆነ እፍረትና የመረረ ፀፀት ተሰማው፡፡ ወደ ቤቱ ሄዶ በሩን ዘጋ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ቀጥታ ወደ አብዱል-ባሃ በመሄድ እግሩ ላይ ወደቀና ይቅርታ ጠየቀ፡፡ 'ከአንተ በር በቀር የትኛውን በር እፈልጋለሁ፣ ከአንተ ፀጋ በቀር ለየትኛው ተስፋ አደርጋለሁ' አለ፡፡ ከዚያም ፅኑ ባሃኢ ሆነ፡፡

የአካ ህዝቦች የጋለ የጥላቻ ስሜት በጥቂት ወራቶች ውስጥ ቀዝቅዘዋል ማለት አይቻልም፡፡ ለውጥ እስኪመጣ

ድረስ፣ እያንዳዳቸው በችግር የተሞሉ፣ ብዙ ወራቶችን ወስደዋል፡፡ አብዱል ባሃ ወደ አካ በሚመጡት ባሃኢዎች ላይ እንዴት ዓይነት ቁጥጥር እንደሚደርግባቸው ሲዘረዝር :–

> በተባረከው ውበት ቀናት፣ የእጅግ ታላቁ እስር ቤት ትዕዛዞች አስቸጋሪና ጥብቅ በነበሩበት ጊዜያት፣ የትኛውም ወዳጆች ከምሽጉ እንዳይወጡ፣ ወይም እንዳይገቡ ተከለከሉ፡፡ [ሁለት የእምነቱ ተቃዋሚ ዎች] መኖሪያ ወደ ከተማው መግቢያ ሁለተኛው በር ላይ ስለነበር፣ በቀንም ሆነ በማታ አዲስ የሚገቡ ትን ኀብኚ ባሃኢዎች ይጠብቁ ነበር፡፡ የትኛውም አዲስ ሰው መምጣቱን ካዩ፣ ለባለሥልጣናት ያሳውቁ ነበር፡፡ ባለስልጣናቱም ሰውዬውን እስር ቤት በመ ክተት፣ በከባድ እስር እንዲቆይ ካደረጉ በኋላ፣ በመጨረሻ ከከተማው ያባርሩታል፡፡ ይህ አሠራር እንደመመሪያ ተወስዶ ለብዙ ጊዜ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

የእነዚህ ሰዎች ሸር እጅግ ከመርቀቁ የተነሳ የባሃኡላህ ሕይወትን ጭምር አደጋ ውስጥ እስከመክተት በመድረሱ፣ ባሃኢዎች ያለማቋረጥ ይረበሹና ይናወጡ ነበር፡፡ ባሃኡላህ ምንም ዓይነት ስጋት በሐሳባቸው እንዳይገባ ያስጠነቅቃቸው ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ ክህደትና በስሜት መሞላት ውጥረት አስፍነው በነበርበት ጊዜ፣ ባሃኡላህ ለምስራቅ ባሃኢዎች (ለአረብኛና ለፋርስ ቋንቋ ተናጋሪዎች) እንዲህ በሚል ጥቅስ መክፈቻ ያለው ፅላት ገልፆ ነበር:- ‘እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የቅኖች ልቦች በመለየት እሣት አለቁ፡፡’ ከባሃኡላህ ፅሁፎች መካከል ይህ ፅላት የተለየ ቦታ አለው፡፡

በዚህ ውስጥ የእርሱን ነፍስ ስቃይ ግልጥ አድርጎ ያሳያል፣ የእርሱን ልመና፣ በሰዎች ምክንያት የደረሰበት ሐዘን እና ከኢአማኒነትና ግዴለሽነት አምላክ እንዲታደጋቸው ይጠይ ቃል፡፡

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው እጅግ አሰቃቂው መከራ ደረሰ፡፡ በተደጋጋሚ የተሰጠውን የባሃኡላህን ምክሮች ከቁብ ባለመቁጠር፣ አንድ ቀን ሌሊት፣ በከተማው ውስጥ ሁሉም ነገር ፀጥ ባለበት ሰዓት የሚርዛ ያህያ ተከታዮች የሚኖሩበት ቤት ውስጥ በመግባት ሁሉንም ገደሏቸው፡፡

ያኔውኑ የሲኦል ደጆች ተከፈቱ፡፡ ጠቅላላው ከተማ ተናወጠ፡፡ የሰዎች ደህንነት አስጊ ሁኔታ ላይ ወደቀ፡፡

ባሃኡላህ እንደገና ለአዳዲስ ውርደቶች ተጋለጠ፡፡ ቤቱ በወታደሮች ተከበበ፡፡ በዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ የረብሻ ጩኸት በረከተ፡፡ ወደ አገረ-ገዢው ዘንድ ተወስዶ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ተደረገ፡፡ አብዱል-ባሃ ተይዞ ወደ እስር ቤት ተወስዶ በሠንሰለት ታሰረ፡፡ ሃያ አምስት ያህል ባሃኢዎችም ታሰሩ፡፡ ሌላው ቀርቶ ህፃናት እንኳ ከአካ ህዝብ ቁጣ ማምለጥ አልቻሉም፡፡ ከየቤታቸው እየተጎተቱ ወጥተው ተሰደቡ በድንጋይ ተወገሩ፡፡ ከሰባ ሰዓት ቆይታ በኋላ ባሃኡላህ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ተፈቀደ፡፡ 'ወደ እስር መወሰዴ ጉዳት ሊያስከትልብኝ አይችልም፣' አለ ባሃኡላህ ሲፅፍ፣ 'ነገር ግን እኔን የሚጎዳኝ፣ የእነዚያ እኔን የሚወዱኝ ባሕርይ ነው፣ ከእኔ ጋር እንደሆኑ ቆጥረው፣ ነገር ግን ልቤና ብዕሬን የሚያሳዝነውን ነገር የሚፈፅሙት ናቸው፡፡' 'የባሃኡላህ ፈተናዎች ፅዋ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ፈሰሰ፣' አለ የእርሱ የልጅ ልጅና የባሃኢ እምነት ሞግዚት ሾጊ ኤፌንዲ፡፡

በዚህ አስከፊ ሰዓት አብዱል-ባሃ ያሳየው ከተዓምር ያልተናነሰ ስብዕና ሲሆን፣ አባቱ ‘የአምላክ ምስጢር’ በሚል ያስገነዘበውን የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ አቻ በሌለው መልኩ የማያታክት ትዕግስተኛነቱን፣ የማያወላውልና የማይነቃ ነቅ ጠንካራነቱን፣ ይቅር ባይና ለጋስነቱን ታማኝነቱን፣ የእርሱ የብቻው የሆነ ደግነቱን አሳይቷል፡፡ እርምጃዎቹ በትህትና መንገድ የተሞሉ ናቸው፡፡ የሚናገረው ያለጥ ርጥር በስልጣን አንደበት ቢሆንም የዋህነትም ይታይበ ታል፡፡ የንጉሣዊነት ግርማ ሞገስ መለኪያ ነበር፡፡ በእርሱ ሰብዕና፣ ተግባራት፣ ቃላቱ ውስጥ መለኮታዊ እይታዎች ተገልፀዋል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ጎልቶ በማይታይ መልኩ ለውጥ መታየት ጀመረ፡፡ ለባሃኡላህና ለእርሱ ተከታዮች ጥሩ አመለካከት የሌለው አገረ-ገዢው የተለየ ችሎታ ባለው ሌላ ባለሥልጣን ተተካ፡፡ አዲሱ አገረ-ገዢ፣ አህመድ ቢግ ታውፊቅ፣ የጠለቀ አስተሳሰብ ያለውና ፍትሃዊ አስተዳዳሪ ነበር፡፡ እንደአገረ-ገዢነቱ ለባሃኡላህ ውለታ ለማድረግ እንዲፈቅድለትና በግሉ ለእርሱ ግልጋሎት ይሰጥ ዘንድ የለመነው ሰው ነበር፡፡ ባሃኡላህ ለአካ ነዋሪዎች ንጹሕ ውሃ ይሰጥ የነበረውን  አሁን ግን በዓመታት ሂደት ተበላሽቶ የነበረውን የውሃ መስመር እንዲያድስ ጠየቀው፡፡ ይህንን ሥራ በመሥራት አህመድ ቢግ ኃላፊነቱን ተወጣ፣ የአካ ህዝብም እጅጉን ተጠቃሚ ሆነ፡፡ በዚያ አካበቢ በሚነገረው ምሳሌያዊ አነጋገር መሠረት፣ አየሩ እጅግ ከመበከሉ የተነሳ በአካ ሰማይ ላይ የምትበር ወፍ ሞታ ትወድቃለች ይባል ነበር፡፡ ነገር ግን ባሃኡላህ በእነርሱ መካከል መኖር ከጀመረ በኋላ ቀስ በቀስ ሁኔታዎች እየተቀየሩ መጡ፡፡ የኮሌራ ወረርሽኝ

በተደጋጋሚ ወደ አካ ከተማ ጥግ ቢደርስም ዘልቆ ገብቶ ከተማውን መበከል አልቻለም።

ይኸው ቅን አገረ-ገዢ ልጁን እንዲያስተምርለት ወደ አብዱል-ባሃ ይልክ ነበር። እርሱም ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲችል ለምክር ወደ አብዱል-ባሃ አዘውትሮ ይመጣ ነበር።

የአካና የአካባቢው ነዋሪዎች ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ሁኔታ በባሃኡላህና በእርሱ ልጅ ተወዳዳሪ የሌለው ግርማ ሞገስ መማረክ ከጀመሩ ቆይተዋል።

ባሃኡላህንና አብዱል-ባሃን በአድሪያኖፐል የመገናኘት አጋጣሚ የነበረው፣ የቤይሩት ዋናው አገረ ገዢ ዓሊ ፓሻ፣ ለባሃኡላህ ካለው አክብሮትና ከእርሱ ልጅ ጋር ከነበረው ወዳጅነት የተነሳ ሊጎበኛቸው መጣ። ከዚያም በኋላ ተደጋጋሚ ጉብኝት አድርጓል። አብዱል-ባሃ ምንም እንኳን እስረኛነቱ በመደበኛነት እንደነበረ ቢሆንም፣ በኦቶማን መንግሥት እጅግ በጣም ብሩህ የመንግሥት ባለ ሟል በሆነው፣ የተሃድሶ ነፃ አስተሳሰብ በነበረው፣ ሱልጣኑ ህገ-መንግሥት እንዲያረቅ ካነሳሱት መካከል አንዱ በሆነው ሚድሃት ፓሻ ጋባዥነት አብዱል ባሃ ወደ ቤይሩት ተጉዞ ነበር። የአብዱል-ባሃ የቤይሩት ጉብኝት በ1878 ገደማ ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ባሃኡላህ ሁኔታውን በማስመልከትና ጠቀሜታውን ለማጉላት የገለጸው ጽላት ሲጀመር እንዲህ ይላል፦

> ሁሉም ስሞች በእርሱ ስም ዙሪያ በሚሽከረከሩት፣ የባ ሀገርን (ቤይሩትን) በእርሱ እዚያ መገኘት ያስከበረው ላይ ውዳሴ ይሁን።

በቤይሩትም ከሚድሃት ፓሻ ሌላ አብዱል-ባሃ በአረብ ዓለም የሚታወቁት ብዙ ሰዎችን አገኘ፡፡ ከእነርሱ መካከል፣ የታወቀው የወደፊቱ የግብፅ ዋና ሙፍቲ፣ ሼይህ ሙሐመድ አብዱ ይገኝበታል፡፡ ይህ የተማረና የተከበረ ሼይህ፣ የፓን-ኢስላሚዝም ዋና አቀንቃኝና የባሃኡላህ እምነት የመቃወም ሱስ ያለበት የሰዒድ ጃማሉድ-ዲን አል-አፍጋኒ ተባባሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ለአብዱል-ባሃ ያለው አድናቆት ከፍተኛ የነበረና እንዲያውም ከእርሱ ጋር በመሆን እስከ አካ ድረስ አብሮት ሊሄድ ፈልጎ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ ድርጊት ጉዳት ሊያመጣ በትና አቋሙንም ችግር ውስጥ ሊከተው እንደሚችል በማሳመን እንዲቀር አድርጎታል፡፡

የአብዱል-ባሃ ዝና አሁን በስፋት ናኘ፡፡ የክርስቶስ የትውልድ ከተማ የሆነችውን ናዝሬትን ሲጎበኝ፣ የከተማው ሙፍቲ የነበረው፣ የተማረና ከፍተኛ ስልጣን ያለው፣ ሼይህ ዩሱፍ፣ የተቀበለው በከፍተኛ ክብር ነበር፡፡ በሙፍ ቲው አቀባበል ስነ-ስርዓት ላይ፣ ኃላፊዎች እና ባለስል ጣናት ከከተማው ውጪ እሩቅ መንገድ በመጓዝ ተቀብለ ውት እስከ ናዝሬት ድረስ አጅበውት ገቡ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አክብሮት የሚሰጠው ለጠቅላይ አገረ-ገዢዎችና ለሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ነበር፡፡ ሼይህ ዩሱፍ በሌላው ቀን አብዱል-ባሃን ሲጋብዝ፣ በተመሳሳይ ደረጃውን የጠበቀ አቀባበል አድረገለት፡፡

የአካው አገረ-ገዢ አህመድ ቢግ፣ በሙስጣፋ ዲያ ፓሻ ተተካ፡፡ አዲሱ አገረ-ገዢ ባሃኡላህን እንደእስረኛ መቁጠ ሩን ቸል ብሎት ነበር፡፡ ከፈለገ፣ ከከተማው ለቅቆ በመውጣት በገጠራማው አካባቢ መኖር እንደሚችልም አሳወቀ፡፡ ባሃኡላህ፣ ምንም እንኳ በግዞቱና እስራቱ

የጨለማ ሰዓት በእስር ቤቱ ምሽግ ውስጥ ሆኖ እንዲህ ብሎ ቢፅፍም፣ አሁን በተሰጠው ዕድል ግን ሊጠቀም አልፈለገም፦

> አትፍሩ፣ እነዚህ በሮች ይከፈታሉ፡፡ ድንኳኔ በቀር ሜሎስ ተራራ ላይ ይተከላል፣ እጅግ ታላቁ ሐሴትም እውን ይሆናል፡፡

ይህ እንዲሆን ጊዜው አልቀረበም ነበር፡፡

ብዙ ድርጊት የተከናወነባቸው ዘጠኝ ዓመታት ተከታተሉ፣ ነገር ግን ባሃኡላህ በከተማው ቅጥር ውስጥ ተወስኖ ቆየ፡፡ ያን ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ አብዱል-ባሃ እንዲህ በማለት ገልፆታል ፦

> ባሃኡላህ የገጠር አካባቢን አረንጓዴንና ልምላሜን ይወዳል፣ አንድ ቀን እንዲህ የሚል አስተያት ሰጥቶ ነበር፦ ‘ለዘጠኝ ዓመታት ልምላሜን አይቼ አላውቅም፡፡ ገጠር የነፍስ ዓለም ነው፣ ከተማ ደግሞ የሥጋ ዓለም ነው፡፡’ ይህንን ስሰማ ገጠር ናፍቆታል ማለት ነው ብዬ አሰብኩ፣ ስለዚህ የእርሱን ምኞት ለመፈፀም የበኩሌን ጥረት ካደረግኩ ይሳካልኛል ማለት ነው አልኩ፡፡ በዚያን ጊዜ በአካ ኗሪ የሆነ እኛን በጣም የሚቃወም ሙሐመድ ፓሻ ሳፍዋት የሚባል አንድ ሰው ነበር፡፡ ከከተማው ወደ ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ ማዝራዒ የሚባል ሰፊ ግቢና የሚያምር ቤት ነበረው፡፡ የሚፈስ ጅረት ያለው በአትክልት የተከበበ፣ በጣም ቆንጆ ቦታ ነው፡፡ ወደ ፓሻው ቤት ሄጄ አስጠራሁት፡፡ እንዲህ አልኩት፣ ‘ፓሻ፣ ይህንን ትልቅ ቤት ባዶ አድርገህ ትተኸዋል፣ አንተ ደግሞ የምትኖረው በአካ ነው፡፡’ እርሱም

እንዲህ አለ 'እኔ የማልረባ ከንቱ ነኝ' ከተማን ለቅቄ መሄድ አልቻልኩም፡፡ እዚያ ከሄድኩ ብቸኛ እሆናለሁ ከጓደኞቼም እቆራረጣለሁ፡፡' እንደገናም እንዲህ አልኩት፣ 'ቤቱ ባዶ ከሚሆን፣ ለእኛ አከራየን፡፡' በቀ ረበለት ሐሳብ እጅግ ተደነቀ፣ ከተመካከርን በኋላ፣ ቤቱን በጣም በርካሽ ዋጋ በአምስት ፓውንድ አከራየን እኔም የአምስት ዓመት ከፈልኩትና ውል ተፈራረምን፡፡ ቦታውን ለማስተካከል፣ የአትክልት ስፍራውን ለማስዋብና የመታጠቢያ ቤት ለማስገን ባት ሞያተኛ ላክኹኝ፡፡ ካለቀም በኋላ የተባረከው ውብትን ለመውሰድ ሠረገላ አዘጋጀሁ፡፡ ከዚያ በፊት ግን አንድ ቀን ቦታውን ለማየት እራሴ ለመሄድ ወሰንኩ፡፡ የሡልጣኑ ትዕዛዝ ቢኖርም በከተማው ዋና በር ወጥቼ ሄድኩ፣ ዘበኞች ጥበቃ ላይ ነበሩ፣ ነገር ግን ምንም ተቃውሞ አላሰሙም፡፡ ከአንዳንድ ወዳጆችና ባለሥልጣናት ጋር፣ በሚቀጥለው ቀን እንደገና ወጥቼ አለፍኩ፡፡ አሁንም ምንም ተቃውሞ አልገጠመኝም፡፡ በሌላ ቀን ከአካ ከተማ ውጪ ታላቅ የእራት ግብዣ አዘጋጀሁ፣ በባሃጂ (በኋላ ላይ የባሃ ኡላህ መኖሪያ የሆነ) የዘንባባ ዛፎች ስር ጠረጴ ዛዎችን ዘረጋሁ፣ በዙሪያውና በከተማው የሚገኙ ታዋቂ ሰዎችንና ባለሥልጣናትን ጋበዝኩ፡፡ አመሻሽ ላይ ሁላችንም ወደ ከተማው ተመለስን፡፡ አንድ ቀን ወደ ተባረከው ውበት ቅዱስ ቅርበት በመሄድ እንዲህ አልኩ፣ 'በማዝራይ ወደሚገኘው የሚያምር ቤት የሚያደርስህ ሠረገላ ለአንተ ዝግጁ ነው፡፡' እንዲህ በማለት መሄዱን ተቃወመ፣ 'እኔ እስረኛ ነኝ'፡፡ ኋላ ላይም እንደገና ጠየቅሁት፣ ያንኑ መልስ ደገመልኝ፡፡

ነገር ግን በአካ፣ ባሃኡላህን የሚወድና ባሃኡላህም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው፣ በጣም ታዋቂና ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነ፣ ሼይህ ነበር፡፡ ሼይሁን አስጠርቼ ሁኔታውን አስረዳሁት፡፡ እንዲህ አልኩት፣ ‘አንተ ደፋር ነህ፣ ዛሬ ማታ ወደ እርሱ ቅርበት ግባና፣ ተንበርክከህ፣ እጆቹን ጥብቅ አድርገህ ያዝ፣ ከዚያም ከተማውን ለቅቆ ለመሄድ ቃል እስኪገባልህ ድረስ አትልቀቀው!’፡፡ እርሱም ወደ ባሃኡላህ በቀጥታ ገብቶ እግሩ ስር ተቀመጠ፡፡ የተባረከውን ውብት እጆች ወስዶ ሳማቸው ከዚያም እንዲህ በማለት ጠየቀ :– ‘ይህንን ከተማ ለምን ለቅቀህ አትወጣም?’ እንዲህ ሲል መለሰለት :– ‘እኔ እስረኛ ነኝ፡፡’ ሼይሁም፣ ‘አምላክ ይቅር ይበል አንተን እስ ረኛ ለማድረግ ኃይል ይኖራልን? እራስህን እስረኛ ያደረግኸው እራስህ ነህ፡፡ ለመታሰር የፈቀድከው እራስህ ነህ፣ እናም አሁን ከዚህ ወጥተህ ወደ ተዘጋጀልህ የሚያምር ቤት እንድትሄድ እለምን ሃለሁ፡፡ ቦታው ለምለምና በጣም የተዋበ ነው፡፡ ዛፎቹ በጣም ያምራሉ ብርቱካናዎቹም የእሣት አሎሎ መስለዋል’ አለው፡፡ የተባረከው ውብትም ‘እኔ እስረኛ ነኝ፣ ሊሆን አይችልም’ ባለ ቁጥር፣ ሼይሁ እጆቹን ይዞ ይስማቸዋል፡፡ ልመናው ከአንድ ሰዓት በላይ ፈጀ፡፡ በመጨረሻም ባሃኡላህ ‘በጣም ጥሩ’ አለ፡፡ የሼይሁ ትግስትና ፅናትም በውጤት ተሸለመ፡፡ ብስራቱን ሊነግረኝም ወደ እኔ መጣ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ባሃኡላህን በፈረስ ሰረገላ ወደሚያምረው ቤት-እልፍኝ ወደሆነው ማዝራይ ወሰድኩት፡፡ ተቃውሞ ያነሳ ማንም አልነበረም፡፡ እኔም እርሱን እዚያ ትቼው ወደ አካ ከተማ ተመለስኩ፡፡

ባሃኡላህ በማዝራይ ቤተ እልፍኝ ውስጥ ለሁለት ዓመት ከኖረ በኂላ፣ ለአካ ከተማ ቀረብ ወደሚለው፣ የተንጣለለ መስክ ላይ ወደሚገኘው፣ የመጨረሻው የመኖሪያ ስፍራው ወደሆነው፣ ባህጂ ቤተ-እልፍኝ ተብሎ ወደሚጠራው ተዛወረ፡፡ ባሃኡላህ በአካ በእስራት በነበረበት ወቅት ይህ ቤተ-እልፍኝ እየተሠራ ነበር፣ ከጠቅላላው አካ ባቢ ከፍ ብሎ የሚታይ እጅግ በጣም ግሩም ህንፃ ነበር፡፡ ነገር ግን በድንገት በተከሰተው ወረርሽኝ፣ ባለቤቱ ቤቱን ትቶ ሄደ፡፡ አብዱል ባሃም ለአባቱ በመጀመሪያ ተከራይቶ ከዚያም በመቀጠል በቋሚነት ገዛው፡፡ ባሃኡላህ ይህን መኖሪያ ስፍራ ‘አምላክ ለሰው ዘር የደነገገው እጅግ ከፍተኛው ቤተ-እልፍኝ’ በማለት ሰየመው፡፡

አብዱል-ባሃ በመቀጠል፣ በወራጅ ውሃ የተከበበ ደሴት የሚመስል ሰርጥ፣ ከአካ በአጭር ርቀት ላይ የሚገኝ የአትክልት ስፍራ ገዛ፡፡ ባሃኡላህ በመጀመሪያ ተልኮውን ያወጀበት፣ ከባግዳድ ወጣ ብሎ የነበረውን የናጂብ ፓሻ አትክልት ስፍራን ለማስታወስ፣ ይህን የአትክልት ስፍራ ‘ሪዝቫን’ በማለት ሰየመው፡፡ የእርሱ ተከታዮች ያሳመሯት ይህች የአትክልት ስፍራ፣ አንዳንድ ግዜ ባሃኡላህ ይንሸራሸርባት ነበር፡፡ አነስ ብሎ መጠነኛ በሆነው የበጋ ቤት ውስጥ በሚገኙት፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑትን ሁለት ክፍሎችን አንዳንዴ ያርፍባቸው ነበር፡፡

በአብዱል-ባሃ ያላሳለሱ ጥረቶች ፣ ባሃኡላህ፣ በመጨረሻ ከአካ እና ከህዝቦቿ ጭቆና ነፃ ወጣ፡፡ አሁን ሙሉ ጊዜውን ተከታዮቹን በመኮትኮት ላይ ማተኮር ቻለ፡፡ በጣም ቀፋፊ በነበረበት ጊዜ በአካ፣ የከተማውን ባለስ ልጣናትና መኳንትን በማግኘት፣ የባሃኢ ማህበረሰብን በመጠበቅ፣ መብታቸውን አስከብሮ፣ ደህንነታቸውን አረጋ

ግጦ፣ አባቱንም ከልሎ ይኖር የነበረው አብዱል-ባሃ ሲሆን፣ ከባሃኡላህ ጋር ለመገናኘት ከአካ እስከ ባህጂ ያለውን ርቀት በእግሩ ይሄድ ነበር፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ በምዕራብ አገሮች በነበረው ጉብኝት፣ ከኒውዮርክ ወደ ሊቨርፑል በመርከብ ሲጓዝ፣ ለብዙ ሰዓት በመርከቡ ላይ በእግሩ ይረማመድ ነበር፤ ከዛም ለማረፍ ይቀመጣል፣ አብረውት ላሉት 1.4 ኪ.ሜትር አካባቢ ተራመድኩ ይላቸዋል፡፡ ይኸም ከአካ እስከ ባሃኡላህ መካነ-መቃብር ያለው ርቀት ነው፡፡ ምናልባት በኋላ ላይ፣ በቅድስት ሀገር፣ ወደ መካነ-መቃብሩ በእግር የመጓዝ አስገዳጅ ሁኔታ ቢገጥመኝ፤ በእግር ለመጓዝ አቅሜ ደክሞ ከዚህ ፀጋ እንዳልነፈግ፣ በእግር መጓዝን መለማመድ እፈልጋለሁ' ብሏቸዋል፡፡ በወቅቱ ዕድሜው ስድሳ ዘጠኝ ነበር፡፡

የታወቁት ዕደ-ሃይማኖት፣ ታራዙላህ ሳማንዳሪ፣ በባሃ ኡላህ የመጨረሻዎቹ ስድስት ወራት የሕይወት ዘመኑ፣ በአሥራ ስድስት ዓመት እድሜያቸው መንፈሳዊ ጎብኚ በመሆን ሄደው ነበር፣ ከአብዱል-ባሃ ጋር ከአካ እስከ ባህጂ የሄዱትን የእግር ጉዞ ያስታውሳሉ፡፡ ዝናብ ጥሎ መሬቱ እርጥብ ነበር፣ መንገዱን ተጉዘን ጠምዘዝ እንዳልን ቤተ-እልፍኙ ሙሉ ለሙሉ መታየት ሲጀመር፣ አብዱል-ባሃ ተንበርክኮ ግንባሩን በዝናብ በበሰበሰው መሬት ላይ አሳረፈ፡፡ ወደ ባህጂ ሲጠጋም ባሃኡላህ፣ በእርሱ አቅራቢያ ወደሚገኙት ባሃኢዎች በመዞር እንዲህ ይላቸው እንደነበረም ተረድተናል፡- ' ጌታው (ማስተር) እየመጣ ነው፡፡ እርሱን ለማጀብ ፍጠኑና ሂዱ ይላቸዋል' ለዚህም ብዙዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሳማንዳሪ በወቅቱ ባሃኡላህ ለእርሳቸው ረጋ ብሎ፣ ርህራሄ በተመላው ሁኔታ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ምክር የሰጣቸውን ቀን ያስታውሳሉ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው ለብዙ ቀናት ወደ ባሃኡላህ ለመቅረብ አልቻሉም ነበርና የቤቱን ትንሽ ልጅ ሲያገኙ፣ የአቤቱታ ደብዳቤያቸውን እንዲያደርስላቸው ይሰጡታል፡፡ ከዚያም ወደ እርሱ ሲቀርቡ፣ ባሃኡላህ እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል:- “አብዱል-ባሃን በየቀኑ አታገኘውምን? የሳማንዳሪ መልስ አዎንታዊ ነበር፡፡ ለብዙ ቀናት እሱን በማግኘት ክብር አብረኸው ሆነህ ሳላ እኔን እንዳላገኘህ ለምን ትቆጥራለህ? አለኝ፡፡ አብዱል-ባሃን ማግኘት እርሱን ከማግኘት ጋር እኩል አደረገው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያወቅናቸው የመጣነው ሐጂ ሚርዛ ሃይዳር-ዓሊ፣ ስለ አብዱል-ባሃ ደረጃና ብቃት ምስክርነታቸውን ዘግበዋል፡፡ በአንድ ወቅት ሐጂው፣ አብዱል-ባሃን የሚያመላክቱ ከእስልምና ትውፊቶች፣ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ አቀናብረው ነበር፡፡ ይህን ጥንቅርና ማብራሪያ ለባሃኡላህ አቀረቡ፡፡ ምክንያታዊ ሃሳቡና ድምዳሜው ፍፁም ትክክል እንደሆነ ባሃኡላህ ነግሯቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ :–

> አሁን የእጅግ ታላቁ ቅርንጫፍ የአንደበት ኃይልና ጉልበት ሙሉ ለሙሉ እየታየ አይደለም፡፡ ወደፊት እርሱ፣ ብቻውንና ያለማንም እርዳታ የእጅግ ታላቁን ስም ሰንደቅ ከፍ በማድረግ በዓለም ልብ ማዕከል ላይ በማውለብለብ የመለኮታዊ ኃይሉና ስልጣኑ ነፀብራቅ የሚታይ ይሆናል፡፡ የምድርን ህዝቦች እንዴት አድርጎ በሰላምና በስምምነት ድንኳን ስር እንደሚሰበስባቸውም እውን ይሆናል፡፡

በእነዚያ ዓመታት በኢራን ባሃኢዎች ላይ ስቃይ፣ ጭቆናና መስዋዕትነት የተለመዱ ሁኔታዎች ነበሩ። ከዓመት ዓመት የሰማዕቱ ቁጥር እያሻቀበ ቁጥራቸው እስከ ሰላሳ ሺህ ደርሶ ነበር። ነገር ግን የባሃኡላህ ተከታዮች ምንም ሊበግራቸው አልቻለም። ጥብቅና ፅኑ ሆነው ከመቆም አላገዳቸውም።

ባሃኡላህ አካ እስር ቤት እያለ ለተከታዮቹ ቃል የገባላቸው፣ ይህ ሁሉ መከራ እንደሚያልፍና ድንኳኑ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ እንደሚተከል ነበር። በሕይወቱ ማምሻ አካባቢ፣ በዚያ የተቀደሰ ቀርሜሎስ ተራራ ላይ ደንኳኑን ተክሎ ቆየ። ለአብዱል ባሃም የሚያከናውነውን የተለየ ተልዕኮ ሲሰጥ፣ አንድ ቀን ከተራራው ግማሽ ላይ በነበሩ የጥድ ዛፎች ስር፣ ከበታቹ የሚገኘውን የቋጥኝ ድንጋይን እያመላከተው፣ በዚህ ቦታ ላይ፣ የእርሱ ቀዳማይ የነበ ረውን፣ በጥይት ተበጣጥሶ መስዋዕት የሆነውን፣ ለብዙ አሥርተ- ዓመታት ከቦታ ወደ ቦታ እየተወሰደ ተደብቆ የቆየውን፣ የባብን ቅሪተ አካል እንዲያኖር አዘዘው። ሁኔታዎች ሲስተካከሉ አብዱል-ባሃ ይህንን ሥራ ተወጥ ቶታል፣ ነገር ግን ሥራው አድካሚና ብዙ ዓመትም ፈጅቷል። ሥራው የአብዱል-ባሃ ችግርን የመቋቋም ችሎታውን ቢያሳይም ነገር ግን ብዙ ሐዘንና ስቃይን አስከትሎበታል። ሆኖም በስተመጨረሻ የአባቱን ትዕዛዝ በሚሟላት በአጥጋቢ ሁኔታ ፈፅሟል።

## ምዕራፍ 3
## የባሃኡላህ እርገት

የባሃኡላህ እርገት የተፈጸመው በሜይ 29 1892 ማለዳ አካባቢ ነበር። የባሃኢዎች ልቦች ተሰበሩ። አብዱል-ባሃ ለቱርኩ ሱልጣን አብዱል ሐሚድ፣ 'የባሃ ፀሐይ ጠልቃለች' የሚል ዜና በቴሌግራም ላከ።

በዚሁ ቴሌግራም ለሱልጣኑ የባሃኡላህ ምድራዊ መቅደስም በባሃጂ ቤተ-እልፍኝ ቅጥር ውስጥ እንደሚያርፍ አሳወቀ። አብዱል-ሐሚድም መስማማቱን ገለፀ። በዚያው ቀን ምሽት ላይ የእምነቱ ተከታይ ያልሆኑ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ነዋሪዎች፣ መኳንንትና በከተማው የታወቁ ሰዎች ለባሃኡላህ ያላቸውን አክብሮት ገለጹ። ከብዙ ሰዓት መጨናነቅ በኋላ ዝምታ ሲሰፍን የተቀደሰውን አካል የያዘው ሣጥን ከቤተ-እልፍኙ ጥቂት ሜትሮች ርቆ ወደ ሚገኘው ቤት ተወሰደ። ይህ ቤት የባሃኡላህ አማች ቤት ነበር። እዚህ ክፍል ውስጥ ከመሬት በታች በጡብ የተገነባ ጉደጓድ ተሰራ፣ ቅሪተ-አካሉም እዚያ ውስጥ እንዲያርፍ ተደረገ።

የአካ ህዝቦችና አዋሳኞቻቸው ሐዘን እጅግ ጥልቅ ነበር። ከዚህም በላይ፣ ሁሉም ሶርያና አጎራባች ግዛቶች ሁሉ አዘኑ። እነዚያ ቀደም ሲል ባሃኢዎችን የሚጠሉና የሚያሾፉባቸው ሁሉ፣ ስለባሃኡላህ በማዘን ወደ ቤተ-እልፍኙ ቀን በቀን በመምጣት ሐዘናቸውን ይገልፁ ነበር። ባለፉት ፀሐፊያንና ገጣሚያን፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፣ ከአካ እስከ ታወቁት የአረብ ከተሞች ደማስቆ፣ ቤይሩት፣ ካይሮ፣ ባግዳድ ባሃኡላህን ብቻ ሳይሆን ልጁን ጭምር የሚያሞግሱ ውዳሴዎች ቀረቡ። ከእነርሱ መካከል፣ ዝናው የገነነው ግብፅዊው ክርስቲያን

አሚን ዛይዳንና፣ ሙስሊሙ በጠቅላላው በሶርያ ታዋቂና በበጎ ሥራው የገነነው ሐጂ ሙሐመድ አብዱል-ሃልቅ ይገኙበታል፡፡ ሁሉም ሐዘናቸውንና አክብሮታቸውን የሚልኩት ለአብዱል-ባሃ ነበር፡፡

በሐዘን ብዛት መኖር ያቃተውና እራሱን ውኃ ውስጥ በማስጠም የገደለው ታሪክ ጸሐፊው ናቢል አዛም እንዲህ ይገልፃል :–

> ሳስበው፣ በአቧራው ዓለም የተነሳው መንፈሳዊ ነውጥ ሁሉንም የአምላክ ዓለማት እንዲንቀጠቀጡ ምክንያት ሆኗል፡፡ ... ውስጣዊውና ውጫዊው አንደበቴ የገባንበትን ሁኔታ ለመግለጽ አቅመ-ቢስ ሆነዋል፡፡ ... ተንሰራፍቶ ባለው ፈርጀ-ብዙ የአካ እና የአጎራባች መንደሮች ግራ መጋባት፣ ቤተ-እልፍኙን ከቦት በሚገኘው መስክ ላይ ተጣብቦ ያለው ህዝብ፣ ሲያለቅሱ፣ ጭንቅላቶቻቸውን ሲደበ ድቡ፣ በሐዘን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲጮሁ ይታያሉ፡፡

በፋርስ፣ በግብፅ፣ በሶሪያ፣ በኢራቅና በኦቶማን ግዛቶች፣ በካውካሰስ፣ ቱርኪስታን እና ሌሎች ቦታዎች ለሚገኙት ባሃኢዎች፣ አብዱል-ባሃ የመጀመሪያ መልዕክቱን አስተላለፈ:–

## እርሱ ንዑዱ ነው

> በአንድ ወቅት ለሁሉም የሰው ዘር አንፀባራቂ የነበረው፣ ለዘለዓለም ከአብሃ አድማስ የሚያበራው፣ የማይደበዝዘው የእርሱ መንግሥት ክብር፣ ከከፍታው የእርሱን ተወዳጆች በማንፀባረቁ ያጥለቀለቃቸው፣ ለልቦቻቸውና ለነፍሶቻቸው ዘለዓለማዊውን እስትንፋስ እፍ ያለባቸው፣ የዓለም

ታላቁ ብርሐን ፀሐይ ጠልቃለች። እናንተ የጌታ ተወዳጆች! ትጠራጠሩና ታወላውሉ እንዳይሆን ተጠንቀቁ። ፍርሃት እንዲወድቅባችሁ፣ ወይም ችግርም እንዲያስጨንቃችሁ አትፍቀዱ።

የእውነት ፀሐይ፣ ያ እጅግ ታላቅ ብርሐን፣ በዓለም አድማስ ላይ በማይሞተው ነፀብራቅ ወሰን በሌለው ግዛት ላይ ነግቷል። በእጅግ ታላቁ ቅዱስ መፅሐፍ ለእርሱ ጥብቅና ፅኑ አማኞች ጥሪ አቅርቧል፡–‘የዓለም ህዝቦች ሆይ! የእኔ ውበት ፀዳል ሲጋረድ፣ የአካሌ መቅደስ ሲደበቅ፣ ግራ የመጋባት ስሜት አይሰማችሁ፣… የእኔ እምነት ድል እንዲያደርግ፣ ለሁሉም የሰው ዘር የእኔ ቃላቶች ይሰሙ ዘንድ፣ ብድግ በማለት ራሳችሁን አንቀሳቅሱ።’

## ምዕራፍ 4

## የቃል-ኪዳኑ ማዕከል

ባሃኡላህ የእርሱን ወደር የሌለውን ልጁን የእርሱ ቃል-ኪዳን ማዕከል ይሆን ዘንድ አነጸው፡፡ በሰው ዘር ቅዱሳን ፅሁፎች ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ፣ ኪታቢ-ኢ-አሐድ—የቃል-ኪዳን መጽሐፍ ብሎ በሰየመው ጽላት ውስጥ፣ አብዱል-ባሃን የእርሱ ሃይማኖት ዋናው ርዕስ፣ የእርሱ ቃላት አብራሪ፣ ሐሰት ከእውነት ተለይቶ እና ተነጥሎ የሚመዘንበት የማይሳሳተው ሚዛን፣ እንደሆነ ግልፅ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ይህ ቃል-ኪዳን ባሃኡላህ በእርሱ ህዝቦች ላይ የመሠረተው ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን የሰው ዘር የሚጨምር ነው፡፡ በሃይማኖት ታሪክ ውስጥ አቻ የለውም፡፡

“ይድረስ ለተኩላው ልጅ” በሚለው በባሃኡላህ ብዕር በተገለጸው የመጨረሻ መጽሐፍ ውስጥ የእርሱን ኪዳን ‘ቀዩ መፅሐፍ’ በሚል ይጠቅሰዋል፡፡ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የቀረበው ‘የእርሱ ምስክርነት ታቦት’ – ማለትም የአምላክ ምስክርነት – በሚል የተዘረዘረው የባሃኡላህ ቃል-ኪዳን ይህ ነው፡፡

ዓለም እንደ ባሃኡላህ ዓይነት ቃል-ኪዳን ፍፁሞ አይቶ አያውቅም፡፡ በአብዱል-ባሃ አገላለፅ፣ የሰው ዘር አንድነት መሽከርከሪያ ከቃል ኪዳኑ በስተቀር ሌላ የለም፡፡… ከዓለም መፈጠር አንስቶ በተፃፉት ጥንታውያኑ መፅሐፍት፣ ፅላቶች እና ቅዱሳን ድርሳናት ‘እርግጠኛው እጅ’ በማለት የተጠቀሰው ቃል ኪዳኑና ኑዛዜው ይኸው ነው፡፡ ‘የቃል ኪዳኑ ሻማ የዓለም ብርሐን ነው፡፡’

የሰው ዘር አንድነትን ተጨባጭ ቅርፅ የሚሰጠው፣ አምላክ ለፍጥረቱ ያደለው አንድነት፣ የባሃኡላህን ትምህርቶችና መርሆዎችን ማስተማር ነው፡፡ መታወቅ ያለበት የማያጠራጥረው እውነታ፣ በሁሉም የምድር ነዋሪዎች መጠበቅ ያለበት፣ በየትኛውም የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ምህዳር ሊተገበር የሚገባው መርህ፣ የሰው ዘር መንፈሳዊ አንድነት ነው፡፡ እርስ በእርስ ከመጠፋፋት የሰውን ልጅ የሚታደገው ይህ እና ይህ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ለማድረግ የባሃኡላህ አስተምህሮት ከመበረዝ ነፃ መሆን አለበት፡፡ ካለበለዚያ ያለጥርጥር እምነቱ ይከሽፋል፡፡ በተደ ጋጋሚ ተሞክሮ የተረጋገጠው፣ የእርሱን ትምህርቶች ፅኑ አቋም ጠብቆ ያቆየው፣ የማይታየው ኃይል የባሃኡላህ ቃል-ኪዳን ነው፡፡ ከአርካሾች እጅ ታድጎት ያለው ቃል ኪዳኑና ቃል ኪዳኑ ብቻ ነው፡፡

አብዱል ባሃ የዚህ ቃል-ኪዳን ማዕከል ነው፡፡ ቃል ኪዳኑ ትርጉም የሚያገኘው በእርሱ እና በእርሱ ብቻ ነው፡፡ አማኙን ከኢአማኒው የመለየት ስልጣን የእርሱ ብቻ ነው፡፡

ባሃኡላህ በኪታቢ-ኢ-አቅዳስ ግልፅ ፅሑፍ፣ እርሱ እራሱ እንደገለጸው፣ የቃል ኪዳኑ ማዕከል ጥብቅ እና ኃያል ነው፣ ዘመን ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየትኛውም ሃይማኖት ግልፀት ታይቶ የማይታውቅ መሆኑንና የእርሱ ትም ህርቶች ተርጓሚም እድርጎ ሰይሞታል፡፡

ባሃኡላህ የእርሱን ቃለ-ኑዛዜ በአደራ የሰጠው ለአብዱል-ባሃ ነው፡፡ እርሱ ባረገ በዘጠነኛው ቀን የያዘው ቁም ነገር ታወቀ፡፡ ባሃኢዎችና፣ በአብዱል-ባሃ የተመረጡ የባሃኡላህ ቤተሰብ አባላት ማህተሙን በመፍታት የቃለ-ኑዛዜውን ምክሮችና ተግሳፆች ለመስማትና ለመመስከር

ተሰበሰቡ። በዚያው ቀን በኋላ ላይ፣ በመካነ-መቃብር ዙሪያ፣ የባሃኡላህ ታማኝ ወንድም እና በአርባ ዓመታቱ ሁሉ በጽናትና በጀግንነት የደገፍው የሚርዛ ሙሳ ልጅ፣ ሚርዛ ማጅዲድ-ዲን፣ ለሁሉም ሰው ኑዛዜውን አነበበ። ባሃኢዎች ወደ ማን እንደሚዞሩ፣ ማንን መታዘዝ እንዳለባቸው፣ ጠቅላላው ስልጣን በማን ትከሻ ላይ እንዳረፈ ግልፅ ሆነ። በወቅቱ ማንም ተቃውሞ ያነሳ አልነበረም። በእዚያ ተሰብስበው የነበሩ ሁሉ፣ አብዱል-ባሃ የባሃኡላህ ወራሽ እንደሆነ አወቁ፣ እርሱ ለሚደነግገው ለመገዛትም ተዘጋጁ።

በዚያን ወቅትም አስከፊ ሁኔታ ተከስቶ ነበር። አብዱል-ባሃ እንደገለፀው፣ የእርሱ ወንድም ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ፣ በማጭበርበር፣ በባሃኡላህ አልጋ አጠገብ የተቀመጡትን፣ ጽሑፎቹን የያዙ ሣጥኖችን ወሰደ። በዚያ አስጨናቂ የእልፈቱ ቀን፣ የባሃኡላህን አካል ለማጠብና ለቀብር ሲሰናዱ፣ ወረቀቶቹ ላይ ውኃ ተረጭቶባቸው እንዳይበላሹ፣ ለአብዱል-ባሃ ሣጥኑን ወደ ሌላ ክፍል እንዲወስድ ያማክረዋል፣ አብዱል-ባሃ በባሃጂ ቤት ውስጥ የራሱ ክፍል ስላልነበረው ይህን አደራ እራሱ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ ይወስዳል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ባሃኡላህ ፅላት የገለጸለት አንድ ባሃኢ፣ ማህተም ለማስመታት አብዱል-ባሃን ይጠይቀዋል። የባሃኡላህን ማህተሞች የያዘው ሣጥን በሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ እጅ በመሆኑ፣ አብዱል-ባሃ ሣጥኑን እንዲያመጣው ጠየቀው፣ የት እንዳለ እንደማያውቅና እርሱ እንዳልወሰደም ይናገራል።

የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ እጅግ ታላቁ ምኞት አባቱ ፅፎ እንዳስቀመጠው እርግጠኛ የሆነበትን ቃለ-ኑዛዜውን በእጁ

ማስገባት ነበር፡፡ ነገር ግን ያ ፅሑፍ የሚገኘው በአብዱል-ባሃ እጅ ነበር፡፡ በመሆኑም የባሃኡላህን ቃል-ኪዳን ለማዛባት የነበረው እቅድ መከነበት፡፡ ነገር ግን ይህ ምኞቱ የኋላ ኋላ የራሱን ሕይወት እስከሚያጠፋው ድረስ ወደ እርጉምነት አዘቅት ውስጥ ከተተው፡፡ እጅግ ለተከበረው የሺራዝ ባሃኢ፣ ለሚርዛ ሙሐመድ-ባቂር ካሃን በተፃፈ ፅላት የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊን አታላይነት አብዱል-ባሃ እንዲህ ይገልጸዋል፡-

> በጠቅላላው፣ የህግ ተላላፊነቱ የማጭበርበር ድርጊት፣ ለዚህ አገልጋይ በተለይ የተሰጠውን መለኮታዊ አደራ ሁሉንም ነገር ወስዶታል የቀረው ነገር አልነበረም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ አላግባብ በእጃቸው ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን የወሰዱት እያንዳንዱ ነገር ለአብዱል-ባሃ በምድርም ሆነ በሰማይ ከሚገኙት ነገሮች ሁሉ እጅግ ውድ ቢሆንም፣ እስከ አሁን ድረስ በዝምታዬ ፀንቼ አንዲት ቃል አልተነፈስኩም፡፡ ምክንያቱም በባዕዳን ዘንድ ስማችን ይጎድፋል በሚል ነው፡፡ ይህ ለእኔ ታላቅ ቅጣት ነው፡፡ ተሰቃየሁ፣ አዘንኩ፣ አለቀስኩ፣ ነገር ግን ምንም አልተናገርኩም፡፡

ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ በከፍተኛ ጥረት የአብዱል-ባሃን ማንነት ከማኮስመኑ በፊት፣ በባሃኢዎች አእምሮ ውስጥ ጥርጣሬን እየዘራ፣ እነዚያን የስልጣን ጥመኞችንና ራስ ወዳዶችን ያሰባስብ ነበር፡፡ የባሃኡላህ ወንድም ሚርዛ ያህያ የራሱ የሆነ ተንኮልና ብልጠት እንዳለው ሁሉ፣ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊም እንደዚሁ ሸረኛ ነበር፡፡ የባሃኡላህን ቃለ-ኑዛዜ በአደባባይ ያነበበው ግልፍተኛው ሚርዛ ማጅደ-ዲንም አንዱ የእርሱ ተጠቂ ነው፡፡ በጣም ተገቢ ባልሆነ

ሁኔታ ኩራተኛና ግትር ነው፡፡ ይህ አሁን ይህን መጽሐፍ እየፃፈላችሁ ያለው ፀሐፊ በሐይፋ መንገዶች ላይ ይህንን ትዕቢተኛና አድብቶ የሚራመድን ሰው በዓይኑ ለማየት ችሎ ነበር፡፡ የእርሱ ታሪክ፣ ከሰማይ ወደ ምድር የተወረወውን ሉሲፈርን በአእምሮ ለማስታወስ ይጋብዛል፡፡

የአብዱል-ባሃም ትንቢት አንድ በአንድ ተፈፅሟል፡፡ ሚርዛ ማጅደ-ዲን፣ መንቀሳቀስ የማይችል፣ መናገር የተሳነው፣ ነገር ግን የሚያዩ ዓይኖች ያሉት፣ አካለ-ስንኩል ሆኖ ከመቶ ዓመት በላይ ኖሯል፡፡ ከባህጂ ቤተ-እልፍኝ ቀጥሎ፣ በሚገኝ አንድ የተተወ ቤት ውስጥ ይህ ቅስሙ የተሰበረ ሰው እስከ 1955 ድረስ ተጎሳቁሎ ተቀምጧል፡፡ ይህ ኃይለኛ ቃል-ኪዳን አፍራሽ ህግ ተላላፊዎች ላይ እምነቱ ድልን ሲቀዳጅ አይቷል፡፡ የአብዱል-ባሃ የልጅ ልጅ፣ የእምነቱ ሞግዚት፣ ሾጊ አፌንዲ፣ በባሃኡላህ ቃል-ኪዳን ማዕከል ተሰይሞ፣ የባሃኡላህን መካነ-መቃብርን፣ ቤተ-እልፍኙንና ሰፊውን የአበባ ስፍራውን በተገቢ ሁኔታ ሲያስውብና ሲያስጌጥ አይቷል፡፡

ሚርዛ ሙሐመድ ዓሊ በወቅቱ፣ ከአብዱል-ባሃ እህት ከታላቋ ቅድስ ቅጠል፣ የባሃኡላህን ግዞቶችና ፈተናዎች አብሮት ከተጋፈጠው ለቃል ኪዳኑ ያለውን ታማኝነት ካረጋገጠው ከባሃኡላህ ወንድም ከሚርዛ ሙሐመድ-ኩሊ ከሚስቱና ከልጆቹ በስተቀር፣ ሌሎቹን ጠቅላላውን የባሃኡ ላህን ቤተሰብ ማሸነፍ ችሎ ነበር፡፡ ሌሎቹ ከሚስቶቻቸውና ከባሎቻቸው ጋር በመሆን ቃል-ኪዳን ሰባሪነቱን መር ጠዋል፡፡ ሌላው የሚቹ የባሃኡላህ ወንድም የሚርዛ ሙሳ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆችም እንደዚሁ ቃል-ኪዳን ሰባሪ ነትን መርጠዋል፡፡ ክርስቶስ እንዲህ

ብሏል፡– ‘መሰናክሎች ይኖራሉ ነገር ግን ለዚያ አሰናካይ ወየውለት፡፡’

እነዚህ የባሃኡላህ ሥጋና ደም የሆኑት እንዴት ቃል-ኪዳን ሰባሪ ይሆናሉ በማለት አንድ ሰው ሊጠይቅ ይችላል። ታሪኩ እየቀጠለ ሲሄድ፣ ያደረጉት ድርጊት እንዴት አስፀያፊ እንደሆነ እናያለን። ባሃኡላህ በሕይወት በነበረበት ጊዜ የቅናታቸውን ፍንጭ ያሳዩ ነበር። አብዱል-ባሃ ገዝፎ ይታይ ነበር። እነርሱ ደግሞ መንፈሰ-ኮስማና ነበሩ፡፡

በባሃኡላህ እንደተመሰከረው፣ ቅናት ስጋን የሚያኝክ በሽታ ነው፡፡ እንደንብረቱ አድርጎ የያዘውን ያወድማል። ለሥልጣን የማይጠረቃ ፍላጎትም እንደዚያው አጥፊ ነው።

ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ የባሃኡላህ ልጅ የነበረና፣ በእርሱ ቃለ-ኑዛዜም ታላቁ ቅርንጫፍ በሚል ተሰይሞ የነበረ ቢሆንም ብዙዎቹ ባሃኢዎች ይህ የባሃኡላህ ልጅ ከዳተኛ ይሆናል ብለው አላሰቡም። ስለዚህ እጅግ ግራ ተጋቡ፡፡

በዚያ የግራ መጋባት ሞገድ ጫፉ ላይ በደረሰበት ወቅት፣ ሌላው ቀርቶ ታማኞቹና ፅኑዎቹ ተወናብደው ነበር። በባሃኡላህ እርገትና በእርሱ ቤተሰብ መካከል የሚታየውን ታማኝነት መጥፋት ምልክት በማየቱ ታሪክ ጸሐፊው ናቢል አዛም እጅግ ልቡ ተሰብሮ ራሱን ባህር ውስጥ ወርውሮ ገደለ። በእውነቱ እጅግ አስቸጋሪ ነበር፣ ባሃኡላህ ተከታዮቹን ቤተሰቡን እንዲያከብሯቸው መግለጹ ሲያስደንቅና ሲያስገርም የነበረ ቢሆንም፣ በሁሉም ዘንድ ሙገሳ የተቸረው እጅግ ታላቁ ቅርንጫፍ ላይ ንትርክ ሲያነሱ፣ በእውነቱ እጅግ አስቸጋሪ ነበር፡፡

አብዱል-ባሃ ፍፁም ብቻውን የሚሆንበት ጊዜ መጣ።

## ምዕራፍ 5
## የለየለት የክህደት አመጽ

ሙሐመድ-ዓሊ በስፋት መጓጓዝና መጻጻፍ ጀመረ፡፡ በቀጣይነትም የሐሰት ዘገባዎችን ያሰራጫል፣ የሽብርተኝነትን መርዝ ይረጫል በዚህም ምክንያት ደብዳቤዎች ወደ ቅድስት ሀገር መጉረፍ ጀመሩ፡፡

በፋርስ፣ በባሃኢዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የእምነቱ ታዋቂ አስተማሪ፣ አቃ ጃማል-ኢ-ቡሩጂርዲ፣ የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ ዋና ተከራካሪ ሆኖ አረፈው፡፡

የአምላክ ቃል-ኪዳን፣ ፀጋዎችንና ማረጋገጫዎችን የሚስብ ማግኔትና ሁሉም ነገሮች የሚዳኙበት እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ከዚያም አንድ ሰው በቃል ኪዳኑ መንገድ ለቅፅበት ከተጠራጠረ፣ በእውነት እርሱ የጥፋት ሠራዊት አባል እንደሚሆን ተጽፏል፡፡ የአቃ ጃማል እጣ ፈንታም አንዱ ምስክር ነው፡፡ የመከፋፈሉን እሳት ለማጋጋል የሞከረው የአካ ጃማል ጥረት ኪሣራ ገጠመው፡፡ ደረጃው ምንም ሊጠቅመው አልቻለም፣ ቀናቶቹም በመከራና በጭንቀት ተጠናቀቁ፡፡

አብዱል ባሃ ከእህቱ፣ ከሚስቱ፣ ከአራት ሴት ልጆቹ፣ እና ዕድሜ ጠገብ አጎቱ ጋር ለብቻቸው በአካ ተገለሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ ወደ አባቱ መካነ-መቃብር እንዳይገባ ተከለከለ፡፡ ፀሎቶቹንና ጉብኝቶችን ከሩቅ መስኩ ላይ ቆሞ የሚያደርግባቸው ጊዜያቶች ብዙ ነበሩ፡፡ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ እና ተባባሪዎቹ በባሃጂ የሚገኘው ቤተ-እልፍኝ፣ መካነ-መቃብሩ እና በአጠገቡ የነበሩት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ በእጃቸው ሆነ፡፡ በቤተ-እልፍኙ የላይኛው በረንዳ ላይ ተሰባስበው፣ የባሃኡላህ ሰብዓዊው መቅደስ

እንዲያርፍ በተደረገበት ቦታ፣ አብዱል-ባሃና የእርሱ ታማኝ ተከታዮች ለፀሎት ሲመጡ የስድብ ናዳ ያወርዱባቸው ነበር፡፡ ከመካነ-መቃብሩ ጎን አብዱል-ባሃ አንድ የአትክልት ስፍራ ለማዘጋጀት ይጣጣር ነበር፡፡ ከጥቅም ውጪ የሆነውን መሬት ለማበልፀግና በአበባ ለማሳመር፣ የለማ አፈርና ውኃ በታማኞቹ እየተረዳና፣ በእራሱ ትከሻ እየተሸከመ ያመጣ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎቹ፣ ያ ሁሉ ወጪ ወጥቶበት፣ ከፍተኛ ሥራና ጉልበት የፈሰሰበት የአትክልት ስፍራ ላይ እጃቸውን ከማሳረፍ አልታቀቡም፡፡

ሾጊ ኤፌንዲ እንደገለፀው፣ አንድ አርባ የሚሆኑ የባሃኡላህ ቤተሰብ አባላት፣ የባብ ዘመዶች፣ ታዋቂ ሰዎችና የእምነቱ አስተማሪዎች፣ የባሃኡላህን ቃል-ኪዳን በማዛ ባት ለአብዱል-ባሃ ታማኝነታቸውን ላለማሳየት ተባብረ ዋል፡፡

በማህበረሰቡ መካከል ጥላቻን ማዛመቱ አልበቃ ብሏቸው፣ የአብዱል-ባሃን ስም መበከል ተያያዙት፡፡ የአምላክ ክስተት ደረጃንና ማዕረግን ለራሱ አድርጓል፤ የባሃኡላህ ቤተሰብ የሆኑትን ዝና ለማጉደፍ ሞክሯል፣ ከሁሉም ነገሮች በማይመጣጠን መልኩ ለባሃኡላህ ኪዳን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፣ በቤተሰቡ መካከል እጅግ አጨቃጫቂ፣ በወንድሞቹና በእህቶቹ መካከል ያለውን ዝምድና ወደ ጎን የተወ ቃል-ኪዳን የሚልና ከትውልድ ውርሳቸው የሚከለክልና ራሱን ብቻ የሚያገን ሰነድ አዘጋጅቷል ፡፡ ባሃኢ ላልሆኑት ሰዎች፣ አብዱል-ባሃ ለዘመድ አዝማዶቹ ውርስ እንደከለከላቸው ይናገራሉ፡፡ እንዲህ ይሏቸዋል፣ ባሃኡላህ፣ የአምላክ ክስተት ነኝ አላለም፣ እርሱ፣ ሰዎችን ወደ አምላክ ለማቅረብ የሚፈልግ፣ ምስጢራዊ ረቂቅ

ሼይህ እንጂ፣ የአምላክ ክስተት ነኝ ብሎም አያውቅም፣ አብዱል-ባሃ ግን አዲስ ሃይማኖት ለመፍጠር የሚፈልግ ነው በማለት ይነግሯቸዋል፡፡

በዚያን ጊዜ የዓይን ምስክር የሆኑት፣ ሐጂ ሚርዛ ሃይዳር-ዓሊ፣ በባሃጂ ቤተ-እልፍኝ በሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ ደጋፊዎች ሲከናወን የነበረውን ሁሉ የፅሁፍ ማብራሪያ ሰጥተዋል፣ በጉልህ እንደሚታየው ከአብዱል-ባሃ በአካ ከነበረው ተራና የተወሰነ ሕይወት አንፃር፣ እነርሱ ያለማቋረጥ እጅግ አብዝተው ምርጥ ምርጡን እንዲደረግላቸው ያዛሉ፣ ከሚያስፈልጋቸው በላይ የሆኑ ሸቀጦችና አልባሳት ይገዛሉ፣ ተገቢ ያልሆኑ ግብዣዎችን ያዘጋጃሉ፣ የቅንጦት ምግቦችን በማዘጋጀት ባለሥልጣናትን ያዝናናሉ፡፡ ዓላማቸውም እነዚህ ባለሥልጣናት በአብዱል-ባሃ ጥላቻ እንዲሞሉ ነበር፡፡ በዚህም አብዱል-ባሃን ወደ ድህነት አዘቅት እንዲወርድና፣ ኪሣራ ውስጥ ለመክተት ነበር፡፡ ነገር ግን አብዱል-ባሃ ለሚያቀርቡት የገንዘብ ጥያቄ ሁሉ በፍፁም አይከለክልም፡፡ ጥያቄያቸው ሲመጣ የእርሱ ባለሟል የሆነውን አቃ ሪዳ-ኢ-ቃናድ፣ እንዲተባበር ያዛል፡፡ ስጦታዎች ሲመጡ አብዱል-ባሃ ወደ ባህጂ እንዲላክ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ በእርሱ ላይ ያሴሩት ክፉ ሥራዎቻቸው ከሚያስከትሉ ባቸው መዓት ለመታደግ፣ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡ ሸፍጣቸውን ለመከለል የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ በባሃኡላህ ቃለ-ኑዛዜ ከአብዱል-ባሃ ቀጥሎ እንዲከተል ደረጃ የተሰጠው ስለሆነ አብዱል-ባሃ ከእርሱ ህልፈት በኋላ የፈለገው ሁሉ እንደሚሆንለት አስታወቀው፡፡ ለዚህ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ የሰጠው ምላሽ፣ ከአብዱል-ባሃ በኋላ በሕይወት ለመቆየቱ ዋስትና እንደሌለው ሲሆን፣ ለስልጣን ያለው ጉጉት ለባሃኡላህ

ቃላት ምንም አይነት የእምነት ጭላንጭል እንዳይኖረው አደረገው፣ ይህም ጥማቱ ወደ ገደል ከተተው፣ አጠፋው። ከአብዱል-ባሃ በኋላ ለአሥራ ስድስት ዓመት በባሃኡላህ የዓለም ማህበረሰብ ተጠልቶ፣ ተስፋ የቆረጠ ሰው ሆኖ፣ በመከራ ኖሯል።

የቃል ኪዳኑ ጥንካሬ ቀስ በቀስ ከፍ ማለት፣ በቃል-ኪዳኑ ዋልታ ሥር የአብዛኛው ባሃኢዎች መሰለፍ፣ ጨመረ። የማዛባትና የማጣመም የማይሳካ ጥረታቸው ለዓመታት ቢቀጥልም፣ ነገር ግን ውድቀታቸው ፈጣን ሆነ።

## ምዕራፍ 6

## የምዕራቡ ዓለም ደቀ-መዛሙርት

የሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ እውነተኛ ማንነት መጋለጥና የባሃኢዎች ወደ አብዱል-ባሃ መዞር በምዕራቡ ዓለም የእምነቱ መተዋወቅ ጋር በትይዩ የተከናወነ ሂደት ነበር፡፡

የባብና የባሃኡላህ እምነት ለምዕራብ አገሮች እንግዳ አልነበረም፡፡ ወደ ምሥራቁ ዓለም በተጓዙ ባለሥልጣናትና ተመራማሪዎች አማካይነት ስለእምነቱ አስተሳሰብ ውልደትና እድገቱ በስፋት በፅሑፍ ይቀርብ ነበር፡፡ አይርላንዳዊዋ ጸሐፊ እመቤት ሺይል፣ “የፋርሳውያን ሕይወትና አኗኗር” በሚል የጻፋቸው የታተመው በ1856 ነበር፡፡ እናም በኦገስት 1852 ስለተከናወኑት ሁኔታዎች ግልፅ እማኝነትን ይሰጣል፡፡ ቋንቋ ተመራማሪው ተጓዥ አር.ቢ.ኤም. ቢኒንግ “የሁለት ዓመት የፋርስ ጉዞ ማስታወሻ” እትም ውስጥ ስለ ባብ ጽፎ ነበር፡፡ ፈረንሳዊው ጸሐፊና አምባሳደር ጆሴፍ ኤ.ጎቢኒኡ በ1865 ያሳተመው “በማዕከላዊ እስያ ውስጥ ሃይማኖቶች እና ፍልስፍናዎች” የተባለው ዝነኛ መፅሐፉ፣ ምዕራቡን ዓለም በፋርስ ስለ ተከናወነው ልዩ ሁኔታዎችን በበቂ ሁኔታ አሳውቋል፡፡ የታወቀው የእንግሊዝ የምስራቅ አህጉራት ተመራማሪ፣ ኤድዋርድ ግራንቪል ብራውን ጥናት እንዲያደርግ ያነሳሳውና ባሃኡላህን ለመጎብኘት ያበቃው ይህ መፅሐፍ ነበር፡፡

1893 ሴፕቴምበር 27፣ በዓለም ሃይማኖቶች ፓርላማ ስብሰባ ወቅት፣ የክርስትና ሃይማኖት ለማስፋፋት የበጎ አድራጎት ሥራ ተልዕኮው በሶርያ ያካሂድ የነበረው የቄስ ሔንሪ ኤች. ጄሰፕ የጥናት ጽሑፍ፣ በተመሳሳይ

አገልግሎት በሚሰጠው በቄስ ጆርጅ ኤ. ፎርድ ቀረበ። ማጠቃለ ያው እንዲህ ይል ነበር:–

ከአካ ምሽግ ውጪ፣ በሶርያ ባህር ዳርቻ፣ ባሃጂ ወይም የደስታ ቤተ-እልፍኝ፣ ከጥቂት ወራት በፊት ዝነኛ የፋርስ ዓዋቂ ሰው፣ የባቢ ቅዱስ ሰው፣ ስሙ ባሃኡላህ – 'የአምላክ ክብር' – የሚባል፣ ሰፊ የሆነው የፋርስ ሙስሊሞች የህዳሴ ለውጥ መሪ፣ አዲስ ኪዳንን እንደአምላክ ቃልና ክርስቶስን እንደ ሰው ልጆች አዳኝ የሚቀበል፣ ሁሉንም አገሮች እንደ አንድ፣ ሁሉንም ሰዎች እንደወንድማማች የሚያይ መሪ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ከሦስት ዓመት በፊት በአንድ የካምብሪጅ ምሁር(ኤድዋርድ ግራን ቪል ብራውን) ተጎብኝቶ ነበር። ምሁሩ ከእርሱ አንደበት የሰማውን በማቅረብ ንግግሬን አበቃለሁ:–

'ሁሉም ሀገሮች በሃይማኖታቸው አንድ እንዲሆኑ እና ሁሉም ሰዎች አንድ እንዲሆኑ ፤ በሰው ልጆች መካከል ፍቅርና አንድነት እንዲጠናከር፤ የሃይማ ኖቶች ልዩነት ያበቃ ዘንድና የዘር ልዩነት ጭራሹን ይወገድ ዘንድ። ...እነዚህ ፍሬቢስ ክርክሮች፣ እነዚህ አጥፊ ጦርነቶች ያልፉሉ፣ "እጅግ ታላቁ ሰላም" ይመጣል። እናንተ በአውሮፓ ያላችሁትስ ይህንን አትፈልጉትምን?'

በሰሜን ሶርያ እየተንቀሳቀሰ ያለው፣ የክርስትና በጎ አድራጎት ቄስ ጆርጅ ፎርድና ሔንሪ ጄሰፕ የጥናት ጽሑፍ በጉባዔው ላይ መቅረቡ፣ እነሱ ባያውቁትም በምዕራቡ ዓለም ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ እንዲከፈት ምክንያት ሆነ።

ኢብራሂም ጆርጅ ካይሩላህ በሊባኖስ ተራራማ አካባቢ ባለ መንደር የተወለደና በሶርያ ፕሮቴስታንት ኮሌጅ የተማረ፣ የአረብ ክርስቲያን ነበር፡፡ ዝናው ከገነነው በቤይሩት ከሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ከመጀመሪያዎቹ የህክምና ተመራቂዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ከሶርያ ወደ ግብፅ በመሄዱ በካይሮ ባሃኢዎችን የመገናኘት ዕድል ገጠመው፡፡ ስለእምነቱ ያስተማረው፣ ከቴህራን የመጣ ነጋዴ፣ በግብፅ የሚኖር፣ ሐጂ አብዱል-ካሪም የሚባል ባሃኢ ነው፡፡ ካይሩላህ እምነቱን የተቀበለው ባሃኡላህ በሕይወት በኖረበት ዘመን ስለነበረ፣ ፅላትን በመጎናፀፍ ክብር አግኝቷል፡፡ በወቅቱ ጨቋኝ ከሆነው የኦቶማን መንግሥት በመሸሽ በአዳዲስ አድማሶች ኑሮን ለመመሥረት በተለይ የክርስቲያን ሊባኖሶች ወደ አሜሪካ በስፋት ይሰደዱ ነበር፡፡ ዶ/ር ካይሩላህ ግን በመካከለኛው ምስራቅ ተወስኖ ነበር አትላንቲክን አቋርጦ መሄድ የሚያነሳሳው ጉዳይ ሆነ፣ ሐጂ አብ ዱል-ከሪምም ማበረታቻ እና ድጋፍ ሰጡት፡፡ ካይሩላህም ለአብዱል-ባሃ በመጻፍ ድጋፉን አገኘ፡፡

በዚህ ምክንያት ዶ/ር ኢብራሂም ጆርጅ ካይሩላህ ዴሴምበር 1892 ወደ ኒውዮርክ ሄደ፡፡ በ1894 የባሃኡላህ ስም በሃይማኖት ጉባዔው ወደ ተጠራባት፣ ወደ ቺካጎ ተዛወረ፡፡ በእዚያም አጅግ በጣም ታላቅ ጥረት በማድረግ እምነቱን ለመስማት የሚሹ ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎችን አገኘ፡፡ በዚያው ዓመት የባሃኡላህ እምነትን ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ የመጀመሪያውን ሰው አገኘ፡፡ ያ ሰው ከጊዜ በኂላ አብዱል-ባሃ ፅኑው የሚል አዲስ ስም የሰጠው፣ ቶርንቶን ቼዝ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ በምዕራብ አገሮች እምነቱን ሲያውጅ በሕይወት ለመቆየት ባይችልም፣ አብዱል-ባሃ አካ በነበረበት ወቅት ጎብኝቶታል፡፡

ከጊዜ በኋላ አብዱል-ባሃ በሳንፍራንሲስኮ ጎዞው ወቅት የቶርንቶን ቼዝን ሞት ሲሰማ፣ ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ፣ በሎስ አንጀለስ ኢንግልውድ ቀብር ስፍራ በዚህ ፅኑ አማኝ መካነ-መቃብር ቦታ ላይ ቆሞ እንዲህ አለ:–

> ይህ የተከበረ ሰው ለአሜሪካ የመጀመሪያው ባሃኢ ነበር። እምነቱን በታማኝነት አገልግሏል፣ ግልጋሎቱም በመጪዎቹ ዓመታትና ዑደቶች የሚዘከር ይሆናል፣...ለአሁኑ ፋይዳው እጅግም ግልፅ አይደለም፣ ነገር ግን ወደፊት ግምቱ የትየለሌ ይሆናል። የእርሱ ፀሐይ እንዳበራ ይቀጥላል፣ የእርሱ ኮኮብም ብርሐኗን እንደሰጠች ትቀጥላለች። ሰዎች ይህንን የቀብር ቦታ በክብር ይጎበኙታል። ስለዚህ፣ የአምላክ ወዳጆች ይህንን የቀብር ቦታ መጎብኘት እና በእኔ ስም አበቦችን በማስቀመጥ የእርሱን መንፈሳዊ ደረጃ ታላቅነትን ማወደስ አለባቸው ይህ ሰው ሊረሳ አይ ገባውም።

አብዱል-ባሃ የእምነቱ ሰንደቅ፣ በማለት የሚጠራት፣ ሾጊ ኤፌንዲ ደግሞ ‘የእምነቱ የምዕራቡ ዓለም እናት’ ሲል የሰየማት፣ ሉዊሲያ ኤ. ሙር፣ ሌላዋ አሜሪካዊ ባሃኢ የተለየችና ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ የነበረች ነች። ሄለን ኤስ. ጉድኦል፣ ኢዛቤላ፣ ሊሊያን፣ አርተር ፒ. ዶጅ፣ ዶ/ር ኤድዋርድ ጌትሲንገር፣ ሐዋርድ ማክነት፣ ፖል እና ቼስተር ጎላ ብለው የሚታዩ ሲሆኑ፣ ከዚያም ያቺ ታዋቂዋና ፅኑዋ፣ እውነተኛዋ ፋና ወጊ፣ ሉዋ ጌትሲንገር መጣች። የባሃኡላህን እምነት ከሉዋ ጌትሲንገር ሰምተው ለእምነቱ ከፍተኛ ግልጋሎት ብርሐን ከሆኑት መካከል፣ ጥበብና እይታ የታደለችው፣ ሜይ ኢሊስ ቦለስ ትገኝበታለች። የታዋቂ ሰው ባለቤት የሆነችው፣ ፊቢ

ኸርስት፣ የባሃኡላህን እምነት የሰማችው ከሉዋ ጌትሲንገር ነበር። በ1898 ኸርስት አዱል-ባሃን ለመጎብኘት ወደ ቅድስት ሀገር ለመሄድ ወሰነች። በዚህ ታሪካዊው የመንፈሳዊ ጉብ ኝት ጉዞ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል የምዕራብ አገራት ባሃኢዎች አብረው እንዲጓዙ ጋበዘች። ከተጋበዙት መካከል ኤድዋርድና ሉዋ ጌትሲንገር እንዲሁም ዶ/ር ኢብራሒም ካይሩላህ ከነሚስቱ ነበሩበት።

በፈረንሳይ ዋና ከተማ በፓሪስ የሚኖሩ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎችም መንፈሳዊ ተጓዦቹን ተቀላቀሉ። ከእነርሱ መካከልም የሚሰስ ኸርስት ዘመድ የሆኑት፣ ኮርበር እና ልጇ ሚሪያም ኮርበርና ሜይ ቦለስ ይገኙበታል። ግብፅ ላይም እንዲሁ ሌሎች ተጨምረዋል፣ ቁጥራቸውም ወደ አሥራምስት ደርሶ ነበር በጊዜው በነበረው አስጊ ሁኔታ ራሳቸውን ለሦስት በመክፈል፣ የመጀመሪያዎቹ በዴሴምበር 10 1898 አካ ደረሱ።

በባሃኡላህ እምነት ታሪክ ውስጥ ይህ እጅግ ታሪካዊ ቀን ነበር። የምዕራብ ሰዎች፣ በስልጣኑና በትምህርቶቹ ፍቅር አድሮባቸው አክብሮታቸውን ሊገልፁ፣ ወደ አምላክ ክስተት በር ደጃፍ ሲመጡ፣ ታይቶ አይታወቅም።

በምዕራብ አገር ያሉ ባሃኢዎች አብዱል-ባሃ ፊት መቅረ ባቸው የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። የዚህ ግንኙነት ውጤት ምንድነው? መንፈሳዊ ተጓዦቹ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጡ? ኮርበር እንዲህ ስትል ጽፋ ነበር፡–

> ከግብፅ ወደ ሐይፋ ለመሄድ አንዲት መጠነኛ መርከብ ተሳፈርን ። ማዕበል ነበር፣ በዚያች እዚህ ግቢ በማትባለው በእንፋሎት የምትሠራዋ መርከብ ላይ ሆነን ማዕበሉ ያለ ርህራሄ ይደበድበን ነበር።

የደረስ ነው በምሽት ሲሆን ለአብዱል-ባሃም ሆነ ወደ ከተ ማዋ ለሚገቡ እንግዶች አደገኛ ስለነበር እንደደረስን ወደ አንድ ሆቴል አመራን፡፡

ከዚያም ሲጨልም ጋሪ ይዘን በባህሩ ዳርቻ አድርገን ወደ ጆርዳን በሚወስደው መንገድ' በአስቸጋሪው የአሸዋ ጎዳና ወደ እስር ከተማው አመራን፡፡ ታማኙ ጋሪ ነጂያችን በደንብ አስተናገደን፡፡ ወደ ከተማው ከገባን በኋላ የሚጠብቁንን ወዳጆች ማግኘት ቻልን አብዱል-ባሃን ለማግኘት የቤቱን ደረጃዎች መውጣት ጀመርን፡፡ አንዲት ትንሽ ሻማ ይዞ የሆነ ሰው ከፊት ለፊታችን ቀደመ፡፡

የሻማው ብርሃን በፈጠረው ጥላ አንድ የተለየ ቅርፅ በድንገት አየን፡፡ የሻማው ብርሃን እየገለጠልን ሲመጣ አብዱል-ባሃ መሆኑን አወቅን፡፡ ነጩ ካባው፣ ብርማ ፀጉሩ፣ የሚያንፀባርቁት ሰማያዊ ዓይኖቹ፣ ከሰውነት ህላዌ ይልቅ የመንፈስ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ስለተቀበለን ጥልቅ ምስጋና ለማቅረብ እየሞከርን ነበር፡፡ አብዱል-ባሃም 'በመምጣታችሁ ብቻ በጣም ጥሩ ሰዎች ናችሁ' አለን፡፡

ከዚያም ፈገግ አለ፣ ደስ የሚልና የሚከበር ብርሐንና ፀዳል ተጎናጽፏል፡፡ እጅግ የሚገርም ነገር ነበር፡፡ ከምዕራቡ ዓለም የመጣነው እኛ አራቱ ጎብኚዎች፣ ተራራውን፣ ባህሩን አገሮችን ስናቋርጥ ከገጠሙን ምቾት የሚነሱ ነገሮች አንጻር፣ አብዱል-ባሃን አግኝተን የመንፈስና የቃላት ሃብት መጎናጸፋችን ጋር ስናስተያየው የከፈልነው ዋጋ ኢምንት ነበር፡፡ ይህም 'ትምህርቶቹን ለማሠራጨት'፣ 'የባሃኡላህን

ስም ለማውሳትና፣ በዓለም ሁሉ የእርሱን መልእክት ለማዳረስ’ በቂያችን ነበር።

ፊቢ. ኸርስት፣ መንፈሳዊ ጉዞዋን በማስመልከት ከአንድ ዓመት በኋላ እንዲህ በማለት ፅፋ ነበር፡-

አካ የቆየነው ለሦስት ቀናት ብቻ ነበር፣ ነገር ግን ላረጋግጥላችሁ የምወደው ነገር እነዚያ ሦስት ቀናት በህይወቴ እጅግ የማይረሱ ቀናት ነበሩ፣ አሁንም ቢሆን በምንም ዓይነት እነዚያን ጊዜያት ልገልፀውና ላብራራው አይቻለኝም።

ከቁሣዊ ሁኔታ አንፃር ምንም ነገር አልነበረም፣ ነገር ግን ቦታውን አልብሶት ያለው መንፈሳዊው ድባብ በአማኞቹ መካከል በህይወታቸውና በድርጊታቸው በግልፅ ይታይ ነበር። በእውነት አስገራሚና ከዚህ በፊት በጭራሽ አጋጥሞኝ የማያውቅ ነው። እነርሱ የተቀደሱ ሰዎች እንደሆኑ በማየት መረዳት ይቻላል።

አብዱል-ባሃን ልገልፀው አልሞክርም። ለማለት የምችለው ነገር ቢኖር በሙሉ ልቤ እርሱ ጌታ እንደ ሆነ አምናለሁ፣ በዚህ ዓለም ላይ ያገኘሁት ታላቅ ቡራኬ የምለው ወደ እርሱ ቅርበት መድረሴንና የእርሱን ቅዱስ ፊት ለማየት መታደሌን ነው። የእርሱ ሕይወት በእውነት የክርስቶስ ሕይወት ነው፣ መላ እርሱነቱ ንፅህናንና ቅድስናን ያንፀባር ቃል!

ያለምንም ጥርጥር አብዱል-ባሃ የዚህ ቀንና የዚህ ትውልድ መሲህ ነው እናም ወደ ሌላ መመልከት የለብንም።

እንደገና በ1899ዎቹ ማገባደጃ ላይ ለአንድ ሰው የቅድስት ሃገር ጉብኝቷን በማስመልከት ደብዳቤ ጽፋ ነበር:–

> ...በአካ ያደረግሁትን ጉብኝቴን በተመለከተ አብዱል-ባሃ ዘንድ የመቅረቤን ዕድልና በቅዱስ ቤተሰቡ ስላሳደረብኝ ተፅዕኖ ጥቂት በማለት፣ እምነቱን ለመቀበል ለፈለገ ሁሉ ያለኝን ለማካፈል ደስተኛ ነኝ፡፡
>
> ለእኔ እንደሚመስለኝ ሐቀኛ እውነት ፈላጊ የሆነ ማንም ሰው ገና በጨሉቅታ ተመልክቶ፣ እርሱ ጌታው እንደሆነ ያውቃል! ያለጥርጥር፡፡ እውነት ለመናገር በዚህ ዓለም ላይ እንዲያጋጥመኝ የምጠብቀው የነበረ እጅግ አስገራሚ ህላዌ ነው፡፡ ምንም እንኳ እርሱ ማንንም ለማስገረም የጣረ ባይሆንም፣ ከእርሱ የሚፈነጠቀው ጥንካሬው፣ ኃይሉ፣ ንፅህናው፣ ፍቅሩና ቅድስናው፣ ግርማ ሞገሱ፣ ትህትና ከተላበሰ ማንነቱ እና ከብቦት ያለው መንፈሳዊው ድባብ በእርሱ አቅራቢያ በሚገኙት ሁሉ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ሙሉ ለሙሉ ለመግለፅ በፍፁም አይቻልም፡፡ እኔ በሙሉ ልቤ እና ነፍሴ በእርሱ አምኛለሁ፡፡ እነዚያ እራሳቸውን አማኞች ብለው የሚጠሩት ለእርሱ ታላቅነት፣ ለእርሱ ክብር፣ እና ለእርሱ ውዳሴ እጃቸውን እንደሰጡ ተስፋ አደርጋለሁ፣ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ የአብ መንፈስ በእርሱ ውስጥ ይኖራል፡፡

አሁን ደግሞ ከምዕራባውያኑ መንፈሳዊ ተጓዦች ወጣት የሆነችው ደፋርና ከፍተኛ ተሰሚነት የነበራት፣ ለቀጣዮቹ አርባ ዓመታት የባሃኡላህን ሃይማኖት በተለየ ታላቅ

ባለሟልነት ያገለገለችው ሜይ ኢሊስ ቦለስ የሰጠችው ምስክርነት ከዚህ የሚከተለው ነው፡–

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በክፍሉ ደጃፍ ላይ ጭል ጭል በሚለው ብርሐን ከግድግዳው አጠገብ በፀጥታ ቁጭ ብዬ፣ የእኔን እጅግ ተወዳጅ አየሁት። እራሴን በእግሮቹ ስር ደፋሁ፣ ቀስ ብሎ አነሳኝና ከአጠገቡ አስ ቀመጠኝ። ከዚያም በመቀጠል ልቤን በሚነቀንቅ ድምፁ በፋርስ ቋንቋ የሆኑ የፍቅር ቃላትን ተናገረ፤ ብቻ በድንገት ወደ ታላቅ ከፍታ ተወሰድኩ፣ ነፍሴ ከመለኮታዊ መንፈስ ጋር ተገናኘች፤ ይህ ፍፁም ንፁህ ኃይል፣ እጅግ ኃያል ስለሆነ ሁለመናዬን አጥለቀለቀው።

ከእርሱ ከተከበረ ገጽ ላይ ዓይኖቻችንን መንቀል አንችልም። በእርሱ ጋባዥነት ሻይ እንጠጣለን፤ ነገር ግን እርሱ አብሮን ሲሆን ሕይወት የቆመ ይመስላል። ከዚያም ብድግ ብሎ ትቶን ሲሄድ ወደ ህይወታችን እንመለሳለን፣… ንጉሡን በእርሱ ውበት ውስጥ አይተነዋል። እጅግ በጣም ሩቅ የሆነውን እውነታ አይተነዋል።

አብዱል-ባሃ መንፈሳዊ ጎብኚዎቹን አንድ ቀን ጠዋት፣ ባሃኡላህ እረፍት ባደረገበት ዛፎች ጥላ ስር በቀርሜሊዮስ ተራራ ላይ ሊያገኛቸው ፈለገ። ነገር ግን ሜይ ቦለስ ታመመች፣ አብዱል-ባሃም ሊጠይቃት ሄደ። የልብ ምቷን አዳመጠና እንዲህ አላት ፡–

‘ዛሬ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ መሰባሰብ አይኖርብንም። የታመመችውን የአምላክ ተወዳጅ ብቸኛዋን ትተናት አንሄድም። ሁሉም ተወዳጆች

ደስተኛ ካል ሆኑ እኛም ደስተኞች ልንሆን አንችልም’ አለ፡፡

ሁላችንም ተገረምን፡፡ በዚያ የተቀደሰ ስፍራ ላይ ሊካሄድ የነበረው እንደዚያ ዓይነቱ በጣም አስፈላጊ ስብሰባ በአንድ ሰው ህመም ምክንያት መሰረዙ ሊዋጥልን አልቻለም፡፡ ከተለመደው አስተሳሰብና አሠራር ሁሉ ተፃራሪ ነበር፣ የቀን ተቀን ሁኔታ ዎችና ቁሳዊ አጋጣሚዎች የላቀ ቅድሚያነት በሚሰጣቸው በዚህ ዓለም ሕይወት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በእርግጥ እውነተኛ መደናገጥ ፈጠረብን፡፡ የአብዱል-ባሃ ቃላት የእግዚአብሔር መንግሥት በሮች በሰፊው ተከፍተው ህጉ ፍቅር ብቻ የሆነበት የወሰን የለሹ ዓለም ራዕይን ሰጠን፡፡ ይህ እንግዲህ የአብዱል-ባሃን ከሁሉም ነገሮች በላይ ለእያንዳንዷ ነፍስ ያለውን ፍቅር፣ ሐዘኔታና ርህራሄ ያየንበት አጋጣሚ ነበር፡፡

በእነዚህ መንፈሳዊ ተጓዦች ውስጥ የሚሲስ ኽርስት ጥቁር ባለሟል ሮበርት ተርነር ተካቷል፡፡ በአሜሪካ አህጉር የባሃኡላህን ሃይማኖት ለመቀበል በእርሱ ዘር የመጀመሪያው የመሆን ዕድልን አግኝቷል፡፡ አንድ ቀን አብዱል-ባሃ ከመንፈሳዊ ጎብኚዎቹ ጋር ተቀምጦ ሳለ፣ ሁሉም አብረው እንዳሉ ጠየቀ፣ ከዚያም ባለሟላቸው አብሯቸው እንዳልሆነ ተገነዘበ፣ ‘ሮበርት የት አለ?’ ሲል ጠየቀ፡፡ ከዚያም ያ ምስኪንና ፅኑ ሰው እነሱ ወዳሉበት ክፍሉ ሲገባ፣ አብዱል-ባሃ ከመቀመጫው ተነስቶ በናፍቆት ሰላምታ ሰጠው፡፡ ሮበርት ከሌሎቹ ጋር አብሮ ተቀመጠ፣ ‘ሮበርት አንተን አምላክ ይወድሃል፣ አምላክ

ጥቁር ቆዳ ሰጥቶሃል፣ልብህም እንደበረዶ የፀዳ ሆኗል፡፡’ አለው፡፡

ጉብኝታቸው በጣም አጭር በመሆኑ የሚሄዱበት ቀን እየተቃረበ መጣ፡፡ ሐሳቡ በራሱ ለመሸከም የሚከብድ ነበር፣ ለመላቀቅም ከባድ ሆነ፡፡ ሩህሩሁ አብዱል-ባሃ እንዲህ አላቸው፡–

> አሁን እኔ ትዕዛዜን እሰጣችኋለሁ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል የሚደረግ ቃል-ኪዳን ነው፡፡ እምነት ይኑራችሁ፡፡ ይህም እምነት እንደአለት የጠነከረ ምንም ዓይነት ማዕበሎች የማያናውጡት፣ ምንም ነገር ሊረብሸው የማይችል፣ ሁሉንም ነገሮች እስከ መጨረሻው መቋቋም የሚችል ሌላው ቀርቶ ጌታችሁ ተሰዋ የሚል ነገር ብትሰሙ እንኳ በእምነታችሁ መናወጥ የለባችሁም፡፡ እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፣ በሕይወት ብኖርም ብሞትም፣ እኔ እስከመጨረሻው ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ እምነቱ እስካላችሁ ድረስ ኃይላችሁና ቡራኬያችሁ አብሯችሁ ይኖራል፡፡ ሚዛኑ ይህ ነው፤ ሚዛኑ ይህ ነው፤ ሚዛኑ ይህ ነው፡፡

በመለያያቸው ሰዓትም እንዲህ አላቸው ፡–

> …መለያየት ለአካል ብቻ ነው፣ በመንፈስ ግን አንድ ነን፡፡ እናንተ እንደሚሰራጭ ብርሐናት ናችሁ፤ እናንተ እንደ ባህር ማዕበል በመስፋፋት ተትረፍርፎ እንደሚፈስሰው ናችሁ፤ ሌላ የምሰጣችሁ ትዕዛዝ፣ እኔ እንደወደድኋችሁ ሁሉ እናንተም እርስ በእርሳ ችሁ ተዋደዱ፤ አንዳችሁ አንዳችሁን በፍፁምነት ዓይን እዩ፤ እኔን ተመልከቱ፣ ተከተሉኝ፣ እንደኔ

ሁኑ፤ ስለእራሳችሁ ሆነ ስለኑሯችሁ፣ ስለመብላታችሁ ወይም ስለመተኛታችሁ፣ ስለምቾታችሁ፣ ስለደህንነታችሁ ሆነ ስለህመማችሁ፣ ከወዳጆቻችሁም ሆነ ከጠላቶቻችሁ ጋር ብትሆኑ፣ ውዳሴ ወይንም ወቀሳ ቢደርስባችሁ ምንም አታስቡ፡፡ እኔን ተመልከቱ እናም እንደ እኔም ሁኑ፤ ስለእራሳችሁና ስለ ዓለም መሞት አለባችሁ፣ ከዚያም ወደ መንግስተ ሰማይ ትገቡ ዘንድ እንደገና ትወለዳላችሁ፡፡ ሻማን ተመልከቱ እንዴት ብርሐን እንደምትሰጥ፡፡ የብርሐን ነበልባሏን ትሰጥ ዘንድ ጠብታ በጠብታ ህይወቷን ታስወግድ ዘንድ ታነባለች፡፡

ለሚይ ቦለስ አብዱል-ባሃ ለብቻዋ የተለየ ሥራ ሰጣት፣ በፓሪስ በመቆየት እምነቱን እንድታስተምር ነገራት፡፡ በጥቂት ወራትም ውስጥ በአውሮፓ አህጉር የመጀመሪያ የሆነውን የባሃኢ ማዕከል በዚያ ከፈተች፡፡ ከሜይ ቦለስ ጋር አብራ መንፈሳዊ ጎብኚ የነበረችዋ እንግሊዝዊት፣ በ1899 በበጋው ወራት በብሪታኒያ ደሴቶች ሁለተኛዋን ባሃኢ ወደ እምነቱ እንድትመጣ ረዳች፡፡ ለባሃኡላህ ሃይማኖት አርአያነት ባላት ፅናት ለቀጣዮቹ ሰላሳ ዓመታት ስታገለግልና ስታስተምር የነበረች አስገራሚ ሴት ኢተል ጀነር ሮስንበርግ በኖቬምበር 17 1930 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡

የመጀመሪያውን እንግሊዛዊ ቶማስ ብሬክዌልን በፓሪስ ያገኘችው ሜይ ቦለስ ስለዚህ አስደናቂ ስሜትን የሚነካ ግንኙነት ስታወሳ፡-

ጊዜው 1901 የበጋ ወራት ነበር፡፡ በሃያዎቹ ዕድሜ የሚገኝ እንግሊዛዊ ወጣት ቶማስ ብሬክዌል፣

> በደቡብ አሜሪካ ለሚገኝ የጥጥ ፋብሪካ ኃላፊ የሆነና በሚያጓጓ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነበር፡፡ ለእረፍትም ወደ አውሮፓ መጣ፡፡ እኔም ቆይታዬን በፓሪስ አድርጌያለሁ፡፡ እናቴ በበጋው ወራት ወደ ብሪትኒ ልትወስደኝ ፈልጋ ነበር፣ ነገር ግን አብዱል-ባሃ በምንም ዓይነት ከፓሪስ እንዳትሄጂ ብሎ አስጠንቅቆኛል፡፡ 'ደስተኛ ያልሆነችውና የተበሳጨ ችው እናቴ ለብቻዬ ትታኝ ሄደች፡፡'

የቶማስ ብሬክዌልና የእርሷ የጋራ ጓደኛ የሆነ ሰው፣ ቶማስ ብሬክዌል ለፍልስፍናና ለየት ላሉ አስተሳሰቦች መሳቡን ያውቅ ስለነበር ከሜይ ቦለስ ጋር እንዲገናኙ አደረገ፡፡ አንድ ቀን ጠዋት ከበሯ ደጃፍ ላይ ሁለቱንም አገኘቻቸው፡፡ እንዲህ ስትል ታስታውሳለች :—

> 'ትኩረቴ በዚህ ወጣት ላይ ሙጭጭ ብሎ ነበር፣ መካከለኛ ቁመት አለው፣ ቀጭን፣ ቀጥ ያለ፣ ጠልቀው የሚያዩ ዓይኖች ያሉት፣ እና በቃላት ሊገለፅ የማይችል ለዛ ያለው ሰው ነበር፡፡' በመጀመሪያው ግንኙነታቸው ወቅት ሜይ ቦለስ በጥልቅ ልቦናና በሙሉ ትጋቷ እያገለገለች ስላለው እምነት ምንም አላላችም፡፡ በስነ መለኮት ዙሪያ በማውራታቸው ስለዚህ እሳቤ ዝንባሌ አላት ሲል ቶማስ ብሬክዌል ገመተ፡፡ ነገር ግን ሜይ በእርሱ ወስጥ ያየችውን ነገር በራሷ ቃላት ስትገልፅ፣ 'ከፍተኛ የአቋም ቁመና ያለው፣ ጨዋ፣ ቀለል የሚል፣ ግልፅ፣ ለሕይወት ባለው አመለካከት ላይ አስመሳይነት የሌለበት፣ እጅግ ብርቅዬ ነበር፡፡' በሚቀጥለው ቀን ተገናኝተው ይጫወቱ እንደሆነ ፍቃድ ጠየቃትና በቀጣዩ ቀን ጠዋት መጣ፡፡ ሲደርስ

> በከፍተኛ ስሜት መነሳሳት ውስጥ ነበር፣ ከዚያም ሜይ ቦለስን ስለእርሱ የሆነ 'የተለየ ነገር' አይታ እንደሆነ ጠየቃት፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ:–
>
> ትናንት እዚህ በነበርኩ ጊዜ የሆነ ኃይል ተሰምቶኛ ነበር፣ ከዚህ በፊት በህይወቴ ላይ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አጋጥሞኝ የነበረ ሲሆን ተፅዕኖውም በዚያን ጊዜ ለሦስት ወራት ያለማቋረጥ ከአምላክ ጋር አገናኘኝ፡፡ በዚያን ወቅት በተዝናና ድባብ ላይ በብርሐንና በውበት ስሄድ ይሰማኝ ነበር፡፡ ልቤ በከፍተኛው ተወዳጅ ፍቅር፣ ተቀጣጥላ ነበር፣ ከእኔም ሆነ ከእኔ ብጤ ሰዎች ሁሉ ጋር ሰላም የሆንኩ ሆኖ ይሰማኝ ነበር፡፡ ትናንት ከአንቺ ከተለየሁ በኋላ ብቻዬን በእግሬ ስሄድ ሳለ አየሩ ሞቃታማ እና ከባድ በመሆኑ ቅጠል እንኳ አትወዛወዝም ነበር፣ ድንገት የሆነ ንፋስ ሽው ብሎ እያፏጨ አለፈኝ፣ ከዚያም በዚያ ንፋስ ውስጥ፣ በቃላት ሊገለፅ በማይችል ጣፋጭነቱ ሰርስሮ ወደ ውስጥ በሚገባ ድምፅ፣ 'ክርስቶስ እንደገና መጥቷል! ክርስቶስ እንደገና መጥቷል!' አለኝ፡፡

ብሬክዌል ሜይ ቦለስን አእምሮዬ ጤነኛ ነው ብለሽ ትገመቺያለሽ ሲል ጠየቃት፣ 'በፍፁም፣ እንዲያውም ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ጤነኛ የሆንከው አሁን ነው፡፡' ብላ ስለ ባሃኡላህ ምፅዓት ነገረችው፡፡ ወዲያው ቶማስ ብሬክዌል ባሃኢ ሆነ፡፡

የቶማስ ብሬክዌል ታሪክ በዚህ አላበቃም፡፡ አንገብጋቢው ምኞቱ ወደ አብዱል-ባሃ የሚሄድበትን መንገድ መፈለግ ነበር፡፡ ከጌታው ጋር ለመገናኘትና አጋርነቱን ለመግለፅ

የጻፈው ቃላትም ‘ጌታዬ፣ አምናለሁ፣ ይቅር በለኝ፣ የአንተው አገልጋይ ቶማስ ብሬክዌል፣’ የሚል ነበር፡፡

የአብዱል-ባሃ ፈቃድ በአጭር ጊዜ ውስጥ መጣለት፣ ቶማስ ብርክዌል ከአንድ ወጣት አዲስ አሜሪካዊ ባሃኢ ኸርበርት ኩፐር ጋር በመሆን አካ ገቡ፡፡ ስለጉብኝታቸው ሜይ ቦለስ ስትጽፍ :–

> …ወደ አንድ ሰፊ ክፍል እንዲገቡ ተደረገ፣ በአን ደኛው በኩል የምስራቃውያን ልብስ የለበሱ ሰዎች ቀጥ ብለው ቆመዋል፡፡ ኸርበርት ኩፐር የት እንደመጣ ስላወቀ ወዲያውኑ ፊቱ በደስታ አበራ፡፡ ብሬክዌል ግን ማወቅ አልቻ ለም ነበር፣ ድንገት ተስፋ በመቁረጡ ተዳከመና አመመው፣ ድካም ተሰማው፣ ከአንድ ጠረጴዛ አጠገብ ባለ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡
>
> በዚያ በተቀመጠበት “ለምን ወደዚህ መጣሁ? ሲል አማረረ፤ ለምን ይህ እንደሆነ ግን አላወቀም፡፡
>
> በከፍተኛ ብዥታ ውስጥ ተዘፍቆ ቆየ፣ ሆኖም ግን ከዚያ ጭለማነት የሚያወጣው ነገር ተከሰተ፡፡ በሩ ወለል ብሎ ሲከፈት የብርሐን ጎርፍ በእርሱ ላይ አበራበት፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባ፣ ቶማስ ብሬክዌልም የተለወጠ ሰው ሆነ፡፡ ከዚያች ቅፅበት በኋላ ብሬክዌል ወደ ኋላ ተመልክቶ አያውቅም፡፡

የብሬክዌል ቀናት በዓይን ምስክሩ የሆኑት፣ የአብዱል-ባሃ ጸሐፊ ዶ/ር ዩኒስ ካሃን “የዘጠኝ ዓመት የአካ ቆይታ” በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ በሚል ተዘግቧል :–

የዚህ ወጣት የጋለ ፍላጎትና እምነት እጅግ ከፍተኛ ባህርይ ስለሆነ የእርሱ የተባረከ ስም በምዕተ-ዓመታት ሁሉ እንደ ደወል ያቃጭላል፣ እናም በብዙ ገድሎችም በጥልቅ ናፍቆት ይዘከራል፡፡ የመንግስቱን ክብር ከፍ የሚያደርጉ የወንጌል ጥቅሶች ከአንደበቱ አይለዩም፡፡ ጉብኝቱ እጅግ አጭር ቢሆንም፣ ነገር ግን ፍቅሩ እጅግ የጋለ ነበር፣ ስሜቱ እጅግ ፅኑ ከመሆኑ የተነሳ እርሱን ለመስማት ለፈቀዱ ሁሉ ልባቸውን በጥልቅ መንካት ይችል ነበር፡፡ ተወዳዳሪ በሌለው ጌታችን (አብዱል-ባሃ) ፊት ሲሆን በአግራሞት ይሞላል፡፡ ሙሉ ለሙሉ ራሱን መስጠቱ ብቻ ምስክር ነው፡፡ በአካ የነበሩ ወዳጆቹን ሁሉ ለማግኘት አልተቻለውም ምክንያቱም ባለስልጣናቱ እንደገና ጫና አሳድረው ነበርና፡፡ በሚሄድበት ቀን አብዱል-ባሃ እንዲህ አለው ‘በፓሪስ ቆይ፡፡’ ሲመለስ፣ እስከ መሳፈሪያው ሸኘሁት፡፡ የሚመለስበት ጀልባ ወደቡን ለቅቆ ከመሄዷ በፊት፣ በአንድ አማኝ መኖሪያ ቤት፣ ለአንድ ለሁለት ሰዓት አብሬው ነበርኩ፡፡ በዚያ ቤት ውስጥ ወደ አካ የሚያሳይ ክፍል ውስጥ ነበርን፡፡ በፀሎት መንፈስ ወደ አካ ዞሮ ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ ዓይኖቹ በእንባ እየታጠቡ እያለ፣ ከአንደበቱ የመማፀን ቃላት ይወጡ ነበር፡፡ በዚያ የነበሩ ሁሉ በእጅጉ ልባቸው ተነካ፡፡ በዚያ የሲቃ ሁኔታ ውስጥ እያለ፣ በየጊዜው ደብዳቤ ለእርሱ እፅፍለት እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ በደብዳቤዎቼ፣ የአንፀባራቂዋን የአካ ከተማ መዓዛዎች አካፍለው ዘንድ ተማፀነኝ፡፡ ስንሰነባበት ሁላችንም በእንባ ታጠብን፡፡

አብዱል-ባሃን፣ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ወቅት፣ ምሳሌያዊ በሆነ ትጋት እንደፀሐፊና እንደ አስተርጓሚ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው፣ ዶ/ር ዩኒስ ካሃን፣ የቶማስ ብሬክዌልን ታሪክ ወደፊት በማስኬድ ፅፏል። እየጨመረ በሚሄድ፣ አቅምን ከሚያሳጣ በሽታ እየታገለ ካለው፣ ፓሪስ ከሚ ገኘው እንግሊዛዊ ወጣት፣ በየአሥራምስት ቀኑ፣ ደብዳቤ ዎች ይደርሱት ነበር። በአንዱ ደብዳቤ ላይ ብሬክዌል፣ አምላክን በህመም በበሽታና በስቃይ ይፈትነው ዘንድ ይማፀን እንደነበር ፍንጭ ሰጥቷል። በበሽታ የሚደርስበት ስቃይ በከፋ ቁጥር፣ ደስታው እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ ዶ/ር ዩኒስ ካሃን ገልጸዋል። ከዚህ ዓለም ሲለይ አብዱል ባሃ የገለጸለትን ፀሎት በማስመልከት ሲጽፉ፡-

> አንድ ቀን አብዱል ባሃን እስከ ቤቱ ለመሸኘት እየሄድን ሳለ፣ ድንገት ወደ እኔ ዞር ብሎ ‘ሰምተሃል?’ አለኝ። ‘እረ አልሰማሁም ጌታዬ።’ አልኩት፣ ‘ብሬክዌል አረፈ። አዝኛለሁ፣ በጣም አዝኛለሁ። ለእርሱ የጉብኝት ፀሎት ፅፌኣለሁ። በጣም ስሜት የሚነካ ነው፣ እየፃፍሁ እያለሁ፣ እጅግ ስሜቴን ከመንካቱ የተነሳ ሁለት ጊዜ እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም፣ የሚያነበው ሁሉ ያለቅስ ዘንድ፣ ጥሩ አድርገህ ልትተረጉመው ይገባል።’ አለኝ። የብሬክዌልን ሞት ለአብዱል-ባሃ ማን እንዳረዳው የማውቀው ነገር አልነበረም። ከሁለት ቀን በኂላ የምተረጉመውን ፀሎት ለእኔ ተሰጠኝ። የማንንም ሰው ልብ የሚነካ ነበር። እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም። ከዚያም ወደ ፈረንሳይኛ ተረጎምኩት፣ እንደገና፣ ከሉዋ ጌትሲንገር ጋር ተረዳድተን ወደ እንግሊዝኛ ተረጎምነው።

ከፀሎቱ የተቀነጨበው ይህንን ይመስላል :–

ብሬክዌል ሆይ፣ የእኔ ተወዳጅ! ያ የሚያምረው ገፅታህ ወዴት አለ፣ ያ አንደበተ ርቱዕነትህስ? ያ አንፀባራቂው ሽፍሽፋትህ እና ያ የሚያበራው ፊትህስ የት ነው? ...

የእኔ የቅርቤ፣ ብሬክዌል ሆይ! እነዚያ ብሩህ ዓይኖችህ ወዴት ናቸው ያ ፈገግታ የማይለያቸው ከናፍሮችህስ የት ናቸው? እነዚያ የሚያምሩ ጉንጮችህና ግርማ ሞገስህስ የት አለ?

የእኔ የቅርቤ፣ ብሬክዌል ሆይ! በእውነት ይህንን አላፊ ዓለም ትተህ ወደ ላይኛው መንግሥት በረሃል፣ የማይታየውን ግዛት ፀጋ ተጎናፅፈህ በስልጣን ጌታ ደጃፍ ላይ እራስህን ሰውተሃል! ...

በአንተ ደስ የሚለኝ የእኔ ተወዳጅ፣ ብሬክዌል ሆይ! የከፍተኛው የሰማያዊ ሠራዊት መስታዎትን በብርሐን ለኩሰሃል፣ ወደ አብሃ ገነትም ገብተሃል፣ በተባረከው ዛፍ ጥላ ስር ተጠልለህ የገነት ነዋሪዎችን አግኝተህ (የእውነት ጌታ) ጋር ደርሰሃል!....

የእኔ ተወዳጅ፣ ብሬክዌል ሆይ! በእውነቱ ጌታህ ለእርሱ ፍቅር ሲል መርጦሃል፣ ወደ እርሱ ቅድስና ደጀሰላም መርቶሃል፣ ወደ እርሱ አጃቢነት ሪዝቫን እንድትገባ አድርጎሃል፣ የእርሱን ውበት እንድታይ ዋስትና ሰጥቶሃል!....

የእኔ ተወዳጅ ብሬክዌል ሆይ! በእጅግ ከፍተኛው አድማስ የአንተ ኮኮብ፣ በመላእክት ሰማይ መካከል ፋኖስ፣ በእጅግ ከፍተኛው ዓለም ሕይወት ያለው

> መንፈስ፣ በሞት አልባው ዙፋን ላይም የተመሠረትህ ሆነሃል!
>
> የእኔ ተወዳጅ፣ ብሬክዌል ሆይ! ያለማቋረጥ ስምህን አነሳለሁ፣ ልረሳህ አይቻለኝም፣ በቀንና በማታ ለአንተ ፀሎት አደርጋለሁ፣… በአንተ ደስ የሚለኝ የእኔ ተወዳጅ፣ ብሬክዌል ሆይ!

ሌላው ወደ እምነቱ የተቀላቀለው የመጀመሪያው የፈረንሳይ ባሃኢ እምነቱን የተዋወቀው በሜይ ቦለስ ነበር። ሂፖላይት ድርፌዩስ ይባላል፣ በፓሪስ ቡድን አማካኝነት ከእምነቱ ጋር የተዋወቀችውን፣ ባሃኢ ላውራ ክሊፎርድ ባርኒን አገባ።

ሂፖላይት ድርፌዩስ፣ የእምነቱ መገኛ የሆነችውን፣ ኢራንን ለመጎብኘት የመጀመሪያው አውሮፓዊ ባሃኢ ሆነ። የባሃኡላህንና የአብዱልባሃን ፅሑፎች ለመተርጎም እንዲያመቸው አረብኛና የፋርስ ቋንቋ ተምሯል። ለእምነቱ ግልጋሎት ምክንያት፣ ወደ ካናዳ፣ አሜሪካና ጃፓን ድረስ በተደጋጋሚ ተጉዟል። ቅዱሳን ፅሑፎቹን በመተርጎም በኩል እና የእምነቱን ታሪክና አስተምህሮቶቹን በተመለከተ ትልቅ ግምት የሚሰጣቸውን የእራሱን መፅሐፍት ፅፏል። ወደ መጨረሻው አካባቢ አብዱል-ባሃ በአውሮፓ ባደረገው ጉዞ ላይ ተገኝቶ በከፍተኛ ፅናትና ወኔ አገልግሏል። ሂፖላይት ድርፌዩስ በ1929 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

ባለቤቱ ላውራ ክሊፎርድ ባርኒይ በስነፅሁፉ ዓለም ታዋቂ ከነበሩት ቤተሰብ መካከል ኑሯቸውን በፓሪስ ከመሠረቱት የአሜሪካ ቤተሰብ የተገኘች ነች። እምነቱን ከተቀበለች በኋላ መንፈሳዊ ጉብኝት በማድረግ አካ ሄደች። በ1904

ለሁለተኛና ለሦስተኛ ጊዜ ኢተል ሮዝንበርግን አጅባ ተጓዘች፡፡ ወደፊት እንደምናየው ያ ወቅት ለአብዱል-ባሃ እምነቱን የመምራት ፈታኝና አደገኛ ጊዜያት ነበሩ፡፡ ከዚያም ለአጭር ጊዜ ግብፅን ከዚያም በፀደይ ወራት ፈጣን ጉብኝት በአውሮፓ አድርጋለች፡፡ እናቷን ይዛ ወደ ቅድስት ሀገር መጥታለች፡፡ በ1905 ከባሏ ሂፖላይት ድርፌዩስ እና ከሌሎች ተጓዥ ወዳጆች ጋር በመሆን የባሃኡላህን የትውልድ ስፍራ ጎብኝታለች፡፡ በአካ ጉብኝቷንና ቆይታዋን እስከ 1906 ድረስ አራዝማለች፡፡ በ1908 እንደገና ሌላ መንፈ ሳዊ ጉዞ አድርጋለች፡፡

የላውራ ክሊፎርድ ባርኒይን የቅድስት ሀገር የተደጋገመና የተራዘመ ጉዞን የተለየ ዓላማን ማወቅ የግድ ይላል፣ ምክንያቱም ለብዙ ዓመታት የተራዘመው፣ ከእምነቱ መስራቾች በተለየ ሁኔታ የተፃፈው መፅሐፍ ቅርፅ ይዞ እውን የሆነው፣ በእነዚያ ወራቶች ነበር፡፡ መፅሐፉም "መልስ የተሰጣቸው ጥያቄዎች" ተብሎ ይጠራል፡፡ ጥያቄዎቹ የመነጩት ከላውራ ባርኒይ ሲሆን መላሹም አብዱል-ባሃ ነበር፡፡ ከመፅሐፉ መግቢያ ገፅ ከተወሰደው በእራሷ ቃላት እንዲህ ብላለች :–

> እነዚህ መልሶች አብዱል-ባሃ ሲናገር የተፃፉት በፋርስኛ ነበር፣ ለህትመት ታስቦ አልነበረም፣ ነገር ግን በቀላሉ ለእኔ ለወደፊት ጥናቴ እንዲያግዘኝ ነበር፡፡ …እኔ ያመንኩት ነገር ቢኖር ለእኔ ጠቃሚ የሆነው ምናልባት ለሌሎችም እንደዚያው ሊሆን ይችላል በሚል ግምት አብዱል-ባሃን እነዚህን ንግግሮች እንዳሳትማቸው ጠየቅሁት፡፡

ጥያቄዋም በ1906 ፈቃድ አገኘ፡፡ በእንግሊዝኛው በ1908 ታተመ፡፡ የፋርስኛው ፅሁፍም በዚያኑ ዓመት ታተመ፡፡

ሂፖላይት ድርፊዩስ (Les Lecons de Saint Jean-d' Acre) በሚል አርዕስት ወደ ፈረንሳይኛ ተረጎመው። የአብዱል-ባሃን ማስተካከያና ማረሚያ ተጨምሮ፣ ዋናው የፋርስኛው ቅፅ፣ በባሃኢ ዓለም ዓቀፍ የመፅሐፍት ቤተ-መዘክር ውስጥ ይገኛል።

ላውራ ባርኒይ ስትናገር አብዱል-ባሃ አንዱን ጥያቄ ከመልሰ በኋላ ከመቀመጫው ላይ እየተነሳ፣ "የተዳከምኩበትን ጊዜዬን ሰጥቻችኋለሁ" ይል ነበር። ጭቆና ተጫጭኖት፣ እነዚያ አላኖር ያሉትና ሊያጠፉት የሚያስቡት ባለስልጣ ናቱን ተጋፍጦ፣ በቅርብ ዘመዶችና ወገኖች ሸር የሚዘወ ረው "የአጣሪው ቡድን ኮሚሽን' በሚል ሽፋን የሚንቀሳቀ ሱትን የኦቶማን ስርወ-መንግሥት ሹማምንትን የሚቋቋ መው እያንዳንዱ የአብዱል-ባሃ ደቂቃዎች የተሞሉት በሐ ዘን ነበሩ። እንግዲህ በእነዚህ ሰዓቶች ነበር ለላውራ ክሊፎርድ ባርኒይ እውቀቱንና ማብራራቱን ይሰጥ የነበረው።

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ፣ የአብዱል-ባሃ ሁሉንም የተመላ ከፍተኛ ተሰጥኦ የታየበት ነው። የአብዱል-ባሃን ሁሉን ዓቀፍ ጥበብ ለመወዳደር አይቻልም። ከዚህ ቀደም ለመንፈሳዊ ጥያቄዎች መልስ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ተነግረው አያውቁም። የእርሱ መልሶች ትኩረትን መሳባቸውና ማሰላሰልን ማነሳሳታቸው፣ እንደባልጩት ድንጋይ ጥርት ብለው የቀረቡት ከጥንካሬ ጋር የተጣመሩት ቃላቶቹና በስሜት ውስጥ የሚከቱት ቋንቋው ማራኪ ናቸው። ዓረፍተ ነገሮቹ ደንቀፍ የማያደርጉ፣ ምሳሌዎቹ ተገቢና ንቁ ናቸው። ምክንያትነታዊነቱ እንከን አልባ ነው። መደምደሚያዎቹ ወሳኝና በቂ መረጃ

ያላቸውና በስልጣን የታዘዙ ናቸው። መፅሐፉ ምንም አቻ የለውም።

የአብዱል-ባሃ ደቀ-መዛሙርት እምነቱን በምዕራቡ ዓለም አቀጣጠሉት። ሆኖም ግን ልፋታቸውን መና ሆኖ ሊያስቀር የሚሞክር አውሎ ንፋስ ኃይሉን አሰባሰበ። እየበራ ያለውን ምሳሌ የሆነ የፅናታቸውን ብርሃን ሊያጠፋ የሚ ያስፈራራ አውሎ ንፋስ መጣ። የባሃኡላህን መልዕክት አትላንቲክ ውቅያኖስን አሻግሮ የወሰደው፣ በምዕራቡ የክ ርስቲያን ዓለም የመጀመሪያውን የባሃኢ ማዕከል የመሠ ረተው፣ በዚያ ሩቅ ሀገር ለስድስት ዓመታት እምነቱን በማስተማርና በመንከባከብ ያሳለፈው ዶ/ር ካይሩላህ የቃል-ኪዳን ሰባሪዎች ማዕበል መጓጓዣ ሆነ። የ'ባሃ ጴጥ ሮስ' በማለት ግልጋሎቱን አብዱል-ባሃ ያሞገሰው፣ የቃል-ኪዳን ሰባሪዎቹን ጎራ ተቀላቀለ። የዶ/ር ካይሩላህ ጥረ ትና ስኬት የኂላ ኂላ የውድቀቱ ምክንያት ሆኗል።

ካይሩላህ የአብዱል-ባሃን ስልጣን ለመጋራት አለመ፣ አደገኛና በተወናበደ አእምሮው አብዱል-ባሃ ምስራቁን እንዲመራና፣ እርሱ ካይሩላህ በእርሱ ጥረት ካመጣው እድገት የተነሳ ምዕራቡን ዓለም እንደ እረኛ ለማገድና ለመምራት አለመ። የስልጣን ቅዠት ስላሳወረውና የመሪ መሆን ምትሃት ልቡን ስለነሳው ካይሩላህ ፊቱን ወደ ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ አዞረ። ከቃል-ኪዳን ሰባሪዎቹ ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት መሠረተ። ብዙም ሳይቆይ በከፋ ሁኔታ መበከሉ ግልፅ እየሆነ መጣ። ሚርዛ ሙሐመድ-ዓሊ፣ የመጀመሪያ ልጁን፣ ሚርዛ ሹአሁላህን፣ እንዲረዳው ወደ አሜሪካ ሰደደው። ከሹአሁላህ ቀጥሎ የአብዱል-ባሃ እጅግ ክፉ የሆነው ጠላት፣ የአቃ

ሙሐመድ-ጃቫድ-ኢ-ቃዝቭኒ ልጅ የሆነው፣ ሚርዛ ጉላሙላህ ተከተለው።

አብዱል-ባሃ ዶ/ር ካይሩላህን ለማዳን ሞክሮ ነበር። ሶሪ ያዊውን ስለ እምነቱ ያስተማረውን፣ ሐጂ አብዱል-ካሪምን በአሜሪካ እያቆጠቆጠ ያለውን ማህበረሰብ እንዲታደግና የቃል-ኪዳን ሰባሪዎቹን ሸርና ስርገትን ለመከላከል፣ በዋና ነት ደግሞ ካይሩላህ ከተሳሳተበት መንገድ እንዲያቀናው ወደ አሜሪካ እንዲጓዝ ሁኔታዎችን አመቻቸለት።

ጊዜው 1900 ነበር። ካይሩላህ እራሱ ወደ እምነቱ እንዲመጡ የረዳቸው ሰዎች ከእርሱ ጎን ላለመቆም እንቢተኝ ነታቸውን ገለፁ። ከጥቂቶች በስተቀር፣ በሁሉም ዘንድ ተወገዘ። ቃል-ኪዳን ሰበራው በአሜሪካ መሬት ላይ ስር መስደድ አልቻለም። ነገር ግን በዚያ እምቦቀቅላ ማህበረ ሰብ ላይ የፈጠረው ውጥረት ቀላል አልነበረም።

በዚያው ዓመት፣ ወደ አሜሪካ ሄዶ የነበረው ሐጂ አብዱልካሪም ወደ ግብፅ ከተመለሰ በኋላ፣ አብዱል-ባሃ ሌላ የፋርስ ባሃኢ ሐጂ ሚርዛ ሐሳን-ኢ-ክሁራሳኒንን ዶ/ር ክሃይሩላህ ወደ ቀልቡ እንዲመለስ ላከበት። ካይሩላህ ግን ሊድን አልቻለም።

አብዱል-ባሃ በተጨማሪ፣ ሚርዛ አሳዱላህ፣ ፅኑ የታብሪዝ ባሃኢ በሆኑት፣ በሁሴይን ሩሂ እንዲታገዙ ወደ አሜሪካ ላከ። በመጨረሻም፣ እጅግ ዕውቀት ያለውን ምሁር ሚርዛ አቡል-ፋድልም ወደ አሜሪካ ተላከ።

አዲስ የተወለደውን የአሜሪካን ባሃኢ ማህበረሰብ ያናወጡት ፈተናዎች እጅግ ከባዶች ነበሩ፣ የቃል-ኪዳን ሰበ ራው ሞገድ ያስነሳው ወጀብ ኃይለኛ ነበር። የአሜሪካ ባሃኢዎች ጥንካሬያቸው የተፈተነበት ጊዜ ነበር።

አስደናቂው ታማኝነታቸው የብስለታቸውን ደረጃ መስክሯል፡፡

በመሆኑም ዶ/ር ኢብራሂም ካይሩላህ ተሸነፈ፡፡ አልፎ አልፎ፣ የማይታዩ፣ አንዳንድ ደካማ የእርሱ ጥረቶች አነስተኛ ሞገዶችን ማስነሳታቸው አልቀረም፣ ነገር ግን ይህም በፍጥነት ከሸፈ፡፡

## ምዕራፍ 7

## የስቃይ ዓመታት

ሰማዕት የሆነው የባሃኡላህ እምነት አብሳሪ ነብዩ ባብ፣ እ.ኤ.አ ጁላይ 9 ቀን 1850 በታብሪዝ አደባባይ ሲረሽን፣ የእርሱ አስከሬን አብሮት ከተሰዋው ከጽኑ አማኙ አሰከሬን ጋር ተዋህዶ ነበር፣ ከዚያም አሞራና አውሬ እንዲበላው በማለት በከተማዋ ዳርቻ ላይ አስከሬናቸው ተጣለ። በተከታዮቹ በአንዱ በሱለይማን ካን ድፍረት በተሞላበት ጥረት እነዚያ አስከሬኖች ተርፈው በድቅድቅ ሌሊት ወደ ሐጂ አህመድ ሐር ፋብሪካ ተወሰዱ። ከዚያም በሐር ጠቅልለው ደበቁት። ባሃኡላህም ወዲያው ለሱለይማን ካን የባብ ቅሪቶች ወደ ቴህራን ተወስደው በሙስሊም ቤተ-መቃብር ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ እንዲቀመጥ መመሪያ ሰጠ። ለሃምሳ ዓመታት እስከ አሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ዓመት ድረስ ከቦታ ወደ ቦታ ከቤተ-መቃብር ጀምሮ በሰዎች ቤትም ውስጥ ሲዘዋወር ቆየ።

የመጀመሪያዎቹ ምዕራባውያን ምዕመናን ለመንፈሳዊ ጉብኝት አካ በደረሱበት በዚያው ዓመት (የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ) ከኢራን ወደ ቅድስት ሀገር የባብን ቅሪቶች የማምጣት አዳጋች ሥራ አብዱል-ባሃ በከፍተኛ ጥንቃቄ አቅዶ ሚርዛ አሳዱላህ-ኢ-እስፋሃኒ ለተባለ ምዕመን አደራ ሰጥቶ ተፈፀመ። ስለዚያ ረዥም እና አደገኛ ጉዞ ዝርዝር ታሪክ የእኛ ዕውቀት አነስተኛ ነው። ሆኖም፣ የሬሳ ሳጥኑ መጀመሪያ ከቴህራን ወደ ኢስፋሃን፣ በመቀጠልም ወደ ኪርማንሻ መወሰድ ነበረበት። ከዚያም ባሃኡላህ ከትውልድ አገሩ ሲጋዝ በተጓዘው በዚያ

መንገድ የሰማዕት-ነቢዩ አፅም ባሃኡላህ ለአሥር ዓመታት ያህል ወደ ተቀመጠባትና ተልዕኮውን ወደ አወጀበት አገር ባግዳድ ተወሰደ። በመቀጠልም በሶርያ በረሃ በማድረግ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊ ወደ ሆነችው ወደ ደማስቆ ተጓዘ። በመጨረሻም በጠቅላላው ረዥሙን ጉዞ ጨርሶ እ.ኤ.አ. 1899 ከቤይሩት በባህር ተጓዞ ቅድስት አገር ደረሰ። በአብዱል-ባሃ አገልግሎት ዘመን ውስጥ ካሉት ዋና ዋና ተግባራት መካከል አንዱና የመጀመሪያው ደረጃ ተጠናቀቀ፤ ተዓምራዊ ውጤትም ተቀዳጀ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጥይት የተበጣጠሰውን የአምላክ መልዕክተኛ ሰብዐዊ ቤተ-መቅደስ ለማቆየት በቀርሜሎስ ተራራ ላይ መካነ መቃብር አልተዘጋጀም ነበር። ይህ መካነ መቃብር የሚታነጽበት ባሃኡላህ የመረጠው ቦታ የመሬቱ ግዢ፣ ከዚያም የመካነ መቃብሩን ሕንፃ ማሰራትና በአንዱ ክፍል ውስጥ ከመሬት በታች ቅሪተ-አካሉን የያዘው ሳጥን የሚቀመጥበት ጉደጓድ ማስገንባት፣ ይህ እራሱ ሌላ አሥርተ ዓመታት ፈጀ። ይህ ረዥም እና ጉልህ ወቅት በአዲስ አደጋዎች እና ችግሮች የተሞላ ሲሆን አብዱል-ባሃ ሰው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሥቃይና መከራ ደርሶበት ነበር ። የእርሱን ሞት ለማጣደፍ እንቅ ስቃሴዎች ተጀምረውም ነበር ። መንገድ ላይ እሱን ለመ ግደል ሙከራም ተደርጓል። በአጠቃላይ እነዛ አሥርተ ዓመታት በአመፅና በጭካኔ ኃይሎች ጥፋት ተጠናቀዋል።

በባሃኡላህ የተደነገገውን መንፈሳዊ መዋቅር ለማፍረስ ቆርጠው የተነሱት የጥፋት ዋና አንቀሳቃሾች የቤተሰቡ አባላት ነበሩ። ቃል ኪዳኑን ለመጣስ ዋና ምንጭ ነበሩ፣

ረብሻ በተሞላው ግዴለሽነትም አሴሩ፡፡ አብዱል-ባሃ ለሰማዕቱ-ነቢይ የቤተ-መቃብር ሕንፃ እንዳይሠራ ለመከላከል ሁሉንም መንገዶች ማለትም ማጭበርበር፣ ከዳተኛነት እና ማዋረድን ተጠቀሙ፡፡ በእነርሱ ድርጊት የተመረዘው ሚርዛ አቃ ጃን እንኳን ደንግጦ ይህንን መዋቅር ለማገድ እንዳይሞክሩ ነግሯቸዋል፡፡ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለፍጻሜው ተንብየዋልና፡፡ እነሱ ግን እንደዚህ ላለው ምክር ጆሮአቸውን አልሰጡም፡፡ የኦቶማን ባለስልጣናትን በመለማመጥ እና ጉቦ በመስጠት በአብዱል-ባሃ ላይ ለማነሳሳት የማያቋርጥ ጥረታቸውን ማሴር ቀጠሉ፡፡

የመጀመሪያዎቹ የምዕራባውያን መንፈሳዊ ጎብኚ ቡድን ወደ ቅድስት ምድር ሲመጡ አብዱል-ባሃ ለባብ መካነ-መቃብር ሕንፃ ማሰሪያ ቦታ አስቀድሞ ገዝቶ ነበር፡፡ አንድ ቀንም አብዱል ባሃ ኢብራሂም ካይሩላህ የተበላ ምዕመንን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ይዞት ሄዶ ተራራውን የሚያስጌጠውን የመቃብር ሕንፃ የመሠረት ድንጋይ አኖረ፡፡ ብዙም ሳይቆይ የራንጉን (ማይናማር) አገር ባሃኢዎች የለገሱት ቅሪተ-አካሉን የሚይዘው የእብነ በረድ ሳጥን ሐይፋ ደረሰ፡፡ ከጥቂት ወራቶች በኋላ አሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሲቃረብ የህንፃው ግንባታ ሥራ ተጀመረ፡፡ ቀድሞውኑ በባሃኢዎች የተወገዱት የቃል ኪዳኑ አፍራሾች አዲስና ጥድፊያ የተመላው እንቅስቃሴ መንደፍ ጀመሩ፡፡ በአንድ በኩል ምዕራባውያን መንፈሳዊ ጎብኝዎች የመጡ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቀርሜሎስ ገዢ በሆነ ከፍታ ቦታ ላይ ሕንፃ የማነፁ ሥራ በሂደት ላይ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የቃል ኪዳኑ አፍራሾች ዕድል እንዳላቸው አዩ፡፡ አብዱል-ባሃ ላይ የተሸረበው ሴራም እንዲህ ነበር የብዙ የተጨቆኑ ሕዝቦችን ለሁከት

አነሳስቶ፣ የአመጽ መሠረት በመጣል፣ የጥፋት ቡድኖችን እየሰበሰበ ሲሆን፣ ከምዕራቡ ዓለም የክርስቲያኖችን ድጋፍ እየጠየቀ ነው፣ ከተማዋንና የአካ ሜዳን በተቆጣጠረው በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ጠንካራ ምሽግ እየሠራ ነው፣ የአመፅን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ለማድረግ እና የሱልጣኑን ታላቅነትና የእስልምናን ከሊፋ ለመቃወም ጊዜን እየጠበቀ ነው በማለት ለጥንታዊዋ ኦቶማን ግዛት ገዢዎች አቤቱታ ለማቅረብ አሰቡ፡፡ በሙስና የተዘፈቁ ባለሥልጣናትን ድጋፍ ለማግኘት ከፍተኛ ገንዘብ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ ገንዘብ ለማግኘት የባሃኢዎች ቅዱስ ቦታ የሆነውን፣ ባሃኡላህ በኋለኛው የሕይወቱ ዘመን እረፍት ያገኘበትን፣ በመጨረሻም ከጎኑ መካነ-መቃ ብሩ ያረፈበትን የባሃጂ ቤቱን በዱቤ አስያዙት፡፡ እንደጉቦ እንዲያገለግልና እንዲሁም አብዱል-ባሃን ለማዋረድ የሚያስችላቸውን መንገዶች ሁሉ ለመጠቀም የባሃኡላህን ልብሶችንና የግል መጠቀሚያዎቹን ሳይቀር ለመንግሥት ሃላፊዎች ሰጡ፡፡ በእነሱም አነሳሽነት የሐይፋ ምክትል ከንቲባ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት ሲሄድ በማንአለብኝነትና ጉራ በተሞላው ሁኔታ የባሃኡላህን ካባ በሚታይ መልኩ ይለብሳል፣ መነጽሩንም ያደርጋል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ይህ ሰው ከስልጣኑ ተባርሮ ለክፉ ቀናት ተዳረገ፡፡ ከዚያም ወደ አብዱል-ባሃ በመሄድ ምህረትን ጠየቀ፡፡ ይህን ያደረገው በአብዱል-ባሃ በገዛ ዘመዶቹ በመነሳሳት እንደሆነም ተናገር፣ አብዱል-ባሃም ሁልጊዜ እርሱን ለበደሉት ሰዎች ያደርግ የነበረውን ሩህሩህነትንና ደግነትን አሳየው፡፡

ቀደም ሲል ባሉት ምዕራፎች እንደተጠቀሰው፣ ለአጭር ጊዜ የአመጽ ማዕከል ከሆነው ከሚርዛ መሐመድ ዓሊ ጋር ሁሉንም ግንኙነቶች አቋርጦ ወደ አብዱል-ባሃ ዞሮ በንስሐና በጸጸት ተመልሶ የነበረው የባሃኡላህ ትንሽ ልጅ

የሚሪዛ ባዲኡላህ ምስክርነት አለ፡፡ የቃል-ኪዳን አፍራሾ ችን አስጸያፊ ድርጊቶችን በዝርዝር በመግለጽ ለዓለም ባሃኢዎች የተላከ ረዥም ደብዳቤ በራሱ ፈቃድ ጻፈ፡፡ በጽሑፉም ውስጥ የኦቶማን ኢምፓየር ገዥዎችን ቁጣ የሚ ቀሰቅስ ክስ በአብዱል-ባሃ ላይ ለማቅረብ የሲሪያ አገረ ገዢ የሆነውን ናዚም ፓሻን በእጃቸው ለማድረግ፣ የባሃጂ መኖሪያ ቤት በዱቤ በማሲያዛቸው በተገኘ ገንዘብ ተጠቅመው ወደ ደማስቆ መሄዳቸውን፣ አገረ-ገዥዎችም እርምጃ እንዲወስዱ ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ በወቅቱ በካይሮ ይኖር የነበረውን ሚርዛ አብዱል ፋድልን መውቀሳቸውን፣ ይህ ታዋቂ ምሁር አብዱል-ባሃን ለማወደስ፣ የማይገባና እና የተጋነኑ የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳቀረበ የሚጠቅሱ በራሪ ጽሑፍ እንደጻፈ የሚጠቅስ የውሸት ታሪክ መፍጠራቸውን፣ ይህ የሐሰት አሉባልታም በባለስልጣኖች እጅ ስለወደቀ ተደናግጠው እርምጃ ለመውሰድ መገደዳቸውንና አብዱል-ባሃን በቁጥጥር ስር እንዲውል ማድረጋቸውን ሁሉ ገለጸ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካ ከተማ ውስጥ በግብዝነቱ የሚታወቅ በመንግሥት ውስጥ ተደማጭነት ያለው የታወቀ አንድ ሰው እንደነበረና የደለበ ጉቦ ስለተ ሰጠው የቃል-ኪዳን አፋራሾቹ ዋና ተቆርቋሪና ተባባሪ መሆኑንም ገለጸ፡፡

እ.ኤ.አ. 1901 አብዱል-ባሃ የባብ እወጃን መታሰቢያ በዓልን ያከበረው በባሃኡላህ መካነ-መቃበር አቅራቢያ ነበር፡፡ ምሽት ላይ ወደ አካ ሲመለስ፣ በሱልጣኑ ትእዛዝ መሠረት እሱና ውንድሞቹ ከአካ ከተማ ክልል ውጪ እንዳይወጡ ታዘዙ፣ የገጠርን ነፃነት ተነፈጉ፡፡ ወንድሞቹ ሚርዛ መሐ መድ ዓሊና ሚርዛ ባዲኡላህ ከባሃጂ ወደ አካ እንዲመጡ ተደረገ፣ ተባባሪያቸው የሆነው ሚርዛ ማጅደዲን ከሚኖርበት ቲቤርያ ከሚባል ቦታ ተይዞ መጣ፡፡

ቀደም ሲል ሚርዛ ያህያ በእራሱ ሴራዎች እራሱን እንደተበተበ ሁሉ፣ አሁንም ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ በተመሳሳይ ሁኔታ በራሱ ወጥመድ ውስጥ ወደቀ። በተጨማሪም ሚርዛ ባዲኡላህ ናዚም ፓሻ ከዚያ በኋላ በሚ ርዛ ሙሐመድ-አሊ ላይ ያደረገውን ተራ አያያዝንም መዝ ግቧል። ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ ከባሃጂ መኖሪያው ተፈ ናቅሎ በአካ ቅጥር ውስጥ ተጠብቆ በሚገኝበት ወቅት ደማስቆ ውስጥ ላለው ለተንኮለኛው አገረ ገዢ ሁለት ተጨማሪ ደብዳቤዎችን ጻፈ። ሆኖም ግን ሁለቱም ደብዳቤዎቹ ምላሽ አላገኙም። ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሚርዛ ሙሐመድ-አሊ፣ ለሚርዛ ባዲኡላህ እና ለሌሎቹ የተማፀ ነው አብዱል-ባሃ ነበር። በከተማው ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገድበው እንዳይቀሩ የአካ አገረ-ገዥን ጠየቀላቸው።

የኦቶማን ቱርኩ ሱልጣን ትእዛዝ በአብዱል-ባሃ ላይ ያደረገው እጅግ አሳዛኝ ድንጋጌ ከአባቱ የመካነ-መቃብር ሥፍራ መለየቱ ነበር። አብዱል-ባሃ እንደገና በአካ ቅጥር ውስጥ እስረኛ ሆነ። እርሱ ሲናገር እንደተሰማው፡- "እስር ቤቱን ወደአሸበረቀ ሕንፃ ለመቀየር ለሠላሳ ዓመታት ያህል ለፋሁ። የቃል ኪዳኑ አፍራሾች ግን ሁኔታውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀለበሱት።"

በአብዱል-ባሃ አገልግሎት ዘመን ውስጥ በጣም አደገኛ የሆነው ጊዜ አሁን ተጀመረ።

የአካ አገረ-ገዥ አብዱል-ባሃ ታግቶ መቀመጡን ማየቱ በጣም አበሳጨው። አብዱል-ባሃ ረጅም ምርመራዎችና ዝርዝር ጥያቄዎች ቀርበውለት ነበር። ባለሥልጣኖቹን ብቻውን በክብር እና በረጋ መንፈስ ተጋፍጧል፣ ይህ

በእንዲህ እንዳለ የአካ ባሃኢዎች የእገዳ ተጽዕኖ ውስጥ ነበሩ፡፡

ብዙም ሳይቆይ የመጀመሪያው አውሎ ነፋስ ረገበ፡፡ አብዱል-ባሃ፣ ለሚርዛ መሃመድ-አሊ እና ሌሎች አብረውት ለታገቱት እንዲሁም ለተከታዮቹ ያቀረበው ልመና ፍፃሜውን አገኘ፡፡ ሚርዛ መሃመድ-አሊና ደጋፊዎቹ ወደ ባሃጂ መኖሪያ ተመለሱ፡፡ የአካ ባሃኢዎችም የዕለት ተዕ ለት የኑሮ ተግባራቸውን ለማከናውን ነፃ ሆኑ፡፡

ከዚያም አገረ ገዢው የባሃኡላህን መካነ-መቃብር እንዲጎበኝ አብዱል-ባሃን ጠየቀ፡፡ ከእርሱ ጋር በመሆን አብዱል-ባሃ ከአካ መውጣት ቻለ፡፡ አገረ ገዥው አሁንም የባለስልጣኖቹን ጥብቅ መመሪያዎች ለመጣስ እየሞከረ፣ እንደገና መካነ-መቃብሩን ለመጎብኘት ጠየቀ ፣ በዚህ ጊዜ ከሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ታጅቦ ነበር፡፡ ከባሃጂ መኖሪያ ቤት በረንዳ ላይ ሆነው ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ እና አጋሮቹ በእልህ ተሞልተው ተሰባስበዋል፣ ባለሥልጣናቱ ለአብዱል-ባሃ የሚያሳዩትን አክብሮት ያያሉ፡፡ ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ባዩት ነገር በመበሳጨት ለአዲስ እርምጃ ተነሳሱና ሌላ ሴራ ለመቀየስ የሱልጣን አብዱል ሀሚድ ጨካኝ ሴራ ጠንሳሽ ወደሆነው ወደ ሼህ አቡል ሁዳ አመሩ፡፡

ሆኖም ግን እ.ኤ.አ. 1902 ሁኔታዎች መቅለል ጀመሩ፡፡ መንፈሳዊ ጎብኚዎችም መጡ፣ ምንም እንኳን አብዱል-ባሃ በአካ ብቻ ተወስኖ የነበረ ቢሆንም የባብ የመቃብር ግንባታው ሥራ በተከታታይ መሻሻል አሳየ፡፡ በስምንት ዓመታቱ ረዥም የሥጋት ጊዜ ውስጥ ሌላ እገዳ ወይም መዘግየት የደረሰበት ማንኛውም ነገር፣ በቀርሜሎስ

ተራራ ላይ ያለውን የግንባታ ሥራ በጭራሽ አላስተጓጎለውም። አብዱል-ባሃ ምንም ይሁን ምን ይህ የባሃኡላህ ትእዛዝ እና ፍላጎት መሟላት እንዳለበት ወስኗል። በአ ዲሱ ክፍለ ዘመን የመክፈቻ ዓመታት ውስጥ (1852-1924) ከነበሩት መንፈሳዊ ጎብኚዎች አንዷ ኢዛቤላ ዲ ብሪቲንግሃም ነበረች። ብሪቲንግሃም ከአሜሪካ የመጀመ ሪያዎቹ ባሃኢዎች አንዷ ነበረች። የአብዱል-ባሃ ሕይወት እና የኖረበት እና የደከመበት ሁኔታ ማንነቷን በጥልቅ ነካው። ወደ አሜሪካ ከተመለሰች በኋላ፣ እምነቱን ለሌ ሎች ለማካፈል በአዲስ ጉልበት እና ቁርጠኝነት ተነሳች። የባሃኡላህን እምነት ያስተማረቻቸው ሰዎች እምነቱን መቀበላቸውን የሚገልጽ ደብዳቤዎች በየሳምንቱ ወደ አብዱል-ባሃ ይደርሱ ጀመር። ከነዚህም ውስጥ አንዷ ዶ/ር ሱዛን ሙዲ ስትሆን፣ ወደ ባሃኡላህ ትውልድ አገር በጣም የሚያስፈልጉ የህክምና እርዳታ ትልክ ጀመር። አብዱል-ባሃ ስለ ብሪቲንግሃም ሲናገር በፈገግታ እሷ ባሃኢዎችን አምራች ናት ይል ነበር፣ ባሃኡላህም ሼክ ስልማንን እንዲሁ ባቢዎችን አምራች ይለው ነበር። (ሰልማን ከአካ እስከ ኢራን እየተመላለሰ የሚሄድ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል መልእክት አድራሽ ነበር። ሁልጊዜም ለባሃኡላህ የአዳዲስ አማኞችን ዝርዝር ያቀርብ ነበር።)

ሉዋ ጌትሲንገር የተባለች ጠንካራ አሜሪካዊት ባሃኢ እንደገና መንፈሳዊ ጉብኝት ለማድረግ አካ መጥታ ነበር፣ በአብዱል-ባሃ ቤት ውስጥ እንግሊዝኛ በማስተማር ከአንድ ዓመት በላይ ቆየች። አንድ ቀን የሚርዛ ሙሀመድ-አሊ ደጋፊ ከሆነው ከሚርዛ ሁሰይን-አሊ-ጃህሩሚ ጋር ፊት ለፊት ተገናኘች። እንዲህ ስትል ጠየቀችው ስለሚርዛ ሙሐመድ-አሊ ማዕረግም ጉዳይ እሷ እንደማያገባት፣ ሆኖም ግን እሷ አሜሪካዊቷ ሴት ያደረገችውን ለምን

እንደማያደርግ ማወቅ እንደምትፈልግ ጠየቀችው፡፡ እሷ የባሃኡላህን መልዕክት ፍላጎት ላላቸው ለብዙ ሰዎች አስተላልፋለች፡፡

ሉዋ ጥዑም ድምጽ የነበራት ስትሆን “አምላኬ ሆይ ወደ አንተ አቅርበኝ ” የሚለውን መዝሙር ባዜመች ቁጥር ፊቷን ወደ ባሃኡላህ መካነ-መቃብር ታዞራለች፣ በዚህም የአብዱል-ባሃ ዓይኖች እንባ ያቀሩ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ ባሃኡላህ መካነ-መቃብር እንዳይሄድ ስለተከለከለ እቤቱ ጣሪያ ላይ የእንጨት ቤት ሰርቶ ነበር፣ ከዚያ ቤት ላይ ሆኖም የባሃኡላህ መካነ-መቃብር ያለበትን ባሃጂን በርቀት እየተመለከተ በፀሎት ተመስጦ ይቆይ ነበር፡፡ ይህንንም ለብዙ ዓመታት አድርጎታል፡፡

ዋናው ቅጂ ባይገኝም ሉዋ ወደ አሜሪካን መመለሻዋ ሲቃረብ አብዱል-ባሃን የሚያወደስ ግጥም ጽፋ ነበር፡፡ በጣም የሚመስጥ ግጥምም ነበር፡፡ ወደ ፋርስኛ ከተተረጎመው የተወሰደው የመጀመሪያው ስንኝም እንዲህ ይላል፡- “ጌታዬ ሆይ በረዥሙ ጉዞዬ አብረኸኝ ሁን፡፡” ሉዋ ከጊዜ በኋላ ካይሮ ከታዋቂው ምሑር ባሃኢ ሚርዛ አብዱል ፋድል አጠገብ ተቀበረች፡፡ ቦታውም ምሥራቁና ምዕራቡ ዓለም የሚገናኝበት ነው፡፡

እ.ኤ.አ ዲሴምበር 1902 በአብዱል-ባሃ ግብዣ መሠረት የኒውዮርክ ፍርድ ቤት ታዋቂ አባል የሆኑት ማይሮንና መኳንንቷ ካና ቫሮ ሙሉውን ወር በአካ ውስጥ አሳለፉ፡፡ ማይሮን ሲጽፍ “እነዛ ወራት በሕይወቴ ጥልቅ ትውስታን የጣሉብኝ ናቸው፣ ስለእምነቱ በቂ የሆነ እይታን ያገኘሁበትና ድንቅ የሆነውን አባስ ኤፌንዲን (አብዱል-ባሃን) በማግኘቴም እድለኛ የሆንኩበት ጊዜ ነበር” ብሏል፡፡ ማይሮንም በቅርብ የአብዱል-ባሃን አኗኗር አይቶ

መስክሯል። "የአባስ ኤፌንዲ ሕይወትና ትምህርቶቹ" ከሚለው መጽሐፉ በሰፊው እንጥቀስ፦

> በጥንታዊዋ አካ ከተማ ውስጥ ባለው ጥንታዊ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንዳለን አስቡት። ይህ ቤት ለአንድ ወር ቤታችን ነበር። እኛ ያለንበት ክፍል ጀርባው በውጪ በኩል የከተማው ጠባብ ጎዳና ግድግዳ ነው። ከላያችን የፍልስጤም የአካ ሞቃታማ ፀሐይ ታበራለች፣ በቀኝ በኩላችን ሰማያዊውን የሜዲትራኒያንን ባሕር እንቃኛለን። መስኮቱን ስንከፍት ወደታች የተጣጣፈ እና የተቀዳደደ ልብስ የለበሱ ብዙ ሰዎችን እንመለከታለን። ወደ ጎዳናው ወርደን ምን እንዳለ እንመልከት።
>
> ብዙም የሚስብ እይታ የለም። በርካቶቹ ዓይነ-ስውሮች ናቸው፤ ብዙዎቹ የገረጡ፣ የተጎሳቆሉና ያረጁ ናቸው ...ሴቶቹ ፊታቸው ሙሉ ለሙሉ ተሸፍኗል፣ ቢገለጥ ብዙ ስቃይና ችግር እንደሚናገር ያስታውቃል። ብዙዎች ሴቶች የደከሙና ፊታቸው የገረጣ ሕፃናት ታቅፈዋል። በመቶዎች የሚቆጠሩ በዚህ ሁኔታ ተሰባስበዋል። ጎዳናው ሁሉንም የሰው ዘር ያካተተ ይመስላል። ሶሪያዎች፣ አረቦች፣ ኢትዮጵያዊያኖች እናም ሌሎች።
>
> ሰዎቹ የቤቱን ግድግዳው ተደግፈው ተኮልኩለው ተቀምጠዋል። ሁሉም አንድ ነገር የሚጠባበቁ ይመስላሉ፤ ምን ይሆን የሚጠብቁት? እስቲ አብረናቸው እንቆይ።
>
> ብዙም አልጠበቅንም። በሩ ተከፈተና አንድ ሰው ወጣ። የመካከለኛ ቁመና ተክለ-ሰውነት ያለው

ጠንከር ያለ ሰውዬ ነው፡፡ ነጣ ያለ ቀለም ያለው ካባ ለብሷል፡፡ ጥምጣምም ጠምጥሟል፡፡ እድሜው 60 ገደማ ይሆናል፡፡ ግራጫ የሆነው ፀጉሩ ትከሻው ላይ ተንዠርፏል፡፡ ፊቱ ሰፊና ዘለግ ያለ ሲሆን፣ አፍንጫው በትንሹ ቆልመም ያለ ነው፣ ጺሙ ሙሉ ግጥም ያለና ነጭ ሲሆን ለእይታ ግን አይከብድም፡፡ ዓይኖቹ ግራጫማ እና ሰማያዊ፣ ትላልቅ እና ለስላሳ ሲሆኑ ዘልቀው የሚገቡ ናቸው፡፡ ሁኔታውና አኳኋኑ ቀለል ያለ ሲሆን ሆኖም ግን በእንቅስቃሴዎቹ ውስጥ ፀጋ የተመላው ደግነት፣ ክብር እና ግርማም አለ፡፡ በሰዎቹም መካከል ሲረማመድ የሰላምታ ቃላትን ይሰነዝራል፣ እኛ ባይገባንም የፊቱን ቸርነትና ሩህሩህነት ግን እናያለን ፡፡ በጠባቡ የጎዳና ጥግ ላይ ቆሞ ወደ እሱ እንዲመጡ ሰዎችን ይጋብዛል፡፡ የተኮለኮሉት ሰዎች ወዲያውኑ ከበቡት፣ እሱም ቀስ ብሎ ገፋ አደረጋቸውና በሰልፍ በየተራ እንዲመጡ አደረጋቸው፡፡ ወደ እርሱ ሲመጡ እጆቻቸውን በሰፊው ይሰዳሉ፡፡ ለእያንዳንዳቸው መጠነኛ የሆነ ሳንቲም ይሰጣቸዋል፡፡ ሁሉንም ያውቃቸዋል፡፡ ፊቶቻቸውን፣ እራሳቸውንና ጆርባዎቻቸውን በእጁ ይዳብሳል፡፡ አንዳንዶቹን ያስቆማቸውን ይጠይቃቸዋል፡፡ አንድ የሚያነክስ ያረጀ ጥቁር ሰውዬ ደግነት በተሞላው ሁኔታ ጥያቄም ሰላምታም ያቀርባል፣ ለጋሻቸው አዛውንት ሰፊ ፊቱ ፀሐያማ በሆነ ፈገግታ አበራ፣ ፈገግ በማለት ለጥያቄው መልስ ሲሰጥ ነጭ ጥርሶቹ የጠያቂው ጥቁር ቆዳዎች ላይ ይንጸባረቁ ነበር፡፡ አንድ ልጅ የያዘች ሴትዩ ደግሞ አስቆመና ልጁን በፍቅር ደባበሰው፡፡ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ሰዎቹ አጠገቡ

ደርሰው ሲያልፉትም አንዳንዶቹ እጁን ይስማሉ፡፡ ለሁሉም "መረሃባ መረሃባ" የሚል የማበረታቻ ሰላምታ ይሰጣቸዋል፡፡

በበዓላት ቀናት ድሆችን በየቤታቸው ይጎበኛቸዋል፡፡ ስለጤናቸው እና ስለደህንነታቸው ይጠይቃቸዋል፣ ሳያገኛቸው የቀሩትን ደግሞ ስም እየጠራ ይጠይቃል፣ ለሁሉም ስጦታዎችን ይቸራል፡፡

ለሚለምኑትን ብቻ አልነበረም የሚረዳው፡፡ መለመን አሳፍሯቸው በጸጥታ የሚሰቃዩትንም፣ የቀን ተቀን የሥራ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦቻቸውን ማኖር ያቃታቸውንም ለሁሉም በድብቅ የሚበሉትን ይልካል፡፡

ሁሉም ሰው ያውቀዋል፣ ይወደዋል፣ ሃብታሙም ድሃውም፣ ወጣቱም አዛውንቱም፣ በእናቱ እቅፍ ውስጥ ያለ ሕፃን እንኳን ያውቀዋል፡፡ በከተማ ውስጥ አንድ ሰው መታመሙን ከሰማ እስላም ይሁን ክርስቲያን ወይንም ሌላ ለእሱ ግድ የለውም፣ ሁሌም አጠገባቸው ሆኖ ያስታምማቸዋል ወይንም ታማኝ የሆነ ሰው ልኮ ያስጠይቃቸዋል፡፡ ሐኪም ካስፈለገና በሽተኛው ድሃ ከሆነ ሐኪም ይዞ ይሄዳል ወይንም ይልካል መድሃኒትም እንዲሁ፡፡ የቤታቸው ጣራ የሚያፈስ ከሆነ ወይንም መስኮታቸው ከተሰበረና ለጤና አስጊ ከሆነ ሠራተኛ ልኮ ያስጠግናል፣ እየሄደም ይቆጣጠራል፡፡ ማንም ሰው ከተቸገረ፣ ልጆቻቸው እስር ቤት ከተጣሉ፣ በሕግ የሚፈለጉም ከሆነ፣ ሌላ ችግርም ከደረሰባቸው አብዱል-ባሃ ነበር ባለስልጣኖችን የሚማጸንላቸውና እርዳታ የሚጠይቅ ላቸው፡፡ ሃብታም ይሁን ድሃ

ሁሉም ለምክር ወደ እርሱ ይመጣሉ፡፡ እርሱ የሁሉም ሰዎች መልካም አባት ነው፡፡

ይህ ሰው ከሰላሳ አራት ዓመታት በላይ በአካ እስረኛ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የእስር ቤቱ ጠባቂዎችም ጓደኞቹ ሆነዋል፡፡ የከተማው ገዥ፣ የሰራዊቱ ጓድ አዛዥ ጭምር እንደወንድማቸው ያከብሩታል፣ያደንቁታል፤ የማንም ሰው ሃሳብና ምክር ከእርሱ የበለጠ ክብደት የለውም፡፡ በትንሹም በትልቁም የከተማው ተወዳጅ ነው፡፡ ሌላ ምን ሊሆን ይች ላል? ለሚጎዱት ሰዎች መልካም ማድረግ ለናዝሬቱ ኢየሱስ እንደሆነው ሁሉ ለዚህም ሰው ሕግ ነው፡፡

ለተቃዋሚዎቹ ያለውን አመለካከት በተመለከተ ከሰማኋቸው ከብዙዎች አንዱ ምሳሌ ልስጥ፡፡ ጌታው አብዱል-ባሃ ወደ አካ በመጣ ጊዜ በጣም ጨካኝ እና ግትር የሆነ አንድ አፍጋኒስታናዊ ሰው ይኖር ነበር፡፡ ይህ ሰው አብዱል-ባሃን የሚያየው እንደመናፍቅ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃን በጣም ጠላው ሌሎችንም በእሱ ላይ አነሳሳ፡፡ በመስጊድ ውስጥ ሰዎች ሲሰባሰቡና እድሉ ሲገኝ በመራራ ቃላት ይወቅሰዋል ፡፡

ይህ ሰው ስለአብዱል-ባሃ ሲናገር “እርሱ እኮ አስመሳይ ነው፣ ለምን ከእርሱ ጋር ትገናኛላችሁ” ይላል፡፡ መንገድ ላይ ሲሄድ አብዱል-ባሃን ካየ እንዳያረክሰው በማለት ፊቱን በካባው ይሸፍን ነበር፡፡

አፍጋኒስታዊው ሰው ይህን ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ አብዱል-ባሃ ያደረገው ግን ይህ ሰው በመስጊድ ውስጥ የሚኖር ድሃና የተራቆተ ስለሆነ ምግብና ውኃ ይልክለት ነበር፡፡ እርሱም የተላከለትን ይቀበላል

ሆኖም ግን አያመሰግንም፡፡ ሲታመም አብዱል-ባሃ ሐኪም፣ ምግብ፣ መድሃኒት፣ ገንዘብ ይዞለት ሄደ፡፡ ይህንንም ተቀበለ፣ ሆኖም ግን ሐኪሙ የልብ ምቱን እንዲመረምር አንዱን እጁን ሲሰጥ በሌላ እጁ ደግሞ ካባውን ሰብስቦ ፊቱን ይሸፍንበት ነበር አብዱል-ባሃን ላለማየት፡፡ ለሃያ አራት ዓመት አብዱል-ባሃ ልግስ ናውን ቀጠለ፣ አፍጋኒስታዊው ሰውዬም በጥላቻው ጸና፡፡ አንድ ቀን ግን ሰውየው አብዱል-ባሃ ቤት ሄደ፣ እግሩ ላይ ወድቆ፣ በተማጽኖ ስቅስቅ ብሎ አለ ቀሰ፡፡

ይቅር በለኝ ጌታዬ ሲል ጮኸ፡፡ ለሃያ አራት ዓመት ክፉት ሰርቼብሃለሁ አንተ ግን መልካም አድርገህል ኛል፡፡ አሁን ስህተት እንደሰራሁ ተረድቻለሁ አለ፡፡

አብዱል-ባሃም ከተንበረከከበት እንዲነሳ አደረገው ወዳጅም ሆኑ፡፡

አብዱል-ባሃን ሲያዩት እንደማንኛውም ሰው ይመስላል፣ ነፍሱ ግን ኃያል ነው፡፡ ለእራሱ ምንም አይፈ ልግም፣ ምቾት፣ ክብር፣ እረፍት አይሻም፡፡ ሦስት ወይንም አራት ሰዓት ከተኛ ይበቃዋል፡፡ ቀሪውን ጊዜውንና ጥንካሬውን ሁሉ በመንፈስ ወይም በአካል ለሚሰቃዩት ሰዎች ድጋፍ ይሰጣል፡፡ “እኔ የአምላክ አገልጋይ ነኝ” ይላል፡፡

የአካው አባስ ኤፌንዲ ማለት ይሄ ነው፡፡

እ.ኤ.አ. 1903 ሚርዛ ባዲኡላህ ከሚርዛ ሙሐመድ-አሊ ጋር ግንኙነቱ መቋረጡንና አብዱል-ባሃን በጥብቅ መከተሉን በማስታወቅ ለባሃኢዎች ደብዳቤ ጻፈ፡፡ በሌላ ደብዳቤ ደግሞ የባብ ዘርና የባሃኡላህ አማች ለሆኑት

ለሃጂ ሰይድ አፍናንም ጻፈ፡፡ በሚርዛ ባዲኡላህ የተፃፈው ጽሑፍ የቃል-ኪዳን አፍራሾችን ሴራ በዝርዝር የሚገልጽ ሲሆን በኋላ ላይም በካይሮ በበራሪ ወረቀት መልክ ተደርጎ ታተመ፡፡ ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ብራውን በ1903 ፀደይ ወቅት ካይሮ ደርሶ ነበር፣ ሚርዛ ባዲኡላህ ግብፅ መድረሱን በሰማበት ጊዜ ማርች 11 ቀን የተፃፈ ደብዳቤ ላከ ለት፡፡ በደብዳቤ ውም፣ ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ ስለ አብዱል-ባሃ ለየሰው ሲነዛ የነበረው ነገር ሁሉ የፈጠራ ወሬ መሆኑን እና በክፋት የተነሳሳና የግል ጥቅምን ብቻ እንደሚፈልግ አረጋግጦለታል፡፡ ሚርዛ ባዲኡላህ ለፕሮፌሰር ብራውን በባሃኡላህ ለተሾመው ለአብዱል-ባሃ ታማኝ መሆኑን ገልጾ ነበር፣ ሆኖም ግን ይህ ታማኝነቱ ሊቆይ አልቻለም፡፡

እ.ኤ.አ. በ1903 በፋርስ ውስጥ ከባድ የስቃይና የእልቂት ወቅት ተከሰተ፡፡ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በአገረ ገዢው (ሱልጣን) ላይ ጫና እየጨመረ መጣ ፡፡ ሴራዎች፣ ክፋቶች እና ስውር ደባዎች መጀመሪያ ላይ ቅጣት ያመራው በዋናነት፣ በአይሁድ እና በዞራስተርያውያን ላይ ነበር፡፡ በሰሜን-ምዕራብ ታብሪዝ ውስጥ የነበረው መረጋጋት በመጀመሪያ ተደመሰሰ፣ የበለጠ ደግሞ በደቡብ ውስጥ የከፋ አረመኔያዊ ድርጊት ተፈጸመ፣ ተጎጂዎቹም ባሃኢዎች ነበሩ፡፡ እንደተለመደው ለችግራቸው ሁሉ ባሃኢ ዎችን መጨፍጨፍ ከችግር መወጣጫቸው አድርገው ወሰዱት፡፡ በቴህራን የእንግሊዝ ሚኒስትር የሆኑት ሰር አርተር ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ሲያደርጉ፡- “በክርስቲያኖች ትምህርት ቤቶች እና ባለሥልጣናት ጥቃቶች ከሚፈጽመው ጉዳት ይልቅ በባቢዎች ላይ የተሰነዘ ረው ጥፋት የበለጠ ውጤት ሊያስገኝ በመቻሉ የአገረ-ገዢው ሱልጣን እንዳስደሰተው ገልጸዋል፡፡”

ሼህ ሙሐመድ-ታቂ በመባል የሚታወቀው፣ ባሃኡላህ “ይድረስ ለተኩላ ልጅ” የሚለውን ጽላቱን የጻፈለት የኢስፋሃን ተደማጭነት ያለው የእስልምና መሪ፣ አመጽ እንዲያስነሱ ሕዝቡን ሰብስቦ ወደ ከተማው አደባባይ ይዟቸው ወጣ፡፡ እሱ ኢስፋሃንን ረብሻ ውስጥ መክተቱ ብቻ ሳይሆን በምሳሌነትም ሆነ በቀጥታ የያዝድ ከተማን ህዝብ ጭምር በማነሳሳት ወደ ጭካኔ እንዲገፋፉ አደረገ፡፡ የያዝዱ አገረ ገዢ ተሰሚነት የሌለውና ዋጋ ቢስ ሰው ስለነበር እራሱን ብቻ አተረፈ፡፡ አክራሪዎቹ ጭካኔያቸው እንደእብድ አደረ ጋቸው፣ አባካኝ የሆኑት የከተማው ሰዎች በዘረፋ የግል ጥቅማቸውን መጠቀሚያ አደረጉት፡፡ ጭካኔው በያዝድ ከተማ ዙሪያ ባሉ መንደሮችም ተዛመተ፡፡ የተደረገው ጭፍጨፋ እ.ኤ.አ. 1852 ባብ መስዕዋት ከሆነ በኋላ ከተ ደረገው ጭፍጨፋ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

ወደፊት ባሉት ዓመታት አብዱል-ባሃ የባሃኢዎች ደም በፋርስ/ኢራን ውስጥ እንደጅረት መፍሰሱ እርሱን እንዴት እንዳሰቃየው ይናገር ነበር፡፡ የጭፍጨፋውን ሁኔታ የሚገልጽ ልዩ የሆነ ጽላትም ገለጸ፡፡ በጭፍጨፋው ዓመታት ወቅትም የአካ ባሃኢዎች ለአጋር ወንድሞቻቸው ለያዝድ ባሃኢዎች እንዲጸልዩም አስደረገ፡፡ በገለጸው ጽላትም ላይ እንዲህ ብሏል፡-

> “በአምላክ ውሳኔ፣ እምነቱን የጋረደው መጋረጃ ይነሳል፣ እናም ይህ ብርሃን የሁሉንም አገራት አድማሶችን ያበራል፡፡ የአምላክ እምነት ማስረጃዎች ያሸንፋሉ፣ የክቡሩ ጌታህ ደረጃዎች የላቀ ከፍታ ላይ ይውለበለባሉ፡፡ የጥርጣሬ መሠረቶች ይፈርሳሉ፣ የጨለማ ደመናዎችም ይበታተናሉ፡፡ የእርግጠኝነት ማለዳ ይነጋል፣ የአስደናቂ ምልክቶች ድምቀትም

> የምድር እና የሰማይ መንግሥትን ያረካል፡፡ ከዚያም የከፋፋዮች ሰንደቅ ይወድቃል፣ የጠላቶች ፊት ይገረጣል፣ የሐሰተኛ መሪዎች ድንጋጌ ውድቅ ይሆናል፣ አማኞች በላቀ ሁኔታ ይደሰታሉ፣ ከሃዲዎች በግልጽ ኪሳራ ውስጥ ይወድቃሉ ፡፡”

የሚርዛ ሙሐመድ-አሊ እና የአጋሮቹ ሴራዎች ማብቂያ የላቸውም ፡፡ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የመቃብር ሕንጻውን ግንባታ ለማስቆም ወይም ለማዘግየት ያደረጉት ሙከራ በተለይ አስከፊ ነበር፡፡ አንዳንድ ባሃኢዎች ቁጣቸው ስላየለ አብዱል-ባሃ የጥፋተኞችን ሴራ እንዲያጋልጥና ጉዳዩን በኦቶማን ባለሥልጣናት ፊት እንዲያቀርብ ጠየቁት፡፡ አብዱል-ባሃ ጥያቄያቸውን አልተቀበለም፡፡ የአንድነት ግንባታ ውን ጥረት ውደቅ በማድረግ መላውን የሰው ዘር አንድ የሚያደርግ ተልእኮው የሆነውን የባሃኡላህን ቤተሰብ በአጠቃላይ ለዓለም ለማቅረብ አልፈልግም አለ፡፡

በምዕራቡ ዓለም ያሉ ባሃኢዎች ከኦቶማን የጭቆና ቀንበር አብዱል-ባሃን ነፃ ለማውጣት መንገዶችንና ዘዴዎችን ይፈልጉ ነበር፡፡ ፓሪስ ባሉ ባሃኢዎች አማካይነት ገንዘብ ተዋጣ፡፡ ዓላማውም የኦቶማን ግዛት ዋና ከተማው ወደ ሆነው ወደ ቁስጥንጥንያ በመሄድ የአብዱል-ባሃን ከእስር መለቀቅ ለማመቻቸት ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ስለሁኔታው ሲነገረው፣ እቅዳቸውን እንዳ ይቀጥሉ በቴሌግራም አሳወቃቸው፡፡ ሳይታወቅ እያደረጉት ያለው ሙከራ ሾልኮ ወጣና መረጃውን የቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ሰሙት፡፡ ይህንን መረጃም አብዱል-ባሃን የበለጠ ለመጉዳት ተጠቀሙበት፡፡

እ.ኤ.አ 1904 አብዱል-ባሃ ሁለት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ የነበራቸው እቅዶች አወጣና ተገበራቸው፡፡ አንደኛው ሺራዝ የሚገኘውን የባብ መኖሪያ ቤት ማሳደስ ሲሆን

ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪያው የባሃኢ ቤተ-መቅደስን ግንባታ በኢሽቃባድ ከተማ ማስጀመር ነው። በፋርስ ባሃኢዎች ላይ ዘላቂ እና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በደረሰበት በዚያን ወቅት፣ አብዱል-ባሃ የባብ ቤት እደሳ ሥራ በፍጥነት እንዲጀመር የባብ ቤተሰብ ዋና ለሆኑት ለአቃ ሚርዛ አቃና ለሚስቱ የወንድም ልጅ ለሆነው አስቸኳይ ጥሪ ላከ። ይህ ባብ ለሙላ ሑሴን እምነቱን ያወጀበት ቤት ከጊዜ በኋላ የባብ የዘር ሐርግ ያላቸው አቃ ሚርዛ አቃ ቤቱን እንዲንከባከቡ ባሃኡላህ ሾሟቸው ነበር። ይህ ቤት በማርጀቱ የተነሳ የቀድሞውን ውበትና ቅርጽ አጥቶ ነበር። በአብ ዱል-ባሃ መመሪያ መሠረት አቃ ሚርዛ አቃ አንድ እቅድ አዘጋጀ፣ እቅዱም ቤቱን በባብ ቀናት ጊዜ እንደነበረው ለማድረግ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ ያከተተ ነበር። ችግሮች እና አደጋዎች ቢያጋጥሙም ቤቱ ታድሶ አለቀ። ከዚያም ጥልቅ የሆነ ዕውቀት የነበራቸውና የቅርብ ክትትል ያደርጉ የነበሩት አቃ ሚርዛ አቃ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የአብዱል-ባሃ አርቆ አሳቢነት በጣም አስፈላጊ እና አንገብጋቢ የሆነውን ስራ ከመዘግየቱ በፊት ወደ ስኬታማ መደምደሚያው አደረሰው።

የአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ በወቅቱ የራሺያ ቱርኪስታን ግዛት የነበረችው ኢሽቃባድ የተባለች አዲስ ከተማ ብቅ ብላ ማደግ ጀምራ ነበር። ኢሽቃባድ የኢራን ድንበር ከተማ ለሆነው ለኩራሳን ቅርብ ነው። ኢራን አገር የተጨቆኑትና የተሰቃዩት ባሃኢዎችና ሌሎችም ሰዎች ወደ ኢሽቃባድ መፍለስ ጀመሩ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ባሃኢዎችን የሚጠሉና የሚቀኑባቸውም ነበሩ። የቅጥረኞች እና የጀብደኞች እጥረትም አልነበረም። በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ሴራ ተጠነሰሰና እ.ኤ.አ. 1889 ሃጂ መሐመድ ሪዳ ኢስፋሃኒ የሚባል ባሃኢ በጠራራ

ፀሐይ በገበያ መሐል በሁለት ቅጥረ- ገዳዮች ጥቃት ደርሶበት በጩቤ ተወግቶ ተገደለ። ፖሊሶቹ እነዚህን ሰዎች በቁጥጥር ስር አዋሉ፣ ነገር ግን የሌሎች ባሃኢዎች ሕይወት አደጋ ላይ ወደቀ። ሰማዕት የሆነው ሐጂ ሙሐመድ ሪዳ ኢማሞቹን በንቀት ተናግሯል በሚል ክስ ተመሰረተበት። የእሱ ያልተገባ አነጋገር ጥልቅ ሃይማኖተኛ የሆኑ ሰዎችንም ቁጣ ቀስቀሷል ተባለ። ሚርዛ አቡል-ፋድል በዛን ወቅት ኢሽቃባድ ውስጥ ነበር። ከራሺያው ገዢ ጋር ስብሰባ በማድረግ የባሃኢዎችን ጉዳይ አቀረበ ። ባሃኢዎቹ በሁሉም የአምላክ መልዕክተኞች እንደሚያምኑና እንደሚያከብሩ፤ ከሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ጋር በስምምነት እንዲኖሩ እምነታቸው እንደ ሚያስገድዳቸው እናም የሺያ እስልምና ኢማሞችንም እንደሚያከብሩ ተናገረ።

የራሺያው ንጉስ አሌክሳንደር፣ የፍርድ ሂደቱን እንዲያካሂድ ከሴንት ፒተርስበርግ (የራሺያ ዋና ከተማ) ወታደራዊ ኮሚሽን ላከ። ሁለቱ ነፍሰ ገዳዮች ወንጀል መፈጸማ ቸው ስለተረጋገጠ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው ። በግድ ያው ሴራ ውስጥ መሳተ ፋቸው የተረጋገጠ ሌሎች ስድ ስት ሰዎች ወደ ሳይቤሪያ እንዲወሰዱ ታዘዘ። ፍርዱ እን ዲለወጥ ከባድ ጥረቶች ቢደረግም አልተሳካም። ሆኖም እዚያው ፍርድ ቤት ውስጥ ባሃኢዎች ወደ ሳይቤሪያ ለተ ሰደዱት በድፍረት አማላጅ መሆናቸውን ተነገሩ። ባሃኢ ዎቹ ከፍተኛ ክብር አገኙ። ከጊዜ በኋላም ት/ቤቶችን ለማቋቋም፣ ቤተ-መፃህፍትና የቤተ-መቅደስ ግንባታን ለማ ስጀመር ምቹ እየሆነላቸው መጣ።

የህንፃውን ግንባታ ተግባር አብዱል-ባሃ ለባብ አጎት ባሃ ኡላህ ኪታብ-ኢቃን ለገለጸለት ለሃጂ ሚርዛ ሙሃመድ-ታኪ አደራ ሰጠ። የቤተ-መቅደሱ አጠቃላይ ንድፍ በእራሱ በአብዱል-ባሃ የተሰራ ሲሆን፣ ራሺያዊው የስነ-ሕንፃ ባለ ሞያው ቮልኮቭ የግንባታ ዝርዝሮችን እቅድ አውጥቶ አስፈጸመ።

የቤተ-መቅደሱ የምሥረታ-ድንጋይ ዲሴምበር 1902 ዋና ባለሥልጣናት በተገኙበት ተደረገ። ከዚያም በኋላ ሥራው ያለማ ቋረጥ ቀጠለ። እ.ኤ.አ. 1907 የቤተ-መቅደሱ ጉልላት ተሰርቶ አለቀ። ሐጂ ሚርዛ ሙሐመድ-ታኪ ያን የከበረ ሕንፃ ለማሰራት አብዛኛውን የራሳቸውን ሀብት ተጠቅመዋል። በዓመቱ መገባደጃ ላይ በአብዱል-ባሃ ጥሪ መሠረት ወደ ቅድስት አገር ሐይፋ ሄዱ። የዓይን እማኝ የሆኑት ዶክተር ሀቢብ ሙዓያድ በአብዱል-ባሃና በሀጂ ሚርዛ ሙሐመድ-ታኪ መካከል የነበረውን ግንኙነት አስቀምጠው ልናል፡- “እርሳቸውን የያዘችው አነስተኛ መርከብ በኃይለኛ የባሕር ሞገድ ተናውጣ ወደብ ደረሰች። እድሜያቸው ስለ ገፋ ይህ ሁኔታ እርሳቸውን አድክሟቸው ነበር። አብዱል-ባሃ ስለጤንነታቸውና ስለደህንነታቸው ተጨንቆ ስለነበር በዚያን ወቅት መንፈሳዊ ጉብኝት እያደረጉ ለነበሩ ሁሉ አብረውት ወደ እርሳቸው ዘንድ እንዲሄዱ ጥሪ አቀረበ።

ሀጂ ሚርዛ መሃመድ-ታኪ ቀሪውን የህይወታቸውን ቀናት በቅድስት ሀገር ሐይፋ ኖሩ፤ በመጨረሻም እ.ኤ.አ በ1911 እዚያው አረፉ። መቃብራቸው በቀርሜሎስ ተራራ ግርጌ፣ የአብዱል-ባሃ ደቀ መዝሙር እና የባሃኡላህ እና የአዲሱ ዘመን ደራሲ ከሆነው ጆን. ኢ. ኤስልሞንት መቃብር አጠገብ ይገኛል።

አብዱል-ባሃ በእነዚያ አደገኛ የመከራ ቀናት ለእኝህ የባብ እኅት እነዚህን ትንቢት አዘል ቃላቶች ነግሯቸው ነበር፡-

"ይህ እምነት እንዴት ታላቅ፣ እንዴት እጅግ ታላቅ ነው! የሁሉም ዓለም ሕዝቦችና ወገኖች ጥቃት ምንኛ የከረረ ነው። በቅርቡ አብዛኛው የመላ አፍሪቃ፣ የመላ አሜሪካ ሕዝብ ሁካታ፣ የአውሮፓውያንና የቱርኮች ጩኸት፣ የቻይና እና የሕንድ ተቃውሞ ከሩቅና ከቅርብ ይሰማል። ሁሉም በሙሉ ኃይላቸው የእርሱን እምነት ለመቃረን ይነሳሉ ። ያን ጊዜ የጌታ ጀግኖች ከሰማይ በሚመጣው ጸጋው እየተረዱ፣ በእምነት ተጠናክረው፣ በግንዛቤ ኃይል እየታገዙና በቃል ኪዳኑ ሠራዊት በመደገፍ ይነሱና "በተሸነፉት ወገኖች ላይ የደረሰውን ግራ መጋባት ተመልከቱ" የተሰኘውን ጥቅስ እውነትነት ያሳያሉ። "

እ.ኤ.አ. 1904 አዲስ መከራዎችን ይዞ መጣ። ክፋት ያዘሉ የአሉባልታ ወሬዎች በሕዝቡ ዘንድ ተሰራጩ፣ ሚርዛ መሐመድ ዓሊ በአካ ውስጥ መከፋፈልንና ግራ መጋባትን ፈጠረ። አዲስ የተሾሙ ባለሥልጣናት ወዳጅነታቸውን አላሉ፣ ጠላትም ሆኑ። የእነርሱ አመለካከት እና የአንዳንድ የአካ እንዲሁም የሐይፋ ነዋሪዎች አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ አደገኛ ሆነ። ስለአብዱል-ባሃ መጥፎ የሆኑ ዘገባዎች በሶሪያ እና በግብፅ ጋዜጦች ላይ ታተሙ።

ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ አሁን በአብዱል-ባሃ ላይ በማይረባ እና መሠረተ-ቢስ በሆኑ አሉባልታዎች ተሞልተው ክስ መሠረቱ። በሐሰት ሰነዶች ላይ ፊርማቸውን ለማኖር ፈቃደኛ እና ዝግጁ የሆኑ ምስክሮች ከአካ ሰዎች መካከል አገኙ። ይህ የሐሰት ሰነድ በሚርዛ መሐመድ ዓሊ ግብረ አበሮች አማካይነት ወደ ቁስጥንጥንያ ተላከ፣ የቱርክ

ግዛት ገዢ አብዱል ሃሚድም ይህን ሰነድ ባገኙ ጊዜ ተቆጥቶ አብዱል-ባሃን ያጠፈዋል የሚል ተስፋም ነበራቸው፡፡ አብዱል-ባሃን ለማጥፋት ባለስልጣኖቹ ጉዳዩን የሚያጣራ ኮሚሽን ወደ አካ ላኩ፡፡

በአብዱል-ባሃ ቤት ዙሪያ ሰላይ ተመደበ፡፡ ሙሉ ቀን በዓይነ ቁራኛ የሚካሄደውን ነገር ሲከታተሉ ይውላሉ፣ ማታ ማታም እንዲሁ ተደብቀው ያመሻሉ፡፡ የአብዱል-ባሃን ቤት የሚያዘወትሩ ሰዎች መፍራት ጀመሩ፣ ወደ እርሱ ቤት መሄድም አቆሙ፡፡ የአካ ባሃኢዎችም እዚያ መኖራቸው እንደማይፈለግ እንዲሰማቸው ተደረገ፡፡ ሸክማቸውን ለማቃለልና ሊፈጠሩ የሚችሉ ተገቢ ያልሆኑ ትዕይንቶችን ለማስቀረት አብዱል-ባሃ ጊዜያዊ መኖሪያቸውን ወደ ሌላ ቦታ ማድረግ እንዳለባቸው ወሰነ፡፡ ብዙዎቹ የአካ ባሃኢዎች ለአጭር ጊዜም ቢሆን ቤታቸውንና ኑሮዋቸውን ትተው ለመሄድ የገንዘብ ድጋፍ የሚፈልጉ ነበሩ፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ ግብፅ መሄዳቸውን ለማመቻቸት በፓሪስ ከሚኖሩ አሜሪካዊ ባሃኢዎች ብዙ ገንዘብ ተበደረ፡፡ በቁ ጥር ሰባ የሚሆኑ ወደ ግብፅ ሄዱ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመንፈሳዊ ጉብኝት ከምስራቅም ሆነ ከምዕራብ አገራት የሚመጡ ምዕመናን ቁጥር መጀመሪያ ላይ እንዲቀንስ ተደረገ ከዚያም ሙሉ ለሙሉ ቆመ፡፡ አንደበተርዕቱ የሆነው አንዳሊብ የተባለው ባሃኢ ባለቅኔ የእነዚያን የመከራ ቀናት ስሜት በተሞላ ሁኔታ የገለጹት ቅኔዎች ባሃኢዎቹ የሚያነቧቸው ሆኑ፡፡ በቃል-ኪዳን አፍራሾች ቅናት ምክን ያት ሐሜትና አሉባልታ በስፋት በዝቶ በስተመጨረሻ የፀጋ በሮች እንዲዘጉ ማድረጋቸውን በመግለጽ ለብዙ ዓመታት ጻፈ፡፡

ኮሚሽኑ አብዱል-ባሃን ጠርቶ በእርሱ ላይ ለተሰነዘሩ ክሶች መልስ እንዲሰጥ ጥሪ አቀረበ፡፡ እሱም ከኮሚሽኑ አባላት ጋር ብዙ ጊዜ ተገናኘ፡፡ በማያወላውል ሁኔታ እርሱ ላይ የተጣሉት ክሶች በተደጋጋሚ የሚነሱና ዋጋ አልባ መሆናቸው የባሃኡላህን ጽሑፎች በማሳየት አስረ ዳቸው፡፡ እርሱ የባሃኡላህ ልጅ እና ተተኪው እንደሆነ፣ የኡቶማን አገዛዝን ለማስወገድ በማንኛውም መጥፎ ሴራ ውስጥ ሊገባ እንደማይችል አስረዳ፡፡ እርሱን ራሱን ለመጉዳት ለሚነሱ ግን ምን ዓይነት ችግሮችንና ፈተናዎችን ለመጋፈጥ ዝግጁ እንደሆነም ተናገረ፡፡ ሌላው ክስ የተመሰረተበት ደግሞ በአካ አቅራቢያ የሚኖር አንድ በቁም ጽሑፍ ችሎታው የታወቀ ሰው "ያ ባሃኡላህ አብሃ" የሚለውን ማወደሻ ስም በእራፊ ጨርቅ ላይ ጽፎ ለመርማሪ ኮሚሽኖቹ በመላክ አብዱል-ባሃ ይህን ማወደሻ ስም እንደ መፈክር በመጠቀም ያሴራል በማለቱ ነበር፡፡ በተጨማሪም ደግሞ የባሃኡላህ ወንድም ልጅ ይህን ማወደሻ ስም እንደ መፈክር በመጠቀም ወደ ገሊላ መንደር ሄዶ ሰዎች እንዲያምጹ ለማድረግ እያሰባሰበ እንደሆነ በተጨማሪም የአካው ሼክ እንዲሁ ጆርዳን አገር ዘላኖችን እንዲያምጹ እንዳነሳ ሱበት ተነገረ፡፡ ለዚህ የተሳሳተ ክስ አብዱል-ባሃ ይህ የማ ወደሻ ስም እንዲህ በየቦታው ለእይታ ሲቀርብ በብዙዎቹ፣ በአገረ ገዢው ራሺድ ፓሻ ወኪሎች(ሰላዮች) አለመታወቁ ተዓምራዊ መሆኑን አስረዳ፡፡ በአብዱል-ባሃ ላይ የተመሠ ረተው ሌላ ክስ ደግሞ እሱ ለመመስረት ለሚጓጓለት መንግሥት መሠረት ሆኖ እንዲያገለግል ሰፋፊ መሬቶችን መያዙ ነው፡፡ አብዱል-ባሃ ምላሽ ሲሰጥ፣ በጥብቅ ክትትል የሚደረግበት፣ እንቅስቃሴዎቹንም በቅርብ የሚከታተሉት እና ምርመራ የሚደረግበት የቱርክ ኢምፓየር እስረኛ ሆኖ

ሳለ፣ መንግሥት ለማቋቋም የተሳካለት ከሆነ ይህ ተዓምር ነው አለ፤ እናም አስፈላጊ ከሆነ ያለው ሰፊ ጋሻ መሬት በሁለት መቶ ፓውንድ ብቻ ለመሸጥ ፍቃደኛ መሆኑን ተናገረ፡፡

ሁሉም ክሶች ውድቅ እየሆኑ መጡ፡፡ ሌላው የመርማሪ ኮሚሽኑ የጠየቀው አሜሪካውያኖቹ ለምን አካ እንደመጡ ነበር፡፡ እነርሱ የመጡት የባሃኡላህን መካነ-መቃብር ለመጎብኘትና መንፈሳዊ አስተምህሮት ለማግኘት ነው ሲል ምላሽ ሰጠ፡፡ ኮሚሽኑ በመቀጠልም አብዱል-ባሃ በእጁ ውስጥ የታዩ አመጽ የሚያስነሱ ጽሑፎችን አሰራጭቷል ለሚለው ክስ ምን እንደሚመልስ ጠየቀ፡፡ እንደዚህ ያሉ ጽሑፎች፣ በእጁ ውስጥ አለመኖሩን አሳወቀ፡፡ መርማሪ ኮሚሽኑ ብዙ ሰዎችን በማባበል፣ ጉቦ በመስጠትና በማስፈራራት በዚህ ጉዳይ ላይ ምስክር እንዲሰጡ አደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ አብዱል-ባሃ በግርማ ሞገስና በአዛዥነት ክብር ብድግ ብሎ፣ በጭራሽ በእጁ ውስጥ አንዳች አመፅ ሊያስነሳ የሚችል ጽሑፍ እንደሌለ በአጽንኦት በመግለጽ ማንም ሳያግደው ክፍሉን ጥሎ ወጣ፡፡ ከዚያም ሁሉም ክስ መና ሆነ ቀረ፡፡

በዚያን ወቅት ለአብዱል-ባሃ የሚጻፉ ደብዳቤዎች ሁሉ ወደ ሐይፋ እንዲላኩ ተደርጎ ነበር፡፡ እዚያም ሲደርሱ ሐይፋ ውስጥ የሚኖር አንድ ባሃኢ ደብዳቤዎቹን ይቀበልና ወደ አብዱል-ባሃ አካ ይልካቸው ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. 1904 በተፈጠሩት ችግሮች ምክንያት ግን የሚላኩለት ደብዳቤዎች ሁሉ የወደብ ከተማ ወደሆነችው ወደ ፖርት ሰይድ እንዲላክ ተደረገ፡፡ አብዱል-ባሃም እዛ የሚደርሱት ደብዳቤዎችም በምንም ዓይነት መልኩ ወደ ሐይፋ ወይ ንም ወደ አካ እንዳይላኩና እዚያው እንዲቀመጡ ትእዛዝ

አስተላለፈ፡፡ ይህ ቢሆንም የአብዱል-ባሃ ብዕር እረፍት አድርጎ አያውቅም፡፡ በተቃራኒው እነዚያ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጉበት የነበሩት ወራቶች እጅግ ውጤታማ ጊዜያቶች ሆኑ፡፡ አብዛኛውን ምሽቶች የእርሱ ክፍል መብራቶች እስኪነጋ ድረስ በርተው ይታዩ ነበር፣ ሌሊቱን ሙሉ ሲጽፍ ያድራል፡፡ በአንድ ቀን እስከ ዘጠና ጽላቶች ይጽፍ ነበር፡፡ በምስራቅና በምዕራብ ያሉ ምዕመናኖችና ሌሎችም በብዛት ይጽፉለት ነበር፡፡ እሱም ለሁሉም ምላሽ ይሰጥ ነበር፡፡

ዓመቱ እያለቀ ሲሄድ ነገሮች ወደ መረጋጋት ተመለሱ፡፡ መንፈሳዊና ሌሎች ጎብኚዎችም መምጣት ጀመሩ፡፡ ግብፅና ሌሎች ቦታዎች ተሰደው የነበሩትም ባሃኢዎች ተመለሱ፡፡ እነዛን አስቸጋሪ የነበሩትን የመንግሥት ሃላፊ ዎች መልካም የሆኑ ተኳቸው፡፡ ከተለወጡት ባለሥልጣ ናት መካከል አንዱ የፖሊስ አዛዣ የሆነው ሰው ሲሆን ይህ ሰው የቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ዋና አጋዥ ነበር፡፡ የእርሱ ሪፖርቶች እና ቴሌግራሞች ሁኔታውን የበለጠ እያጋጋሉት በቁስጥንጥንያ ያሉ ባለሥልጣናትን ጥርጣሬ እንዲጨምር አድርጎ ነበር፡፡ ነገር ግን ከራሱ ከፍ ያለ ደረጃ ያለው ሌላ የኦቶማን ባለሥልጣንን ከጉዳዩ ጋር ለማያያዝ ሲሞክር ወደ ደማስቆ እዲመጣ ታዘዘ፡፡ በሁኔታው ተስፋ በመቁረጥ ቤተሰቡን እንዲጠብቅለት ወደ አብዱል-ባሃ ሄደ፡፡ አብዱል-ባሃም ቃል ገብቶ ቤተሰቡን ተንከባከበለት፣ እርሱ ግን ከቃል-ኪዳን አፍራሾች ጋር መገናኘቱን አላቆ መም ነበር፡፡ ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ጠንካራ ማስረጃ ነው ብለው ያሰቡትን በእንግሊዝኛ ጻፉ፡፡ በዚህ ጽሑፍም ባሃኢ ዎች አብዱል-ባሃን የሚያዩት የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አድርገው እንደሆነና ሁሉም መንግሥታት ለእርሱ መገዛት አለባቸው ብለውም

እንደሚያምኑ ጠቀሱ። የእነሱ ዓላማ ግልፅ ሲሆን፤ በምዕራቡ ዓለም ውስጥ የባሃኢ አስተምህሮቶችን ለማዛባት ነበር። በተያያዥነትም በደቡብ ምስራቅ አውሮፓ የኦቶማን ግዛት ብጥብጥ ስለነበር አብዱል-ባሃ ስልጣን ሊይዝ ይፈልጋል ብለው መወንጀላቸው ንጉሱን ያስቆጣል ብለው አሰቡ። ያዘጋጁትንም የእንግሊዝኛ የሐሰት ጽሑፍ ቅጅ ወደ ደማስቆ የፖሊስ አዛዥ ወደነበረው ሰው ልከው ወደ አረብኛ እና ቱርክኛ ቋንቋ አስተርጉመው ሁለቱን ቅጅዎች ለግዛቱ መሪዎች ማስጠንቀቂያ ይሆን ዘንድ አሳትመው ሰጡ። ይህ የታተመው ጽሑፍ ዋናው ከተማው ቁስጥንጥንያ ደረሰ። አብዱል-ባሃ ግን የቀድሞ የፖሊስ አዛዡን ቤተሰብ መንከባከቡን ቀጥሎ ነበር።

ከብዙ ዓመታት በፊት፣ በባሃኡላህ ዘመን አካ በመንግሥት ቢሮ ውስጥ ጸሐፊ ሆኖ የሚሰራ ሙስጠፋ ኤፌንዲ የሚባል ሰው ነበር፤ ባሃኢዎች ምቹ ሕይወት እንዳይኖሩ ገዥውን ሁልጊዜ በክፋት ያነሳሳል። እናም አገረ ገዢው አጋጣሚውን ለግል ጥቅሙ ለማዋል ፈለገ። አብዱል-ባሃ የተለያዩ የእርሱ ተንኮሎችን ትኩረት አልሰጣቸውም ነበር። አገረ ገዢው የባሃኢዎችን የንግድ ሱቅ እንዲዘጋ የማስገደድ ሀሳብን አቀረበ። አብዱል-ባሃ ይህን ተንኮሉን እንዲተው መከረው። ምክሩን ችላ ብሎ፣ አገረ ገዢው ባሃኢዎችን የሚጠሉ ታዋቂ ሰዎችንና የሃይማኖት መሪ ዎችን በመኖሪያ ቤት ውስጥ ለስብሰባ ጠራ። ዓላማውም እርምጃ ለመውሰድ እቅድ እንዲያወጡ ነበር። … ሆኖም ግን አገረ ገዢውንና ሌሎችንም ጭምር ከስራ እንደተባረሩ የሚገልጽ ቴሌግራም ቤይሩት ካለ የኦቶማን ባለሥልጣን ደረሳቸው። ከሶስት ወር በኋላ ይህ አገረ ገዢ የበለጠ ተዋርዶ ወደ ደማስቆ ተሰደደ። ቤተሰቡን አካ መተው

ነበረበት፡፡ አብዱል-ባሃም የእሱን ቤተሰብ ይንከባከብለት ጀመር፣ ጊዜው ሲመቻችም ወጪያቸውን ችሎ እርሱ ወዳለበት እንዲሄዱ አደረገ፡፡ አብዱል-ባሃ ወድቀት (ውርደት) የደረሰባቸውን ሰዎች የሚንከባከበው በዚህ ሁኔታ ነበር፡፡

የ1905 እና የ1906 ዓመታት በአንፃራዊነት ጫና እና እገዳ የሌለባቸው ነበሩ፡፡ መንፈሳዊ ጉብኚዎችና የአካ ነዋሪ ባሃኢዎች የተረጋጋ ሁኔታ አገኙ፡፡ በሌላ በኩል የኦቶማን ግዛቶች እና ፋርስ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነበሩ፡፡ የሻሁ አባካኝ ድርጊቶች ፋርስን ከአስከፊ የውጭ ብድር ስለዘፈቃት ራሺያንና እንግሊዝን ትማጸናለች፡፡

የኦቶማኑ ሱልጣን አብዱል-ሀሚድም በሁኔታዎች ምክንያት መፍራት ጀመረ፡፡ ቃል-ኪዳን አፍራሾችም ምንም እንኳን ጥንካሬያቸው የቀነሰ ቢሆንም ፍርሃቱን የመጠ ቀም ዕድል እንዳያመልጣቸው መጣር እንዳለባቸው ተገነ ዘቡ፡፡ የማይረባ ቢሆንም የመጨረሻ የተቀናጀ ጥቃት ለማ ድረግ ኃይሎቻቸውን አሰባሰቡ፡፡

በተንኮላቸው ምክንያት አራት ሰዎችን የያዘ መርማሪ ኮሚሽን እ.ኤ.አ. 1907 በፍጥነት ከኦቶማን ግዛት ዋና መቀመጫ ተላከ፡፡ የቀድሞው አጣሪ ኮሚሽን ማስረጃ እንደሌላቸው አረጋግጦ ያስወገዳቸውን ሰነዶችና ወረቀቶች ይዘው መጡ፡፡ መኖሪያቸው ንም የከተማው ታዋቂ ነጋዴ ቤት አደረጉ፡፡ ይህ ሰው የቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ቅርብ ወዳጅ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ተግባራቸው በአካ መስተዳደር ላይ የበላይነታቸውን ማሳየት ነበር፡፡ የአብዱል-ባሃ ወዳጅ ናቸው ያሏቸውን የከተማውን ገዢ ጨምሮ ሌሎች ባለሥልጣናት ወዲያውኑ አስወገዱ፡፡ ፖስታ ቤት እና ቴሌግራምን በጥብቅ ቁጥጥር ስር አዋሉ፤

በወቅቱ የተከበረ የበላይነት የነበረው የደማስቆ ገዢ ችላ ተባለና በቀጥታ ከዋናው የቱርክ ከተማ ኢስታንቡል ሚኒስትሮች ጋር ግንኙነት ተዘረጋ። ሰላዮች እንደገና አብዱል-ባሃ ቤት ዙሪያ ተመደቡ በዚህም ምክንያት ሰዎች እንዳይመጡ ተደረገ። የአካ ድሆች በየሣምንቱ አርብ ቀን ምጽዋት ለመቀበል ለመምጣት ፈሩ።

አብዱል-ባሃ የሊቢያ ግዛት ወደነበረው ትሪፖሊታኒያ ፋዚን ወደሚባል ከመላው ዓለም የተቆራረጠ ጭው ወዳለ በረሃ ሊጋዝ ነው የሚል ወሬ ተነዛ። ይህ ሁሉ በእንዲህ እያለ አብዱል-ባሃ ግን የአካ ነዋሪዎችን እስኪገርማቸው ድረስ የተለመደውን እንቅስቃሴ ያካሂዳል፣ ስለሚወራው ወሬም ግንዛቤ አልነበረውም፣ ኃይለኛ እና ከፍተኛ እጅ ያለው አጣሪ ኮሚሽን በመኖሩም ሙሉ በሙሉ ግድ የለሽ ነበር። የተከራየውን ቤት ጥገና ሲከታተል ይውላል። የአካራዩ ተወካይም ግራ ይገባው ጀመር። ሁሉም ሰው እንዳረጋገጠውና እርሱም እንዳመነው አብዱል-ባሃ በጥቂት ጊዜ ያቶች ውስጥ ከአካ እንደሚጋዝ ያውቅ ስለነበር ለምን ለቤት እደሳና ጥገና ይህን ያህል እንክብካቤና ገንዘብ እንደ ሚያወጣ አይገባውም ነበር። ከአካ ታዋቂ ሰዎች አንዱ አብዱል-ባሃ ዛፍ ሲተክል ያገኘዋል። ለማን ነው ዛፍ የምትተክለው ይለዋል? ከእኛ በፊት የነበሩት ሰዎች ዛፍ ተክለው እኛ ፍሬውን በልተናል፣ እኛም እንደነርሱ ለወደ ፊቱ ትውልድ መትከል አለብን አለው። የአካ ሰዎች አብዱል-ባሃ ለክረምቱ ነዳጅ እየገዛ እና እያከማቸ መሆኑን ሲያውቁ ደግሞ ይበልጥ ተገረሙ።

መርማሪ ኮሚሽኑ አካ ከመድረሱ ከጥቂት ቀናት በፊት አብዱል-ባሃ ሕልም አይቶ ነበር ለባሃኢዎቹ ነገራቸው።

በሕልሙም አንድ መርከብ ወደ ሐይፋ ወደብ ስትመጣ ያያል፣ ፈንጂ የሚመስሉ እርግቦችም ከመርከቡ እየወጡ ወደ ወደቡ ይበራሉ፡፡ የአካ ነዋሪዎች በሁኔታው በጣም ፈርተዋል እርሱ ግን በተረጋጋና ዘና ባለ ሁኔታ እርግቦቹን ያያል፡፡ በፈንጂ የተመሰሉት እርግቦቹ የወደብ ከተማው ላይ አንዣበው፣ አንዣበው ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡ ምንም ዓይነት ፍንዳታም አልተከሰተም፡፡ አብዱል-ባሃም አደጋ ተከስቶ እንደነበረና ሆኖም ግን ምንም ጉዳት ሳያደርስ እንዳለፈ ተነገረ፡፡

ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ መርማሪ ኮሚሽኑ በመምጣቱ ተደሰቱ፡፡ የኮሚሽኑ አባላት መኖሪያቸው ለእነርሱ ቅርብ ስለነበር የሚፈልጉትን ዜና ሁሉ ማግኘት ይችሉም ነበር፡፡ ሚርዛ መሃመድ-አሊ እና ግብረ-አበሮቹ ኮሚሽኑ የመጣ በትን ቀን ለማክበር በወዳጃቸው ሱቅ ውስጥ ተሰባስበው ነበር፡፡ እስካሁን የለፉበትና የጣሩበት፣ ተበድረው ጉቦ የሰጡበት እቅድ አሁን ለእነሱ በሚያጓጓ ሁኔታ ቅርባቸው ሆነ፡፡ የአብዱል-ባሃ እጣ ፋንታ እንደሰማያዊው የሜድትራንያን ባሕር ግልጽ ሆኖ ታያቸው፡፡ የሊቢያ ግዛት የሆነው ፋዚን በረሃ ሊያጠፋው ይጠባበቀዋልም አሉ፡፡ ከእዚያ አስቸጋሪ እና የማይመች ክልል በሕይወት ፈጽሞ ሊወጣ አይችልም ብለው አሰቡ፡፡ የወደፊቱ አጓጊ ራዕያቸው እንዲህ ነበር፣ ደስታቸውም ለአንድ ወር ያህል ቆየ፡፡

አብዱል-ባሃ ለመርማሪ ኮሚሽኑ ጥሪ ማድረግ ወይንም ወደ እነሱ መሄድ አልፈለገም፡፡ ይህን ቢያደርግ ኮሚሽኑ አስቀድመው ስለክሱ ይነግሩታል፣ ይህም ሁኔታ ለሰዎች ይደርስና አብዱል-ባሃ ጉቦ በመስጠት ከክሱ ነፃ ሆኗል ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች መርማሪ

ባይሆኑና ጎብኚ ቢሆኑ ኖሮ አብዱል-ባሃ ያለምንም ማመንታት ጥሪ ያድርግላቸው ነበር። የወንጀለኛ ፍርድ ቤቱን የሚመራውን ሰው አብዱል-ባሃ ሀሳቡን እንዲቀይር እንዲያሳምነው ላኩት። እርሱም አብዱል-ባሃን ከአንተ በስተ ቀር ሁሉም የአካ ታዋቂ ሰዎች መርማሪ ኮሚሽኑን እየ ሄዱ አግኝተዋቸዋል። ያንተ ወደ እነሱ አለመሄድ አስቆጥ ቷቸዋል፣ ቁጣቸውን ለማብረድ ያለህ ዝም ብለህ ሂደህ አግኛቸው አለው። ሰውየው የበለጠ ለማሳሰብ ለእራሱ ደህንነት ሲል ሁሉም ታዋቂ ሰዎች እንዳደረጉት እሱርም እንዲያደርግ ነገረው። አብዱል-ባሃም ሲመልስ አንተ ያልከውን ባደርግ ችሮታ ወይንም አድሎ እንዲያደርጉልኝ የምፈልግ ይመስላል፣ እኔ ግን ምንም የምሰጠው ምላሽም ሆነ የምፈልገው ችሮታ የለም አለ። የተላከው ሰውዬም በሃፍረት ተመለሰ።

የቤይሩቱ አገረ ገዢ ለምክትሉ አካ ላለው አገረ ገዢ አብዱል-ባሃን ለፍርድ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ እንዲጽፍ አሳሰበ። ቤይሩት እና ካይሮ ያሉ ጋዜጦች በአካ ውስጥ የፋርስ ሕዝቦች ጥቃት እንደደረሰባቸው ዘገቡ። በግብፅ የተደላደለ ንግድ ያላቸው ባሃኢዎች ወደ አካ እንዳይሄዱ ተከለከሉ፣ በአካ ውስጥ ያሉ ባሃኢዎች በከባድ ቁጥጥር ስር ዋሉ። ኢስታንቡል የሚገኘው የኢራን (የፋርስ) አምባሳደር ጋዜጦች ላይ እነዚህን ሁኔታዎች በማንበቡ በአካ ያሉ የፋርስ ሕዝቦችን እንዲታደግ ወኪሉን ላከ። ሆኖም ግን አካ ያሉ ባለሥልጣናት ችላ አሉት ወኪሉም ስለሁኔ ታው ለማሳወቅ በቤይሩትና በኢስታንቡል ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ ለማስደረግ አቀደ። አብዱል-ባሃ እንዲረጋጋ መከረው፡- “እነዚህ ችግሮች አይቆዩም ያልፋሉ” አለው። እንዳለውም ብዙ ሳይቆዩ አለፉ።

አንድ ቀን ምሽት ላይ አንድ ሰውዬ ሽፋን ባለው የፈረስ ጋሪ ከሐይፋ ወደ አካ ይመጣል። ጣሊያናዊ ሲሆን የእስፔን አገር ቆንስላም ነበር። ቤተሰቦቹ ደግሞ የጣሊያን መርከብ ኩባንያ ወኪል ነበሩ። ማንም ሳያየው ተጠንቅቆ አብዱል-ባሃ ቤት ይሄድና ቶሎ እርሱን ለማግኘት ይጠይቃል። ካገኘውም በኋላ ይህ ሰው አብዱል-ባሃን በጣም ስለሚወድና ስለሚያከብር እርሱን ከአካ ለማውጣትና ወደ ሚፈልገው ቦታ ለመውሰድ አንድ መርከብ አካ ወደብ እንደወደበች ይነግረዋል። ሁኔታው አጣዳፊ ስለነበር አብዱል-ባሃም ሃጂ ሚርዛ ሃይዳር-አሊን፣ አቃ ሪዳ አኩንድን፣ ሚርዛ ማህሙድ-ካሺን፣ የባለቤቱ ወንድም የሆነውን ሰይድ ያህያ እና ሚርዛ አሳዱአላህን እንዲ መካከሩበትና አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ጠየቀ። አብዱል-ባሃ የእስፔን ቆንስላው ያቀረበውን ጥያቄ እንዲቀበል በአንድ ድምፅ ውሳኔ አስተላለፉ። የአብዱል-ባሃ ምላሽ ግን ባብ አላፈገፈገም፣ እኔም አላፈገፍግም አለ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አጣሪ ኮሚሽኑ የክስ ደብዳቤዎችን ከፈረሙ ሰዎች ማስረጃ እያሰባሰበ ነበር። በመጠናቀቅ ላይ ያለውን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የሚገነባውን የመቃብር ሕንፃ ጎበኙ። ለታቃደለት ዓላማ የሚሆን ጠንካራ ይዘት ያለው ሕንፃ ነበር። አጣሪ ኮሚሽኑ ስለሚሰራው ሕንፃ ዓላማ ግን ግድ አልነበራቸውም። ከሕንፃው ስር የተገነባ ጉድጓድ ነበር ይህ ጉድጓድ አብዱል-ባሃ ምሽግ እየሰራ ነው ለተባለው ክስ ማስረጃ እንደሆነም አወቁ።

ከዚህ ጉብኝታቸው በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ከቁስጥንጥንያ ያመጣቻቸውን መርከብ ተሳፍረው ወደ ሐይፋ መጓዝ ጀመሩ። ጉዟቸውን እንደጀመሩ ፀሐይ መጥለቅ ጀምራ

ነበር። ከዚያም መርከቧ አቅጣጫዋን እንደገና ወደ አካ ቀየረች። የአካና የሐይፋ ከተማ ነዋሪዎች አስደንጋጭ የሆነውን የመርከቧን አቅጣጫ መቀየር እያዩ ነበር። አብዱል-ባሃን አስረው ለመውሰድ እየመጡ ነው ብለው አመኑ። የአብዱል-ባሃ ቤተሰቦችና ባሃኢዎቹ በፍርሃት ተዋጡ። አብዱል-ባሃ ተረጋግቶና ሰክኖ በቤቱ ግቢ ውስጥ ብቻውን እየተረማመደ ነበር። አካ ባሕሩ ዳርቻ በየቦታው ተኮልኩለው የዚህችን መጥፎ ነገር ልታመጣባቸው ያለ ችውን መርከብ አካሄድ የሚከታተሉ ባሃኢዎች ነበሩ። ፀሐይ በሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ እየሰጠመች ነበር መርከቧም መንገዷን ወደ አካ እያቀናች ነበር፣ ሆኖም ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በድንገት አቅጣጫዋን ቀይራ ወደ ሰፊው ባሕር መጓዝ ጀመረች። በድንገት ሊጋረጥባቸው የነበረው አደጋ ጠፋ። አብዱል-ባሃ ደህንነቱ ተጠበቀ። ምሽት ላይ ዜናውን ሊነግሩት ወደ እሱ ሲሄዱ አሁንም በእርጋታ በደማቅ ገጽታ በግቢው ውስጥ እየተረማመደ ነበር ።

በፍጥነት የመርማሪ ኮሚሽኑ መመለስን ተከትሎ ከኢስታንቡል የመጣው ሌላ ዜና የኦቶማን ንጉስ አብዱል-ሃሚድ ከሞት ማምለጡ ነበር ። ለእርሱ የታሰበ ቦምብ ፈንድቶ ሌሎችን ገደለ እርሱም ቆሰለ። የመርማሪ ኮሚሽኑ ኢስታንቡል የደረሰው በጣም አስጊ በሆነ ጊዜ ነበር። አብዱል-ሃሚድ በቅርቡ ሊከሰትበት ስለሚችለው አብዮት ስጋት ውስጥ ጣለው። ሁሉም ሀሳቡ እና ተግባሩ በዋና ከተማው እና በዙሪያው የነበሩትን አብዮተኞች ፈልጎ በማጥፋት ላይ ያተኮረ ሆነ። እጅግ ብዙ ገንዘብ ወጪ አደረገ፣ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰላዮችም አሰማራ እናም በፓሪስ የነበረው አምባሳደሩ ከንጉሡ ጭቆና ሸሽቶ የተሰደደው የቀድሞው የፓሪስ አምባሳደር እርሱን

ከስልጣን ለማውረድ ሲዶልትና ሲያሴሩ እንደነበር ደረሰበት፡፡ የዚህ ሴራ ጠንሳሽ መሪ ግን ሳይታወቅ ቀረ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አካ የነበረው መርማሪ ኮሚሽን እውነታ የሌለው ዳጎስ ያለ ሪፖርታቸውን ለአብዱል ሃሚድ ቢያቀርቡም ሊመለከተው አልፈቀደም፡፡ እናም የአብዱል-ባሃ ተቃዋሚዎች ተስፋቸውን የጣሉበት ዘገባ መና ቀረ፡፡ ከወራት በኋላ የአብዱል-ሃሚድ ትኩረት ወደ አጣሪው ኮሚሽን ሪፖርት ሲዞር በጣም ዘግይቶ ነበር፡፡ የወጣት ቱርኮች ሕብረት እና የእድገት ኮሚቴ የአብዮት ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አደረጉ፤ አብዱል ሃሚድ የስልጣን ጊዜ በጣት የሚቆጠሩ እንደሆነ አወቀ፡፡ ምንም አማራጭ ስላልነበረው እጁን ሰጠ፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው እ.ኤ.አ. ጁላይ 23 ቀን 1908 በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ለሠላሳ ዓመታት ታግዶ የነበረው ሕገ-መንግሥት እንደ ገና ሥራ ላይ እንዲውል መግለጫ ሰጠ፡፡ የአብዱል-ሃሚድ የፖለቲካ እና የሃይ ማኖት እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ ተደረገ፡፡ አካ ውስጥም ፍርሃቶች እና ተቃውሞዎች ተፈጥረው የነበሩ ሲሆን፣ ባለሥልጣናቱም አብዱል-ባሃ ነፃነት ይሰጠው እንደሆነ ለመጠየቅ ወደ ቁስጥንጥንያ ቴሌግራም ላኩ፡፡ እንዲፈቱ ትም ትእዛዝ ተሰጣቸው፡፡ አብዱል-ባሃ ቃለ-ኑዛዜውንና ቃለ-ኪዳኑን የጻፈው በእነዚህ የአደጋ ዓመታት ውስጥ ነበር፡፡ ይህንን ሰነድ የልጅ ልጁ እና የእምነቱ ሞግዚት የሆነው ሾጊ ኤፌንዲ የአዲሱ የዓለም ሥርዓት ቻርተር ነው ብሎታል፡፡ ከቃለ-ኑዛዜውንና ከቃለ-ኪዳኑ የተወሰደው አንዱ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡- “እጅግ የተወደዳችሁ ወዳጆች ሆይ! እኔ አሁን በከባድ አደጋ ውስጥ ነኝ፣ የአንድ ሰዓት ሕይወት ተስፋ እንኳን የለኝም ስለዚህ የአምላክን እምነት ለመከላከል፣ የእርሱን ሕግ ለመጠበቅ፣ ቃሉን

ለመንከባከብና የትምህርቶቹን ደህንነት ለመጠበቅ ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ ተገድጃለሁ፡፡ በጥንታዊው ውበት! ይህ ግፍ የተፈጸመበት ለማንም ክፉ አልተመኘም፣ አይመኝምም፤ በማንም ላይ መጥፎ ስሜት የለውም፣ እንዲሁም ለዓለም ደህንነት ከሚጠቅም በቀር ሌላ ምንም ቃል አይናገርም፡፡ ሆኖም ከሁሉ የላቀው ግዴታዬ የግድ የአምላክ እምነትን እንድንከባከብና ደህንነቱን እንድጠብቅ ያነሣሣኛል፡፡”

## ምዕራፍ 8
## የአምላክን ቤተ-መቅደስ ማነጽ

የኦቶማን ንጉስ አብዱል-ሐሚድ ከመውደቁ አንድ ወር በፊት እ.ኤ.አ. ማርች 21 ቀን 1909 አብዱል-ባሃ የባብን አስከሬን በቀርሜሎስ ተራራ እምብርት ላይ በተሰራው የመካነ መቃብር ሕንፃታች ባለው የተገነባ ጉድጓድ ማዕከላዊ ስፋራ ውስጥ አሳረፈው፡፡ ለባሃኢዎችም እንዲህ ሲል ጻፈ፡-

እጅግ አስደሳች ዜና ይህ ነው፣ ቅዱሱ፣ ብሩህ የሆነው የባብ አካል… በጠላቶች የበላይነት ምክንያትና ተንኮል ሰሪዎችን ከመፍራት የተነሳ፣ ዕረፍትንም ሆነ መረጋጋ ትን ሳያገኝ፣ ለስልሳ ዓመታት ከቦታ ወደ ቦታ ከተዘዋወረ በኋላ፣ በአብሃ ውበት ምህረት፣ በናው-ሩዝ ቀን፣ በተከበረ ሣጥን ውስጥ፣ ቀርሜሎስ ተራራ ላይ ባለው በተቀደሰው የመካነ-መቃብር ሕንፃ ውስጥ በሥነ-ሥርዓታዊ ክንዋኔ ግበዓተ-መሬቱ ተከናውኗል፡፡ ባልተጠበቀ አጋጣሚ በዚያው በናውሩዝ ቀን ከቺካጎ አንድ ቴሌግራም ደርሶናል፣ በእያንዳንዱ የአሜሪካ ማዕከላት ያሉ አማኞች ተወካያቸውን መርጠው ወደ ቺካጎ ከተማ መላካቸውን አስታወቁ… ማሽሪኩል-አድህካር (ቤተ-መቅደስ) የሚሰራበትን ቦታ እና ግንባታውን ወሰኑ፡፡

ይህ በደስታና በድል አድራጊነት የተደመደመው የአብዱል-ባሃ ድርጊት የባሃኡላህን ትእዛዝ ለመፈፀም የመጀመሪያውን እርምጃ በወሰደበት ለሰማዕቱ-ነቢይ መካነ-መቃብር ሕንፃ ማሰሪያ መሬት ለማግኘት ሲጥር ለአሥርተ ዓመታት ጥልቅ ሃዘን ውስጥ ቆይቶ ነበር፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አብዱል-ባሃ ሲናገር “ሕንጻው የተሰራበት እያንዳንዱ ድንጋይ፣ ወደ እዚያም የሚውስደው መንገድ

እያንዳንዱ ድንጋይ ሳይቀር የተገነባውና መልክ የያዘው ማለቂያ በሌለው እንባ እና በከፍተኛ ወጪ ነበር፡፡”

ተቃውሞው በዋነኝነት በሚርዛ መሐመድ-አሊ እና ባልደረቦቹ የተቀየሰ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ አብዱል-ባሃን ወክሎ የባብ መካነ መቃብር ሕንፃ ከሚሰራበት ከመሬቱ ባለቤት ጋር ሲደራደር የነበረ በሐይፋ ነዋሪ የሆነ አንድ ጀርመናዊ ነጋዴ፣ የግዢ ስምምነቱን እንዴት ሊያከ ናውን እንደሚችል በግልፅ ለመጠየቅ ጉዳዩን ወደ አብ ዱል-ባሃ ለመመለስ ተገደደ፣ ምክንያቱም የአብዱልባሃ ወንድም እንቅፋት እየሆነ ስላስቸገረው ነበር፡፡ በመጨረሻም ባለቤቱ በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ በተስማማበት ጊዜ ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ ለመንግሥት አቤቱታ ለማቅረብ የበርካታ ሰዎችን ፊርማ በማሰባሰብ ለመሬቱ ባለቤትነት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ የይገባኛል ሐሰተኛነታቸው እስኪረጋገጥ ድረስ ሌላ ስድስት ወራት ፈጀ፡፡ በመጨረሻም መሬቱ ተገዝቶ አብዱል-ባሃ የመካነ-መቃብሩን ማሰሪያ የመሠረት ድንጋይ አኖረ፡፡

ከዚያም ግንባታው በታሰበው እቅድ መሠረት ተጀመረ፡፡ ወደሚገነባው ህንፃ የሚወስደው መንገድ በጣም ድንጋያማ ሲሆን መንገዱን ለማሻሻል ከባለቤቶቹ ጋር ድርድር ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ የተሻለ መግቢያ መንገድ ለማግኘትም ጥረት ተደርጓል፡፡ አዲስ ማጭበርበር ባይከሰት ኖሮ የሚፈለገውን መሬት ለማግኘት ቀላል ነበር፡፡ ቃል-ኪዳን አፍራሾቹ የመሬቱን ባለቤት በተገቢው ዋጋ እንዳይሸጥ፣ ከፍተኛ ዋጋ እስኪያገኝ ድረስ እንዲያዘገየው አማከሩት፡፡ የሐይፋ ምክትል ገዥ እንዲሁ አከራካሪ ሃሳብ አቀረበ፡፡ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የተገነባው ሕንፃ ከከተማው በጣም ሩቅና፣ ተስማሚ ያለሆነ ቦታ ላይ

ስለሆነ ግንባታው የሱልጣን ፈቃድ ሊኖረው ይገባል በማለት ተከራከረ። የመሬት ምዝገባ ኃላፊ በበኩሉ በተመከረው መሠረት የፖለቲካ ሀሳቦችን ጣልቃ በማስገባት ግንባታው መቆም አለበት አለ።

ስለዚህ ጉዳዩ ለአካ አገረ-ገዥ ቀረበ። ጉዳዩን መርምረው ሪፖርት እንዲያደርጉ የከተማዋን መሐንዲስና ሌላ የሃይፋ ባለሥልጣን ሾመ። በሪፖርታቸውም ምንም የፖለ ቲካ ወይም የስትራቴጂያዊ ግምት ሊኖር እንደማይችል፣ ግንባታው ስድስት ክፍሎችን ብቻ ያካተተና በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተነጥሎ የሚገኝ እንደሆነና፣ በተጨማሪም በተራራው ትከሻ ላይ አንድ ሌላ ትልቅ ገዳም ያለ ሲሆን ጀርመኖችም በአካባቢው ሕንፃዎች እንዳሏቸው አረጋግጠው ጻፉ። አገረ ገዢው ግን ሪፖርቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ በሙሉ ወደ ሱልጣን እንዲቀርብ አጥብቆ ጠየቀ። አብዱል-ባሃ በዚህን ጊዜ የሱልጣኑ ጥርጣሬዎች ጥልቅ እንደሚሆን ያውቅ ነበር። ስለሆነም ምክትል አገረ-ገዥውን በአካል ለማግኘት ሄደ። አገረ-ገዢው ፕሮጀክቱን ለመቃወም ያነሳሳውን ምክንያቶች አጥብቆ ሲጠየቅ ሥራው እንዲቀጥል ለመፍቀድ ኃላፊነቱን ለመሸከም እንደፈራ ተናገረ። ከዚያም አብዱል-ባሃ ከቢሮው እስከ ቤቱ አብሮት ሄደ። የቤቱ ደጃፍ ላይ ሲደርስ አገረ-ገዢው እራሱን ስቶ በመውደቅ ሞተ። የእርሱ ሞት በአሳዛኝ ምዕራፍ እንዲዘጋ ሆነ።

የሕንፃ ሥራው ቀጠለ፣ ሆኖም ግን ወደ ሕንፃው የመ ግቢያ መንገድ ጥያቄ ሳይፈታ ቆየ። የመሬቱ ባለቤት ለመ ሸጥ ከተስማማ በኋላ በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሃሳቡን ሁለት ጊዜ ቀይሮ ነበር። ሁልጊዜም ሴረኞቹ ጫና እንዲፈ

ጠር ያደረጉ ነበር፣ ሳይሸጥ እንዲቆይ ያግባቡታል፣ ከመጠን በላይ የሆነ ትርፍ ሊያገኝ እንደሚችል ያጓጉታል። በሁለተኛው ጊዜ ላይ ቃሉን አፍርሶ የነበረው የሚሸጠው መሬት ላይ ያሉትን ዛፎች ባለቤትነት የእርሱ እንዲሆኑ በመጠየቅ ነበር፣ አብዱል-ባሃም ፍቃደኝነቱን ገልጾ ነበር፤ በመቀጠልም ቀሪውን መሬቱን ለማስጠበቅ የሽቦ አጥር እንደሚፈልግ ገለፀ። አብዱል-ባሃም ግንብ አጥር ሊሰራለት ሃሳብ አቀረበ። ከዚያም ደግሞ ቀሪው መሬቱ ደህንነቱ አስተማማኝና የተጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጥለት ዋስትና ሊኖረው እንደሚገባ ገለጸ። ሳዲቅ ፓሻ የተባለ በጣም ተሰሚነት ያለውን ሰው ባለአደራው እንዲሆን ወከለ። ሁሉም ሳዲቅ ፓሻ ቤት እንዲገናኙ ቀጠሮ ተደረገ፣ የመሬቱ ባለቤት ግን በጭራሽ አልተገኘም፣ ወቅቱ ዝናብ የነበረ ቢሆንም ሳዲቅ ፓሻ የመሬቱን ባለቤት ፈልጎ ለማምጣት ቤቱ ድረስ ሄደ፣ ሊያገኘው ግን አልቻለም፣ በዝናብም ረጥቦ ተናዶ ተመለሰ ።

በዚያን ቀን ምሽት አብዱል-ባሃ መብላትም ሆነ መተኛት አልቻለም። በጭንቀት ውስጥ ሆኖ የባብን ጸሎት ተረጋግቶ እንቅልፉ እስኪመጣ እስከ ንጋት ድረስ ሲደግም አደረ። ከእንቅልፉ ሲነቃ የጀርመን ቆንስላ አስተርጓሚና የቆንስሉ የወንድም ልጅ እርሱን ለማየት ለረጅም ጊዜ ሲጠብቁት እንደነበር ተነገረው። መሬቱን እንዲገዛ ለማግባባት እንደመጡ ነገሩት።

ከዚያም እ.ኤ.አ1901 ከቁስጥንጥንያ አዲስ ትዕዛዝ መጣ፣ አብዱል-ባሃ እንደገና በአካ ከተማ ቅጥር ውስጥ ታሰረ። የባብን የመካነ መቃብር ሕንፃ ግንባታ በግል መቆጣጠር አልቻለም፣ ሥራው ግን በእነዚህ አደገኛ ዓመታት ውስጥ ያለማቋረጥ ወደ ፊት ገሰገሰ። ከዛም የአብዱል-ሃሚድ

አገዛዝ ሲወድቅ መካነ መቃብሩ የሰማዕት-ነብዩን አፅም ለመቀበል ዝግጁ ሆኖ ተጠናቀቀ፡፡

እ.ኤ.አ ማርች 21 1909 የናው-ሩዝ ቀን ጠዋት ላይ አብዱል-ባሃ የራንጉን ባሃኢዎች ስጦታ በሆነው የእብነበረድ ሳጥን ውስጥ የባብን አጽም በማስገባት ወደ ቀርሜሎስ ተራራ በመውሰድ በተዘጋጀለት ቦታ እንዲያርፍ አደረገ፡፡ ስለዚህ ክንዋኔ ዘካሪያስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሲናገር "እንዲህም በለው፦ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ ስሙ ቍጥቋጦ የሚባል ሰው በስፍራው ይበቅላል የእግዚአብሔርንም መቅደስ ይሠራል፡፡ …" ትንቢቱ በምሥጢራዊ እና በማያሻማ ሁኔታ ተፈጽሟል፡፡ 'ቅርንጫፉ' (ቍጥቋጦ) 'የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ' ገንብቷል፣ 'በተራራው ላይ' - በእግዚአብ ሔር ተራራ ላይ 'ማደሪያውን' ከፍ አደረገ፡፡

በዚያው ምሽት በመካነ-መቃብሩ ዙሪያ ከአብዱል-ባሃ ጋር የምስራቅና የምዕራብ ዓለም ባሃኢዎች ነበሩ፡፡ እጅግ በጣም ጨለማ በሆነባቸው የእምነቱ ጊዜያት ጀግኖች የነበሩ ባሃኢዎችም ሲሆኑ ከእነርሱ መካከል የባብ አጎት የሆኑት የመጀመሪያውን የባሃኢ ቤተ-መቅደስ ያሰሩት ሀጂ ሚርዛ ሙሃመድ-ታኪ እና የቃል ኪዳኑ ዋና መከታ የነበሩት ካርቱም ለብዙ ዓመት የታሰሩት ሃጂ ሚርዛ ሃይደር አሊ ይገኙበታል፡፡

የሺራዝ ሰማዕት-ነብይ ምድራዊ ፍፃሜ በመጨረሻ የእግዚአብሔር ቅዱስ ተራራ እቅፍ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ የዘለዓለም ዕረፍቱ እየተጠናቀቀ ባለበት ሂደት፣ አብዱል-ባሃ ጥምጣሙን ከእራሱ ላይ አውጥቶ፣ ጫማውን አውልቆ፣ ካባውን ጥሎ፣ ወደ ጉድጓድ እየገባ

ያለው የእብነበረድ ሳጥን ላይ አጎንበሶ ተደፋ፣ ረጅሙ ብርማ ፀጉሩ ፊቱ ላይ ተደፍቶ እየተውለበለበ፣ ፊቱ እያንጸባረቀ፣ ጮክ ብሎ ያለቅስ ጀመር፣ በከፍተኛ ሁኔታ ያለቅስ ስለነበር በዙሪያው የነበሩት ሁሉ ማልቀስ ጀመሩ፡፡ የእድሜ ልክ ሃዘኑ በእምባ ጠመቀው፡፡ በዚያን ቀን ሌሊት ሳይተኛ አደረ፡፡

አብዱል-ባሃ እ.ኤ.አ. በ1909 ያገኘው ድል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚሄድ ግርማው ያበራል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 9

## በአውሮፓና በአሜሪካ የአብዱል-ባሃ ጉዞ

"God passes by" ከሚለው በሾጊ ኤፌንዲ ከተጻፈው መጽሐፍ
በከፊል የተወሰደ።

"አብዱል-ባሃ በእነዚህ ጊዜያት ጤንነቱ ታውኮ ነበር። ሙሉ ለሙሉ ሊሆን ምንም ያህል ላልቀረው ጊዜ በግዞትና በእስራት አሳዛኝ ሕይወት ውስጥ በበሽታ ዎች ተዘፍቆ ነበር። የሰባ ዓመት ዕድሜ መያዣ ውም ላይ ነበር። ያም ሆኖ የባብን ቅሪተ-አካል ደህንነቱ በሚጠበቅ ቦታ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ካሳረፈ በኋላና ከዚያ ጋር ከተያያዙ ብርቱ ጭንቀቶች ነፃ እንደሆነ ወዲያውኑ በምዕተ-ዓመታት ታሪክ ውስጥ ምንም ተመሳሳይ ለማይገኝለት፣ ለጀግንነት ታሪክ በሕይወቱ መገባደጃ ላይ የቀረውን ጥቂት ጉልበት ለመስጠት በላቀ ወኔ፣ በቁርጠኝነት ተነሳ።

በመጀመሪያ ወደ ግብፅ፣ ከዚያም ወደ አውሮፓና አሜሪካ ያደረጋቸውን የሦስት ዓመታት ጉዞ በትክክል ከገመገምነው በእምነቱ የመቶ ዓመት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ወሳኝ ደረጃን ያመ ለክታል። እምነቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ከስድሳ ስድስት ዓመታት በኋላ ባብንና ባሃኡላህን በእጅግ አስከፊ ሁኔታ ነፃነታቸውን ያሳጣቸውን ሰንሰለቶች እሱ ሰባበረው ።

አንድ በወጣትነቱ እስር ቤት ገብቶ ሽማግሌ ሆኖ የወጣ፣ በሕይወቱ ውስጥ ሕዝብ ፊት ንግግር ለማድረግ ሞክሮ የማያውቅ፣ ትምህርት ቤትም ያልገባ፣ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ማሕበራዊ ኑሮ፣ ልማዶችና ቋንቋ ጋር የማይተዋወቅ፣ በአንዳንድ የአውሮፓ ታላላቅ ከተሞችና በዋና ዋና አሜሪካ ግዛቶች ውስጥ በአባቱ እምነት ጎልተው የተቀመጡትን እውነታዎች ...በመድረኮቻቸው ላይ ለማወጅ ተነሳ።

...እ.ኤ.አ በ1910 ሴብቴምበር ወር ላይ በመርከብ ወደ ግብፅ ተጓዘ። ሰይድ በሚባል የወደብ ከተማ ለአንድ ወር ያህል ሰንብቶ ወደ አውሮፓ ለመሄድ መርከብ ተሳፈረ፣ ሆኖም ግን ጤንነቱ ስለታወከ ጉዞውን አቋርጦ ግብፅ አሌክዛንደሪያ በሚባል ከተማ በመቆየት ጉዞውን የግድ ማስተላለፍ እንዳለበት ታወቀ። አሌክዛንደሪያ ውስጥ ራማሌህ በሚባል ቦታ መኖሪያውን በማድረግ ዛይቱንና ካይሮን በመጎብኘት በሚቀጥለው ዓመት ኦገስት 11 ቀን ከአራት አብረውት ከነበሩ ተጓዦች ጋር በመሆን መርከብ ተሳፍሮ ወደ ማርሴል ፈረንሳይ ተጓዘ ከዛም የፈረንሳይ ምስራቃዊ የባሕር ዳርቻ በሆነችው ከተማ(Thonon-les-Bains) የአጭር ጊዜ ቆይታ በማድረግ ወደ ለንደን ጉዞውን ቀጠለ። ከአንድ ወር ገደማ ጉብኝት በኋላ ወደ ፓሪስ ተመለሰ። እዚያም ዘጠኝ ሳምንታት ያህል ቆየ። እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 1911 ወደ ግብፅ ተመለሰና ክረምቱን ለማሳለፍ እንደገና በራማሌህ ቆየ። ከዛም ወደ ምዕራቡ ዓለም ሁለተኛ ጉዞውን ጀመረ። እ.ኤ.አ. ማርች 25 1912 ሴድሪክ የምትባል መርከብን ተሳፍሮ በኔፓልስ አድርጎ ኒውዮርክ ኤፕሪል 11 ቀን ደረሰ። ከጠረፍ እስከ ጠረፍ ባዳረሰው የስምንት ወር ቆይታው

ዋሽንግተን፣ ቺካጎን፣ ክሊቭላንድም፣ ፒትስበርግን፣ ሞንትክላየርን፣ ቦስተንን፣ ዎርስተርን፣ ብሩክሊን፣ ፋንዉድን፣ ሚልፎርድን፣ ፊላዴልፊያን፣ ዌስትኤንግ ለዉድን፣ ጀርሲ ሲቲን፣ ካምብሪጅን፣ ሜድፎርድን፣ ሞሪስ ታውንን፣ ዱብሊን፣ ግሪን ኤከርን፣ ሞንትሪያልን፣ ማልደንን፣ ቡፋሎን፣ ኬኖሻንን፣ ሚኒያፖሊስን፣ ሴንት ፖልን፣ ኦማሃን፣ ሊንከንን፣ ዴንቨርን፣ ግሌንዉድስ ፕሪንግስን፣ ሶልት ሌክ ሲቲን፣ ሳንፍራንሲስኮንን፣ ኦክላንድን፣ ፓሎአልቶን፣ በርክሌይን፣ ፓሳዴናን፣ ሎስአንጀለስን፣ ሳክራሜንቶን፣ ሲንሲናቲ እና ባልቲሞርን ጎበኘ፡፡ ከዛም ከኒውዮርክ ዲሴምበር 5 ቀን በመርከብ ወደ ሊቨርፑል (እንግሊዝ) ተጓዘ፤ ከዛም ባቡር ተሳፍሮ ለንደን ደረሰ፡፡ በመቀጠልም ኦክስፎርድን፣ ኤዲንብራንና ብሪስቶልን ጎብኝቶ እንደገና ወደ ለንደን ተመለሰ፡፡ ከዛም እ.ኤ.አ.ጃንዋሪ 21/1913 ወደ ፓሪስ ተጓዘ፡፡ በመቀጠልም ማርች 30 ወደ ስቱትጋርት ጀርመን ተጓዘ፣ ከዚያም ኤፕሪል 9 ወደ ቡዳፔስት ተጓዘ፡፡ ከዘጠኝ ቀናት በኋላ ቪየናን ጎበኘ ፣ ኤፕሪል 25 ወደ ስቱትጋርት ተመለሰ፣ ከዛም ተነስቶ ፓሪስ ሜይ 1 ገባ፣ እዛም እስከ ጁን 12 ቆየ፣ በሚቀጥ ለው ቀን በመርከብ ከማርሴልስ ተነስቶ በሂማላያ አድርጎ ከአራት ቀናት በኋላ ወደ ፖርት ሳይድ ግብፅ ተመለሰ፡፡ ኢስማኢሊዩይህ እና አቡኪር የሚባሉ ቦታዎችን ለአጭር ጊዜ ጎበኘ፣ ረዘም ላለ ጊዜ በራማሌህ ከቆየ በኋላ ዲሴምበር 5 ቀን 1913 ታሪካዊ ጉዞዎውን በማጠናቀቅ ወደ ሐይፋ ተመለሰ ፡፡

በእነዚህ የዘመን ምዕራፍ ከፋች ጉዞዎች ወቅት አንዳንድ ጊዜ ከሺህ ሰዎች በሚበልጡ ታዳሚዎች ፊት ቆሞ አብዱል-ባሃ ለመጀመሪያ ጊዜ

በሚያስገርም ሁኔታና በሚያሳምን ኃይል፣ እነዚያ የአባቱ እምነት መሠረታዊ መርሆዎች የሆኑትን፣ አምላክ ለሰው ልጅ ለወቅቱ የሰጣቸውን በኪታቢ-አቅዳስ ውስጥ የተገለጹትን ህጎች እና አስተምህሮቶች እንዲህ በማለት አብራራ፡- በአጉል እምነት ወይም በባህል ሳይታገዱ በነፃነት እውነትን መመርመር፤ የእምነቱ መሠረታዊ መርሆ እና አስተምህሮ የሆ ነው የመላው የሰው ዘር አንድነትና የሁሉም ሃይ ማኖቶች መሠረታዊ አንድነት፤ ሁሉንም ዓይነት የሃይማኖት፣ የዘር፣ የመደብ ወይም የአገር ጭፍን ጥላቻን ማውገዝ፤ በሃይማኖት እና በሳይንስ መካ ከል ሊኖር ስለሚገባው ስምምነት፤ እንደ ወፍ የሚ መሰለው የሰው ዘር የሚበርበት ሁለት ክንፎች የወንዶች እና የሴቶች እኩልነት፣ ትምህርት የግዴታ መሆኑን ማሳወቅ፣ ዓለምአቀፋዊ የሚሆን ረዳት ቋንቋን መምረጥ፤ የሀብት እና የድህነት ከልክ ያለፉ ጽንፎችን ማስወገድ፣ በአገራት መካከል አለመግባባ ቶች እንዲዳኙ የዓለም ፍርድ ቤት ማቋቋም፤ በአገልግሎት መንፈስ የተከናወነን ሥራ ወደ ስግደት ደረጃ ከፍ ማድረግ፣ ፍትህ በሰው ልጅ ህብረተሰብ ውስጥ እንደገዥ መርሆ መከበሩንና ሃይማኖትም የሁሉም ህዝቦች እና ብሄሮች ጠባቂ ምሽግ መሆኑን፣ እንዲሁም የሁሉም የሰው ልጆች የበላይ ግብ ዘላቂ እና ሁለንተናዊ ሰላም መመስረት መሆኑን ተናገረ፤ ....እነዚህ በጉዞው ያወጃቸው የዚያ የመለኮታዊ ተቋም እቅድ አስፈላጊ ገጽታዎች ናቸው:: ...አንድ መምጣቱ የማይቀር ከቁጥጥር ውጪ የሚሆን እሳት የዓለም መሪዎች ሊመልሱት ካልቻሉ መላውን የአውሮፓ ክፍለ-አህጉር እንደሚያጋይ ጽኑ የሆነ ተደጋጋሚ

ማስጠንቀቂያዎችንም ሰጥቶ ነበር በተጨማሪም በእነዚህ ጉዞዎቹ ጊዜ በዚያ ክፍለ-አህጉር ውስጥ የሚደረጉ ሥርነቀል ለውጦች እንደሚኖሩ ተነበየ፣ … የፖለቲካ ሥልጣንን ማዕከላዊነት የሚጻረር ንቅናቄ እንደሚመጣ ጠቆመ፣ …በአውሮፓ ክፍለ-አህጉር ውስጥ ወደፊት የአይሁዶች መሰቃየት እንደሚመጣ አሳወቀ፣ እንዲሁም "የሰው ዘር የአንድነት አርማ እንደሚውለበለብ፣ ዓለም አቀፋዊ የሰላም ድንኳን አንደሚተከል ዓለም ሌላ ዓለም እንደምትሆን" ያልጥርጥር ተናገረ፡፡

አብዱል-ባሃ በእነዚህ የጉዞዎቹ ጊዜያት እነዚያ የእሱን የዕለት ተዕለት ተግባር በቅርብ ሆነው ለመመልከት ለቻሉት የመደነቅና የእርካታን ስሜት ቀስቅሶባቸው የነበረው ብርታቱ፣ ወኔው፣ አንድ ዓላማ ብቻ ማራመዱና እራሱን መስጠቱ ነበር፡፡ በተለምዶ የጎብኚዎች ትኩረትን የሚስቡትን ነገሮች ቸል በማለት፣ ለእራሱ ጤንነትና ምቾት ምንም ጥንቃቄ ሳያደርግ፣ በየቀኑ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ መላ ጉልበቱን እስከ ጠብታው ድረስ በየቀኑ ሰጠ፤ ለጉዞ ወጪ የሚሆን ማንኛውንም ስጦታዎች ሳይቀበል፣ ለታመመው ለአዘነው፣ ለተጨቆነው አዛኝነቱን ሳያቋርጥ፣ መብት ለተነፈጉ ዘሮችና መደቦች ተቆርቋሪነቱን ሳያላላ፣ ልግስናውን ለድሆች አዘነበ፤ ነቅተው በሚጠብቁ በአክራሪ የኦርቶዶክስ አራማጆችና ቅርንጫፎች በእርሱ ላይ የጀመሩትን ጥቃቶችን ንቆ፣ በየመድረኩና በየመናገሪ ያው ማማ ላይ ለአይሁዶች የእየሱስን ነብያዊ ተልዕኮ፣ በአብያተ-ክርስቲያኖችና በሙክራቦች፣ የእስልምናን መለኮታዊ ምንጭነትን፣ ለቁስ አካላዊያን የሃይማኖትን አስፈጊነት ሲያስረዳ

በግልጽነቱ የሚያስገርም ነበር፡፡ የባሃኡላህን ክብር ሲያወድስ የማያወላዳ ነበር፣ በእንግሊዝ እና በአሜሪካን አገር ውስጥ የታወቁ ሰዎችንና ባለሃብቶችን ድጋፍ ለማግኘት ደጅ ሳይጠና፣ ሆኖም ግን መንገድ ላይ በእግሩ ሲሄድ፣ በመናፈሻ ወይንም በሕዝብ አደባባዮች ውስጥ እንዲሁም በእንግዳ መቀበያዎች ወይም በግብዣዎች ላይ፣ በመጠነኛ ቤቶችም ሆነ ወይም በታላላቅ ቤቶች ውስጥ፣ በተከታዮቹ ስብሰባዎች ላይም ሆነ የተማሩ ሰዎች ስብሰባ ውስጥ፣ በሚጓጓዝበት ጊዜ በአጋጣሚም ሆነ ቀድሞ ለሚያውቃቸው ሰዎች፣ ለምዕመናንም ሆነ ለማያምኑት፣ ለሃብታምም ለድሃም፣ ለከፍተኛውም ሆነ ለዝቅተኛው የሚያሳየው የርህራሄና የፍቅራዊ ደግነቱ በተፈጥሮአዊነቱና በልባዊነቱ አንድ ዓይነት ሲሆን በጋለ ስሜቱ ወደር የማይገኝለት የአንድ ባሃኢ ስነ-ምግባር መገለጫም ነበር፡፡ ይህ ለእያንዳንዱ ባሃኢ አርዓያ የሆነው በዓለማዊነት ውስጥ ለተዘፈቀውና በአሁኑ ጊዜ በጦርነት ሥር ለሚገኙ ሁሉ፣ በአባቱ ግልጸት ውስጥ የሰፈሩትን ከእግዚአብሔር የተሰጡ ፈዋሽ እውነቶች እዚያ በነበረበት ጊዜ ለሦስት ዓመታት ማሰማቱን ቀጥሎ ነበር፡፡

በግብፅ ውስጥ ባደረጋቸው ብዙ ጉብኝቶች ወቅት የግብፅ ገዢ ከነበረው ከዳግማዊ ካዲቭ ሃልሚ ጋር ተገናኝቶ ተነጋግሯል፣ ከእንግሊዛዊው ክቡር ኪቼነር፣ ከሙፍቲ ሼክ ሙሐመድ ባሂት እንዲሁም ከካዲብ ኢማም ሙሐመድ ራሺድ ጋር ተዋወቀ፣ ከብዙ ዑላማዎች፣ ከፋርስ ታዋቂ ሰዎች፣ ለቱርክ የፓርላማ አባሎች፣ በካይሮና በአሌክዛንደሪያ ውስጥ ከሚገኙ ከዋና ዋና የጋዜጣ አዘጋጆችና ከሌሎች የሃይማኖታዊና የዓለማዊ ተቋሞች ተወካዮች ጋር

ተዋውቆ ነበር።

በእንግሊዝ አገር በነበረበት ጊዜ ይጠቀምበት የነበረው ቤት ለሁሉም ዓይነትና ለተለያዩ ሰዎች ተስማሚ ስፍራ ሆኖ ነበር። ታላቋን ከተማቸውን በምዕራቡ ዓለም ለሚያደርገው አድካሚ እንቅስቃሴ የመጀመሪያው አድርጎ ስለመረጠ የአካውን እስረኛ ለመጎብኘት ሁሉም ይጎርፉ ነበር። ለንደን በቆየባቸው ጊዜያት ስለታማኝ እንግዶቹ እማኝነት ሲሰጥ፣ "አቤት እነዚህ መንፈሳዊ ጎብኚዎች፣ እነዚህ እንግዶች፣ እነዚህ ጎብኚዎች! እነዚያን ቀናቶች ስናስታውስ [በትዝታ] የእግሮቻቸው ዳና ድምጽ ጆሮዎቻችንን ይሞላዋል። እነሱ ከሁሉም የዓለም ሀገራት የመጡ ነበሩ። በየቀኑ፣ የማያቋርጥ ጅረት፣ የማያቋርጥ ሰልፍ! ሚኒስትሮች እና ሚስዮናውያን፣ የምስራቃዊያን ምሁራን እና ስለሕቡዕ መንፈሳዊ ሚስጥሮች የሚያጠኑ ተመራማሪዎች፣ ተግባራዊ ሰዎች እና መንፈሳዊ ምስጢር አዋቂ ግለሰቦች፣ አንግሊካኖች፣ ካቶሊኮች እና በተደራጀ የሃይማኖት ተቋም የማያምኑ ግለሰቦች፣ ቴዎሶፊስቶች (በፀሎት በመመሰጥ በቀጥታ ከአምላክ መገናኘት) ሂንዱዎች፣ ክርስቲያን ሳይንቲስቶችና ሐኪሞች፣ ሙስሊሞች፣ ቡድሂስቶች እና ዞሮስታራውያን ነበሩ። ፖለቲከኞችና ሌሎች ለሰብአዊ ጥቅም የሚሰሩ ግለሰቦች፣ የሴቶች መብት ታጋዮች፣ ጋዜጠኞች፣ ፀሃፊዎች፣ ገጣሚዎች እና ፈዋሾች፣ ታላላቅ ሴቶች፣ አርቲስቶች እና የእጅ ባለሞያዎች፣ ድሃዎች፣ ሥራ የሌላቸው ሰዎች እና ባለፀጋ ነጋዴዎች፣ የትያትር እና የሙዚቃ ባለሙያዎች

እና ሌሎችም ሁሉ ይመጡ ነበር ። አብዱል-ባሃ በምዕራባዊያን ታዳሚዎች ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የቀረበው በለንደን እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 10 ቀን 1911 ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሲሆን፣ ከቤተ-ክርስቲያኑ የመናገሪያው ማማ ላይ ሆኖ ለተጥለቀለቀው ታዳሚ ንግግር አደረገ። ፓስተር አር. ጄ. ካምቤል ካስተዋወቀ በኋላ፣ አብዱል-ባሃ በቀላል እና በሚያነቃቃ ቋንቋ እና በደማቅ ድምፅ የእግዚአብሔርን አንድነት በማወጅ የሃይማኖትን መሠረታዊ አንድነት አረጋገጠ፣ የሰው ልጆች፣ የሁሉም ዘሮች፣ ሃይማኖቶች እና ክፍሎች አንድነት ጊዜ መምጣቱን አበሰረ። በሌላው ደግሞ ሴፕቴምበር 17 ቀን ክቡር ሊቀ ዲያቆን ዊልበር ፎርስ በጠየቁት መሠረት ያደረገው ሲሆን፣ በዌስትሚኒስተር ለቅዱስ ዮሐንስ [ቤተ-ክርስቲያን] መለኮታዊ ጉባኤ ታዳሚዎችም ንግግር አደረገ፣ የመረጠውም ርዕስ ባሃኡላህ በኪታቢ ኢቃን ውስጥ ያብራራውንና ያረጋገጠውን የመለኮታዊው አምላክ እጹብ ድንቅነትን ነበር ።

በለንደን ከንቲባ ግብዣ ተደርጎለት በእንግዳ ማረፊያ ቤታቸው ውስጥ አብሮ ተመግቧል፤ በፕሬዚዳንታቸው ፈጣን ጥያቄ መሠረት ለቲዎሶፊካዊ ማኅበር በዋናው መሥሪያ ቤታቸው ተገኝቶ ንግግር አድርጓል። በእንግሊዝ ሙስሊም ማህበረሰብ ግብዣ መሠረት በመስጊድ ውስጥ ስለዓለም አንድነት ንግግር አድርጓል፣ የመለኮት ተመራመሪና እና የመጽሐፍ ቅዱስ አብራሪ የሆነው ዶክተር ቲ. ኬ. ቼይን ቤት በማረፍ፣ በማንቼስተር ኮሌጅ ውስጥ “ጥልቅ ፍላጎት ላላቸው ብዙ ታዳሚዎች”፣ ከፍተኛ

ምሁራዊ ይዘት ያለው ንግግር አድርጓል…። አንድ ፓስተር ባቀረበው ጥያቄ መሠረትም እንዲሁ በለንደን ምስራቅ መጨረሻ በሚገኘው የማኅበረ ቅዱሳን ቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ንግግር አድርጓል፤ በክቡር ቶማስ ባርክሌይ ሰብሳቢነት በካክሰቶን አዳራሽ እና በዌስትሚኒስቴር አዳራሽ በተካሄደው ስብሰባ ላይ እንዲሁ ንግግር አድርጎ ነበር። በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስ ሕይወት የሚያሳይ ቲያትርም ላይ ታድሞ ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት እና መከራዎች ትዕይንት በእንባ አጠበው ።

“ፓስሞር ኤድዋርድስ” የሚባል የእርዳታ ድርጅት አዳራሽ ውስጥ ወደ አራት መቶ ስልሳ ለሚጠጉ ተወካዮች ንግግር አደረገ፣ የድርጅቱ መሪ በፕሮፌሰር ሚካኤል ሳድለር ብዙ ሴቶችን ጋብዞ ነበር… ለሁለተኛ ጊዜም ተገናኝቶ ነበር በዚያ ወቅት እሱን ለማየት የተሰበሰቡ ሁሉም ዓይነት ሰዎች ነበሩ ከነዚህ መካከል “የብዙ ቤተ እምነት ቀሳውስቶች ፣ የወንዶች የመንግሥት ትምህርት ቤት ዋና አስተ ዳዳሪ፣ የፓርላማ አባል፣ ዶክተር፣ ታዋቂ የፖለቲካ ፀሐፊ፣ የዩኒቨርሲቲውም ቻንስለር፣ በርካታ ጋዜጠኞች፣ አንዳንድ ታዋቂ ገጣሚያንና ከለንደን የመጡት ዳኛ ነበሩ። ” …

በእንግሊዝ እና በስኮትላንድ ባሳለፋቸው የማይረሱ ቀናት ውስጥ እርሱን ከጠሩትና አብረውት ከቆዩቱ ታላላቅ ሰዎች መካከል የተከበሩ ሊቀ ዲያቆን ዊልበርፎርስ፣ ታዋቂው ሰባኪ የተከበሩ አር.ጄ ካምፕቤል፣ የተከበሩ ቄስ ሬንዳ ዊሊያምስ፣

የተከበሩ ቄስ ሮላንድ ኮርቤት፣ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አስተዳዳሪ የነበሩት ሎርድ ላሚንግተን፣ ነጋዴው በጎ አድራጊ እና የሊበራል ፓርቲ ፖለቲከኛው ሰር ሪቻርድ እና ሌዲ ስታፕሊ፣ የታሪክና የትምህርት ምሁር የዩኒቨርሲቲ አስተዳዳሪ ሰር ሚካኤል ሳድለር፣ የዚሉ-ሱልጣን (የፋርስ ልዑል) ልጅ ጃል ሉድ-ዳውሊህ፣ በተደጋጋሚ የጎበኘውና ሰፊ የእራት ግብዣ ያደረገው የጃህዋር (ምዕራባዊ ሕንድ) የመጨረሻው መሃራጃ (ገዢ) ሰር አሜር አሊ፣ የራጅጉታና (ሕንድ) መሃራጃ፣ የሳራዋክ (ማሌዢያ ግዛት) ራኒ (ንግስት)፣ የስዊድን ልዕልት ኬረጂያ፣ ባሮነስ ባርነኮው (የአውሮፓ ልዑላዊያን ቤተሰብ)፣ የእንግሊዝ መድሃኒት ፖሊሲ ማሻሻያ ተከራካሪና የምርምር አስተባባሪ የሆነችው ሌዲ ዌምሲስ እና እህቷ ሌዲ ግሌን ኮርነር፣ የታዋቂው ፖለቲከኛ ልጅ ሌዲ አግኔው፣ ደራሲና የሴቶች መብት ታጋይ ኮንስታንስ ማድ፣ የማሕበረሰብ ሕይወት ተመራማሪውና ባሃኡላህን የጎበኘው ፕሮፌሰር ኢ.ጂ. ብራውን፣ ባዮሎጂስት፣ ሶሽዮሎጂስት፣ ጂኦግራፈር፣ በጎ አድራጎት እና የከተማ ፕላን አስፈላጊነትን ያስጀመረው ፕሮፌሰር ፓትሪክ ጌደስ፣ የክርስቲያን የጋራ ሃብት ልማት ጋዜጣ አርታኢና ጋዜጠኛ ሚስተር አልበርት ዳውሰን፣ ፖለቲከኛና የፓርላማ አባል ዴቪድ ግራሃም ዋል፣ ሶሻሊስት፣ ቲዎሶፊስት፣ የሴቶች መብት ተሟጋች፣ ጸሐፊ፣ ተናጋሪ እና የትምህርት ምሁር አኒ ቤሳን፣ የፖለቲካ አክቲቪስት፣ የእንግሊዝ የሴቶችን እንቅስቃሴ በማደራጀት እና የመምረጥ መብትን

እንዲያገኙ በመታገል የሚታወቁት ፓንክረስት እንዲሁም ጋዜጠኛና አርታኢው እስቲድ ይገኙበታል። እርሱን በግል የማግኘት ዕድል ያገኙት እንግዶች የፈጠረባቸውን ስሜቶች ያዩ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- " እነዛ እርሱን ለማግኘት የቻሉ ለየት ያለ ተሞክሮ አግኝተው የነበረ ሲሆን፣ አብዱል-ባሃ ፊት መቅረብ ምን ያህል ለየት ያለ እንደሆነ የሚያውቁት የቀረቡት ናቸው፣ እርሱን አግኝተው ሲወጡ ፊታቸው ላይ የሚነበበው የመለኮታዊነት ጭላንጭል ነው፣ ገጽታቸው ግርምት፣ መደነቅ፣ የረጋ ደስታ ይታይበታል። ምድራዊ ነገሮች ተመልሶ ከእነሱ እንዳይነጥቃቸው ከፍተኛ ደስታቸውን አጥብቀው ለመያዝ፣ አንዳንድ ጊዜ ወደ ውጭው ዓለም ለመምጣት በውስጣቸው አለመፈለግ እንዳለ አውቀን ነበር።

ወደ ፓሪስ ባደረጋቸው ጉብኝቶቹ፣ ለተወሰነ ጊዜ "በአቬኑ ዴ ካሞንስ" ውስጥ አፓርትመንት ያዘ፣ ይህ ቤት በለንደን ከወዳጆቹ እና ከተከታዮቹ ከተደረገለት አቀባበል ያላነሰ ሞቅ ያለ መስተንግዶ የተደረገበት በመሆን ይታወቃል። በፓሪስ ጉብኝቱ ወቅት ወደዚያ ከተማ አብራው የተጓዘችው እንግሊዛዊቷ ሌዲ ብሉምፊልድ እንደመሰከረችው "የፓሪስ ጉብኝቱ ልክ እንደለንደን ጉብኝቱ ሁሉ የዕለት ተዕለት ውሎው የመንፈሳዊ ክስተቶች ድባብ ነበሩት፣ በየቀኑ ጠዋት፣ በዙርያው ለተሰበሰቡት ለተማሩት እና ላልተማሩት፣ ጉጉ እና አክብሮት ላላቸው ሁሉ የባሃኡላህን አስተምህሮት መርሆዎች ያብራራላቸዋል። ከምሥራቅና ከምዕራብ የመጡ የሁሉም ዓይነት አገር ሰዎችና የተለያየ እምነት

ያላቸው ነበሩ… ተከታታይ ቃለ መጠይቆች ነበሩበት፣ የተለያየ የክርስትና እምነት ቅርንጫፍ ተወካዮች ይመጣሉ፣ አንዳንዶቹ የእውነትን አዳዲስ ገጽታዎች ለማግኘት በጣም የጓጉ ነበሩ… አንዳንዶች ደግሞ እንዳይሰሙና እንዳይረዱ ሲሉ ጆሯቸውን የደፈኑም ነበሩ፡፡

የፋርስ ልዑላኖች፣ መኳንንቶች እና የቀድሞ ሚኒስትሮች ነበሩ፣ በፓሪስ የቱርክ አምባሳደር፣ የቀደሞ የቤይሩት ገዢ፣ እርሱ ፊት የመቅረብ ዕድል ካገኙት አንዳንዶቹ ናቸው፡፡ የኤስፔራንቶ ቋንቋ ሰዎችና ቴዎሶፊስቶች፣ ለሥነ-መለኮት ተማሪዎች እና የመንፈሳዊነት ትብብር ለሚባሉ ብዙ ታዳሚዎች ንግግር አድርጓል፤ የድሆች መንደር ውስጥ በሚገኝ የበጎ አድራጎት አዳራሽ ውስጥ በፓስተሩ ግብዣ መሠረት ለተሰበሰቡት ሰዎች ንግግር አድርጓል…

አጭር ግን የማይረሳ ቆይታ ባደረገበት ስቱትጋርት ጀርመን ከተማ ውስጥ፣ የጤና እክል ቢያጋጥመውም ከታታሪዎቹና ከሚወዳቸው የጀርመን ህብረተሰብ ወዳጆቹ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ተጉዞ ነበር፣ በታማኝ ተከታዮቹ ስብሰባዎች ላይ ከመገኘቱ ባሻገር ለወጣት ቡድን አባላት የተትረፈረፈ በረከትን በመስጠት በኤስሊንገን ከተማ ተሰብስቧል፣ በተጨማሪም በአውሮፓ የኤስፓራንቲስቶች ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ክሪስታሌ ግብዣ የእስፔራንቲስቶች ታላቅ ስብሰባ ላይ በክለባቸው ተገኝቷል፡፡ የዓይን እማኝ የሆነው ሲጽፍ “ የጀርመን አማኞች

ትህትና፣ ፍቅር እና መሰጠት የአብዱል-ባሃን ልብ አስደሰተ፣ እናም የእርሱን በረከቶች፣ የተሟላ አክብሮትና የሚያበረታቱ ምክሮችን ፍጹም በሆነ ተገዥነት ተቀበሉ።... እርሱን ለማየት ከቅርብና ከእሩቅ መጥተውም ነበር። ባረፈበት ሆቴል የማያቋርጥ የጎብኝዎች ፍሰት ነበር። አብዱል-ባሃ በፍቅር እና ቸርነት ስለተቀበላቸው በደስታ እና በፍስሃ አበሩ።"

አብዱል-ባሃ ጥቂት ቀናት በቆየበት ኦስትሪያ ቬየና በዚያች ከተማ በቴዎሶፊስቶች ስብሰባ ላይ ንግግር አደረገ፣ በሃንጋሪ ቡዳፔስት ከተማ ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ቃለ መጠይቅ ሰጠ፣ ከታዋቂው የምሥራቃዊው ፕሮፌሰር አርሚኒየስ ቫም ቤሪ ጋር በበርካታ አጋጣሚዎች ተገናኘ፣ ለቲኦሶፊካዊ ማኅበር ንግግር አደረገ፣ የቱራን ፕሬዝዳንት  እና የቱርክ ማኅበራት ተወካዮች፣ የጦር መኮንኖች፣ በርካታ የፓርላማ አባላት ጎበኙት፣ በተጨማሪም በፕሮፌሰር ጁሊየስ የሚመራው የወጣት ቱርኮች ተወካይ ደማቅ አቀባበል አድርገውለታል። የዶ/ር ሩዝተም ቫምቤሪ የጽሑፍ ምስክርነት "በዚያ ወቅት፣ አብዱል-ባሃ በዱና ፓሎታ ሆቴል ውስጥ የምስራቅ ውስጠ-ምስጢራዊ ዕውቀት እና ጥበብ ለሚስቧቸው ሁሉ እውነተኛ ማዕከል ሆኗቸው ነበር። ከጎብኝዎቹ መካከል የሃንጋሪ የመሳፍንት ቤተሰብና ፖለቲከኛው አልበርት አፖኒያይ፣ የካቶሊክ ከፍተኛ የቤተ-ክህነት ሰው አሌክሳንደር ጂስዌይን፣ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር የሆነው ፕሮፌሰር ኢግአዝ ጎልድዚሄር፣ በዓለም ዙሪያ ታዋቂው

የምሥራቃውያን ባሕል፣ ቋንቋና ሃይማኖት ተመራመሪው ፕሮፌሰር ሮበርት ኤ ናድለር፣ ታዋቂው የቡዳፔስት ሰዓሊ እና የሃንጋሪ ቲዎሶፊካዊ ማኅበር መሪ ነበሩ፡፡

የአብዱል-ባሃ ገደብ የለሽ የሕይወት ኃይል እጅግ አስገራሚ መግለጫ በእነዚህ ጉዞዎች ውስጥ ታይቷል፡፡ በአሜሪካ እና በካናዳ በተከታዮቹ የተደራጀ ማህበረሰብ የተገኘው አስደናቂ እድገት፣ የአሜሪካ ህዝብ ለመልዕክቱ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው መሆኑ እንዲሁም የዚያ አህጉር ህዝብ የሚጠብቀውን ከፍተኛ እጣ ፈንታ መገንዘቡ፣ ለዚህ በጣም አስፈላጊ የጉዞው ምዕራፍ ያጠፋው ጊዜ እና ጉልበትን …ሙሉ በሙሉ አረጋግጧል፡፡ ከኤፕሪል እስከ ዲሴምበር ድረስ የዘለቀ ከአምስት ሺህ ማይሎች በላይ ጉዞ ያስፈለገው ጉብኝት፣ ከአትላንቲክ እስከ ፓስፊክ ዳርቻ ደርሶ የተመለሰበት ከሦስት ያላነሱ ጥራዞችን ለመሙላት የሚያስችሉ ንግግሮችን ያደረገበት ሲሆን፣ የጉዞው የላቀ ደረጃን የተቀዳጀበትና የልፋቱ ውጤት መጠነ-ሰፊ ውጤት እንደሚያመጣ ሙሉ በሙሉ ያረጋገጠበት ነው፡፡ በኒውዮርክ ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘታቸውን ምክንያት በማድረግ ለተሰበሰቡ ተከታዮቹ ሲናገር "ይህ ረጅም ጉዞ፣ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ብዙ ችግሮች እና ውጣ ውረዶች የነበሩ ቢሆንም፣ ነገር ግን ከእናንተ ጋር ለመገናኘት በማሰቤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ጠፉና ተረሱ፡፡"

እርሱ ያከናወናቸው ድርጊቶችና ባህሪዎች ለጉብኝቱ ያለውን አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ አሳይቷል። በቺካጎ አካባቢ በሚሺጋን ሐይቅ ዳርቻ፣ እሱ ራሱ ለማሽሪኩል-አድህካር (ቤተ-መቅደስ) ማሰሪያ በተገዛው ቦታ ላይ፣ የምዕራብና የምሥራቅ ባሃኢዎች ተወካዮች በተሰበሰቡበት የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጡ፤ "የቃል ኪዳኑ ከተማ" ተብሎ በተሰየመው በኒውዮርክ ከተማ በተከታዮቹ አጠቃላይ ስብሰባ በወቅቱ የተተረጎመውን የቅርንጫፍ ጽላት ንባብ ተከትሎ በባሃኡላህ የተቋቋመው የቃል ኪዳኑ አንድምታ ሕይወታማ ኃይልን እራሱ ማረጋገጡ፤ በምዕራቡ ዓለም የባሃኡላህን እምነት በቀዳሚነት የተቀበለው "የመጀመሪያው አሜሪካዊ አማኝ" ቶርንቶን ቼዝ በካሊፎርኒያ በኢንግልውድ ውስጥ ወደነበረው መቃብሩ ልዩ መንፈሳዊ ጉዞ ባደረገበት ጊዜ የነበረው ስሜት የሚነካ ዝግጅት፣ በአረንጓዴ ስፍራ መስክ ላይ በጁን (ፀሐያማ) ወር በኒው ጀርሲ ዌስት ኢንግልዉድ ውስጥ በስፋት ለተሰበሰቡት ደቀ-ዛሙርቶቹ ልዩ የሆነ ግብዣ እርሱ እራሱ በማድረጉ፤ ሰሜን ምስራቅ የአሜሪካን ግዛት በሜይን ውስጥ በፒስካተኳ ወንዝ ዳርቻ ብዙ ተከታዮቹ በተሰበሰቡበት የምዕራባዊው ንፍቀ ክበብ የመጀመሪያዎቹ የባሃኢ የበጋ ትምህርት ቤት ወደ መሆን ወደተሸጋገረው… በግሪን ኤክር መድረክ ላይ የሰጠው ቡራኬ፤… እነዚህ የአሜሪካን አማኞች ማህበረሰብን በጎበኘበት ጊዜ ካደረጋቸው አስደናቂ ተግባራት መካከል መመደብ ያለባቸው ሲሆኑ፣ እነዚህ ተግበራትም ማዕከላዊውን ቤተ-

መቅደሳቸውን እንዲሰሩ መንገድ የከፈተ፣ በቅርቡ የሚጋፈጡትን ፈተናዎች በጽናት እንዲቋቋሙ የሚያደርጋቸው፣ አንድነታቸውን የሚያጠነክርላቸውና በቅርቡ የሚጀምሩትንና ስኬት ያገኙበትን የአስተዳደራዊ ሥርዓት ጅማሬዎችን ባርኮላቸውም ነበር።

አብዱል-ባሃ የአሜሪካ አህጉራትን በጎበኘበት ወቅት ካገኛቸው በርካታ ሰዎች  ያከናወናቸው ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የበለጠ አስደናቂ ነበር። ለስምንት ወራት የእርሱን ቀናት ያጨናነቁትን የእነዚህ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሙሉ ዘገባ ማግኘት፣ ከዚህ የዳሰሳ ጥናት ወሰን በላይ ይሆናል። በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ብቻ ከሃምሳ አምስት በማያንሱ የተለያዩ ቦታዎች፣ የህዝብ አድራሾች ንግግርና መደበኛ ጉብኝቶችን ማድረጉ በቂ ነው ። የሰላም ማኅበራት፣ የክርስቲያን እና የአይሁድ መሰባሰቢያ ቤተ-ፀሎቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች፣ የበጎ አድራጎት እና የእርዳታ ድርጅቶች፣ የሥነ ምግባር አምልኮ አባላት፣ የአዲስ አስተሳሰብ አራማጅ ማዕከላት፣ የሥነ-መለኮታዊ ቡድኖች፣ የሴቶች ክበባት፣ የሳይንሳዊ ማህበራት፣ የቲዎሶፊስቶች፣ የሞርሞኖች እና የአግኖስቲክስ ስብስቦች፣ የእስያና የአፍሪካ ሰዎች እድገት ኢንስቲትዩት፣ የሶሪያ፣ የአርሜኒያ፣ የግሪክ፣ የቻይና እና የጃፓን ማህበረሰቦች ተወካዮች፤ ሁሉም የእርሱን ሕይወታማ ኃይል ተቋድሰዋል፣ ከአንደበቱ የአባቱን መልዕክት የመስማት ልዩ ዕድል አግኝተዋል። ኒውዮርክ በሞሆኮ ሐይቅ ዳርቻ በተካሄደው የሰላም ኮንፈረንሶች ላይ ያደረገው

ውይይት፤ በኮሎምቢያ፣ በሀዋርድ እና በኒውዮርክ ዩኒቨርስቲዎች ለተሰባሰቡ ብዙ ሰዎች ያደረገው ንግግር፤ የአፍሪካና እስያሰዎች እድገት ብሔራዊ ማህበር ባዘጋጀው አራተኛው ዓመታዊ ጉባዔ ላይ መሳተፉ፤ ከሁለት ሺህ ሰዎች በላይ በተገኙበት፣ በሳንፍራንሲስኮ በሚገኘው የአይሁድ ምኩራብ ቤተ-መቅደስ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስንና ነብዩ መሐመድ [የአምላክ መልዕክተኛነት] ተልዕኮ እንዳላቸው በድፍረት ማረጋገጡ፤ በሊላንድ እስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ በአንድ ሺህ ስምንት መቶ ተማሪዎች እና በመቶ ሰማኒያ መምህራንና ፕሮፌሰሮች ፊት ያደረገው ደማቅ ንግግር፤ በኒውዮርክ የድሆች ሰፈር የበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ ያደረገው የማይረሳ ጉብኝት፤ በዋና ከተማው በዋሽንግተን ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ በስፋት ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ለእርሱ ክብር ያቀረቡበት ደማቅ ግብዣ፣ እነዚህ የአባቱን እምነት ለማገልገል ላደረገው የማይረሳው ተልእኮ ዋና ዋና ነገሮች ሆነው ጎልተው ይታያሉ። የመንግሥት ጸሐፊ ሚኒስቴሮች፣ አምባሳደሮች፣ የፓርላማ አባላት፣ የታወቁ ራቢዎች (የአይሁድ ሊቀ-ቀሳውስት)፣ የቤተክርስቲያን ሰዎች እና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች እርሱን አግኝተዋል፣ ከእነዚህ መካከል የሊላንድ እስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር ዴስ ጆርዳን፣ የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ጃክሰን፣ የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ጃክ፣ የኒውዮርክ ራቢ እስጢፋኖስ ዊዝ፣ ራቢ ዶ/ር ማርቲን ኤ ሜየር፣ ራቢ ጆሴፍ ኤል ሌቪ፣ ራቢ አብራምስምን፤ አሌክሳንደር ግራሃም ቤል ፣ ባላቅኔው ራቢንድ

ራናት ታጎር፣ ተራማጅ ፖለቲከኛው ክቡር ፍራንክሊን ኬ.ሌን፣ የዲሞክራት ፓርቲ አባልና ለፕሬዘደንትነት እጩ የነበረው ዊሊያም ጄኒንዝ ብራያን፣ የኢንዱስትሪ ባለሙያ እና በጎ አድራጊው አንድሪው ካርኔጊ፣ የዩናይትድ ስቴትስ የግምጃ ቤት ፀሐፊ ክቡር ፍራንክሊን ሜክቬይ፣ ታዋቂው ስፖርተኛ ሊማክለንግ፣ ከ1901—1909 የአሜሪካ ፕሬዝደንት የነበሩት ሩዝቬልት፣ አድሚራል ዋይንራይት፣ አድሚራል ፔሪ፣ በዋሽንግተን የእንግሊዝ፣ የደች እና የስዊዘርላንድ ሚኒስትሮች፣ የቱርክ አምባሳደር ዩሱፍ ዲያ ፓሻ፣ ጠበቃ፣ ፖለቲከኛና ከንቲባ ዊሊያም ሱልዘር እንዲሁም ግብፃዊው ልዑል ሙሐመድ አሊ ይገኙበታል፡፡

የአሜሪካን ጉዞዎቹን የዘገበው ጸሐፊ “አብዱል-ባሃ በ1912 ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን አገር ሲጎበኝ፣ ብዙ የሆኑ ቅን ግንዛቤ ያላቸው ታዳሚዎች በግል ሊያገኙትና አፍቃሪ እና መንፈሳዊ የሆኑ መልእክቶቹን ከእራሱ አፍ ለመስማት ይጠባበቁ ነበር፣… ከሚናገረው ቃላት ባሻገር የእርሱ ማንነት የመጡትን ሁሉ በጥልቅ የሚያስደምም ሊገለጽ የማይችል ባሕሪይ ነበረው፡፡ …”

ይህን የዳሰሳ ዘገባ አብዱል-ባሃ በአውሮፓና በአሜሪካ ጉብኝት የተለያዩ እና ግዙፍ ተግባራትን በተመለከተ፣ ብዙውን ጊዜ ከእሱ የግል ግንኙነት ጋር የተያያዙ አንዳንድ ልዩ የሆኑ ክስተቶችን ሳይጠቅሱ ማለፍ የተሟላ አያደርገውም፡፡ የአንድ የማይበገር ወጣት ድፍረት፣ አብዱል-ባሃ ምዕራባዊ የአሜሪካ ከተሞችን አይጎበኝ ይሆናል ብሎ

በመፍራት፣ ወደ ኒውኢንግላንድ ከተማ የባቡር ጉዞ ለመክፈል አቅም ስላልነበረው፣ በባቡር ኃማዎች መካከል ባለው የብረት ዘንግ ላይ ተኝቶ ከሚኒያፖሊስ እስከ ሜይን ድረስ ተጉዟል፤ በእንግሊዝ አገር ውስጥ የዳሬክተር ልጅ ሕይወት ውስጥ የተካሄደው የለውጥ ሂደት ሕይወቱን ለማጥፋት ወደ ቴምስ ወንዝ ዳር ቻዎች እየተጓዘ እያለ፣ በአንድ ሱቅ መስኮት ላይ የአብዱል-ባሃን ፎቶግራፍ ተለጥፎ በማየቱ ስለእሱ ጠየቀ፣ ከዚያም በፍጥነት አብዱል-ባሃ ወደአረፈበት ቤት ሄደ፣ በደስታ እና በማጽናኛ ቃላቱ ታደሰ፣ ለችግሩ እና ለድህነቱ መፍትሄ ሰጠው፣ እራስን የማጥፋትን አስተሳሰብንም ተወ፤ የአንዲት ሴትዮ ትንሽ ሴት ልጅ በሕልሟ ጌታ ክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣቱን በማየቷ አጥብቃ የጠየቀችበት ልዩ የሆነ ክስተት ከዚያም በመጽሔት መደብር መስኮት ላይ የአብዱል-ባሃን ምስል ስታይ ወዲያውኑ የሕልሟ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መለየቷ፣ እናቷም አብዱል-ባሃ በፓሪስ ውስጥ እንዳለ ካነበበች በኋላ ወደ አውሮፓ የሚሄደውን መርከብ ተሳፍራ በመጓዝ እሱን ለማግኘት ያነሳሳት አስገዳጅ ድርጊት በዚያን ወቅት ከኢሽቃባድ ወደ ለንደን ከመጣው ፋርሳዊው ወዳጅ በዛ ከተማ ከሚኖሩ ድሃ ባሃኢዎች የተላከለትን በጥጥ ጨርቅ መሃረብ የተጠቀለለ የደረቀ ጥቁር ዳቦና ፖም ስጦታ አብዱል-ባሃ ከእጁ ሲቀበል የነበረው ልብ የሚነካ ትዕይንት፣ እሱም የተሰበሰቡት ሰዎች ፊት ከፍቶት ለእርሱ የተዘጋጀለትን ምሳ ትቶ፣ ከዳቦው ላይ ትንሽ ቆርሶ ከበላ በኋላ ለሌሎችም ያካፈለበት ሁኔታ-እነዚህ

የእርሱ የማይረሱ ጉዞዎችን አንዳንድ ግላዊ ገጽታዎችን እንደብርሃን ገልጠው የሚያሳዩ ጥቂት ክስተቶች ናቸው።

እንዲሁም በአውሮፓ እና በአሜሪካ ከተሞች ሲዘዋወር፣ በዚያ ግርማና ገዢ የሆነ የአዛውንት ገጽታ ባለው ስብዕና ዙሪያ የሚካሄዱ መሳጭ ትዕይንቶች፣ ከአእምሮ ሊፋቁ አይችሉም። አብዱል-ባሃ ባደረገው አስገራሚ ቃለ ምልልስ ወቅት በሊቀ-ዲያቆን ዊልበርፎርስ ራስ ላይ በፍቅር እጁን ሲጭንበት፣ ከዛም በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ክብር ያለው ሰው ከጎኑ ባለው ዝቅተኛ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ ለሊቀ ዲያቆን ብዙ ጥያቄዎች መልስ ሰጠ፤ ከዚያው ሊቀ ዲያቆን ጋር የነበረው ሌላው አስደናቂው ትዕይንት በቅዱስ ዮሐንስ ቤተ-ክርስቲያን በረከት ለመቀበል ከመላው ምዕመናን ጋር በጉልበቱ ተንበርክኮ ከቆየ በኋላ፣ ከእንግዳው (ከአብ ዱል-ባሃ) ጋር በመሆን የተሰበሰበው ምዕመናን እየ ዘመረ ሳላ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከቅዱሰ ቅዱሳኑ ወርደው በመተላለፊያው አብረው መሄዳቸው፤ የፋርሱ ልዑል ጃለሉድ-ዳውሊህ በእግሮቹ ላይ ወድቆ፣ ለቀደሞዎቹ በደሎች ይቅርታ በመጠየቅ ምህረቱን ሲለምን፤… በቦስተን የምትኖር አንዲት ሶርያዊት ሴት በዙሪያዋ የተሰበሰበውን ህዝብ ገፈታትራ እግሩ ላይ ወድቃ፣ ድምጿን ከፍ አድርጋ በመጮህ "በአንተ ውስጥ የእግዚአብሔርን መንፈስ እና እራሱን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየሁ እመሰክራለሁ" ማለቷ፤ ከዚያች ከተማ (ከለንድን) ወደ ዱብሊን ሲሄድ ሁለት አድናቂዎች የሆኑ አረቦች በፊቱ እራሳቸውን ደፍተው፣ ጮክ ብለው

እያለቀሱ እርሱ ለሰው ልጆች የአምላክ መልእክተኛ መሆኑን መመስከራቸው፤ ዞሮአስተራዊ የሆነው ሐኪም አብዱል-ባሃ ለንደንን ለቅቆ በሚሄድበት ቀን ጠዋት ላይ ትንፋሹ እስኪ ቆራረጥ በፍጥነት ገስግሶ በመድረስ የመልካም ጉዞ ምኞቱን ለመግለጽ ጥዑም ሽታ ያለው ዘይት የአብ ዱል-ባሃን እራስና ደረት ቀብቶት፣ ክብ ዘለበት ላይ የተጎነጎነ እንቡጥ አበባ አንገቱ ላይ ካደረገለት በኋላ የተሰበሰቡትን ሰዎች እጅ በጨበጠበት ልዩ የሆነ ክብሩን መግለጹ፤ ጎህ ሲቀድ በትእግስት ባረፈበት ቤት ደጃፍ ላይ በሩ እስኪከፈት ድረስ በመጠበቅ የሚሰበሰቡት የጎብኝዎች ብዛት፣ በቤተ-ክርስቲያን እና በምኩራብ በመድረኮች ላይ እንዲሁም በአክ ብሮት አድማጮች ፊት በጠንካራ እርምጃዎቹ ሲራ መድ ያለው ግርማ ሞገስ፤ ....እንደነዚህ ያሉት ዘገ ባውን በቀለም የሚያደምቁት ክንዋኔዎች የራሳቸው የሆኑ መስህብና ኃይል አላቸው። ”

አብዱል-ባሃ አሜሪካ ከመድረሱ በፊት እና እዚያም በነበረበት የስምንት ወር የጉብኝት ወቅት፣ ከዛም ደግሞ ሊመለስ ሲዘጋጅ የሰሜን አሜሪካ ባሃኢዎች የጉዞውን ወጪ በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸፈን ገንዘብን ሊሰጡት ብዙ ጊዜ ደጋግመው ሞክረው ነበር። በቀጥታ ለእርሱ ጻፉ፣ አነጋገሩትም፣ የጉዞ ባልደረቦቹንም ምክር ጠየቁ። አብዱል-ባሃ ለእነዚህ ሁሉ አቤቱታዎች፣ ምስጋናውን ቢገልጽም፣ ምላሹ ግን አሉታዊ ነበር። ቀደም ሲል በግብፅ አገር ሳለ ወደ እርሱ የተላከው ከፍተኛ ገንዘብ ተመላሽ ተደርጓል። ...ለእርሱ ለግሰውት የነበረው ገንዘብ ለድሆችና ለተቸገሩት መሰጠት አለበት ብሏቸዋል። ከአሜሪካ የመመለሻ ጊዜው እየተቃረበ ሲመጣ በርካታ

ባሃኢዎች ወደ አብዱል-ባሃ በመሄድ ስጦታቸውን እንዲቀበል ለመኑት፡፡ አብዱል-ባሃም እንዲህ አላቸው ላደረጋችሁት ግልጋሎት በጣም አመስጋኝ ነኝ፡፡ በእርግጥ በጥሩ ሁኔታ አገልግላችሁኛል፣ ከፍ ያለ እንግዳ ተቀባይነታችሁንም አሳይታችሁኛል፡፡ ቀን ከሌሊት ለማገልገል ተነስታችኋል፤ የአምላክን ጥዑም ሽታዎች ለማሰራጨት ተግታችኋል ፡፡ የአምላክን በጎ ፈቃድ ከመፈለግ እና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከመግባት በቀር ሌላ ደረጃ ስለ ማትፈለጉ አገልግሎታችሁን በጭራሽ አልረሳውም፡፡ እነሆ ለቤተሰቦቼ አባላት ስጦታዎች አመጣችሁ፡፡ እነዚህ ስጦታዎች በጣም ጥሩ እና በጣም ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፤ ነገር ግን ከእነዚህ ስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠው በልቦች መዝገብ ውስጥ የሚቀመጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ስጦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው፣ እነዚያኞቹ ስጦታዎች ግን ዘላለማዊ ናቸው፡፡ ጌጣጌጦች በሳጥኖች እና በድብቅ ማስቀመጫዎች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው እናም በመጨረሻ አገልግሎታ ቸው ያበቃል፡፡ እነዚያ ጌጣጌጦች ግን በልቦች ግምጃ ቤቶች ውስጥ ይቆያሉ፣ በእግዚአብሔር ዓለማት ውስጥም ለዘላለም ይኖራሉ፡፡ እኔ ቤት ያሉ የአልማዝ ቀለበቶችን አያደርጉም፡፡ ሩቢዎችን (የከበረ ደንጋይ) አይጠቀሙም፡፡ ያ ቤት ከእንደ ዚህ ዓይነት የሚያቁለጨልጨ ነገሮች ነፃ ነው፡፡ አሁን እነዚህን ስጦታዎች ተቀብያለሁ፣ ነገር ግን ተሸጠው ገንዘቡ በቺካጎ ለሚገኘው ማሽሪኩል-አድህካር (ቤተ-መቅደስ) ማሰሪያ እንዲሆን በአደራ ሰጥቻለሁ፡፡

አብዱል-ባሃ ዲሴምበር 5 1912 ከአሜሪካን ወደ አውሮፓ በመርከብ ተጓዘ፡፡ የአሜሪካን ባሃኢዎችን ሲሰናበት፡-

አሁን ለመጓዝ መርከብ ልሳፈር ነው፣ ይህ የመጨ ረሻ ስንብቴ ነው። እነዚህ የመጨረሻ የምክር ቃሎቼ ናቸው። እኔ በተደጋጋሚ፣ ወደ ሰው ዘር ዓለም አንድነት እናንተን እየጠራሁ ነው፣ የሰው ልጆች ሁሉ የአንድ አምላክ አገልጋዮች መሆናቸውን እያወጅኩ ነው፤ አምላክ የሁሉ ነገሮች ፈጣሪ ነው፤ እርሱ ለጋስ እና ሕይወት ሰጪ ነው፤ ሁሉም በእርሱ የተወደዱ ናቸው… ስለዚህ እናንተ፣ አክራሪነትን ወደ ጎን በመተው፣ ሃይማኖታዊ፣ ብሄራዊ እና የዘር ጭፍን ጥላቻን በማስወገድ ለዓለም ሕዝቦች ታላቅ ደግነትና ፍቅር ማሳየት አለባችሁ።

ስለዚህ ማንም ሌላውን ቢያስቀይም አምላክን ያስቀ ይማል። የሰማይ አባታችን ምኞት እያንዳንዱ ልብ እንዲደሰት እና በደስታ እንዲሞላ ነው፤ በተድላ እና በደስታ አብረን እንድንኖር ነው። ለሰው ልጅ ደስታ መሰናክል የዘር ወይም የሃይማኖት ጭፍን ጥላቻ፣ የህልውና ተፎካካሪነት መኖር እና እርስ በእርስ ኢሰብአዊነት ነው።

ከእግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችሁን እንዳትለዩ፣ ማንኛውንም ልብ እንዳታሰናክሉ፣ አንድ ሰው በሌለ በት ስለእሱ እንዳትናገሩ ተጠንቀቁ። ሁሉንም አገልጋዮቹን እንደእራሳችሁ ቤተሰብ እና ዘመድ አድርጋችሁ መቁጠር አለባችሁ። ጥሪታችሁን ተስፋ ወደቆረጡት ሰዎች ደስታ አዙሩ፣ ለተራቡ ምግብ ስጡ፣ ችግረኞችን አልብሱ፣ ትሑታንንም አክብሩ። በእናንተ ስም ከአምላክ ዘላለማዊ ክብርን እጠይቃለሁ፤ ይህ የእኔ ፀሎትና ምልጃ ነው።

> የእግዚአብሔር ሚስጥሮች ስለተነገራችሁ የእናንተ ግዴታ ሌላ ዓይነት ነው፡፡ ዓይኖቻችሁ በርተዋል፣ ጆሮዎቻችሁ በመስማት ተነቃቅተዋል፡፡ ስለሆነም እርስ በእርስ በመተያየት ከዚያም በኋላ በከፍተኛ ፍቅር እና ቸርነት ወደ ሰው ልጆች መመልከት አለባችሁ፡፡ እንደትእዛዙ ለመኖር ካቃታችሁ ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት ምንም ሰበብ የላችሁም፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ምን እንደሆነ ተነግሯችኋል፡፡ መርሆዎቹንና ትእዛዛቱን ሰምታችኋል፡፡ ስለዚህ ለሰው ሁሉ ቸር መሆን ይገባችኋል፤ ጠላቶቻችሁን እንኳን እንደ ጓደኞችሁ አድርጋችሁ መያዝ አለባችሁ፡፡ …ይህ አለመግባባትና የግጭት ጨለማ ከሰዎች መካከል እንዲጠፋ እና መለኮታ ዊው ብርሃን እንዲበራ፣ ለእናንተ ክፉ ተመኚዎችን እንደመልካም ወዳጆቻችሁ አድርጋችሁ መቁጠር አለባችሁ፤ ሰው ወደዚህ ከፍ ያለ ደረጃ እስካልደረሰ ድረስ የሰው ልጅ ዓለም እረፍት አያገኝም፣ ዘላለማዊ ደስታም አይደረስበትም ፡፡…

[ከዚህ የምክክር ንግግር] በኋላ አብዱል-ባሃ ሄደ፡፡ ሴልቲክ የተባለችው አብዱል-ባሃ የተሳፈረባት መርከብ አርብ ዲሴምበር 13 ቀን 1912 ሊቨርፑል እንግሊዝ ደረሰች፡፡ ሂፖላይት ድራይፉስ-በርኒ ከፓሪስ፣ ኤሊዛቤት ሄሪክ እና ኢዛቤል ፍሬዘር ከለንደን፣ ኢቲ ሆል እና ጆን ክሬቨን ከማንቸስተር፣ ጆን ዳውንስ ከሊድስ እና የአብዱል-ባሃ አማች አቃ አሕመድ-ያዝዲ ሊቀበሉት ተገኝተው ነበር፡፡

ከዚያም ዲሴምበር 16 ከሊቨርፑል ወደ ለንደን ተጓዘ፡፡ ሌዲ ብሎምፊልድ ከልጇ ጋር እንዲሁም ኢቴል

ሮዝንበርግ፣ ሚሲስ ቶርንበርግ-ክሮፐር፣ ኤልሲ ሊ፣ አኒ ጋም ብል፣ ሉቱፉላህ ሀኪም፣ አርተር ኩትበርት እና ሌሎች በርካታ ባሃኢዎች ባቡር ጣቢያው ጋር የእርሱን መምጣት እየተጠባበቁ ነበር፡፡

[አንድ ወር ከሳምንት በእንግሊዝ አገር ቆየ] የመጨረሻው ቀን ምሽት በለንድን የሊቃውንቶች ማዕከል ንግግር ካደረገ በኂላ ጃንዋሪ 21 ቀን ወደ ፓሪስ ሄደ፡፡

አብዱል-ባሃ ለሁለተኛ ጊዜ በፓሪስ ያደረገው ጉብኝት፣ በርካታ ሳምንታትን ያስቆጠረ ሲሆን የእራሱ የሆኑ የተወሰኑ ባህሪያትም ነበሩት፡፡ ጥቂት የህዝብ ንግግሮችም አድርጓል፡፡

[ሁለት ወር በፓሪስ ከቆየ በኂላ ማርች 30 ቀን ወደ ስቱትጋርት ጀርመን እንደገና ሄደ፡፡ ከዚያም ወደ ቡዳፔስት ኤፕሪል 9 ቀን ሄደ፡፡ ኤፕሪል 19 ቀን ደግሞ ከቡዳፔስት ወደ ቬይና ተጓዘ፡፡ በኤፕሪል 24 ወደ ስቱትጋርት ተመለሰ፡፡ ጤንነቱ ታውኮ ስለነበር አንድ ሣምንት እዚ ያው ቆየ፡፡]

አብዱል-ባሃ በዚህ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ስቱትጋርት ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ለአንድ ሳምንት የዘለቀ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜም ጤንነት አልነበረውም፡፡ በቡዳፔስት የያዘው ጉንፋን አሁን ወደ ደረቱ ወርዶ ሕመሙ በረታ፡፡ የስቱትጋርት ባሃኢዎች  ምሽት ላይ በሙዚየም ውስጥ ስብሰባ አዘጋጅተው ነበር፡፡ ከሰዓት በኂላ ላይ የጉንፋኑ ሁኔታ እየተባባሰ በመሄድ ከፍተኛ ስጋት ፈጠረ፡፡ ሐኪሞችም መውጣት እንደሌለበት እና በተቻለ መጠን ንግግር መቀነስ እንዳለበት መከሩት፡፡ ወደ ስብሰባው የላከው ባልደረባው አብዱል-ባሃን መገናኘት ከተነፈጉ

እዚያ የተሰበሰቡት በርካታ እና በጉጉት የሚጠብቁት ታዳሚዎች ተስፋ እንደሚቆርጥ እና እንደሚደናገጡ ተሰማው፡፡ ሌሎች የአብዱል-ባሃን ጤና የሚጠብቅና ህዝቡ እሱን የሚያገኝበት ሁኔታ ይፈጠርለታል ብሎ ያሰቡትን እቅድ ይዘው ወደ አብዱል-ባሃ ሆቴል ሄዱ፡፡ ከአየሩ ሁኔታ በደንብ የሚጠብቀው መኪና አብዱል-ባህን ወደ ሙዚየሙ ያደርሰዋል ከዚያም ከዋናው አዳራሽ ውጭ በአንድ ክፍል ውስጥ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ይህንን እቅድ ለአብዱል-ባሃ እንዳቀረቡለትና የታዳሚዎችን ጉጉት እና ብስጭት እንደነገሩት ወዲያው ከአልጋው ተነሳ፡፡ ዊልሄልም ሄሪጌል በእርሱ ምትክ ንግግር እያደረገ እያለ አብዱል-ባሃ ወደ አዳራሹ ገባ፣ ታዳሚዎቹ በሁኔታው እስኪደሰቱና እስኪደነቁ ድረስ፣ ሙሉ ድምፁን በመጠቀም ስለዓለም ሰላም አስፈላጊነት እና ዋስትና ስለሚሰጠው ኃይል ላይ ንግግር አደረገ፡፡ ንግግሩን ጨርሶ በፍጥነት ወደ ሆቴሉ ሊመለስ ሲል፣ የለቅሶ ድምፅ ሰማ፡፡ ቆም ብሎ አብረውት የነበሩትን ሰዎች ስለለቅሶው እንዲጠይቁ ነገራቸው፡፡ አብዱል-ባሃን ለማግኘት ሞክራ በህዝቡ ብዛት ምክንያት ታግዳ የነበረች አንዲት ሴት እያለቀሰች መሆኗን ነገሩት፡፡ አብዱል-ባሃም እሷን በማግኘት መልካም የሆነ ቃላቶቹን አካፈላት፡፡ በቀጣዩ ቀን ስለ ጤናው ለቀረቡለት ጥያቄዎች የቀድሞው ምሽት ድርጊቱ ምንም እንኳን በጣም አደገኛ ቢሆንም ለእሱ ትክክለኛ መድሃኒት መሆኑን አረጋገጠላቸው፡፡

[ሜይ 1 ቀን ወደ ፓሪስ ተመለሰ] የአብዱል-ባሃ ታሪካዊው የምዕራቡ ዓለም ጉብኝት አሁን ወደ ፍጻሜው እየተቃረበ ነበር፡፡ ሚርዛ አሊ-አክባር-ናክጃቫኒ ከቅድስት ሀገር ተመልሶ በመምጣት፣ የአብዱል-ባሃ መመለስን

በመጠባበቅ ላይ ያሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው መንፈሳዊ ጎብኚ ምዕመናን እንዳሉ ዜናውን አደረሰ፡፡

ጁን 12/ 1913 ከጠዋቱ 2 ሰዓት ላይ አብዱል-ባሃ ፓሪስ ካረፈበት ሆቴል ለቆ ወደ ባቡር ጣቢያው ሄደ፡፡ ለመሰናበት የመጡትን ባሃኢዎች አነጋግራቸው ሁልጊዜ አንድ እንዲሆኑም ጥሪ አቀረበላቸው፡፡ እኩለ ቀን ላይ ባቡሩ ተነሳ፣ ከአሥራ ሁለት ሰዓታት ጉዞ በኋላ ማርሴ ደረሰ ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ሌላ መርከብን ተሳፈረ ፡፡

አንድ ህንዳዊ ተሳፋሪ ማደሪያ ክፍሉ ከአብዱል-ባሃ አጠገብ ነበር፡፡ እሱ እና ሌሎች በርካታ ሕንዶች ለተወሰኑ ሰዓታት ከአብዱል ባሃ ጋር አሳለፉ፡፡ አንድ የእንግሊዝ ባለሥልጣን እና ሴት ልጁም አገኙት፣ እንግሊዝ ውስጥ ዊኪንግ የሚባል ቦታ  መስጊድ ሲጎበኝ የሚያሳይ ፎቶግራፉን የያዘ ጋዜጣ አበረከቱለት፡፡

እ.ኤ.አ. ጁን 17 ቀን 1913 ከሰዓት በኋላ አብዱል-ባሃ ግብፅ ፖርት ሳይድ ደረሰ፡፡

# ክፍል ሦስት

## ምዕራፍ 10

## ወደ ግብፅ ከዚያም ወደ ቅድስት አገር

አብዱል-ባሃ በፍጥነት ወደ ቅድስት ሀገር ለመጓዝ አልወሰነም፡፡ በሐይፋ ውስጥ የተሰባሰቡ መንፈሳዊ ኅብኚዎች ወደ ግብፅ እንዲመጡ ቴሌግራም ተላከላቸው፡፡ ይቆዩበት የነበረው ሆቴል ለቁጥራቸው እና ለእንቅስቃሴዎቻቸው በጣም አነስተኛ በመሆኑ ግብፃውያን ለሕዝብ አገልግሎት የሚጠቀሙበት አንድ ግዙፍ ድንኳን በሆቴሉ ጣሪያ ላይ ተጣለ፡፡ በዚያ ድንኳን ጥላ ስር የማይቋረጥ ስብሰባዎች ይካሄዱ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ብዙ ጊዜ የተናገረባቸው ስብሰባዎች እዚያ ተካሄዱ ፡፡

አብዱል-ባሃ በዚያ ድንኳን ስር የተሰበሰቡትን የተለያዩ ሰዎች በመመልከት እንዲህ ያለው ስብሰባ መቻሉ በእውነቱ አስደናቂ ነው ብሏል፡፡ አርብ ጁን 27 ቀን 1913 የግብፅ ጋዜጣ “አብዱል-ባሃ በግብፅ” በሚል ርዕስ አንድ መጣጥፍ ይዞ ወጣ፡፡ በፖርት ሳይድ ውስጥ አስደናቂ ትዕይንት ነበር፡፡ ምሥራቃዊ ባሃኢዎች በስፋት ተሰባሰቡ፡፡ አብዱል-ባሃ አሁን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በሥራ ተጠመደ፡፡ ብዙ መንፈሳዊ ኅብኚዎች፣ ብዙ ከእርሱ ጋር ለመገናኘትና ለመወያየት የሚፈልጉ የግብፅ ባሃኢዎች ነበሩ፣ መልስ የሚጽፍላቸው ብዙ ደብዳቤዎችም ነበሩ፡፡ ደብዳቤዎች፣ ተማጽኖዎች እና ቴሌግራሞች ከምስራቅና ከምዕራብ ይጎርፉ ጀመር፡፡ በዚያን ጊዜ የተጻፉት ጽላቶች ሁሉ በእራሱ የእጅ ጽሑፍ የተጻፉ ነበሩ፡፡

ባሃኢዎችን ብቻ አልነበረም የሚያገኘው። አንድ ቀን ብዙ ከጻፈና ብዙ ንግግር ካደረገ በኋላ በቀኑ መጨረሻ ላይ በጣም ተዳክሞ ነበር፣ ከዚያም የተለመደውን የዕለት ተዕለት የእግር ጉዞውን ለማድረግ ከቤቱ ሲወጣ፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎቶች በቡድን ሆነው እርሱን ለማግኘት ወደ ቤቱ መጡ። አብዱል-ባሃ በተለመደው ጨዋነቱ እና ቸርነቱ ተቀበላቸው። ብዙም ሳይቆይ ሙስሊሞችን እና እስልምናን በጥብቅ ይተቹ ጀመር። አብዱል-ባሃም እነሱ የሚናገሩት ነገር እውነተኛው እስልምናን ሳይሆን በእስልምና ስም ያሉ አስመሳዮችንና ጥቃቅን የሆኑ ነገሮች እንደሆነ ነገራቸው፣ ከዛም ከቁርአን ውስጥ ስለክርስቶስ አንድ ጥቅስ ነገራቸው፡- "|እነዚያ ያመኑ እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ ክርስቲያኖችም፣ ሳቢያኖችም (ከእነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው። በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም።" (2፡62)

ሚርዛ ጃፋር-ራህማኒ-ሺ-ሽራዚ በፖርት ሳይድ የሚገኙ ትን ሁሉንም ባሃኢዎች ራት ጋበዘ። ከሰባ በላይ ነበሩ። በድንኳን ጥላ ሥር ሁሉም ተመገቡ አብዱል-ባሃም ያስተናግድ ነበር፣ ከዛም ለሁሉም ጣፋጭ ተሰጣቸው። በሚቀጥለው ቀን ጁን 28 ብዙዎቹ ከሐይፋ የመጡ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ተመለሱ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከሚሄደው ለአብዱል-ባሃ ከሚላኩት መልዕክቶች መካከል አንድ ቀን በርካታ ደብዳቤዎች ከኢስታንቡል መጡ። ወደ ኢስታንቡል በመሄድ የባሃኡላህን ጥሪ ማወጅ እንደሚችል ተናገረ፣ ነገር ግን በቅድስት አገር አስከፊ መዘዞች ይከሰታሉ፣

ብዙዎች እምነቱ ላይ ይነሳሉ፣ የአክራሪዎች ቁጣ ይጨምራል፣ እናም ቅዱሳን ስፍራዎች ላይ ጥቃት ይሰነዘራሉ አለ፡፡

…በፖርት ሳይድ መጥፎ የአየር ሁኔታ ስለመጣ አብዱል-ባሃ ወደ ኢስማኢለያህ ሚርዛ ሙኒርንና አቃ ኹስራውን ይዞ ሄደ፡፡ አብዱል-ባሃ ከሳምንት በኋላ ወደ ኢስማኢለያህ የጠራቸው ጥቂት ባሃኢዎች በጄ. ቦስታ ሆቴል ውስጥ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ አገኙት፣ ከበፊቱ በበለጠ ትኩሳት ይዞትና ተዳክሞ ነበር፡፡ ለደብዳቤዎቹ ግን ምላሽ እየሰጠ ነበር፡፡

ኢስማኢለያህ ብዙም ወበቅ አልነበረውም ሆኖም ግን የአብዱል-ባሃ የትኩሳት መጠን የበለጠ ሆነ፡፡ የአሌክዛንድሪያ ዳርቻ የሆነችው ራምሊ የተሻለ የጤንነት ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ስለታሰበ ጁላይ 17 ቀን አብዱል-ባሃ ወደ አሌክዛንድሪያ ተጓዘ፡፡ በራምሊህ ሆቴል ቪክቶሪያ ውስጥ ለሁለት ሳምንት ከቆየ በኋላ በማዝሉም ፓሻ ጣቢያ አካባቢ ወደ ተከራየው ቤት ተዛወረ፡፡ እንዲሁም ለፀሐፊዎቹ እና እሱን ሊጎበኙ ለሚመጡት ሌሎች ሰዎች ሁለተኛ ቤት ተከራየ፡፡ ሦስተኛ ቤት በአቅራቢያው ለሚርዛ አብዱል-ፋድል ተያዘ ፡፡

ሉዋ ጌትሲንገር ጁላይ 23 ቀን ፖርት ሳይድ ደረሰች፣ ባለቤቷ ኤድዋርድ ጌትሲንገርም ብዙም ሳይቆይ መጣ፡፡ ሉዋ ከዛ በኋላ የትውልድ አገሯን አሜሪካንን አላየችም፡፡ በፓሪስ ውስጥ የተደረጉትን ንግግሮችን የያዘው የአብዱል-ባሃን መለኮታዊ ፍልስፍና ያቀፈው መጽሐፍ ያጠናቀረችው ኢዛቤል፣ አብዱል-ባሃ አንድ ተልዕኮ ሊሰጣት ስላቀደ በቀጣዩቹ ቀናት መጣች፡፡ በግብፅ ውስጥ ሌሎች ምዕራባዊ ባሃኢዎች ነበሩ፤ ሚስተር እስታናርድ፣

በወደፊቶቹ ዓመታት በጄኔቫ የባሃኢ ቢሮ ያቋቋመችው እንግሊዛዊቷ እመቤት እና በካይሮ ውስጥ የሚሰራው ፈረንሳዊው የጥርስ ሀኪም ዶ/ር ጆሴፍ ዴ. ቦንስ ነበሩ፡፡

አብዱል-ባሃ የራምሊህ አየር ለእርሱ ተስማማው ጤናውም ተሻሻለ፡፡

ባሃኢዎች በተለይም የምስራቅ ባሃኢዎች የተለያዩ ጉዳዮቻቸውን በተመለከተ ይጽፉለታል፤ አንዱ መሬት ስለመግዛት ምክሩን ይጠይቃል፣ ሌላኛው አዲስ ለተወለደ ልጁ ስም ይጠይቃል፣ አንዱ ማግባት ወይንም አለማግባት ይሻለው እንደሆነ ይጠይቃል፣ ሌላኛው ወደ አንድ ቦታ ጉዞ ስለማድረግ ይጠይቃል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አለመግባባቶችን ይፈታል፣ ስሜቶችን ያረጋጋል፡፡ የባሃኢ ቡድኖች፣ ማህበረሰቦች እና መንፈሳዊ ጉባዔዎች፣ ቁጥራቸው እየጨመረ በመምጣቱ ምክር እና መመሪያ መስጠት የበለጠ ጊዜውን ይወስድበት ነበር፡፡ የእሱ ደብዳቤዎች በባሃኢዎች ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ ምዕመናን ያልሆኑ ወደ እርሱ የሚጽፉ እና ምላሹን የሚጠብቁ ብዙዎች ነበሩ፡፡ በምዕራቡ ዓለም ያሉ ማኅበራት፣ ፓርላማዎች፣ ኮንፍረንሶች ለእርሱ መጻፍ ጀምረው ነበር፡፡ በፓሪስ በተካሄደው ከስድስተኛው ዓለም አቀፍ የነፃ እና ተራማጅ ክርስቲያኖች እና ሌሎች የሃይማኖት ሊበራል ስብሰባዎች በፀሐፊዋ በኩል ደብዳቤ ደርሶታል ፡፡

የአብዱል-ባሃ የልጅ ልጅ ሾጊ ኤፌንዲ፣ እህቱ ታላቋ ቅድስት ቅጠል እና ታላቅ ሴት ልጁ፣ ኦገስት 1 ቀን ከሐይፋ መጡ፡፡ አንድ ባሃኢ ወደ አብዱል-ባሃ ቤት በማለዳ ሲሄድ ሾጊ ኤፌንዲ አብዱል-ባሃ እያስተማረው ጸሎትን ሲያዜም ሰማ፡፡

የግብፅ ከዳይፍ አባስ ሕልሚ ፓሻ ኦገስት 17 ቀን ለሦስተኛ ጊዜ ከአብዱል-ባሃ ጋር ተገናኝ፣ የከዳይፍ ወንድም ልዑል መሐመድ-ዓሊም ከአንድ ወር በኋላ አብዱል-ባሃን ጠርቶታል። የከዳይፍ ኡስማን ፓሻ ሙርታዳ ባለሚል ለአብዱል-ባሃ ክብር ያለው ሰው ነበር በእሱ አማካይነት ከአባስ ሕልሚ ፓሻ ጋር ስብሰባ እንዲያደርጉ አመቻችቷል። አብዱል-ባሃ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 1919 ለዑስማን ፓሻ የላከለት ጽላት የሰውየውን አቋም የሚያሳይ ሲሆን፣ አሚር አለ ዋፋ (የታማኝነት ልዑል) ይባል ነበር።

አብዱል-ባሃን በራምሊህ ውስጥ ለማግኘት ከፈለጉት ጎብኝዎች መካከል የቱርክ ፓርላማ ተወካዮች እና የሶሪያ ፕሮቴስታንት ኮሌጅ (የቤይሩት አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ) የአካዳሚክ ሠራተኞች አባላት ይገኙበታል። የበጋ ዕረፍታ ቸውን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ እያሳለፉ የነበሩ የኮሌጁ ባሃኢ ተማሪዎችም አብዱል-ባሃን ለማግኘት በሁለት ቡድን ሆነው ወደ ራምሊህ ሄደው ነበር።

በበጋው ወራት እና በመኸር መጀመሪያ ላይ የአብዱል-ባሃ ጤና በጣም ተሻሽሎ ነበር፣ ሆኖም ግን ዓመቱ እየገፋ ሲሄድ ፣ የቀድሞው የበሽታው ምልክቶች ተመለሱ። አካላዊ ጥንካሬውን የሚያሳጣው ትኩሳት እና እንቅልፍ ማጣት እንደገና ጀመሩት። ለጥቂት ቀናት ወደ አቡኪር ሄደ፣ ነገር ግን አካባቢ መለወጡ ምንም እፎይታ ስላልሰጠው ግብፅን ለመልቀቅ ወሰነ፣ በተለይም ቤተሰቦቹ እና በቅድስት አገር ያሉ ባሃኢዎች እንዲመለስ ይለምኑት ነበር። ዲሴምበር 2 ቀን መርከብ ተሳፈረ። መርከቡም በፖርት ሳይድ እና ጃፋ ላይ ሁለት ጊዜ ቆመ፣ በእነዚህ ከተሞች የሚኖሩ ባሃኢዎች ከአብዱል-ባሃ ጋር ለአጭር

ጊዜም ቢሆን እርሱን የማግኘት ዕድል አገኙ። ዲሴምበር 5 ቀን 1913 ከሰዓት በኂላ ጀልባዋ በሐይፋ ወደብ ላይ መልህቅዋን ጣለች ። አብዱል-ባሃ አገልጋዮቹን ወደ ባህሩ ዳርቻ ላከና ባሃኢዎች ሊቀበሉት እንዳይሰባሰቡ እንዲነግሯቸው አደረገ። ሲመሽ እርሱ ራሱ ከመርከቡ ወረደ።

አሜሪካዊቷ ባሃኢ ኤምጊን ሆግ በዚህ ወቅት ሐይፋ ስለነበረች የአብዱል-ባሃን መምጣት ስትዘግብ፡-

> …በአብዱል-ባሃ ቤት ውስጥ በዙሪያው ሌሎች ክፍሎችን የሚያገናኝ በጣም ትልቅ ማዕከላዊ ክፍል አለ፣ ክፍሉ ምንጣፍ ተነጥፎበታል፣ ፍራፍሬዎችና ጣፋጮች የያዘ ጠረጴዛም ተቀምጧል።
>
> … አብዱል-ባሃ ሲገባና ድምጹ ሲሰማ፣ የጋለ ስሜት ተፈጠረ ወደ ክፍሉም ሲያመራ ሁሉም ሰው በአክብሮት አንገቱን ደፋ። ከጥቂት ጊዜያት በኂላ ሁሉንም ለመቀበል ተመለሰ። የክፍሉ ጫፍ ላይ ያለ ወንበር ላይ ተቀመጠ፣ አብዛኛዎቹ አማኞች ወለሉ ላይ ተቀመጡ። አብዱል-ባሃ ደክሞት ስለነበረ ለአጭር ጊዜ ቆየ፣ በሴት ልጁ ጸሎት ከተዜመ በኂላ ወደ ክፍሉ ተመለሰ ።
>
> የእነዚያን ጠንካራ፣ ቅን ልብ ያላቸውን ሰዎች ፊት ማየት የእምነታቸውን ግለት፣ የዓላማቸውን ቅንነትና ጽናት የሚናገረውን ፊታቸውን ማየት የማይረሳ ትዝታ አለው። በእርግጠኛነት በእንባ ያልራሰ አንድም ሰው አልነበረም፤ አዛውንቶች እና ወጣቶች ልባቸው በደስታ በመሞላቱ ስሜታቸውን ከማሳየት መቆጠብ አልቻሉም ። አቀባበል

ካደረገላቸው በኋላ መሬት ላይ ተቀምጦ ለአጭር ጊዜ አነጋግሯቸው ከዚያ በኋላ ለማረፍ ሄደ…

በማግስቱ ጠዋት አብዱል-ባሃ በማይበገር ልፋትና ሊነገር በማይችል ሃዘን ወደ አስገነባው ወደ ተራራው የባብ መካነ መቃብር ሄደ። በቅድስት አገር ያሉ ባሃኢዎች እና መንፈሳዊ ጎብኚዎች ቀድመው ወደ መካነ-መቃብሩ በሚወስደው መንገድ ላይ ተሰብስበው ነበር። አብዱል-ባሃ የተሰበሰ ቡትን ወደ ውስጠኛው መካነ-መቃብር ክፍል በምሥራቅ በር በኩል እንዲገቡ አደረገ። እርሱ ብቻውን በምዕራብ በኩል ባለው በር ገባ።

በቀጣዩ ቀን በአካ የምሳ ግብዣ አደረገላቸው፣ ከዚያ በኋላ ወደ ባህጂ ወደ ባሃኡላህ መካነ-መቃብር ሄዱ። እርሱ ግን አብሯቸው አልነበረም። የአባቱ እንደ ቤተ-መቅደስ የሆነው አካሉ ባረፈበት ክፍል ደፍ ላይ ግንባሩን በመድፋት ብቻውን መሆን ነበረበትና ነው።

እ.ኤ.አ 1914 የመጀመሪያው ግማሽ ዓመታት ከምስራቅ እና ከምዕራብ መንፈሳዊ ጎብኚዎች አብዱል-ባሃ ዘንድ በተከታታይ ይመጡ ነበር። እንዲሁም ሁሉንም ዓይነት ሰዎች ያለማቋረጥ ይቀበል ነበር። የሶሪያ የፕሮቴስታንት ኮሌጅ ፕሬዚደንት ዶ/ር ሆዋርድ ብሊስ ፌብሯሪ 15 አብዱል-ባሃን ጎብኝቷል። ከእንግሊዝ የመጡ የቱሪስቶች ቡድን ፌብሯሪ 22 ጎብኝተውታል። ሌላ ቀን ደግሞ ጽላቶችን በጸሐፊው አማካይነት እያጻፈ ሳለ ሁለት የተጣሉ አረቦች አብዱል-ባሃን ለማየት ጠየቁ፣ አብዱል-ባሃም የሚያስቅ ታሪክ ተረከላቸው፤ የእርሱ ቤት የሰላም፣ የሳቅ፣ የደስታ መሆኑን ነገራቸው። በልባቸው ውስጥ የጠላትነት ስሜት ይዘው መውጣት እንደሌለባቸውም አሳወቃቸው። ለተወሰነ ጊዜ ትቷቸው

ሄደና የወዳጅነታቸው መገለጫም እንዲሆን ጣፋጮች እና ሁለት የፋርስ የሐር መሃረቦች ይዞላቸው መጣ፡፡ በዚያችን ቀን እግሮቻቸውን ወደ አብዱል-ባሃ ቤት የመራው አምላክ መሆኑን ተገነዘቡ፣ በደስታ እና በሳቅም ተመለሱ፡፡

ከዚያም አብዱል-ባሃ መንፈሳዊ ጎብኚዎችን እንዲመጡ የማይፈቅድበት ጊዜ መጣ፣ እ.ኤ.አ. ጁን 29 ቀን ቅድስት አገር የሚገኙትም ምዕመናን እንዲመለሱ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ አብዱል-ባሃም "ይህ የመሰናበቻ ቀን ነው፣ የመሰናበት ቀን በጣም ከባድ ነው፡፡ የአረቡ ባለቅኔ ሲናገር "ከተወዳጅ ጋር የሆንኩባቸው ቀናት በጣም ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ ሰላምታው የስንብት ነበር፡፡" በእውነት በጣም አዝኛለሁ፣ ሆኖም ግን አልሰናበታችሁም ምክንያቱም በልቦቻችን መካ ከል የተሟላ ግንኙነት፣ በነፍሶቻችንም መካከል አንድነት እና ስምምነት አለና፡፡ እርስ በእርሳችን በምንም ዓይነት አንለያይም፡፡ ይህ ቅርበት እና ሩቅነት የአካልን ዓለም ይመለከታል፡፡ በመንፈስ እና በነፍስ ዓለም ውስጥ አንድነት አለ፣ በጭራሽ አይለያይም፡፡ ልብ ህብረቱ ይሰማዋል፡፡ ዓይን ይመለከትና ያየውን ወደ ልብ ያስተላልፋል ልብም ተጽእኖ ያድርበታል፡፡ ልብ ከጓደኞች ጋር ከተጣመረ መለያየት አይኖርም፣ በተለይም ወደ አምላክ እምነት አገልግሎት ውስጥ ከገቡ…"

አብዱል-ባሃ አስቀድሞ የተናገረው የመከፋፈል አውሎ ነፋስ አውሮፓን እና መላውን ዓለም ሁሉ ሊያምስ እንደሆነ አውቆ ነበር ፡፡

በዓመቱ አጋማሽ ላይ የዶ/ር ፋሪድ ስህተተኝነት ወደ አደባባይ ወጣ የምዕራቡ ዓለም ባሃኢዎችም ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባ ነበር፡፡ ፋሪድ አብዱል-ባሃን በመቃወም ስብሰባዎች እንዲዘጋጁለት አስቀድሞ

መምጣቱን በማስታወቅ አውሮፓ ውስጥ ይጓዝ ጀመር፡፡ በለንደን ውስጥ ኪንግስዌይ አዳራሽ ተያዘ፣ ስብሰባ እንደሚደረግም አሳወጀ፡፡ ጊዜው የበጋ ወቅት ስለነበር ሌዲ ብሎምፊልድ በለንደን ከተማ ውስጥ አልነበረችም፡፡ ሆኖም የዶ/ር ላቲፉአላህ ጣልቃ ገብነት ፋሪድን እንዳይናገር አግዶታል ፡፡ አንዳንድ ባሃኢዎች በዚህ ክስተት በአስከፊ ሁኔታ ተናወጡ ጥቂቶችም ወደቁ፡፡ ማሕበረሰቡ የዳነበት ሁኔታ በቤቷ የተወሰነው አኒ ጋምብል የጥንካሬ አለት መሆኗ ተረጋገጠ፡፡ ጆርጅ ላቲመር እና ቻርለስ ሜሶን ሬሜ በአብዱል-ባሃ ትእዛዝ መሠረት ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ በመምጣትም በዚህ ወቅት ተገኝተው ነበር ፡፡

ጁላይ አጋማሽ ላይ አብዱል-ባሃ በሶሪያ የፕሮቴስታንት ኮሌጅ ውስጥ የህክምና ትምህርቱን ያጠናቀቀውን ዶ/ር ሀቢቡላህ ኩዳ ባክሽ (በኋላ ዶ/ር ሙአያድ ተብሏል) እና ተማሪ የነበረውን አዚዝሁላህ ባህዱርን በወቅቱ ሁለቱም ሐይፋ ውስጥ ስለ ነበሩ በፍጥነት ወደ አውሮፓ በመሄድ የፋሪድን እንቅስቃሴ እንዲቋቋሙ አዘዘ፡፡ አንደኛው የዓለም ጦርነት በተነሳበት ጊዜ ስቱትጋርት ውስጥ ነበሩ፡፡ አብዱል-ባሃም ወደ ሐይፋ እንዲመለሱ ጆርጅ ላቲመር እና ቻርለስ ሜሰን ሬሜይም አብሯቸው እንዲጓዙ አደረገ ሴብቴምበር 28 ቀን አሌዛንድርያ ከዚያም ኦክቶበር 5 ቀን ሐይፋ ደረሱ ፡፡

ቃል ኪዳኑን የጣሱ ሁሉ ጥረታቸው ከንቱ እንደሆነ ሁሉ የፋሪድም ጥረት ከንቱ ሆነ፡፡ የመውደቁ ዋና ምክንያት ገንዘብን የማይጠግብ ስግብግብ መሆኑ ሲሆን፣ በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ ሰበቦች ከባሃኢዎች በተለይም በአሜሪካ ከሚገኙ ሀብታም ሰዎች ሚሲስ ሐረስት እና ከሚ ሲስ ፓርሰንስ ገንዘብ ለማግኘት ሞክሮ ነበር፡፡ ለአንዳንዶች አብዱል-ባሃ ገንዘብ ከእነሱ በቀጥታ

ለመቀበል ባይፈ ልግም እንደሚያስፈልገው በሹክሹክታ ይነግራቸዋል፤ ከሌሎች ደግሞ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ሆስፒታል እንዲ ገነባ ገንዘብ ይጠይቃቸዋል። ይህ ሁሉ በአሜሪካ ውስጥ ከባድ ችግርን አስከተለ። በዚህ ምክንያት አብዱል-ባሃ ባይ ናገርም በዝምታ ተሠቃየ ፣… ላደረገለት ነገር አመስጋ ኝነቱ እጅግ አስጸያፊ ነበር፣ ምክንያቱም ከልጅነቱ ጀምሮ እንዲማርና ከዛም ደግሞ አሜሪካን አገር ዩኒቨርሲቲ እንዲገባ ያደረገው አብዱል-ባሃ ነበር ።

ከድርጊቱ እንዲታቀብ ለማድረግ ከቅድስት አገር ወደ ለንደን የተጓዘው የፋሪድ አባት ሚርዛ አሳዱላህ ተልዕኮው አለመሳካቱ ብቻ ሳይሆን በመጨረሻም ወደ እሱ ጎራ መግባቱ ነው። የእህቱ ባል ሲድኒ እስፕራግም ተቀላቀለ፤ እስፕራግ ምን ያህል ከባድ ስህተት እንደሠራ የተገነዘበው እ.ኤ.አ. 1937 ላይ ነበር። እንደገና ወደ እምነቱ እቅፍ ውስጥ ተመልሶ በመግባት ለማስተማር ወደ ደቡብ አሜሪካ ተጓዘ፣ ከዛም ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞተ። ዶ/ር ፋሪድ ግን [የእም ቢተኝነትን] ምድረ በዳ እስከ መራራ ፍፃሜው ድረስ ተጉዞ እ.ኤ.አ. 1953 ሞተ።

ጦርነት በአውሮፓ ተጀመረ፣ ቱርክ ለማዕከላዊ ኃይሎች ጀርመን እና ኦስትሪያ-ሃንጋሪ ራሷን ልትሰጥ ተቃረበች። … በኦክቶበር ወር 1914 መጨረሻ ላይ እድሏ ተወሰነ፣ ኖቬምበር የመጀመሪያ ሳምንት ታላቋ ብሪታንያ እና ፈረንሳይ በቱርክ ላይ ጦርነት አወጁ።

የቱርክ በጦርነት ውስጥ መግባት መካከለኛው ምስራቅን ወደ አዲስ ትርምስ ዳረገው፣ አብዱል-ባሃም አዲስ አደጋ ዎች ውስጥ ወደቀ።

## ምዕራፍ 11

## የጦርነቱ ዓመታት

ቱርክ ወደ ጦርነቱ በገባች በጥቂት ሳምንታት ውስጥ እንግሊዞች የባስራ ወደብን ተቆጣጠሩ፣ የግብፅን ኪዲቭ (ባለሥልጣናት) አስወገዱ፣ የሀገሪቱ የበላይ ጠባቂ መሆና ቸውን አወጁ፣ የኦቶማን ቱርክ ግዛቶችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ፖሊሲዎችን ማስፈጸም ጀመሩ።

በቅድስት አገር ሰላዮች በሁሉም ቦታ ነበሩ፣ ባለሥልጣ ናትም ጨቋኝ እየሆኑ መጡ። ፍርሃት ተሰራጨ። እንደ ወረርሽኝ ሕዝቡን የሚጨርስ ፍርሃት፣ ጦርነቱ ትንንሽና ትልልቅ ከተሞችን ከመሬት ሊያደባይ ይችላል የሚል ፍራቻን አመጣ። አንድ የጠላት ጦር መርከብ በአካ እና በሐይፋ መካከል ያሉትን የባቡር ሀዲድ ድልድዮችን በቦንብ መታ። በዚያን ጊዜ በሪድቫን የአትክልት ስፍራ አንድ ቦንብ ወድቆ ነበር ግን አልፈነዳም።

አብዱል-ባሃ የሐይፋ እና የአካ ባሃኢዎች በአካባቢያቸው ከሚገኘው ውርጅብኝ እንዲገላገሉ በማለት ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄዱ ወሰነ። ለእነሱ ጊዜያዊ መኖሪያ እንዲሆን ከአካ በስተምሥራቅ የምትገኘውን የድሩዝ መንደር የሆነችውን አቡ-ሲናን መረጠ ። አብዱል-ባሃ ግን ከአንድ አገልጋዩ ጋር በመሆን በአካ ውስጥ ቆየ፤  አልፎ አልፎ ግን ወደ አቡ-ሲና እየሄደ አንድ ወይም ሁለት ሌሊቶችን ያሳልፍ ነበር። የደሩዞቹ አለቃ ሼህ ሳሊህ ለአብዱል-ባሃ ቤተሰቦች የራሱን ቤት ሰጠ፣ እነሱም እዚያ ይኖሩ ጀመር። በመንደሩ ነዋሪዎች ቤት ውስጥ ለሌሎቹ ባሃኢዎች መስፈሪያ ቦታ ተገኘላቸው። ባሃኡላህም በእነዚህ ወዳጃዊ

ሰዎች መካከል በአንድ ወቅት ለሦስት ወራት ያህል በገሊላ ተራራማ አካባቢ ኖሮ ነበር፡፡

ዶ/ር ሙዓያድ በአቡ-ሲና አንድ የሕክምና ጣቢያ ከፈተ፡፡ የባሃኢ ማህበረሰብ አባል ያልሆኑ ሰዎችም ለህክምና ይመጡ ነበር፡፡ እኩል ትኩረት ይሰጣቸው የነበረ ሲሆን እነሱም እንደየአቅማቸው ይከፍሉ ነበር፡፡ ብዙዎቹን ግን በነፃ ያክም ነበር፡፡ ዶ/ር ሙዓያድ ቀዶ ጥገና ያከናውን የነበረ ሲሆን ሉዋ ጌትሲንገርም ታግዘው ነበር፡፡ ሌላኛው የሶሪያ ፕሮቴስታንት ኮሌጅ ምሩቅ ባዲ ቡሽሩይ ለባሃኢ ልጆች ከሕክምናው ጣቢያ ጎን ትምህርት ቤት ከፍቶ ያካሂድ ነበር፡፡ በተራራዎች ዙሪያ ያለው ይህ ገለልተኛ መንደር ውስጥ ሕይወታቸው ጥንታዊ አኗኗር ሆኖ ነበር ፡፡

ሚርዛ ፋዱሉላህ ካሃን ጃንዋሪ 19 /1915 የሺራዝ ከተማ ባሃኢዎችን ገጸ-በረከት በመያዝ ወደ ሐይፋ መጣ፡፡ የእሱ መምጣት ከውጭው ዓለም ጋር ያገናኛቸው የመጨረሻው ሆነ፡፡ ከህንድ ወደ ሐይፋ መጓዝ ስለነበረበት ጉዞው በብዙ ችግር የተሞላ ነበር፡፡ ስኬታማ መሆን በእርግጥ ድል ነው፡፡

በጦርነቱ ዓመታት ሀጂ ረመዳን ተብሎ የሚጠራው በእድሜ የገፋው አንድ አረብ ባሃኢ ሁሉንም አደጋዎች በድፍረት በመወጣት ቴህራን መድረስ ችሏል፡፡ አደገኛ ጉዞው ለአርባ አምስት ቀናት በእግር መጓዝን ያጠቃልላል፡፡ አብዱል-ባሃ በአደራ የሰጠውን ጽላት ለባሃኢዎች አስረከበ፣ ወርቅ እና ደብዳቤዎችን ይዞ ተመለሰ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ያንን የጀግንነት ተግባር ሞከረ፣ ነገር ግን ያሰበበት ቦታም አልደረሰም፣ የት እንደደረሰም በጭራሽ ሊታወቅ አልቻለም፡፡

እ.ኤ.አ. በ1915 መጀመሪያ ላይ የጀማል ፓሻ ድርጊት ተከሰተ፣ ይህ ሰው የ4ኛው ክፍለ-ጦር አዛዥ የነበረ ሲሆን ተልዕኮውም የሱዌዝን ሰርጥ በመውረር እንግሊዞችን ከግብፅ ማስወጣት ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር የሽብር ዘመን መጣ፡፡ መላው ሶሪያን ቅድስት አገር ጨምሮ በጦር ኃይሉ ሕግ ቁጥጥር ስር ወደቀ፡፡ ከ1915 እስከሚቀጥለው ዓመት ድረስ ጀማል ፓሻ የአረብ ብሔሮችን በወታደራዊ ፍርድ ቤቶቹ ለፍርድ እያቀረበ ነበር፡፡ ከመካከላቸው 34ቱ የተገደሉ ሲሆን ብዙዎች ደግሞ ከሀገር ተባርረዋል፡፡ ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ እና አጋሮቻቸው ለረጅም ጊዜ የተናቁ እና በዝምታ የተጠመዱ የነበረ ሲሆን አሁን ግን አብዱል-ባሃ ላይ ለማሴር አዲስ ዕድሎችን አገኙ፡፡ የተለያዩ አሉባልታዎችን ለማቅረብ ወደ ጀማል ፓሻ ሄዱ፡፡ ማጅ ደዲን የተባለው አንዱ ሴረኛ አብዱል-ባሃ ለህብረቱ እና ለእድገት ሂደቱ ኮሚቴ ጠላት እንደሆነ በውሸት ተናገረ፡፡ ባሃኡላህ ይጠቀምበት የነበረውን ድንኳን፣ ለጀማል ፓሻ ሰጠ፡፡ አብዱል-ባሃ ይህን ድንኳን “የታላቁ ሰላም ተምሳሌት” ይለው ነበር፡፡ ከዚያም ግራ መጋባትን ለመፍጠር ወታደራዊው መንግሥት አብዱል-ባሃን ወደ ደማስቆ ማባረሩን ወሬ አዛመቱ፡፡

ጀማል ፓሻ አካ አካባቢ በሰፈረበት ጊዜ አብዱል-ባሃን ወዲያውኑ ማየት እንዳለበት ለከንቲባው ተናገረ፡፡ አብዱል-ባሃ አህያውን እየጋለበ ወደ ወታደራዊ ጦር ሰፈር ሄደ፡፡ ጀማል ፓሻ በትህትና ከተቀበለው በኋላ የሃይማኖት ጥፋተኛ መሆኑን ነገረው፣ ቀድሞ ጊዜም በእስር እንድትቆይ የተደረገው ለዚሁ ነበር አለው፡፡ በአብዱል-ሀሚድ ዘመን ጀማል ፓሻ እራሱ የፖለቲካ ጥፋተኛ ተብሎ ይታወቅ ነበር፡፡ ስለዚህም አብዱል-ባሃ ጥፋተኝነት ሁለት ዓይነት ነው ሲል መለሰለት ሲያብራራም አንዱ

ፖለቲካዊ ሌላው ሃይማኖታዊ ነው አለው፡፡ ወደ እብሪተኛው ፓሻ በመጠቆም እስካሁን የፖለቲካ ጥፋት አድራጊው ምንም ዓይነት ጉዳት አላደረሰም፤ እናም የሃይማኖታዊው ጥፋተኛም እንዲሁ ምንም አያደርግም የሚል ተስፋ አለን አለው፡፡

ሌዲ ብሎምፊልድ በአብዱል-ባሃ እና በጀማል ፓሻ መካከል ሌላ ገጠመኝ መዝግባለች፣ ታሪኩ የተነገረው በአብዱል-ባሃ አማች በሚርዛ ጃላል ነው፡-

እ.ኤ.አ. በ1916 መጀመሪያ ላይ አንድ ቀን ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ አብዱል-ባሃ ወደ ታማኝ ጋሪ ነጂው ላከኝ፡፡ እንዲህም አለኝ “ጋሪዬን እንዲያመጣ ለኢስፋንዲይር ንገረው፣ እናም አንተ እና ኹሱሩ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ወደ ናዝሬት አብራችሁኝ ለመሄድ ዝግጁ ሁኑ፡፡” እንዳዘዘን አደረግን እናም በተጠቀሰው ሰዓት ከአብዱል-ባሃ ጋር ኹሱሩ እና እኔ በመሆን ሐይፋ ውስጥ ከሚገኘው ቤታቸው ተነስተን ሄድን፡፡ በተባረከው ፊት ላይ የድካም ምልክቶች ይታይ ስለነበር የዚያን ቀን ጤናው እጅግም አጥጋቢ እንዳልሆነ ያስታውቅ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የሶርያ እና የፍልስጤም ግንባር ዋና አዛዥ ጀማል ፓሻ ናዝሬት ስለነበር አብዱል-ባሃ ሊያገኘው ወሰነ ስለዚህም ከባድ ድካምና መዛል ቢኖርበትም ጉዞውን ጀመረ፡፡

አብዱል-ባሃ… ምሽት ሰባት ሰዓት ላይ ናዝሬት ደረሰ በጀርመን ሆቴልም አረፈ፡፡

በቀጣዩ ቀን በናዝሬት ከተማ ከሚታወቁ ሰዎች በአንዱ ቤት ውስጥ ምሳ ተጋበዘ፡፡ በዚያን ቀን ጀማል ፓሻ እና ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ የጦር መሪዎቹ ምሳ ግብዣው

ላይ ተገኙ፡፡ አብዱል-ባሃ ከሰባት ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት በምሳ ግብዣው ላይ ቆየ፡፡

በግብዣው ላይ አብዱል-ባሃ በቱርክ ቋንቋ ስለፍልስፍና እና ስለሳይንሳዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለመንፈሳዊ ትምህርቶች ይናገር ነበር፡፡ የሚናገረው ነገር በጣም ጠለቅ ያለ በመሆኑ የሚያዳምጡት ሁሉ መብላት አቆሙ፡፡

…በሐሰት ውንጀላዎች ምክንያት እጅግ ጠልቶት የነበረው ጀማል ፓሻ በመጀመሪያ ሲመጣ ለአብዱል-ባሃ ተገቢ ክብር አልሰጠውም፡፡ አሁን ግን ምሁራዊ በሆነና በጥበብ ሲናገር ከሰማ በኋላ በጣም አከበረው ጨዋነት የተሞላውም ሆነ፡፡ አብዱል-ባሃ ከምሳ ግብዣው ሊነሳ ሲል ጀማል ፓሻ እርሱን ለመርዳት ፈጥኖ ተነሳና ደገፍ እድርጎት ወደ ማረፊያው ክፍል ወሰደው በምቾት እንዲቀመጠም ረዳው፡፡

በመጨረሻም፣ ለተጨማሪ ጥያቄዎች መልስ ከሰጠ በኋላ እና በብዙ ጉዳዮች ላይ አስደናቂ ብርሃን ከፈነጠቀ በኋላ አስተናጋጁን ለመሰናበት ተነሳ፡፡ ጀማል ፓሻ ከቤት እስኪ ወጣና እስከ ደረጃዎቹ ታችኛው መዳረሻ ድረስ እስኪ ደርስ አጀበው፣ አብሮት መሄድ ይችል ነበር ነገር ግን አብዱል-ባሃ በታላቅ ደግነት አመስግኖት እንዲመለስ አሳሰበው፡፡ ጀማል ፓሻ ለማንም አክብሮት ለመስጠት ከመቀመጫው አይነሳም ነበር… አብዱል-ባሃ ከመጠን በላይ ደክሞት ስለነበረ በዚያ ምሽት በጀርመን ሆቴል በናዝሬት ቆየ፡፡

ነገር ግን ከጊዜ በኋላ የቃል-ኪዳን አፍራሾቹ የማያቋርጥ ማጭበርበር ተጽዕኖ አሳደረበት፡፡ ጀማል ፓሻም ከዘመቻው በድል ሲመለስ አብዱል-ባሃን እንደሚሰቅለው

ገለጸ፡፡ ተመልሶ ሲመጣ ግን ተሸንፎ ተዋርዶ ነበር ዛቻ ውንም ለማስፈፀም አልቻለም፡፡

በጦርነቱ የመጀመሪያ ወራቶች አብዱል-ባሃ አንድ ቀን እንደተናገረው የአመፀኞች ሴራ ባይሆን ኖሮ ከሙስሊሞች እና ከክርስቲያኖች መካከል ዋና መሪዎቻቸውን አንድ ላይ ሰብስቦ፣ ስርዓት አልበኝነትን ለመከላከል ጥረታቸውን በአንድነት እንዲያጠናክሩ ይመክራቸው ነበር፡፡ ሆኖም ግን የሴረኞቹ ድርጊቶች ይህንን ከማድረግ አገዱት፡፡

እ.ኤ.አ 1915 የመጀመሪያው ወራቶች ውስጥ እንቅስቃሴ-አልባነት እና ማግለል እየጨመረ ስለመጣ አብዱል-ባሃ በከፍተኛ ሁኔታ ወደሚፈለግበት ወደ ህንድ መሄድ እንደሚመኝ ተናግሮ ነበር፡፡ የሚሠራው ሥራ ባለመኖሩ፣ በአካላዊ ሁኔታው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረበትም ተናግሯል፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ ጎብኚዎች መምጣት ባይችሉም፣ የደብዳቤ ልውውጥ ቢቆምም፣ አብዱል-ባሃ በአካባቢው ጉዳዮች ተጠምዶ ነበር፡፡ ለባሃኢ ማህበ ረሰብ እና ለተቸገሩ ብዙዎች ምግብ በማሰባሰብ እና በማ ቅረብ ሥራ ወዲያውኑ ተጠመደ፡፡ የተሳሳተ አስተዳደር እና የኦቶማን የበላይ አለቃ ጭቆና ቀስ በቀስ አገሩቱን ወደ ረሃብ ሁኔታ ወስዷት ነበር፡፡

ምንም ያህል ዘና ያለ ወይም አድካሚ ሕይወት ቢኖረውም አብዱል-ባሃ ሁልጊዜ አስቂኝ/የሚያዝናና ሁኔታን ያገኛል ወይም የሚያዝናና ሁኔታን ያስታውሳል፡፡ ከወንበሩ አጠገብ ያለው ድመት ያስደስተዋል፣ ይህ ድመት በእውነቱ ደስተኛ፣ ግድየለሽ፣ ከፍርሃት ነፃ ነው ይላል፡፡ መን ገድ ላይ የቆመ አንድ አህያ ሲያይ በአሜሪካን አገር ውስጥ አህዮች እንዳላየ እንዲያስታውስ ያደርገዋል፡፡ ፈረንሳይ አገር ፓርክ ውስጥ ያሉ እንስሶች ለመናገር

እንደሚፈልጉ ሁሉ አትኩረው እያዩ "እንዴት ነው ከነዚህ ሰዎች ጋር የተቀራኘሁት? ማለት የፈለጉ ይመስል ነበር ይላል።… አብዱል-ባሃ እንዴት እንደሆነ ለመጠየቅ አንድ ሰው ይጽፋል፣ አብዱል-ባሃም በፈገግታ በመድፍ አፍ ፊት ተደቅኛለሁ ብሎ ይመልስለታል።

በአካ እና በሐይፋ ውስጥ ሕይወት ወደ መደበኛው ባይመለስም የጦርነቱ ትኩሳት ቀስ እያለ እየቀነሰ መጣ፣ ዓመቱ እየገፋ በሄደ ቁጥር የተረጋጋ እና ይበልጥ የሰከነ ሆነ። አብዱል-ባሃም ባሃኢዎች ወደቤታቸው መመለስ እንደሚችሉ ተሰማው። ሌሎች ምዕራባዊ ባሃኢዎች በተመለሱ ጊዜ ወደኋላ የቀረችውና አቡ-ሲናን የቆየችው ኤዲት ሳንደርሰን ጃንዋሪ 1915 ወደ አገሯ ተመለሰች። በዚያን ቀን በታላቋ ቅድስት ቅጠል ክፍል ውስጥ ለብዙ ጊዜ ተቀምጦ የነበረው የባብ እና ባሃኡላህን ፎቶግራፍ የያዘው ሣጥን በባዲ ቡሽሩይ እና በዶ/ር ሙዓያድ አማካይነት ወደ ሐይፋ ተመለሰ ።

ባሃኢዎች ወደ ሐይፋ ስለተመለሱ ሳምንታዊ ስብሰባዎች በአብዱል-ባሃ ቤት እንደገና ተጀመረ፣ "የታማኞቹ መታሰቢያዎች" (Memorials of the Faithful) የሚለው የአብ ዱል-ባሃ መጽሐፍ ቅርፅ የያዘው በዚህ ጊዜ ነበር። የመጀመሪያዎቹን ባሃኢዎች አጭር የሕይወት ታሪክ የሚተርከው ይህ መጽሐፍ፣ በአንደበተ ርቱዕነት እና ነጸብራቅ በተሞላው ሁኔታ፣ በሚያነቃቃ እና ፍሰት በተሞላው ሁኔታ፣ በእነዚህ ስብሰባዎች ጊዜ አብዱል-ባሃ ይተርካቸው ነበር። እያንዳንዳቸው፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁና ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው። ሰባ ዘጠኝ ሰዎች የተጠቀሱ ሲሆን አብዛኛዎቹ ከባሃኡላህ ጋር ወደ አካ የተሰደዱ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የኢሽቃባድ ቤተ-

መቅደስን ያስገነቡት ሐጂ ሚርዛ ሙሐመድ-ታቂ እና ወንድማቸው ሐጂ ሚርዛ ሙሐመድ-አሊ ሲሆኑ፣ ታሂሬ፣ ምንም እንኳን የባብ ግልጸት ዘመን ብርሃን ብትሆንም በዚያ እንደጋላክሲ በሆነው ጽሑፍ ውስጥ ተካታትለች። እነዚህ የአብዱል-ባሃ ንግግሮች እ.ኤ.አ. በ1924 "የታማኞቹ መታሰቢያዎች" በሚል ርዕስ በመጽሐፍ መልኩ በሐይፋ ታተመ።

የጦርነቱ ዓመታት የኦቶማን ባለሥልጣናት ውድቀትን፣ የተሳሳተ አስተዳደርንና የመዳከም ሁኔታን አመጣ፤ አንበጣዎች ያስከተሉት ውድመት ደግሞ ተጨመረ፣ ስለሆነም እጥረቶች እና ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆነ። አብዱል-ባሃም መከራን ለመታደግ ተነሳ። በዮርዳኖስ ሸለቆ እና ባሻገሩ፣ በሳምራ እና በአዳዊያህ እንዲሁም በገሊላ ባሕር (ቲቤሪስ ሐይቅ) ዳርቻ አብዱል-ባሃ ለም መሬት ነበረው። በተጨማሪም የባሃኡላህ ታማኝ ወንድም የሚርዛ ሙሐመድ-ቁሊ ልጆች አባታቸው በተቀበረበት በገሊላ ባሕር ሰሜናዊ ዳርቻ ላይ መሬት ነበራቸው።

አብዱል-ባሃ ከእነዚህ ቦታዎች ወደ አካ የሚልከው ስንዴ በጣም ለሚያምናት ሳኪኒህ ሱልጣን ለምትባል ሴት እንዲሰጥ ያደርግ ነበር። ለእሷ በተጻፈላት ጽላት ውስጥ አብዱል-ባሃ በጣም ስለሚሞቅና አተነፋፈሱ ላይ ተጽዕኖ ስላሳደረ ወደ ቲቤሪስ መሄድ እንደነበረበት ይገልጽና እርሱ በቲቤሪስ ውስጥ እፎይታ ካገኘ፣ ስንዴው ሁሉ ተሰብስቦ እስከሚያልቅ እንደሚቆይ፣ አለበለዚያ ግን ወደ አካና ሐይፋ እንደሚመለስ ይገልጻል። በተጨማሪም በተላከው ዝርዝር መሠረት እንዲሰራጭ ለጊዜው የተወሰነ ስንዴ መላኩንና ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀርም ዋጋዎች

ከሦስት እጥፍ በላይ እንደጨመሩና የትራንስፖርት ዋጋም በሁለትና በሦስት እጥፍ ማደጉን ይገልጻል፡፡ ለማጓጓዝ የግመሎች እጥረት እንደነበረ ተጠቁሞ፣ ግመሎች ሲገኙ ብዙ ስንዴ እንደሚላክ ይጠቅሳል፡፡

የስንዴ ስርጭትን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ለሳኪኒ ሱልጣን የተላለፉት መልዕክቶች የስምና የመጠኖችን ዝርዝር ያካተቱ ናቸው ፡፡

| | |
|---|---|
| ለጎረቤት ሴት ልጆች | 25ራትል(የመጠን መለኪያ) |
| ለአህመድ ኤፌንዲ ልጅ አብዱረህማን | 30 |
| ለሃነስ ሚስት | 15 |
| ለወፍራሚ ሴትዩ | 25 |
| ለራፊህ | 25 |
| ድምር | 120 |

ምንም እንኳን በጦርነቱ ጊዜም ሆነ በኋላ ለአብዱል-ባሃ እንግዶች የተመረጡ ምግቦች ይሰጥ የነበረ ቢሆንም እሱ ራሱ ምግብ የሚያበስልባቸው ጊዜያትም ነበሩ፣ እሱ የሚበላው ምግብ ግን በጣም ቀለል ያለ ነው፡፡ ትንሽ ሥጋና ትንሽ ፍራፍሬ ሲሆን፣ የበለጠ የሚወደው ግን ወተት፣ ቺዝና እንደሚንት፣ ታርጎንና ቤዝል ያሉ ቅጠሎችን ነው፡፡

የጦርነት ውድመቶች እየጨመሩ መጡ፡፡ የእንግሊዝ-ህንድ ጦር ወደ ሜሶፖታሚያ እየገሰገሰ መጣ፣ እ.ኤ.አ. 1916 ያፈገፈገ ቢሆንም እንደገና ቦታዎችን ይዞ ማርች 1917 ባግዳድን ተቆጣጠረ፡፡ ከአንድ ወር በኋላ አሜሪካ በጀርመን ላይ ጦርነት አወጀች፡፡ የቅድስት ሀገር ተገልሎ መቆየት ሊጠናቀቅ ተቃረበ፡፡

ሾጊ ኤፌንዲ በእነዚያ ቀናት ስለ አብዱል-ባሃ ሁኔታ ሲናገር፦

> እሱ አቅርቧቸው ለነበሩ ጥሪዎች የሰው ዘር ለመቀበል ሳይችል በመቅረቱ ወይንም እሱ ሰጥቷቸው የነበሩት ማስጠንቀቂያዎች ለማጤን ባለመብቃቱ ምክ ንያት በተከተሉት የሰው ዘር ጭፍጨፋ ትዕይንቶች የእርሱ ነፍስ በሐዘን ተውጣ ነበር። በእውነቱ እሱ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ የአባቱን እምነት ግልጋሎት በጀግንነት ተወጥቷል፣ የፈተናዎችና የውጣ ውረዶች ሐዘን ሸክም ተደራርቦበታል።

የመለኮታዊ እቅድ ጽላቶች በቁጥር አሥራ አራት ሲሆኑ በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ተገልጸዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ ስምንቱ እ.ኤ.አ በ1916 ሲሆኑ ሌሎቹ ስድስቱ ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1917 ነው። ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው ነው፦

1. እሁድ ጠዋት ማርች 26 ቀን 1916 ባህጂ በሚገኘው ቤት በአብዱል-ባሃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ ዘጠኝ ለሆኑ በአሜሪካ የሰሜን ምስራቅ ግዛት ውስጥ ያሉ ባሃኢዎችን የሚመለከት ሲሆን እነሱም ሜይን፣ ኒው ሃምፕሻየር፣ ሮድ አይላንድ፣ ኮነቲከት፣ ቨርሞንት፣ ፔንሲልቬንያ፣ ማሳቹሴትስ፣ ኒው ጀርሲ እና ኒው ዮርክ ናቸው ።

2. ከባሃኡላህ መካነ-መቃበር አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ሰኞ ጠዋት ማርች 27 ቀን 1916 ተገለጸ፣ በአሜሪካ አሥራ ስድስት የደቡብ ግዛት ውስጥ ያሉ ባሃኢዎችን የሚመለከት ሲሆን እነሱም ደላዌር፣ ሜሪላንድ፣ ቨርጂኒያ፣ ዌስት ቨርጂኒያ፣ ኖርዝ ካሮላይና፣

ሳውዝ ካሮላ ይና፣ ጆርጂያ፣ ፍሎሪዳ፣ አላባማ፣ ሚሲሲፒ፣ ቴኔሲ፣ ኬንታኪ፣ ሉዊዚያና፣ አርካንሳስ፣ ኦክላሆማ እና ቴክሳስ ናቸው።

3. እሮብ ጠዋት ማርች 29 ቀን 1916 የተገለጸው ባህጂ በሚገኘው ቤት ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ በአሥራ ሁለት የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ የሚገኙ ባሃኢዎች የሚመለከት ሲሆን እነሱም ሚሺጋን፣ ዊስኮንሲን፣ ኢሊኖይስ፣ ኢንዲያና፣ ኦሃዮ፣ ሚኔሶታ፣ አይዋ፣ ሚዙሪ፣ ሰሜን ዳኮታ፣ ደቡብ ዳኮታ፣ ነብራስካ እና ካንሳስ ናቸው ።

4. ቅዳሜ ጠዋት ኤፕሪል 1 ቀን 1916 ባህጂ በሚገኘው ቤት በአብዱል-ባሃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ ለአሥራ አንድ በምዕራባዊ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ የሚገኙ ባሃኢዎችን የሚመለከት ሲሆን እነሱም ኒው ሜክሲኮ፣ ኮሎራዶ፣ አሪዞና፣ ኔቫዳ፣ ዩታ፣ ካሊፎርኒያ፣ ዋዮሚንግ፣ ሞንታና፣ አይዳሆ፣ ኦሪገን እና ዋሽንግተን ናቸው።

5. ከባሃኡላህ መካነ-መቃበር አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ሰኞ ጠዋት ኤፕሪል 5 ቀን 1916 ተገለጸ፣ የሚመለከተውም ካናዳ፣ ኒውፋውንድላንድ፣ ልዑል ኤድዋርድ ደሴት፣ ኖቫስኮሲያ፣ ኒው ብሩንስዊክ፣ ኩቤክ፣ ማኒቶባ፣ አልቤርታ፣ ኦንታሪዮ ፣ ሳስቼቼዋን፣ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ፣ ዩኮን፣ ማኬንዚ፣ ኡንቫቫ፣ ኬዋቲን፣ ፍራንክሊን ደሴቶች እና ግሪንላንድ ውስጥ የሚገኙ ባሃኢዎችን ነው።

6. ከባሃኡላህ መካነ-መቃበር አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ቅዳሜ ጠዋት ኤፕሪል 8 ቀን 1916 ተገለጸ፣ የሚመለከተውም የአሜሪካ እና የካናዳ ባሃኢዎችን ነው።

7. ማክሰኞ ጠዋት ኤፕሪል 11 ቀን 1916 ባህጂ በሚገኘው ቤት በአብዱል-ባሃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም የአሜሪካ እና የካናዳ ባሃኢዎችን ነው፡፡

8. እሮብ ጠዋት ኤፕሪል 19 ቀን 1916 ባህጂ በሚገኘው ቤት በአብዱል-ባሃ ክፍል ውስጥ፣ ሐሙስ ጠዋት ኤፕሪል 20 ባህጂ ባለው የመንፈሳዊ ጎብኚዎች ማረፊያ ክፍል ውስጥ፣ ቅዳሜ ጠዋት ኤፕሪል 22 ደግሞ ከባሃኡላህ መካነ-መቃብር አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም የአሜሪካ እና የካናዳ ባሃኢዎችን ነው፡፡

9. ዓርብ ጠዋት ፌብሯሪ 2 ቀን 1917 ሐይፋ በአብዱል-ባሃ ቤት እስማኢል አቃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም ዘጠኙን የሰሜን ምስራቅ የአሜሪካንን ግዛቶች ውስጥ ያሉ ባሃኢዎችን ነው፡፡

10 ቅዳሜ ጠዋት፣ ፌብሯሪ 3 ቀን 1917 ሐይፋ በአብዱል-ባሃ ቤት እዚያው እስማኢል አቃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ አሥራ ስድስቱን የደቡባዊ አሜሪካ ግዛቶች ባሃኢዎችን የሚመለከት ነው፡፡

11. ሐሙስ ፌብሯሪ 8 ቀን 1917 አካ በሚገኘው አቡድ በሚባለው ቤት የባሃኡላህ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም አሥራ ሁለቱን የአሜሪካ ግዛቶች ባሃኢዎችን ነው፡፡

12. ሐሙስ ፌብሯሪ 15 ቀን 1917 ማታ ላይ አካ በሚገኘው አቡድ በሚባለው ቤት የባሃኡላህ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም አሥራ አንዱን ምዕራባዊ የአሜሪካ ግዛቶች ባሃኢዎችን ነው፡፡

13. እሮብ ጠዋት ፌብሯሪ 21 ቀን 1917 አካ በሚገኘው አቡድ በሚባለው ቤት የባሃኡላህ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የሚመለከተውም የካናዳ ባሃኢዎችን ነው፡፡

14 ቅዳሜ ጠዋት፣ ማርች8 ቀን 1917 ሐይፋ በአብዱል-ባሃ ቤት እስማኢል አቃ ክፍል ውስጥ ተገለጸ፣ የአሜሪካ እና የካናዳ ባሃኢዎችን የሚመለከት ነው፡፡

በአጠቃላይ አብዱል-ባሃ በእነዚህ ጽላቶች ውስጥ የባሃኡላህ መልዕክት ሊደርስባቸው የሚገባ 120 ያህል ግዛቶችን እና ደሴቶችን በስም ጠቅሷል፡፡ ይህን በሚያደርግበት ወቅት ባሃኢዎች በ35 አገራት ውስጥ ብቻ ነበሩ፡፡ ከዓለም ሁሉ 'በስርዓት እና በጋለ ስሜት' 'የሰው ልጅ አንድነትን ለማወጅ' አፋጣኝ ምላሽ ከልብ ከሚያፈቅሩትና ከጽኑዎች መጣ፣ ከዚህ በፊት ግን መጀመሪያ ለጋራ የማስተማር ሂደቱ አውታር የሚሆነው የአስተዳደር ሥርዓቱ መጎልበት ነበረበት፤ አብዱል-ባሃ ካለፈ በኂላ በእምነቱ ሞግዚት በተጀመረው የአሥራ ስድስት ዓመታት ታላቅ ሥራ አማካይነት እ.ኤ.አ. በ1937 የመለኮታዊ እቅድ ጽላቶችን ለመፈፀም የመጀመሪያው ደረጃ በአሜሪካ የባሃኢ ማህበረሰብ የሰባት አመት እቅድ ጊዜ ተመርቆ ሊጀመር ቻለ፡፡

እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 9 ቀን 1917 ጄኔራል አለንቢ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡ በቅድስት ምድር የኦቶማን አገዛዝ ቀናት የተቆጠሩ መሆናቸው አሁን የተረጋገጠ ሆነ፡፡ የአብዱል-ባሃ ሕይወት ግን አሁንም አደጋ ላይ ነበር፡፡ ያንን አደጋ ለማስወገድ የረዱ አካላት ሲናገሩ፣ በቀዳሚነት ሌዲ ብሎምፊልድ፡-

> እ.ኤ.አ. በ1918 የፀደይ ወቅት በስልክ መልዕክት ምክንያት ተደናገጥኩ እና በጣም ተረበሽኩ መልዕክቱም:- 'አብዱል-ባሃ በከባድ አደጋ ውስጥ ነው። አፋጣኝ እርምጃ ውሰጂ' የሚል ነበር። መልዕክቱ የመጣው ከባለሥልጣን ምንጭ ነበር። አብዱል-ባሃን ለማዳን የሚጠፋ ጊዜ አልነበረም ሊገኝ የሚችል ኃይል ሁሉ መጠቀም ነበረብን።
>
> ወዲያውኑ ወደ ተከበሩ ላሚንግተን (የእንግሊዝ ፖለቲከኛ እና የቅኝ ገዥ አስተዳዳሪ) ሄድኩ። ለአብዱል-ባሃ ያለው ርህራሄ የተሞላው አክብሮት፣ ስለተወሳሰቡ ችግሮች ያለው ግንዛቤ እና አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድ አስፈላጊ ከሆነም ያለው ተሰሚነት በዋጋ የማይተመን ነበር።

ለእውነተኛ ሰላም አስፈላጊነት እና ለብዙ ሺህ ሰዎች መንፈሳዊ ደህንነት የአብዱል-ባሃ አቋምን በተመለከተ ለማስረዳት ወዲያውኑ ለውጪ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ደብዳቤ ተጻፈ። በተከበሩ ላሚንግተን ተጽዕኖ እና በአፋጣኝ እርዳታው አሳሳቢ ዜናውን የያዘው ደብዳቤው በአንድ ጊዜ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ጸሐፊ የነበሩት የተከበሩ ባልፎር እጅ ገባ።

በዚያው ምሽት ይህ መመሪያ በቴሌግራም ለጄኔራል አሌንቢ ተላከ፡- “የእንግሊዝ ወታደሮች ሀይፋ ሲገቡ አስፈላጊውን ጥበቃ እና እንክብካቤ ለአብዱል-ባሃ፣ ለቤተሰቡ እና ለወዳጆቹ ይደረግ።”

በተከበሩ ላሚንግተን፣ በተከበሩ ባልፎር እና በሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት ባሉ ባልደረቦቻቸው አማካይነት እና በቱርክ

በሚገኘው በሻለቃ ቲዮዶር-ፖል ታማኝነት፣ ቅልጥፍና እና ፈጣን ተገንዛቢነት፣ አሳሳቢው አደጋ ተቀለበሰ፡፡

ቱርኮች በአብዱል-ባሃ ጠላቶች በጣም በመገፋፋታቸው የተነሳ እርሱን እና መላ ቤተሰቡን በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ለመስቀል ዝተው ነበር፡፡

ጄኔራል አሌንቢ ሐይፋን ሲቆጣጠር፣... ሁሉም ሰው እንዲደነቅ ያደረገውን የኬብል ቴሌግራም ወደ ለንደን ላከ፣ በተለይ ደግሞ በዓለም ዙሪያ ያሉ ባሃኢዎች ልብ ሁሉን ቻይ ለሆነው ጠባቂ ባቀረቡት በጥልቅ ምስጋና ተሞላ፡፡

ጄኔራል አሌንቢ የላከው መልዕክት እንደሚከተለው ነበር “ዛሬ ፍልስጤምን ተቆጣጥረናል፡፡ አብዱል-ባሃ ደህና መሆኑን ለዓለም አሳውቁ፡፡”

ሻለቃ ቲዮዶር-ፖል እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> ስለአብዱል-ባሃ፣ ስለቤተሰቦቹ እና ስለተከታዮቹ ደህንነት ከፍተኛ ጭንቀት የያዘኝ እ.ኤ.አ. በ 1918 የፀደይ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ ዲሴምበር ወር 1917 ኢየሩሳሌም ላይ ጥቃት በሚደረግበት ወቅት ከግዳጅ ወጣሁ፣ መደበኛ አገልግሎቴ ለጊዜው ተቋረጠና ለደህንነት ሥራ መጀመሪያ በካይሮ በኋላ ሉድ፣ ጃፋ እና እየሩሳሌም ተዛወርኩ ፡፡
>
> በጃፋ እና አካባቢው ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በዚያን ጊዜ ወደ ሐይፋ እና ወደ ሰሜን ለመግዝ መዘጋጀት ጀመርን፡፡ በበርካታ ምክንያቶች፣ የሰዎች እና የጦር መሣሪያዎችን እጥረትን ጨምሮ፣ የእንግሊዝ ጦር ግስጋሴ እስከ 1918 ክረምት ድረስ ዘገየ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አብዱል-ባሃ ላይ ሊመጣ ስለሚችለው አደጋ የሚደርሰኝ ዜና በጣም አስደንጋጭ ሆነ፡፡ የደህንነት አገልግሎት ተግባራት ተጠያቂ ከሆኑት መካ ከል በጉዳዩ ላይ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማነሳሳት ሞከ ርኩ፡፡… እኔም ጉዳዩን ለራሴ አለቃ ለጄኔራል ሰር አርተር ሞኒይ አቀረብኩ፡፡

በዚህ ጊዜ በለንደን ውስጥ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነቶቹ ጠንካራ ከሆነ የጦር መኮንን ጋር እንድገናኝ ሆነ፡፡ እርሱ ከጨዋነቱ እና ካለው ፍላጎት የተነሳ ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ቢሮ አስቸኳይ መልዕክት እንዲላክ ተደረገ፡፡

በእንግሊዝ ከሚገኘው ከባሃኢ እምነት ጋር ግንኙነት ባላቸው ወዳጆች በኩል ለንደን ውስጥ ወደ ባለስልጣኖች የሚያቀርብ ገለልተኛ መንገድ ተገኘ፡፡

በእነዚህ ዘዴዎች አማካይነት ክቡር ባልፎር፣ ክቡር ኩርዞን እና ሌሎችም የካቢኔ አባላት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ሐይፋ ውስጥ ስላለው ወሳኝ ሁኔታ ተማክረዋል፡፡ የክቡር ላሚንግተን ተጽዕኖ በዚህ ወቅት ልዩ ድጋፍ አድርጓል፡፡ የእነዚህ የተለያዩ ተግባራት ጅምር ፍሬ አፍርቶ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ የእንግሊዝ ጦር ሃይፋን እንደያዘ ወዲያውኑ የአብዱል-ባሃ እና የቤተሰቦቹን ደህንነት እንዲጠብቅ ለጄኔራል አሌንቢ ቴሌግራም ላከ፡፡

በሉድ ወደሚገኘው የጦር ሠራዊት ዋና መሥሪያ ቤት የሚሄደው ይህ መልዕክት ካይሮ ውስጥ በእኔ በኩል አለፈ፣ … እና አስቸኳይ የደህንነት መረጃ እንዲቀረብ ተጠየቀ፡፡ በጊዜው ካይሮ ውስጥ ሳቮ ሆቴል ወደሚገኘው

የስለላ ዋና መስሪያ ቤት ይህ መረጃ ተጠየቀ፣ በመጨረሻም እርምጃ እንድወስድ ለእኔ ተላለፈ። በዚህ ምክንያት ጄኔራል አሌንቢ ስለ አብዱል-ባሃ ሙሉ ዝርዝር መረጃዎች ቀረበለት…

አለንቢ በአንድ ጊዜ ለሐይፋ ግንባር ለጠቅላይ አዛዡ መኮንን ወዲያውኑ ትእዛዝ አስተላለፈ። ስለሆነም አንድ የእንግሊዝ ወታደር በአብዱል-ባሃ ቤት ዙሪያ ለጥበቃ መደበ፣ ተጨማሪ ጥበቃ በቤተሰቡ እና በተከታዮቹ ዘንድ እንዲመደብ አደረገ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጦርነቱ የትርምስ ሁኔታ ውስጥ አብዱል-ባሃን በቀርሜሎስ ተራራ ቤቱ መኀብኘት የሰላምና የመታደስ ስሜትን የማግኘት አስደናቂ ተሞክሮ ነበር።

መላው የቁሳዊ ዓለም መሠረቶች በተናጋበት በዚያ ጊዜ ግርማ ሞገስ ተሞልቶ፣ በአትክልት ስፍራው ውስጥ ወደ ላይ እና ወደ ታች እየተንጎራደደ ስለዘላለማዊ እውነታዎች የነገረኝን አስታውሳለሁ። የመለኮታዊ ኃይል መንፈስ በእርሱ አማካይነት ይንጸባርቃል፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት ታላላቅ ነቢያት□ በጦርነት በተጎዳው ዓለም ውስጥ ይሰጡት የነበረውን ዓይነት ስሜት ለሰው ዘር አነቃቂ እና መንፈሳዊ መመሪያ ይሰጥ ነበር።

ከሐይፋ መያዝ ጋር ተያይዞ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተከሰቱ አንድ ወይም ሁለት ክስተቶችን መዘገቡ አስፈላጊ ነው። ከደቡብ በኩል የእንግሊዝ ጦር በገሰገሰበት ወቅት የመድፈኛው ክፍለ-ጦር ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ደቡብ ምስራቅ  ከፍታ ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር፣ ዓላማው በቀርሜሎስ ተራራ ረዥም ርቀት ላይ ሐይፋን

መምታት ነበር፡፡ በሰሜናዊው የቀርሜሎስ ተራራ ላይ የሚኖሩ ባሃኢዎች አንዳንዶቹ እየተረበሹ፣ ወደ አብዱል-ባሃ መኖሪያ ቤት በመሄድ ሊከሰት የሚችለውን አሳዛኝ ሁኔታ በተመለከተ ፍርሃታቸውን ገለጹ፡፡ የዚህ ትዕይንት የዓይን እማኝ የሆነው እንደነገረኝ፣ አብዱል-ባሃ የተጨነቁ ተከታዮቹን በማረጋጋት ፀሎት እንዲያደርጉ ጠራቸው፡፡ ከዚያ ሁሉም ደህና እንደሚሆኑና የእንግሊዝ መድፍ በሃይፋ እና በአካባቢው ላይ ሞት ወይም ጉዳት እንደማያደርስ ነገራቸው፡፡

በታሪክ እደተመዘገበው፣ የተጠቀሰው የመስክ መድፍ ኢላማውን የመምታት ግምቱ ትክክለኛ አልነበረም፣ የተተኮሰው መድፍ ከተማዋ ላይ ምንም ጉዳት ሳያደርስ ከማ ለፉ ባሻገር ወደ አካ የባህር ወሽመጥ ላይ ወድቋል፡፡

ምንም እንኳን እኔ እራሴ ሙሉ ለሙሉ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ባልችልም፣ በእነዚያ ውጥንቅጥ ጊዜያት ሌላው መጠቀስ ያለበት ክስተት፣ ሐይፋ ከመያዙ በፊት አብዱል-ባሃ አንድ ቀን በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ስለ እንግሊዝ ዘመቻ እየተወያየ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ተስፋ ከሚደረገው በተቃራኒ ስለሚሆነው ሁኔታ ሲናገር ሐይፋ እና አካባቢው የአካን ከተማ ጨምሮ ያለ ምንም ደም መፋሰስ ይያዛሉ አለ፡፡ ይህ ትንበያ እውነተኝነቱም ተረጋገጠ፡፡ በተጨማሪም ቱርኮች ለሁለት ላልታጠቁ የእንግሊዝ ወታደሮች አካን በምርኮ እንደሚሰጡ ገልጿል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለመሰብሰብ የቻልኩት የመረጃ ውጤት የሚከተለው ነው፡-

“ወታደሮቻችን ወደ ሐይፋ መግባታቸውን ተከትሎ፣ የጦር ግንባሩ ወደ አካ የባህር ወሽመጥ በኩል በግማሽ አቅጣጫ ገፍቶ ነበር፡፡ ከራሱ ከአካ አራት ማይሎች ርቀት

ላይ በሚገኘው የባሕር ወሽመጥ አሸዋማ ሥፍራ ላይ የመከላ ከያ ሠራዊቱ ተመድ ቧል፡፡ አካ በምሽግና በግምብ የታጠረች ከተማ እንደ መሆኗ በቱርክ ወታደሮች ተሞልታለች ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ ማለዳ ላይ መንገድ የጠፋቸው ሁለት የእንግሊዝ ጦር መኮንኖች በአካ በሮች ላይ ተገኙ፡፡ እነሱም ከተማው በእንግሊዝ ጦር የተያዘች መስሏቸው ነበር፡፡ የከተማው ከንቲባ የእንግሊዝን ወታደሮችን ከበሩ ውጭ ሲያይ ወደእነሱ በመምጣት እጅ መስጠታቸውን ለማሳወቅ የከተማውን ቁልፍ ሰጧቸው!" ሴፕቴምበር 23 ቀን የእንግሊዝ የጦር ኃይል በባህር ዳርቻው መንገድ በኩል በመምጣት በቀርሜሎስ ተራራ በኩል ዞረው ሐይፋ ከተማ ገቡ፡፡ ከንቲባው እና መኳንንቱም እጅ ሰጡ፡፡ የእንግሊዙ አዛዥ መኮንን ለሐይፋ ከንቲባ ያቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ "አብዱል-ባሃ በከተማ ውስጥ አለ ወይ? ደህና ነው?" ነበር፡፡ አብዱል-ባሃም በቤቱ በረንዳ ላይ ተረጋግቶና ሳይረበሽ ተቀምጦ ነበር፡፡ ባሃኢዎች በዙሪያው ነበሩ፣ በውጥረት ውስጥ ሆነው ስለሁኔታው ዜና እየተጠባበቁ ነበር፡፡ የሕንድ የጦር ቡድን በፍጥነት ከቤቱ በሮች ደረሱ፡፡ በቀጣዩ ቀን ምሽት የኢየሩሳሌም ገዥ አክብሮቱን በአካል ለመግለጽ አብዱል-ባሃ ቤት ተገኝቷል፡፡ ሌ/ኮሎኔል (በኋላ የክቡርነት ማዕረግ ያገኘው) ሮናልድ ስቶርስ ስለአብዱል-ባሃ እንግዳ አልነበረም፡፡ አብዱል-ባሃን በአካ ከተማ ቅጥር ውስጥ ታስሮ በነበረበት ጊዜ ያውቀው ነበር፡፡ በማግስቱ ጠዋት ሴፕቴምበር 25 ቀን ወደ እየሩሳሌም ከመመለሱ በፊት እንደገና ጎብኝቶታል ፡፡

# ምዕራፍ 12

## የአገልግሎቱ የመጨረሻ ዓመታት

የጦርነቱ ሁኔታ ጥቂት ተጨማሪ ሳምንቶች የቀሩት የነበረ ቢሆንም የቅድስት ሀገር ከሌላው ዓለም መገለል ግን አብቅቶ ነበር። ከቅድስት ምድር ውጭ ስላሉ ባሃኢ ዎች ከጦርነት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጃ የተገኘው ሻለቃ ቲዮዶር-ፖል ወደ ሐይፋ ሲመጣ ነበር። እ.ኤ.አ ኖቬምበር 19ቀን 1918 አካ ከተማ ውስጥ በአቡድ ቤት አብዱል-ባሃን አግኝቷል። እንዲህ ሲልም ጽፏል፡-

> ….አብዱል-ባሃ በታዋቂው በዚያ ብሩህ ፈገግታውና ደስታ ተሞልቶ "እንኳን ደህና መጣህ" በማለት ሊቀበለኝ የቤቱ ደረጃ ላይ ቆሞ ነበር። አብዱል-ባሃ ለሰባ አራት ረጅም ዓመታት በአሰቃቂ ሁኔታ እና በችግር ውስጥ ኖሯል፣ ግን የደስታ ብሩህ ተስፋ ውን፣ መንፈሳዊ ግንዛቤውን እና የቀልድ ስሜቱን የሚነጥቀው ምንም ነገር አልነበረም።
>
> ከሰባት ዓመት በፊት ካየሁት አሁን በመጠኑ አርጅቷል፣ በጣም አድካሚ ከሆነው የአሜሪካ ጉዞ በኋላ በእንግሊዝ ከነበረው ሁኔታ አሁን የበለጠ ጠንክሯል። ድምፁ እንደበፊቱ ሁሉ ጠንካራ ነው፣ አረማመዱም የማይነቃነቅ ፣ ጸጉሩ እና ጺሙ ከበፊቱ የበለጠ ብርማ-ነጭ ሆነዋል።
>
> እሱ አሁንም። በአካ እስር ቤት ውስጥ ጥቂት ሳምንታትን በተደጋጋሚ ያሳልፋል …
>
> ከምሳ በኋላ ከከተማው ሁለት ማይሎች ርቆ ወደሚገኘው የባሃኡላህ መካነ-መቃብር የአትክልት

ስፍራ ወሰደኝ። ጎንበስ ብሎ እየጸለየ በፍፁም ዝምታ ወደ መቃብሩ ቀረበ ነጭ ጥምጣሙ እና የሚያምር ግራጫ ካባው አስደናቂ የተከበረ ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል።

ወደ መቃብሩ ደጃፍ ሲደርስ በረጅሙ ሰገደ፣ ከዚያም ወደ ውስጠኛው ክፍል የሚወስዱትን ደረጃዎች ሳማቸው። ግርማ የተመላ ትህትናውን ለመግለጽ የሚከብድ ድርጊት ነበር ።

….ከዚያ በኋላ ለወታደራዊ ገዥው አክብሮቴን ለመስጠት ወደ ከተማ ሄድኩ።

….ወደ ወህኒ ቤት ተመለስኩና ከአብዱል-ባሃ ጋር ሻይ በመጠጣት አመሸሁ፣ ስለአዲሱ አስተዳደር በተመለከተ ለሚጠይቀኝ ጥያቄዎች መልስ እሰጥም ነበር።

ከአብዱል-ባሃ ቀጥሎ ባለው ክፍልም ውስጥ ተኛሁ፣ ክፍሉ እንደሰገነት ያለ ሲሆን ወለሉ ድንጋይ ነበር ምንም የቤት እቃም የለውም። አብዱል-ባሃ አሁንም ቢሆን ሁሉንም ገንዘቡን ይሰጣል፣ እሱ ራሱ ግን የድህነት ሕይወት ይኖራል።

ከቁርስ በፊት ቤቱ የጠዋት በረከት ለመቀበል በመጡ አማኞች ተሞላ።

ለአብዱል-ባሃ ከሁሉም የዓለም ክፍሎች ደብዳቤ አምጥቼ ነበር፣ ስመለስ እንድወስዳቸው ጠዋቱን ሙሉ ለእነዚህ ደብዳቤዎች መልስ ሲያጽፍ ቆየ። የፋርስ የግመል ፀጉር ካባ ሰጠሁት እጅግም ደስ

አሰኘው፣ ክረምት ስለነበር ሁሉንም ካባዎቹን ሰጥቶ ነበር፣ ይሄን የሰጠሁትን ክረምቱን እንዲለብሰው ቃል አስገባሁት፣ ቃሉን እንደሚጠብቅ አምናለሁ።

በምሳ ሰዓት ላይ ሌላ ረዥም ውይይት አደረግን፣ ከዚያም የመሰናበቻና የአብዱል-ባሃን ምርቃት የመቀበል ሰዓት ደረሰ። በግብፅ፣ በአውሮፓ፣ በእንግሊዝ እና በአሜሪካ ላሉ ወዳጆቹ በሙሉ በእኔ በኩል ሰላምታ ላከ!

ወደ ሐይፋ በተመለስኩበት ወቅት ስጓዝ፣ በሚያስጠላው የአካ ጎዳና ላይ ለሰላም ለሚደረገው ክበረ-በዓል ላይ ለመገኘት ከዘራውን ይዞ መንገዱን ሲረማመድ በጨለቅታ አየሁት። በግርማ ሞገሱ ጎልቶ ይታይ ነበር…

ሾጊ ኤፌንዲ በተመሳሳይ ጊዜ ለንደን ላለው ለዶ/ር ሉቱፉ ኡላህ ጽፋዋል ፡-

ካፒቴን [በኋላ ሜጀር] ቲዮዶር-ፖል ባልተጠበቀ ሁኔታ ከግብፅ በመምጣት እኛን አስገርሞናል አስደቶናልም።… በዛ ወቅት ተወዳጁ አብዱል-ባሃም በየቀኑ የአባቱን መቃብር እየጎበኘና ለተባረከው ፍጹምነት ለበጎነቱ፣ ለእንክብካቤውና ለጥበቃው ምስጋናውን በማቅረብ በአካ ለአንድ ወር ተኩል ያህል ቆይቷል።

በአሜሪካን ቤይሩት ዩኒቨርስቲ የስነ-ሳይንስ ትምህርቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ ተወዳጃችንን ለማገልገል በመቻሌ በጣም ደስ ብሎኛል፣ ልዩ ዕድልም አግኝቻለሁ። …ስለአንተ እና ለእምነቱ ስለምትሰጠው አገልግሎት ለመንገር በጣም

ጓጉቻለሁ፣ ለተወዳጃችን ስነግረውም ያስደስተዋል፣ የምስራች ይሆነዋል እናም ያበረታዋል…

እ.ኤ.አ. በ1920 ጸደይ ወቅት ወደ እንግሊዝ ኦክስፎርድ ኮሌጅ ትምህርቱን ለመቀጠል እስኪሄድ ድረስ ሾጊ ኤፌንዲ የአብዱል-ባሃ ጸሐፊ በመሆን የሚገልጻቸውን ጽላቶች ለምዕራቡ ዓለም ባሃኢዎች ተርጉሟል።

ላውራ እና ሂፖላይት ድርፌስ ባርኒ በጦርነቱ መደምደሚያ ማግስት ከምዕራቡ ዓለም የመጡ የመጀመሪያዎቹ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ነበሩ። ሻለቃ ቲዮዶር-ፖል በካይሮ በኩል በሕጋዊ መንገድ እንዲሄዱ ጉዞአቸውን አመቻቸ።

ቅድስት ሀገር ከኦቶማን ገዥዎች እጅ እንደወጣች ሚሲስ ፓርሰን አሜሪካንን እንደገና እንዲጎበኝ ለአብዱል-ባሃ ደብዳቤ ላከች። ይህ ከመሆኑ ከጥቂት ቀናት በፊት ቺካጎ ኦክቶበር 16 ቀን ሊዮ ፐሮን ቤት ውስጥ የ19ነኛው ቀን በዓል እየተከበረ ነበር። አብዱል-ባሃ እንደገና አሜሪካ እንዲመጣ ለመጠየቅ ሃሳብ አቀረቡ። የቺካጎ የመንፈሳዊ ነት ስብሰባ (የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔ) እንዲህ ያለው ጥያቄ ከሁሉም የአገሪቱ ባሃኢዎች መምጣት እንዳለበት ወሰነ። በመጨረሻም ከሌሎች ከአካባቢው ባሃኢ ማህበረሰቦች ጋር ሲደመር ከአንድ ሺህ በላይ ፊርማዎች ተገኘ ። ደብዳቤው እንዲህ ይላል፡-

ለተወዳጁ አብዱል-ባሃ፡-

እኛ፣ በአሜሪካ ውስጥ ያለን ጽኑ አገልጋዮችህ የግንኙነት በሩ በመከፈቱ ደስ ብሎናል እናም እንደዚያው እንዲቆይ እግዚአብሔርን እንለምነዋለን።

> እኛ ብቁ አይደለንም፣ ሆኖም ግን እንለምንሃለን፣ በምዕራብና በምስራቅ ያሉ ሁሉም አካባቢዎች በክብርህ ሕያው እንዲሆን የአምላክ ፈቃድ ከሆነ የተባረከ ፊትህን ወደ እኛ እንድታዞር እንለምንሃለን፡፡
>
> ከዚህ በፊት የወዳጆች ልብ በተዋሃደ ጊዜ እንደገና አሜሪካንን እንደምትጎበኝ ፍጻሜ በተላበሱ ቃላት ቃል ገብተህልናል፡፡
>
> ልባችን ስለ አንተ በማያቋርጥ ናፍቆት አንድ ሆነዋል፣ በፍጹም ፍቅርህ እና በእውነተኛ ትእዛዝህ ላይ ጥገኛ ሆነናል፡፡ ለአንተ ያለን ከፍተኛ ፍላጎት በፍጥነት ወደ ምዕራባውያን እና ወደ እኛ ይሳብህ ዘንድ፣ በቅዱስ አስደናቂው የኤል-አብሃ ስም ሰላምታ እናቀርባለን፡፡

አብዱል-ባሃ ሜይ 1919 ምላሽ ሰጠ፣ የእነሱ አንድነትና ጥንካሬ እሱን ወደ አሜሪካ ለመሳብ ማግኔት ቢሆንም ሳይሄድ ቀርቷል፡፡ ቀደም ብሎ ግን በኒውዮርክ ከተማ ሆቴል ማካልፒን የሚካሄደው ጉባዔ “የቃል ኪዳኑ ጉባዔ” መሆን አለበት ብሎ ቴሌግራም ልኮ ነበር፣ ምክንያቱም የመለኮታዊ ዕቅድ ጽላቶች ይፋ የሚሆንበት ቀን እንዲሆን፡፡ እነዚህ ጽላቶች በጦርነቱ ወቅት ቀርሜሎስ ተራራ ላይ በሚገኘው የባብ መካነ-መቃብር ምድር ቤት ግምጃ ቤት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር፡፡ ከዚያም እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 23 ቀን 1918 አህመድ ሶህራብ ጽላቶቹን ወደ አሜሪካ አገር ወሰደ፡፡ በእነዚያ በማይረሱ የጉባዔ ቀናት ከኤፕሪል 26 እስከ 30 (የባሃኢ ቤተ-መቅደስ አንድነት ዓመታዊ ስብሰባ)፣ ጽላቶቹ ቀርበው ለአሜሪካ ባሃኢዎች ተነበቡ ፡፡

ጦርነቱ ሲያበቃ ደብዳቤዎችና ልመናዎች ይጎርፉ ጀመር፡፡ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 29 ቀን 1919 ሾጊ ኤፌንዲ ለአሜሪካን ባሃኢዎች ወደ መቶ የሚጠጉ ጽላቶች እንደተገለጹ አሜሪካን አገር ለሚኖረው ለዶ/ር ባግዳዲ አሳውቆ ነበር፡፡ የምሥራቅና የአውሮፓ ባሃኢዎችም ከዚህ ችሮታ ድርሻ ቸውን አግኝተዋል፡፡ መንፈሳዊ ጎብኚዎችም እንዲሁ ከምሥራቅና ከምዕራብ መምጣት ጀመሩ፡፡ አዲስ የተቋቋመውም የእንግሊዝ አስተዳደር ባለሥልጣናት አብዱል-ባሃን በተደጋጋሚ ይጠሩት ጀመር፡፡

ወታደራዊው አስተዳደር ሀይፋ ውስጥ የእርዳታ ፈንድ ከፈተ፣አብዱል-ባሃም ሃምሳ የግብፅ ፓውንድ አበረከተ፡፡ ስሙም በእርዳታው ዝርዝር መዝገብ ላይ ዋናኛ ሆኖ ሰፈረ፡፡ በድጋሚም ተጨማሪ አስተዋፅዖ አድርጓል፤ ፌብሯሪ 10 ቀን 1919 የተጻፈለት የሚከተለው ደብዳቤ ይህን ይናገራል፡-

> የተከበሩት፡-
>
> ለሐይፋ የእርዳታ ፈንድ ከእራስዎ ተጨማሪ ልገሳ ዛሬ ከልጅ ልጅዎ [ሾጊ ኤፌንዲ] ተቀብያለሁ፡፡ ለድሆች ለሚያደርጉት ልግስናዎና እንክብካቤዎ፣ በአስተዳደር ኮሚቴው ስም ከልብ የመነጨ እና እጅግ ከፍ ያለ ምስጋናዬን ይቀበሉ፣ በእነሱ በድሆቹ ስም ስለልግስናዎ ለዘላለም ይባረኩ፡፡ ጥልቅ ማረጋገጫዬ እና ከልብ የመነጨ አክብሮቴን እባክዎን ይቀበሉ፡፡ ኮሎኔል ጂ. ኤ. ስታንታን ወታደራዊ አስተዳደር፡፡
>
> ፊርማ

አብዱል-ባሃ በጣም ያበረታታው ሌላ የእርዳታ ፕሮጀክት ዛሬ በመላው ዓለም የሚሠራው የሕፃናት አድን ድርጅት

ነው። ኤግለቲን ጄብ የድርጅቱ መስራች ነበረች። እርሷ እና እህቷ በመጀመሪያ ደረጃ በተለይም በማዕከላዊ እና ምስራቅ አውሮፓ ባሉ ሕፃናት አሳዛኝ ሁኔታ ምክንያት ተግባሩን ጀመሩ። ኤግለቲን ጄብ ጓደኛ የነበረችው ሌዲ ብሎምፊልድ በዚህ ሰብአዊ ሥራ ከእርሷ ጋር አብራ ሆነች፣ የዓለም አቀፍ የሕፃናት አድን ሕብረት ዋና መሥሪያ ቤት በነበረው ጄነቭ በእነዛ ዓመታት ጥሩ ቦታ ውስጥ ትኖር ስለነበር ልዩ "የብሎምፊልድ ፈንድ" የሚል አቋቋመች። የብሎምፊልድ ፈንድ (ለንደን ውስጥ በሎርድ ዌርዴል የሚደገፈው) ዓላማ "የልጆችንና ለሌላ ገንቢ የሥራ ዘርፎችን በገንዘብ ለመርዳት ሲሆን፣ የሕፃናት አድን ድርጅት እንቅስቃሴ የበለጠ እና በጣም አስፈላጊ ሥራን የሚጨምር ነው። ለዚህ ጉዳይ ሌዲ ብሎምፊልድ "የመጀመሪያ ግዴታ" በሚል ርዕስ ከጻፈችው በራሪ ወረቀት መግቢያው ላይ የተጠቀሰው፦

> አብዱል-ባሃ አባስ ለሌዲ ብሎምፊልድ ከፃፈው ጽላት የተወሰደ በጁላይ 23 ቀን 1921 በፍልስጤም ቀርሜሎስ ተራራ ላይ የተጻፈ፦
>
> እነዚህን መድረሻ የሌላቸውን ልጆች እንዲረዳቸው ለሰብዓዊው ዓለም ጥሪ የሚያቀርቡ በራሪ ወረቀቶች ማዘጋጀትሽ ትክክለኛነቱን እያረጋገጥን፣ ለጅማሬውም እነዚህን ቃላት ጽፈናል፦
>
> ለእነዚህ አሳዛኝ ሕፃናት ዓላማ አስተዋጽኦ ማድረግ እና እነሱን መጠበቅና መንከባከብ ከፍተኛ የሆነ እራስን መስዕዋት የማድረግ እና የአምልኮ መገለጫ ነው፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን፣ መለኮታዊ ለጋሱ ልዑል አምላክን ደስ የሚያሰኝ ነው። ለእነዚህ ትናንሽ ልጆች መከታ የሚሆን አባት እና እናት

የላቸውም፣ ተንከባካቢ የላቸውም፣ መኖሪያ ቤት፣ ልብስ፣ ምግብ፣ ምቾትና ማረፊያም የላቸውም።

በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ የእኛን ደግነት ይጣራሉ፣ እርዳታችን የሚገባቸው ናቸው፣ እነሱ ምህረት እና እጅግ በጣም ርህራሄ ይገባቸዋል።

ፍትሕን የሚወዱ ዐይኖች ሁሉ በእንባ ተሞሉ፣ አስተዋይ ልቦችም በሃዘኔታ ተቀጣጠሉ!

የዓለም ሕዝቦች ሆይ ፣ ርህራሄን አሳዩ!

እናንተ የጠቢባን ስብስቦች ሆይ ፣ ለማገዝ እጆቻችሁን ዘርጉ!

መኳንንቶች ሆይ፣ ፍቅራዊ ደግነትን አሳዩ። ለጋሶች ሁኑ!

እናንተ የምድር ሀብታሞች ሆይ፣ አስተዋፅዖዋችሁን አጉርፉ!

ጠንካራ እና ልበ ደፋር የሆናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ቸርነታችሁን ግለጹ!

ጁላይ 21 ቀን 1919 አመሻሹ ላይ በባህጂ በአንድ መንፈሳዊ ኅብኚ አማካይነት የእራት ግብዣ ተዘጋጀ። አርባ የሚሆኑ ሰዎች በዚህ የተትረፈረፈ ግብዣ ላይ ተገኙ። አብዱል-ባሃ እየተዟዟረ እንግዶቹን አስተናገደ። ከዚያም ልጆቻቸው መጡ ለእያንዳንዱ ልጅ አብዱል-ባሃ ሳንቲም ሰጣቸው። በማግስቱ ጠዋት መንፈሳዊ ኅብኚዎችና እንግዶቹ ወደ ሐይፋ እና ወደ አካ ሲሄዱ አብዱል-ባሃ በባሃኡላህ መካነ-መቃበር አጠገብ ባለው የአትክልት ስፍራ ውስጥ ተቀምጦ በምዕራብ አገር ላሉ ባሃኢዎች ጽላቶችን መግለጽ ጀመረ…

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፓሪስ ውስጥ እየተካሄደ ያለው የሰላም ኮንፈረንስ አዲስ ውዝግቦች ውስጥ ገባ፣ በምስራቅና በመካከለኛው አውሮፓ ሰቆቃ እየጨመረ መጣ። አብዱል-ባሃ ፖርትላንድ ኦሪገን ለሚገኘው ለዴቪድ ቡቻን ጽላት ገለጸ፡-

> እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2 ቀን 1918 የተጻፈው ደብዳቤህ ደርሶኛል። ምንም እንኳን የተለያዩ መንግሥታት ተወካዮች ሁሉን አቀፍ ሰላም ለመመስረት በፓሪስ ውስጥ ተሰብስበው ለሰው ልጅ ዓለም እረፍት እና መፅናናትን ለመስጠት ቢሹም፣ ሆኖም በአንዳንድ ግለሰቦች መካከል አለመግባባት አሁንም ከፍተኛ ሆኗል እናም የግል ፍላጎቶች ተስፋፍተዋል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሁለንተናዊ ሰላም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፣ ይልቁንም አዳዲስ ችግሮች ይነሳሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት ፍላጎቶች የሚጋጩ በመሆናቸውና ዓላማዎች የተለያዩ ስለሆኑ ነው።

አብዱል-ባሃ ሄይግ ኔዘር ላንድ ውስጥ ለሚገኘው የዘላቂ ሰላም ማዕከላዊ ድርጅት እጅግ አስደናቂ ከሆኑት ጽላቶች ውስጥ አንዱን ገለጸ። የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ፕሬዝዳንት ሆላንዳዊው ዶክተር ኤች. ሲ. ዲርሴልሁይስ ነበሩ። ታላቋ ብሪታንያ በጂ. ሎውስ ዲኪንሰን፣ ኦስትሪያ ደግሞ በፕሮፌሰር ዶ/ር ኤች. ላሚሽ ተወክለዋል። ሁሉም በየአገሮቻቸው የታወቁ ተራማጅ አሳቢዎች ነበሩ። አብዱል-ባሃ የጻፈላቸው፡-

> እናንተ ለሰው ልጆች ዓለም በጎ ተመኚ ለሆኑት ፈርቀዳጅ የሆናችሁ ሆይ! በጦርነቱ ወቅት የላካችሁት ደብዳቤዎች አልደረሱንም፣ ፌብሯሪ 11 ቀን 1916 የጻፉችሁት ደብዳቤ አሁን ደርሷል፣ ወዲያውኑ ምላሽ ጽፈናል። ዓላማችሁ ሺህ ጊዜ

ውዳሴ ይገባዋል፣ ምክንያቱም ለሰው ልጆች ዓለም እያገለገላችሁ ስለሆነ፣ ይህ ለሁሉም ደስታና ደህንነት ተስማሚ ነው ። ይህ የቅርብ ጊዜ ጦርነት ለዓለምና ለሕዝቧ ውድመት መሆኑን አረጋግጧል፣ ዓለምአቀፋዊው ሰላም ግን ገንቢ ነው…

አብዱል-ባሃ፣ ሌሎች እነዚህን ትምህርቶች እንደራሳቸው አድርገው ሊያቀርቡ ስለሚችሉ የእምነቱ መሠረታዊ መርሆዎች ምን እንደሆኑ ለኮሚቴው በማሳሰብ አስረድቷል። ስለሰላም ጥያቄ ሲጽፍ፡-

… ምንም እንኳን የተባበሩት መንግሥታት ሊግ ወደ ሕልውና ቢመጣም አሁንም ቢሆን ሁለንተናዊ ሰላም የማቋቋም አቅም የለውም። ሆኖም ግን ከፍተኛው ፍርድ ቤት…ባሃኡላህ ሲያብራራ ይህንን ቅዱስ ተግባር በፍፁም ኃያልነት እና ኃይል እንደሚያስ ተገብረው ገልጿዋል። የእርሱ እቅድም ይህ ነው፡- የእያንዳንዱ ሀገር እና ብሄራዊ መንፈሳዊ ጉባዔዎች ማለትም ፓርላማዎች እንደማለት ነው የየአገሩ ምርጥ ሰዎች የሆኑ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎችን መምረጥ አለበት፣ እነሱም ዓለም አቀፍ ህጎችን እና በመንግሥታት መካከል ስላለው ግንኙነት በሚገባ የተገነዘቡ እና የሰው ልጅ ዓለም አስፈላጊ ፍላጎቶችን የሚያውቁ መሆን አለባቸው። የእነዚህ ተወካዮች ብዛት ከዚያ ሀገር ነዋሪዎች ቁጥር ጋር መመጣጠን አለበት። የእነዚህ ብሔራዊ ጉባዔው ማለትም ፓርላማው የተመረጡት ነፍሶች (ሰዎች)፣ በከፍተኛው ምክር ቤት፣ በኮንግረሱ እና በካቢኔው እንዲሁም በፕሬዚዳንቱ ወይም በንጉሡ መረጋገጥ አለበት ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በጠቅላላው በአገሩ እና በመንግሥት የተመረጡ እንዲሆኑ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል የከፍተኛ ፍርድ ቤት አባላት

> ይመረጣሉ፣ እነዚህ ልዑካን እያንዳንዳቸው አገሮቻቸውን ሙሉ በሙሉ የሚወክሉ በመሆናቸው የሰው ልጆች ሁሉ በዚህ ውስጥ ድርሻ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በአንድ ድምፅ ወይም በድምጽ ብልጫ በማንኛውም ዓለም አቀፍ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ለተከሳሹ ከዚህ በኋላ ለከሳሹ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ለማድረግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ማናቸ ውም መንግሥታት ወይም አገራት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱን የማይካድ ውሳኔ ሲያስፈጽም ቸልተኛ ወይም ዘገምተኛ ከሆነ የተቀሩት አገራት በእሱ ላይ ይነሱበታል፣ ምክንያቱም ሁሉም የዓለም መንግሥታት እና አገራት የዚህ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ደጋፊዎች ናቸውና፡፡ ይህ ምን ያህል ጠንካራ መሠረት እንደሆነ አጢኑ! ይህ የተገደበ እና ውስንነት ያለው ሊግ ዓላማውን እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሳካ አይችልም፡፡

አብዱል-ባሃ ጁላይ 1920 ለሁለተኛ ጊዜ አጭር ጽላት ሔግ ላለው ኮሚቴ ገልጿል፡-

> እ.ኤ.አ. ጁን 12 ቀን 1920 ለደብዳቤዬ የላከው ደግነት የተሞላው ምላሽ ደርሶኛል፣ በጣምም ደስ ብሎኛል፡፡ ቀስቃሽ ግብህ እና ዓላማህ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን የሚያመለክት ስለነበረ አምላክን አናመሰግነዋለን፡፡ ይዘቱም ከልብ የመነጨ ፍቅርን የሚገልጹ መንፈሳዊ ተጋላጭነቶችን ያቀፉ ናቸው፡፡
>
> እኛ ባሃኢዎች ለዚህ ክቡር ጉባኤ ታላቅ ፍቅር ይሰማናል፡፡ ስለሆነም ጠንካራ የተከበረ ግንኙነታችንን ለማመልከት ሁለት የተከበሩ ሰዎችን ወደዚያ ከፍ ወዳለው ጉባዔ ልከናል፡፡ እነሱም ሂፖላይት ድርፊስ ባርኒ እና የቴሄራኑ አሕመድ ያዝዳኒ ናቸው፡፡

ሎርድ (የተከበሩ) ላሚንግተን እ.ኤ.አ. በ1919 መጀመሪያ ላይ የሶሪያን የእርዳታ ሥራ ይመራ የነበረ ሲሆን፣ ዋና መስሪያ ቤቱም ደማስቆ ነበር፡፡ በእራሱ ቃላት እንደተናገረው "የእርሱን ምርቃት ለማግኘት" ጁላይ 15 ቀን አብዱል-ባሃን ለማግኘት ጥሪ አቀረበ፡፡ አብዱል-ባሃ የሎርድ ላሚንግተን ጉብኝቱን ምላሽ ለመስጠት የገለጸውን ፍላጎት በተመለከተ እንዲህ ብሏል፡- "የእኔ ግዴታ እና መብቴ በግል አንተን ማግኘት ነው፣ ወደ እኔ ለመምጣት ችግር ውስጥ እንድትገባ አልፈልግም፡፡" ሎርድ ላሚንግተን ለመሰናበት እንደገና በጁላይ 17 ቀን መጣ፡፡ በዚህ አጋጣሚም አብዱል-ባሃ ቀለበቱን ሰጠው፡፡ ለሎርድ ላሚንግተን ጥያቄም፣ አብዱል-ባሃ ሲመልስ ሁኔታዎች ከፈቀዱ ወደ ኢሽቃባድ ከዚያም ጃፓን እና ህንድን ለመጎብኘት እንደሚጓዝ ተናግሯል፡፡

የተያዘውን መሬት የደቡብ ክፍል ዋና አስተዳዳሪ ሜጀር ጄኔራል ዋትሰንን በወታደራዊው አገረ ገዢ ኮሎኔል ስታንታን ቤት ኦገስት 23 ቀን በሐይፋ ውስጥ ከአብዱል-ባሃ ጋር ተገናኝተዋል፡፡ ኦክቶበር 4፣ አብዱል-ባሃ፣ በሃይፋ ተጠባባቂ የወታደራዊ ገዥ ሻለቃ ዊሊያምሰን ግብዣ አማካይነት ኤች ኤም.ኤስ.ኤስ ማርልቦሮ የተባለውን የጦር መርከብ ጎብኝቷል፣ ከመርከቡ አዛዥ ሜጀር ዊሊያምሰን እና (ከአካው ምክትል ወታደራዊ ገዥ) ካፒቴን ሎውክ ጋር መርከቡ ላይ ሻይ ሲጠጡ፣ የጦር መርከብ ላይ ሲወጣ በሕይወቱ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ እንደሆነ ተናግሯል፣ ሁሉም የጦር መሳሪያዎችና መተግበሪያዎች አንድ ቀን ሰላምን እና የኢንዱስትሪ ብልጽግናን ለማሳደግ ወደ አንድ ዘዴ እንደሚለወጡ ተስፋ እና እምነት እንዳ ለው፣ ሁሉም ተዋጊዎች በመጨረሻ የንግድ መርከቦች በመሆን የንግድ እና ኢንዱስትሪን የሚያነቃቁ ይሆናሉ ብሏል፡፡

ኦክቶበር 20 ከሰዓት በኋላ ሁለት ጽኑ የሆኑ ሙስሊም የሕንድ ወታደሮች ወደ አብዱል-ባሃ ቤት በመሄድ እርሱን ለመገናኘት ጠየቁ። ካምፓቸው ከሐይፋ ጥቂት ርቀት ላይ የነበረ ሲሆን እርሱ ጋር ለመድረስ ተጉዘው መጡ። በሕንድ ሳሉ ስለእርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሙ ሲሆን ከዛም ወደ መካ በመሄድ የሐጅ (መንፈሳዊ ጉብኝት) ሥነ-ሥር ዓታቸውን አከናውነው ነበር። አሁን፣ ግዴታቸው ሆኖ ስለተሰማቸው በመጀመሪያው አጋጣሚ እርሱን ለማየት መጡ። በፊቱ ተንበርክከው በደስታ አለቀሱ። አብዱል-ባሃ ለእነሱ በጣም ደግ ነበር፣ እናም እንደ አባት ተቀበላቸው፤ በኋላም አብዱል-ባሃን ተከትለው ወደ ባብ መካነ-መቃበር ሄዱ።

በአብዱል-ባሃ ሕይወት ውስጥ እንደዚህ ያሉ ክስተቶች ብዙ ነበሩ።

ከምዕራቡ ዓለም የሚመጡ ብዙ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ነበሩ፣ ከእነርሱ መካከል ለአንድ ዓመት የቆዩት ዶ/ር ባግዳዲና ባለቤታቸው፣ ጆርጅ ላቲመር፣ ዊሊያም ራንዳልና ባለቤታቸው ከሴት ልጃቸው ማርጋሬት ጋር፣ ሚሲስ ኮርኔን ትሩ እና ሴት ልጃቸው ኤድና ትሩ ይገኙበታል። ባሃኡላህና አዲሱ ዘመንን የጻፈው ዶ/ር ጆን ኤስሌሞንትም ኖቬምበር 4 ቀን ሐይፋ መጣ። ስለቆይታው ሲጽፍም፡-

> እ.ኤ.አ. ከ1919-20 የፀደይ ወቅት በሐይፋ የአብዱል-ባሃ እንግዳ ሆኜ ለሁለት ወር ተኩል የመቆየትና የዕለት ተዕለት ኑሮን በትኩረት የመከታተል ታላቅ ዕድል አግኝቼ ነበር። በዚያን ጊዜ፣ ወደ ሰባስድስት ዓመቱ ቢጠጋም፣ አሁንም በሚያስደንቅ ሁኔታ ጠንካራ ሲሆን፣ በየቀኑ እጅግ አስደናቂ የሆነ ሥራ ያከናውን ነበር። ምንም እንኳን ብዙውን ጊዜ በጣም ቢደክምም አስደናቂ የማገገም

ኃይሎች ነበሩት፣ አገልግሎቱንም በጣም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁል ጊዜም ይሰጣል፡፡ የማያቋርጥ ትዕግስቱ፣ የዋህነቱ፣ ቸርነቱ እና ብልሃቱ… እንደበረከት ነው፡፡ የእያንዳንዱን ምሽት ረጅም ጊዜ በጸሎት እና በማሰላሰል ማሳለፍ ልማዱ ነበር፡፡ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ከምሳ በኋላ ለአጭር ጊዜ እረፍት ካደረገ በኋላ ከብዙ አገራት የተላኩ ደብዳቤዎችን በማንበብ እና በመመለስ ከዚያም ደግሞ የቤቱን እና የእምነቱን ሁለገብ ጉዳዮች በመከታተል ላይ ተጠምዶ ይውላል፡፡ ከሰዓት በኋላ ብዙውን ጊዜ በእግር ትንሽ በመሄድ ዘና ይላል፣ ነገር ግን ያኔም ቢሆን ብዙውን ጊዜ ከአንድ ወይም ከሁለት ወይም ከብዙ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ጋር አብሮ በመሆን ስለመንፈሳዊ ጉዳዮች ያወጋል ወይንም አንዳንድ ድሆችን ለማግኘት እና ለማገልገል መንገድ ይፈልጋል፡፡ ከተመለሰ በኋላም ወዳጆችን በመጥራት በሳሎን ውስጥ የተለመደውን የምሽት ስብሰባ ያደርጋል፡፡ በምሳም ሆነ በእራት ጊዜ በርካታ መንፈሳዊ ጎብኚዎችንና ወዳጆችን ያስተናግዳል፣ እንግዶቹን በሚያስደስት እና በሚያስቅ ታሪኮች ያዝናናል እንዲሁም በብዙ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ድንቅ ንግግሮች ያደርጋል፡፡ 'ቤቴ የሳቅና የደስታ ቤት ነው' ይላል፣ እውነትም እንደዚያ ነበር፡፡ በእንግዳ ተቀባይነቱ የተለያዩ ዘር፣ ቀለም፣ አገር እና ሃይማኖቶች ያላቸውን ሰዎች በአንድነት በማሰባሰቡ ደስተኛ ነው፡፡ እርሱ በእውነት በሐይፋ ለሚገኙ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ላሉ የባሃኢ ማህበረሰብ አፍቃሪ አባት ነበር፡፡

ዶ/ር ኤስሌሞንት በመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደሚናገረው አብዱል-ባሃ እንዲመጣ በጋበዘው ጊዜ የጽሑፉን ረቂቅ

ሐይፋ ይዞ እንደመጣ ይናገራል፣ በበርካታ አጋጣሚዎች ከእሱ ጋር በመወያየት እና አንዳንድ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ጠቃሚ አስተያየቶችን ለግሶታል፡፡ የአብዱል-ባሃ ሃሳብ አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ እንዲያነበው እና እንዲያሻሽለው ወደ ፋርስኛ እንዲተረጎም ማድረግ ነበር፤ ሆኖም ግን ከዚህ ዓለም ከማለፉ በፊት ሦስት ግማሽ ምዕራፎችን ብቻ ማረም ችሏል፡፡ ዶ/ር ኤስ ሌሞንት እ.ኤ.አ. በ1924 በሾጊ ኤፈንዲ ግብዣ መሠረት እንግሊዝን ለቅቆ ወደ ሐይፋ መጣ፣ ከዚያም በኖቬምበር 1925 ሞተ እና ከሞተም በኋላ የእምነቱ ሞግዚት የአምላክ እደ-ሃይማኖት ማዕረግን ሰጠው፡፡

ሊቅ የነበረው የኢራን ባሃኢ ሚርዛ አሳዱአላህ ፋዲል-ማዚንዳራኒ እ.ኤ.አ. በ 1919 መገባደጃ ላይ ከመጡት መንፈሳዊ ጎብኚዎች አንዱ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ አሜሪካ እንዲሄድ አደረገው፡፡ የባሃኢ መቅደስ አንድነት አሥራ ሁለተኛው ዓመታዊ ስብሰባ (1920) ሊካሄድ ሲል ፋዲል ኒው ዮርክ ደረሰ፡፡ የባሃኢ ማህበረሰቦች ለመርዳት እና ለማነቃቃት በአገሪቱ ውስጥ በመዘዋወር በአሜሪካ አንድ ዓመት ቆየ፡፡

ማክሰኞ ኤፕሪል 27 ቀን በስብሰባው የከሰዓት በኋላ ክፍለ-ጊዜ በኢሊኖይ ውስጥ በዊልሜቴ የሚሰራውን የመሻሪኩል-አድ ህካር ሕንፃ ንድፍ በተገኙት አርባ ዘጠኝ ልዑካን አማካይነት ተመረጠ፡፡ የሕንፃው ንድፍ በሶስት አርክ ቴክቶች ቀረበ ሉዊስ ቦርጌይስ፣ ዊሊያም ሴዘርላንድ ማክስዌል እና ቻርለስ ሜሰን ሬሚ ነበሩ፡፡ የሉዊስ ቡርጌይስ ንደፊ-ሕንፃ በተወካዮቹ አብላጫ ድምፅ ተመረጠ፡፡ የሕንፃው መሠረት ሥራ የተጀመረው እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 24 ቀን 1920 ነበር፡፡

በኤፕሪል 27 ቀን 1920 በሐይፋ ወታደራዊ ገዥ አማካይነት አብዱል-ባሃ በእንግሊዝ ኢምፓየር የባላባትነት ማዕረግ ተሰጠው፡፡ የባላባትነት ማዕረግ የተሰጠው በጦርነቱ ወቅት የደረሰውን ችግር እና ረሃብ ለመታደግ ለሰብዕዊ እርዳታው እውቅና በመስጠት ነበር፡፡ የክብሩን ስጦታ ተቀበለ እንጂ የማዕረግ ስሙን በጭራሽ አልተጠቀመም፡፡ ሌዲ ብሎምፊልድ ስትጽፍ፡-

ለአብዱል-ባሃ የክብር ማዕረግ ለመስጠት የጓጉት ከኢየሩሳሌም የመጡት የእንግሊዝ ዘውድ መኳንን ቶች በሐይፋ ተሰብስበው ነበር፣ ለእያንዳንዱ ሰው ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ ለሚሰጠው የአገልግሎት ሕይወቱ ይወዱትና ያከብሩት ነበር፡፡ አብዱል-ባሃን ወደ ሥነ ሥርዓቱ ለማምጣት ምርጥ የሆነ መኪና ተላከ፡፡ አብዱል-ባሃን ግን ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ እርሱን ለመፈለግ ሰዎች በየአቅጣጫው ተላኩ፣ በድንገት ባልታሰበ በኩል ብቻውን፣ ሁልጊዜም በሚታይበት በማይከብድ ግርማዊነቱ፣ በንጉሳዊው አረማመዱ እየተራመደ ሲሄድ ታየ፡፡

ጌታውን በማጓጓዝ በመርዳቱ ለብዙ ዓመታት የተደሰተው ታማኝ አገልጋዩ ኢስፍንድያር አብዱል-ባሃን ለመውሰድ የመጣውን የሚያምር ምርጥ መኪና በማየቱ አዝኖ ቆሞ ነበር፡፡

"ከአሁን በኋላ አላስፈልግም ማለት ነው" አለ፡፡

ሃዘኑን ያየው አብዱል-ባሃ፣ ዕድሜው የጠናው ኢስፍንድያር ፈረሱን እንዲያመጣ ነገረው፡፡ እሱም ፈረሱን ለማምጣት በፍጥነት ተጣደፈ፣ ጋሪውን በታችኛው በር ላይ በኩል አመጣው፣ አብዱል-ባሃም በጋሪው ተሳፍሮ ወደ ፎኖሺያው ገዢ (ምስራቃዊ

ሜዲትራኒያን፣ በዋነኝነት የአሁኑ ሊባኖስና አካባቢው) የአትክልት ስፍራ ሄደ።

ጄኔራል አሌንቢ ሌላ ታዋቂ ጎብኚ ነበር። እሱና ባለቤቱ ከአብዱል-ባሃ ጋር በባሃጂ ምሳ በሉ፣ ከዚያም አብዱል-ባሃ ራሱ ወደ ባሃኡላህ መካነ-መቃብር ወሰዳቸው። የተከበረው ሄርበርት ሳሙኤል በ1920 የፍልስጤም ከፍተኛ ኮሚሽነር ሆኖ ተሾመ። ሐይፋ ውስጥ በሚገኘው ቤቱ አብዱል-ባሃን ብዙ ጊዜ አግኝቶታል።

ዶ/ር ባግዳዲ ከአንድ አመት ቆይታ በኋላ ኦክቶበር 1920 ወደ አሜሪካ ተመለሰ። ለአሜሪካ ባሃኢዎች የሚነግራቸው ብዙ ነገር ነበረው። አብዱል-ባሃ በፋርስ ውስጥ ያለቸውን የሰማዕት ሚስት ታሪክ ነግሮት ነበር። ሴትየዋ ሁለት ልጆቿን ለማሳደግ ካልሲዎች በመስፋት ትተዳደር ነበር። አንድ ጥንድ ለልጆቿ የኑሮ አስፈላጊ ነገሮችን ለማቅረብ የምትሰራ ሲሆን ሌላ ጥንድ ደግሞ በአሜሪካ ውስጥ ለሚሰራው ማሽሪኩል-አድህካር ገንዘብ ለማዋጣት ትሰራላች። አብዱል-ባሃ በዘር ስምምነቶች ጥያቄ ላይ ለዶ/ር ባግዳዲ የሰጠው ማብራሪያ፣ በአሜሪካ ውስጥ በጥቁር እና በነጭ መካከል መግባባት ለመፍጠር አንድ ነገር ካልተደረገ ደም ይፈሳል ብሎታል።

ለመለኮታዊ እቅድ ጽላቶች የተሰጠው የመጀመሪያ ምላሽ፣ ለአብዱል-ባሃ ልዩ ደስታን አመጣ። ክላራ እና ሃይድ ዳን ከካሊፎርኒያ ወደ አውስትራሊያ ለመኖር ሄዱ፣ እ.ኤ.አ 1920 እዚያ ደረሱ። ሃይድ ዳን በኋላ አባባ ዳን የተባሉት 62 ዓመታቸው ነበር። በ1934 በአውስትራሊያ እና በኒውዚላንድ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ ሲቋቋም ለማየት ችለዋል። ፌብሯሪ 1941 ሲሞቱ፣ የእምነቱ ሞግዚት የአውስትራሊያ ‘መንፈሳዊ ድል አድራጊ’ የሚልና ከጥቂት ዓመታት በኋላም እንዲሁ የእደ-ሃይማኖትነት ማዕረግ

ሰጥቷቸዋል። እማማ ዳንንም ፌብሯሪ 1952 ሞግዚቱ ወደ እደ-ሃይማኖትነት ደረጃ ከፍ አደርጓቸዋል፣ በዘጠና ሁለት ዓመታቸው የጀግንነትና የአነቃቂነት ግልጋሎታቸውን ቀጥለዋል። በኖቬምበር 1960 አረፉ።

በሙያዋ ጋዜጠኛ የነበረችው ማርታ ሩት ጁላይ 1920 ወደ ደቡብ አሜሪካ ተጓዘች። ወደ እያንዳንዱ የዓለም ክፍል ጉዞዋን የጀመረችበት ጊዜ ነበር፣ ነገሥታት እና ንግስቶችን፣ ፕሬዚዳንቶች እና የአገራት ባለስልጣኖችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን እና ኮሌጆችን በአካዳሚው ዓለምና በሰዎች ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ጎበኘች። የባሃኡላህን ስም ለማሳወቅ እና የሰው ልጆችን ጉዳዮች በትምህርቱ አማካይነት እንዲመሩ የማድረግን ብቸኛ ዓላማን ይዛ በልዩ ልዩ ስብሰባዎች እና ኮንፈረንሶች ላይ ተገኘች። ያቺ ጀግና ሴት እ.ኤ.አ. በ 1939 የሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንደተቀሰቀሰ እና ትኩስ ችግሮች ሊመጡ እንዳሉ በሃዋይ ሆንሉሉ ውስጥ ይህን ዓለም ለቅቃ ተሰናበተች። በእንደዚህ ዓይነት ፍቅር እና ታማኝነት ያገለገለችው የእምነቱ ሞግዚት፣ ከሞተች በኋላ በተስፋ ቃላት አክብሯታል።

የመጀመሪያው የመላው የሕንድ ባሃኢዎች ስብሰባ እ.ኤ.አ. 1920 ከዲሴምበር 27 እስከ 29 በቦምቤይ ተካሂዷል። ሕንድን እንዲጎበኝ ወደ አብዱል-ባሃ ልመና ተላከ። የሕንድ ታይምስ ጋዜጣ የስብሰባውን ሂደት በብቃት ዘግቧል፤ ስብሰባውን የጎበኘው ታዋቂው በወቅቱ የእጽዋት ምርምር የቦምቤይ ዩኒቨርሲቲ ሰብሳቢ የነበረው ክቡር ፓትሪክ ጌድስ ነበር።

በአሜሪካ ውስጥ የማሽሪኩል-አድህካር ግንባታ ብዙ ችግሮችን እያመጣ ነበር፣ አብዱል-ባሃ ምክር ተጠየቀ። አብዱል ባሃም ይህን ጉዳይ ለመጪው ዓመታዊ ጉባዔ እንዲያቀርቡ ለአሜሪካን ባሃኢዎች ነገራቸው።

ፉጂታ ከአሜሪካ እና ዶ/ር ሉቱፉአላህ ከለንደን አብዱል-ባሃን ለማገልገል ቅድስት አገር መጥተው ነበር። መንፈሳዊ ጎብኚዎችን በመቀበልና በማስተናገድ በዋናነት ረድተዋል። ለአብዱል-ባሃ መኖሪያ ቅርብ የሆነ ቤት ከምእራቡ ዓለም ለሚመጡ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ተዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን ሚሲስ ኢሞገን ሆግ በ 1921 የበጋ ወቅት እዚያ የነበሩትን መንፈሳዊ ጎብኚዎች ይንከባከቡ ነበር። ከአብ ዱል-ባሃ ቤት ትንሽ ከፍ ብሎ ለወደፊቱ የምዕራባዊያን መንፈሳዊ ጎብኚዎችን ለማስተናገድ የሚሆን ቤት ለመስራት መሬት ተገዛ።

አብዱል-ባሃ እ.ኤ.አ 1921 መጀመሪያ ላይ ጤንነቱ ታወከ። ማርች ወር ላይ በቲቢሪያስ ለጥቂት ጊዜ ለመቆየት ሄደ። ወደ ሐይፋ ከተመለሰ በኋላም፣ በባብ መካነ-መቃብር አቅራቢያ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የተወሰኑ ሌሊቶችን አሳለፈ።

በበጋ ወቅት ላይ አብዱል-ባሃ ከታወቀው ከስዊስ ሳይካትሪስት እና ኢንቶሞሎጂስት ከዶ/ር አውጉስተ ፎረል ደብዳቤ ደረሰው። በኋላ ላይ ፎርል እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> እ.ኤ.አ. በ1920 በካርልስሩዋ ጀርመን፣ ከሰባ ዓመታት በፊት በምሥራቅ ፋርስ በባሃኡላህ ከተመሠረተው ከባሃኢ እጅግ የላቀ ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖት ጋር ተዋወቅኩ። ለሰዎች ደህንነት እውነተኛ ሃይማኖት ነው፣ ካህናትም ሆነ ቀኖናዎች የሉትም፣ በዚህች ትንሽ ከባባዊ ዓለም ውስጥ የተጎዱትን የሰው ልጆች ሁሉ ያገናኛል። ባሃኢ ሆንኩ። ይህ ሃይማኖት የሚቀጥልና የስኬት ዘውድ የሚቀዳጅ ይሁን፤ ይህ እጅግ በጣም የምመኘው ምኞቴ ነው።

ለደብዳቤው መልስ አብዱል-ባሃ የገለጸለትን ጽላት ሾጊ ኤፌንዲ ሲያብራራው “አብዱል-ባሃ (Master) ከፃፈው እጅግ በጣም ጥልቅ ጽላት አንዱ ነው ብሏል። የጽላቱ መክፈቻ ቃላት እነዚህ ናቸው፡-

> የተከበርከው እውነትን የምትወድ ሆይ! ጁላይ 28 ቀን 1921 የጻፍከው ደብዳቤህ ደርሷል። በውስጡ ያለው ይዘት በጣም አስደሳች ነበር፣ እና ጌታ ይመስገን፣ ገና ወጣት ነህ እናም እውነትን እየፈለግህ እየመረመርክ ነው፣ የአስተሳሰብህ ኃይል ይጠነክራል፣ የአዕምሮህ ግኝቶችም ይከሰታሉ።

የማጠቃለያ ቃላቶቹ ደግሞ፡-

> ለማጠቃለል፣ እነዚህ ጥቂት ቃላት ተጽፈዋል፣ እናም ለሁሉም ሰው ግልጽ እና ተጨባጭ የእውነት ማስረጃ ይሆናሉ። በልብህ አስባቸው/ አውጠንጥ ናቸው። በግዛቱ ዘመን የእያንዳንዱ ሉዓላዊ ፈቃድ ይገዛል፣ የእያንዳንዱ ፈላስፋ ፈቃድ በሕይወት ዘመኑ በጥቂት ደቀ-መዛሙርት ውስጥ መግለጫን ያገኛል፣ ሆኖም ግን በአምላክ መልዕክተኞች እውነታዎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በብሩህነት ያበራል እና ለብዙ ሺህ ዓመታት በታላቅ ህዝብ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር የሰውን ነፍስ እንደገና ለማደስ እና የሰውን ልጅ ለማነቃቃት ኃይላቸውን ያጠናክራል። ይህ ኃይል ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አስብ! ታላቅ የሆነ ኃይል ነው፣ የአምላክ ነቢያት ተልዕኮ እውነት መሆኑን ሙሉ በሙሉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው፣ እናም የመለኮታዊ ተመስጦ ኃይልን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው።
>
> የክብሮች ክብር በአንተ ላይ ይረፍ።

በጦርነቱ ጫና ምክንያት ከቅድስት አገር መነጠል ስለተፈጠረ በአሜሪካ ውስጥ ለሚገኙት ለቃል-ኪዳን አፍራሾች እንደገና እንዲረብሹ ዕድል ሰጥቷቸዋል። ዶ/ር ፋሪድም ተቀላቅሏቸዋል። የአሜሪካውን የባሃኢ ማህበረሰብ ለመከፋፈል በጣም ብዙ ሞክረዋል፣ የአብዱል-ባሃ የመጨረሻ ዓመታትም በእነሱ እንቅስቃሴ ምክንያት የበለጠ ሸክም ሆኖበት ነበር፣ ሆኖም ግን በመጨረሻ እነሱ በአስከፊ ሁኔታ ወድቀዋል።

አብዱል-ባሃ ከመሞቱ አንድ ሳምንት በፊት ለአሜሪካ ባሃኢዎች በተጻፈው በመጨረሻው ጽላት ላይ እንዲህ ብሏል፡-

> እናንተ የአምላክ ወዳጆች ሆይ! የአምላክ ወዳጆች ለእርሱ ውድ ናቸውና አብዱል-ባሃ ሌት ከቀን ያስባችኋል ስለ እናንተም ያወሳል። እናንተ ብሩህ ሻማዎች እንድትሆኑ፣ በመመሪያ ብርሃን እንድታበሩ እና የስህተትን ጨለማ እንድታስወግዱ፣ በየቀኑ ማለዳ ላይ የአምላክን መንግሥት እለምናለሁ እናም በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ እንድትሞሉ እጠይቃለሁ። የአብሃ መንግሥት ማረጋገጫዎች ያለማቋ ረጥ ወደ እናንተ እንደሚደርሱ እርግጠኛ ሁኑ።
>
> በመለኮታዊው የፀደይ ወቅት ኃይል፣ በሰማያዊ ደመናዎች ዝናብ እና በእውነተኛው የፀሐይ ሙቀት፣ የሕይወት ዛፍ ማደግ ጀምሯል። ብዙም ሳይቆይ ቡቃያዎችን፣ ቅጠሎችን እና ፍሬዎችን ያፈራል፣ በምስራቅና በምዕራብ ላይም ጥላውን ያጠላል። ይህ የሕይወት ዛፍ የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ነው።

ይህ ደማቅ ብርሃን እንዲጠፋ ተስፋ በማድረግና ይህ የሕይወት ዛፍ እንዲነቀል በማለት በአሜሪካ ውስጥ በእነዚህ ቀናት ኃይለኛ ነፋሳት የቃል ኪዳኑን መብራት ከበዋል፡፡ የተወሰኑ ደካማ፣ ወላዋይ፣ ተንኮለኛ እና አላዋቂ ነፍሳት በጥላቻና ጠላትነት የመሬት መንቀጥቀጥ ተርበድብደዋል፣ መለኮታዊውን ቃል ኪዳኑን እና ኑዛዜውን ለማፍረስ ጥረት አድርገዋል፣ ዓሳ ለማጥመድ ሲሉ ጥርት ያለውን ውሃ ጭቃ አድርገውታል፡፡ የባያን ሰዎች የተባረከውን ውበት እንዳጠቁ ሁሉ አሁንም በቃል ኪዳኑ ማዕከል ላይ ተነስተዋል በእያንዳንዱ ቅጽበት አስጸያፊ ነገርን ያወራሉ፡፡ የባሃኡላህ ቃል-ኪዳን በአሜሪካ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲደመሰስ በየቀኑ ሰበብን ይፈልጋሉ እናም ጥርጣሬን በድብቅ ያነሳሳሉ፡፡

የአምላክ ወዳጆች ሆይ! ንቁ፣ ንቁ፣ ነቅታችሁ ጠብቁ፣ ነቅታችሁ ጠብቁ…

ያ ባሃኡላህ አብሃ! እምነቱን ከፍ እስኪያደርግ ድረስ እና የአብሃ መንግሥት ሰንደቅ በዓለም ላይ እስኪ ውለበለብ ድረስ አብዱል-ባሃ ለትንሽ ጊዜም ቢሆን አያርፍም፡፡ አሁን አንዳንድ ሰዎች ይህንን ባንዲራ በአሜሪካን ውስጥ ለመጨፍለቅ በተንኮል እና በክፉ ምኞቶች ተነሱ፣ ተስፋዬ ያለው በእናንተ የጥንካሬ ማረጋገጫ ውስጥ ነው፡፡

ከዕርገቱ አሥራ ስድስት ቀናት በፊት ኖቬበር 12 ቀን አብዱል-ባሃ በኒውዮርክ ወደሚገኘው ሮይ ዊልሄልም ኬብል ላከ፣ የምዕራቡ ማህበረሰብ ስለመመስረቱ፣ ስለሥልጠናው እና ጥበቃው ያለውን ጥልቅ አትኩሮት

የአገልግሎት ዘመኑ ዋና ገጽታዎች አንዱ እንደሆነ አሳየ። ይህ ቴሌግራምም ለመንፈሳዊ ደህንነታቸው ናፍቆት የልቡ ስሜት መግለጫ ነው፡- “ከመለኮታዊ ችሮታ ጤንነትን እለምናለሁ።” አባስ

የአሜሪካው የባሃኢ ማህበረሰብ ጽኑ እና ያልተከፋፈለ ሆኖ ቆይቷል።

## ምዕራፍ 13

## የአብዱል-ባሃ እልፈት

ጁላይ 10 ቀን 1921 አብዱል-ባሃ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ በባብ መካነ-መቃብር ነበር። እዛም ሆኖ፣ በወቅቱ ለሞቱ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ አባት ለሆኑት ለባብ ዘመድ፣ መታሰቢያ ጽላት እና ጸሎት ገልጿል። አብዱል-ባሃ በዚህ ጸሎት ውስጥ፣ ራሱ ከዚህ ዓለም ነፃ እንዲወጣ አምላክን ለመነ። ስለ "ብቸኝነቱ"፣ "ክንፉ" ስለመሰበሩ፣ "በሐዘን ባሕሮች ውስጥ መስጠሙን" ይናገራል፡- 'ጌታ ሆይ! አጥንቶቼ ተዳክመዋል፣ በእራሴ ላይ ያሉት ግራጫ ፀጉሮቼ በመሸበታቸው ምክንያት ያብለጨልጫሉ… አሁን ወደ እርጅና ደርሻለሁ፣ ኃይሌን አጥቻለሁ… ተወዳጆችህን ተነስቼ የማገለግልበት በእኔ ውስጥ ምንም ኃይል የለም… ጌታዬ፣ አምላኬ ሆይ! ዕርገቴን ወደ ክቡር ደጃፍና በታላቅ ምሕረትህ ጥላ ስር ወደ ጸጋህ በር መምጣቴን አፋጥነው….'

ያ ጸሎት ከአምስት ወራት በኋላ መልስ አግኝቷል። ኖቬምበር 28 ቀን ለሊት ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

በዚያ ሰዓት ወደ አልጋው ተጠርቶ ዓይኖቹን የጨፈነለት የኒውዮርኩ ሐኪም ዶክተር ፍሎሪያን ክሩግ ነበር፣ ይህ ሰው ለባሃኡላህ እምነት የመረረ ጥላቻ የነበረውና ሚስቱ ለእምነቱ ባላት ጥልቅ ቁርጠኝነት ምክንያት በሕግ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው ሳይካትሪስቶች እንዲመረምሯት ፈልጎ የነበረ ሰው ነው። በወቅቱ መንፈሳዊ ጎብኚ ሆኖ፣ ከባለቤቱ ጋር መጥቶ ሳለ፣ አብዱል-ባሃም በቤቱ ውስጥ አንድ ክፍል ሰጥቷቸው ነበር።

ጠዋት ላይ የአብዱል-ባሃ ቤተሰቦችና በሐይፋ የሚገኙ ባሃኢዎች ሕይወቱ ከዚህ ዓለም ማለፉንና በቀጣዩ ቀን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ እንደሚፈጸም ለሕዝብ ተነገረ።

> ሰኞ በማለዳ... የዚህ ድንገተኛ አደጋ ዜና በከተማው ተሰራጨ፣ ያልተጠበቀ ሁከትና ብጥብጥም አስከተለ፣ የሁሉም ሰዎች ልቦችም ሊገለጽ በማይችል ሀዘን ተሞሉ።

ከሰዓት በኂላ ይህ መግለጫ ተለቀቀ፡-

> *ሁላችንም የአምላክ ነን ሁላችንም ወደ እርሱ እንመለሳለን። የእስልምና ተቋም እጅግ ሊቅ የሆነውን፣ እጅግ ምሁሩን፣ ለጋስ የሆነውን፣ ብፁሑ አብዱል-ባሃ በመሞቱ እጅግ ማዘናችንን እንገልጻለን። ቅሪተ-አካሉን የያዘው ሳጥን ከቤቱ ነገ ማክሰኞ ቀን ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ይወጣል። በቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ለመገኘት ይህንን መልዕክት እንደ ልዩ ግብዣ እንድትቀበሉ እንጠይቃለን። አምላክ ወሰን በሌለው ምሕረቱ ውስጥ ያስጥመው፣ ለቤተሰቡ እና ለእሱ ሰዎች መጽናናትን ይስጣቸው።*

እኛ ቅድስት አገር ብለን በምናውቃት ምድር፣ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ሁከት በተንሰራፋበት ታሪኳ ውስጥ፣ ሁሉንም የተለያየ እምነት ምንጫቸውና ዓላማ ቸው የተለያየ ሰዎችን እንደአብዱል-ባሃ ህልፈት በአንድ የአስተሳሰብና የስሜት መግለጫ አንድ የሚያደርግ ክስ ተት አልተፈጠረም ነበር። አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች።

ድሩዞች፣ ዓረቦች፣ ቱርኮች፣ ኩርዶች፣ አርመናውያን እና ሌሎች ጎሳዎች በእሱ ሞት ሐዘን አንድ ሆነዋል፣ ስለገጠማቸው ትልቅ እጦት አውቀዋል።

ከሻለቃ ቲዮዶር-ፖል የግል ማስታወሻ ውስጥ የተወሰደ፡-

ማክሰኞ ህዳር 29 ቀን 1921 ከቀኑ 3;30 ላይ "ሳይክሎሜትሪ ለንደን" በሚል የተላከው ቴሌግራም እኛ ቢሮ ደረሰ። እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 28 ቀን 1921 ከሰዓት በኋላ 9 ሰዓት ላይ ነበር ከሐይፋ የተላከው። የሚከተለውን አስደንጋጭ ዜና ይዟል፡-

"ቅዱሱ አብዱል-ባሃ ወደ አብሃ መንግሥት አርጓል። እባክዎን ለወዳጆች ያሳውቁ። ፊርማ ታላቋ ቅድስት ቅጠል።

ለንደን ውስጥ ያሉ ወዳጆች ወዲያውኑ በቴሌግ ራም፣ በስልክ እና በደብዳቤ፣ ተነገራቸው፤ እዚህ ሀገር ውስጥ ያሉት ሁሉም ወዳጆች ማዘናቸውንና ፍቅራዊ ርህራሄያቸውን በመግለጽ በቴሌግራም በሀይፋ ለሚገኙት ቅዱሳን ቤተሰቦች ላኩ።

በኢየሩሳሌም ውስጥ ላለው ለከፍተኛው ኮሚሽነር ለዊንድሃም ዲድስ ቴሌግራም ተላከ፣ በሐይፋ እና አካላሉ ቤተሰቦችና ለባሃኢ ማህበረሰብ የሚፈለገውን ማንኛውንም አገልግሎት ለመስጠት በፍልስጤም (እስራዔል) ውስጥ ያሉ የእንግሊዝ ባለሥልጣናት ለተወዳጁ እልፈት አክብሮት ለማሳየት እያንዳንዱን እርምጃ ወስደዋል።

የአብዱል-ባሃን ዕርገት ለወዳጆች ለማሳወቅና በሁሉም የዓለም ክፍሎች ውስጥ የወዳጆችን ፍቅር

እና ርህራሄም ለማስተላለፍ ለኢሽቃባድና ለሌሎች የባሃኢ ማህበረሰቦች ቴሌግራም ተላከ።

ይህንን ቴሌግራም እንዲላክ ከአሜሪካ ቀይ መስቀል ባለሥልጣናት እና በሞስኮ ከሚገኘው የእንግሊዝ የንግድ ተልዕኮ ጋር ግንኙነት ተደረገ፤ …

ክቡር ላሚንግተን፣ ሐዘናቸውን ሲገልጹ፣ ለቢሮው ምክር የሰጡት፣ የቅኝ ግዛት ጽ/ቤት የአብዱል-ባሃ ቀብር ላይ የብሪታንያ(እንግሊዝ) ውክልና እንዲኖር ምክራቸውን ለግሰዋል።

የቀድሞው የፍልስጤም ዋና አስተዳዳሪ ጄኔራል ሰር አርተር ሞኔይ እ.ኤ.አ. በ2/12/1921 ሲጽፉ፦

"የአብዱል-ባሃን ሞት ስሰማ በጣም አዝኛለሁ። ለእሱ ጠንካራ አክብሮት እና አድናቆት ነበረኝ እናም ምክሩን ሁልጊዜ ከፍ አድርጌ እመለከተዋለሁ። በፍልስጤም ውስጥ ያለውን ተፅዕኖ ሁሉ ለበጎ ምግባር ተጠቅሟል፣ ሕግንና ስርዓትን ለመመስረት አስተዳደሩን ለመርዳት ሁልጊዜ ዝግጁ ነበር።"

ኒው ዮርክ፣ ሮይ ዊልሄልም ይህንን ቴሌግራም ከሐይፋ፣ ኖቬምበር 28 ተቀብሏል፦

ለሮይ ዊልሄልም ኒው ዮርክ ዊልሄልሚት፣ ብፁዕ ቅዱሱ አብዱል-ባሃ ወደ አብሃ መንግሥት አርጓል። ወዳጆችን አሳውቅ። ታላቋ ቅድስት ቅጠል።

በአሜሪካ ከሚገኘው ከባሃኢ ቤተ-መቅደስ አንድነት ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ስም ወደ ቅድስት አገር ይህ መልዕክት ተላከ፦

> እርሱ የሚሻውን ሁሉ ያደርጋል። ልቦች በዚህ ታላቁ መከራ አነቡ። የአሜሪካ ወዳጆች በአንድነት ቦርድ አማካይነት ብሩህ ፍቅር፣ ወሰን የለሽ ሃዘንና እራስን ማስገዛት ልከዋል። መገኘቱ ስለማያቋርጥና ቅርበቱን ስለምናውቅ ጸንተን እንቆማለን።

የቴህራን ባሃኢዎች በመንፈሳዊ ጉባኤያቸው አማካይነት የሚከተለውን መልዕክት ለአሜሪካ እና ለእንግሊዝ ባሃኢ ዎች ላኩ፡-

የቃል-ኪዳን ብርሃን ከዓይን ወደ ልብ ተላለፈ። የማስተማር፣ የአንድነትና እራስን መሥዋዕት የማድረግ ቀን ነው።

የጀርመን ጽኑ ባሃኢዎች ይህንን ቴሌግራም ወደ ታላቋ ቅድስት ቅጠል ላኩ፡-

> የማይተካውን የአብዱል-ባሃን ውድ ሕይወት በማጣታችን አማኞች ሁሉ በጥልቅ አዝነዋል። ቅዱሱ ሃይማኖት መንግስተ-ሰማያዊ ጥበቃ እንዲያገኝ እንጸልያለን እናም ለቃል ኪዳኑ ማዕከል ታማኝ ለመሆንና ለመታዘዝ ቃል እንገባለን።

የቅኝ ግዛቶች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል ለፍልስጤም ከፍተኛ ኮሚሽነር በላኩት ቴሌግራም፡-

> .....በክቡር አብዱል- ባሃ አባስ ሞት የተሰማንን ሀዘን እንገልጻለን፤ በግርማዊው መንግሥት ስም ለባሃኢ ማህበረሰብ መጽናናትን እንገልጻለን።

በፍልስጤም ከፍተኛው ኮሚሽነር በሰር ኸርበርት ሳሙኤል በኩል፣ የግብፅ ከፍተኛ ኮሚሽነር የተከበሩ አለንቢይ፣ የሚከተለውን መልዕክት ኖቬበር 29 ልከዋል፡-

> እባክዎን ለሚቹ ክቡር አብዱል-ባሃ አባስ ኤፍንዲ ዘመዶች እና ለባሃኢ ማህበረሰብ የተከበረ መሪያቸውን በማጣታቸው የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን አስተላልፍ።

በፍልስጤም ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት በኩል የተላለፈው ሌላ መልዕክት የግብፅ ልዩ ኃይል ዋና አዛዥ የላከው ነው፡-

ጄኔራል ኮንግሬቭ ለሚቹ ክቡር አብዱል-ባሃ ቤተሰቦች ጥልቅ ሀዘኑ እንዲተላለፍለት ይለምናል።

በባግዳድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዲሴምበር 8 ቀን ይህንን መልዕክት አስተላልፏል፡-

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክቡር ሰይድ አብዱራህማን ለቅዱስነታቸው አብዱል-ባሃ ቤተሰቦች ሀዘኑን መግለፅ ይፈልጋል።

የናዝሬት ከተማ ታዋቂ ሰው በላኩት ቴሌግራም፡-

> የምስራቅ የቀን ኮከብ በመጥለቁ በጥልቅ ሀዘንና ፀፀት ከእናንተ ጋር እናዝናለን። እኛ ከአምላክ ነን ወደርሱም እንመለሳለን።

ብዙ ተጨማሪ ወደ አብዱል-ባሃ ቤተሰብ የደረሱ የሐዘን መልዕክቶች ነበሩ።

ሾጊ ኤፈንዲ እና ሌዲይ ብሎምፊልድ ስለአብዱል-ባሃ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

> አብዱል-ባሃ በምድር ላይ ያለው ተልዕኮ የሚጠናቀቅበትን ቀን እና ሰዓት ያውቅ እንደነበር አሁን ገብቶናል፣ ወደ ሰማይ መጠለያው

ተመልሷል። እሱ ግን ቤተሰቡ ስለሚመጣው ሀዘን ምንም ዓይነት ቅድመ-ሃዘን እንዳይኖር ጥንቃቄ አድርጓል። ለወዳጆቹ ባለው በፍቅራዊ አሳቢነት ዓይኖቻቸው የተሸፈኑ ይመስል፣ የተለዩ ሕልሞችን ማየት አላስፈለጋቸ ውም ወይንም መጨረሻን የሚያሳይ የምልክቶች ክስ ተት ማየት አልነበረባቸውም። ታላቁን መከራ በሚ መጣበት ጊዜ ለመጋፈጥ ኃይላቸው ተጠብቆ እንዲቆይ የእሱ ሀሳብ መሆኑን ተገንዝበዋል፣ መሆኑ በማይቀር ነገር በአእምሮ ጭንቀት ኃይላቸው መሸመድመድ የለበትም።

ሰዓቱ ሲቃረብ ከብዙ ምልክቶች ውስጥ በምድር ላይ ስለሠራው ሥራ ሲናገር፡- "አብቅቷል" ብሏል። ያያቸው የሚከተሉት ሁለት ሕልሞች አስደናቂ ይመስላሉ። አብዱል-ባሃ ከማለፉ ከስምንት ሳምንታት በፊት ይህንን ህልም ለቤተሰቡ ነግሯቸዋል፡-

"በራሱ በኢማሙ ቦታ...በታላቅ መስጊድ ውስጥ የቆምኩ ይመስለኛል። ብዙ ሰዎች ወደ መስጊድ እየጎረፉ መሆኑን ተረዳሁ፤ ብዙዎች እየተጨናነቁ ገቡ፣ በርካታ እስኪሆኑ ድረስ ከበስተጒላዬ በረድፍ ቦታቸውን ይዘዋል። እንደቆምኩ "ለጸሎት ጥሪ" ከፍ ባለ ድምፅ ተጣራሁ። በድንገት ከመስጊዱ ለመውጣት ሀሳብ መጣልኝ።

"ከዚያም እራሴን ከውጪ አገኘሁት፣ በውስጤ እንዲህ አልኩ፣ "ጸሎቱን ሳልመራ በምን ምክንያት ወጣሁ? ነገር ግን ግድ የለም አልኩ፤

> ምክንያቱም የፀሎት ጥሪውን ስላደረኩ፣ የተሰበሰቡት ሰዎች እራሳቸው ጸሎቱን ያደርጋሉ።”

ካለፈው ሕልም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አብዱል-ባሃ ከጊዜ በኋላ ይኖርበት ከነበረው ከአትክልቱ ሥፍራ አካባቢ ካለው ብቸኛ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ሳለ እንዲህ አለ፡-

> “ሕልም አየሁ የተባረከውን ውበት አየሁት . . መጥቶም “ይህን ክፍል አፍርስ” አለኝ።”

በሌሊት ብቻውን በመሆኑ ደስተኛ ያልሆነው ቤተሰቡ ዋናው ቤት ውስጥ መጥቶ እንዲተኛ ይመኙ ስለነበር፣ እንዲህ አሉ ’ልክ ነው፣ ሕልምህ ያንን ክፍል ትተህ ወደ ዋናው ቤት መግባት አለብህ ማለት ነው።’ ይህንን ከእኛ ሲሰማ በትርጓሜያችን አልተስማማም። ከዚያ በኋላ “ክፍል” ማለት የአካሉ መቅደሱን ማለት መሆኑን ተረዳን።

ቱርካዊው ወዳጅ ዶክተር ሱለይማን ራፋት ቤይ አብዱል-ባሃ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት፣ በእሱ ቤት ውስጥ እንግዳው ነበር፣ እዛ ሳለም የወንድሙን ድንገተኛ ሞት የሚነግረው ቴሌግራም ደረሰው። አብዱል-ባሃ ለእርሱ የማጽናኛ ቃላትን ሲናገር ፣ ’እሱ ከዚህኛው ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ስለተላለፈ አትዘን። እኔም በቅርቡ ወደእዚያ እተላለፋለሁ፣ ቀናቴ በጣት የሚቆጠሩ ሆነዋል’ አለው። ከዚያም ትከሻውን ቀስ ብሎ መታ መታ እያደረገለት፣ ፊቱን እያየ ‘በቅርብ ቀናትም ውስጥ ይሆናል’ አለ።

በዚያው ሳምንት የሚከተለው ጸሎት የሚገኝበትን ጽላት ለአሜሪካ ገለጸ፡-

ያ ባሃ ኤል አብሃ ! (የክቡሮች ክብር ሆይ)፣ እኔ ዓለምን እና ሕዝቦቿን ትቻለሁ፣ በካሐዲዎች የተነሳ ልቤ ተሰብሮ በጣም ተሠቃይቻለሁ። በዚህ ዓለም እስር ቤት ውስጥ እንደፈራች ወፍ እንቀጠቀጣለሁ፣ ወደ መንግሥትህ ለመሄድ በየቀኑ እጓጓለሁ።

ያ ባሃ ኤል አብሃ! የመሥዋዕቱን ጽዋ አጠጣኝና ነፃ አውጣኝ። ከእነዚህ ስቃዮች እና ፈተናዎች፣ ከእነዚህ መከራዎች እና ችግሮች አርቀኝ። አንተ አጋዥ፣ ረጂው፣ ጠባቂው፣ የእርዳታ እጁን የሚዘረጋው ነህና።

በምድር ላይ በቆየበት በመጨረሻው ዓርብ ጠዋት (ኖቬምበር 25) ለሴት ልጆቹ እንዲህ አለ፡- 'የኩህስሩዉ (በአብዱል-ባሃ ቤት ውስጥ ያገለግል የነበረ) ሠርግ ዛሬ መከናወን አለበት። በጣም ከተጨናነቃችሁ እኔ ራሴ አስፈላጊውን ዝግጅት አደርጋለሁ፣ ምክንያቱም ዛሬ መከናወን አለበት። ...'

በዚያው ቀን አብዱል-ባሃ የቀትር ፀሎት ላይ በመስጊድ ተገኘ። ፀሎት ጨርሶ ሲወጣም ዘወትር አርብ እንደተለመደው ምጽዋቱን የሚጠባበቁ ድሆችን አገኘ። በጣም ቢደክመውም ያን ቀንም እንደተለመደው ቆሞ፣ ለእያንዳንዱ ሳንቲሞችን አደለ።

ከምሳ በኋላ የመጨረሻዎቹን የተወሰኑ ጽላቶች፣ ለሩሂ ኤፈንዲ ገለጸ። እረፍት ካደረገ በኋላም በአትክልት ሥፍራው ውስጥ በእግሩ ተንሸራሸረ።

መልካም እና ታማኝ አገልጋዩ ኢስማኢል አቃ የሚከተለውን ተርኳል፡-

"አንዳንድ ጊዜ፣ ጌታዬ (አብዱል-ባሃ) ከመሞቱ ከሃያ ቀናት በፊት፣ በአትክልቱ አቅራቢያ አንድ አዛውንት አማኝን ሲጠራ ሰማሁ፣ እንዲህም አለው፡-

"የአትክልቱን ውበት አብረን እናደንቅ ዘንድ ከእኔ ጋር ና። እነሆ፣ የአምልኮ መንፈስ ምን ሊያሳካ እንደሚችል ተመልከት! ይህ የበለፀገ ቦታ ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ የድንጋይ ክምር ነበር፣ አሁን በቅጠሎች እና በአበቦች ተሞልቷል። ምኞቴ እኔ ከሄድኩ በኋላ ተወዳጆች ሁሉ መለኮታዊውን ጉዳይ ለማገልገል እንዲነሱ ነው፣ እንደዚህ እንዲሆን አምላክን እንማጸናለን። ሳይዘገይም ለዓለም ሕይወትን የሚሰጡ ሰዎች ይነሳሉ።"

'ከጥቂት ቀናት በኋላ እንዲህ አለ፡- "በጣም ደክሞኛል! ሁሉንም ነገር ትቼ የሚሄድበት ጊዜ ደርሷል። ለመራመድ በጣም ደክሞኛል።" አለ ከዚያም ቀጥሎ "በተወደጁ ውበት የመጨረሻ ቀናት፣ በባህጂ በጽሕፈት ቤቱ ክፍሉ ውስጥ በሶፋው ስር ተበታትነው የነበሩት ወረቀቶቹን አንድ ላይ በማሰባሰብ ሥራ ላይ ተጠምጄ ሳለ፣ ወደ እኔ ዞረና እንዲህ አለኝ፣' እነሱን መሰብሰብ ምንም አይጠቅምም፣ ትቼያቸው መሄድ አለብኝ። '

"እኔም ሥራዬን ጨርሻለሁ፣ ተጨማሪ ምንም ማድረግ አልችልም፣ ስለዚህ እኔም ትቼ መሄድ አለብኝ።"

'ከማረጉ ሶስት ቀን በፊት በአትክልቱ ስፍራ ተቀምጦ፣ ጠራኝና እንዲህ አለኝ፣ "በድካም ታምሜያለሁ። ሁለት ብርቱካን አምጣልኝ በአንተ

ስም ልብላቸው” አለኝ፡፡ ይህን አደረግሁ፣ እርሱም ከበላ በኋላ ወደ እኔ ዞሮ፣ እንዲህ አለ “ጣፋጭ ሎሚ አለህን?” ጥቂት እንዳመጣለት ጠየቀኝ … እኔም እየለቀምኩ ሳለሁ፣ ወደ ሎሚው ዛፍ መጥቶ “ በእራሴ እጆች መቅጠፍ አለብኝ” አለ፡፡ በልቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ እኔ ዞር ብሎ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ “ሌላ ከእኔ የምትፈልገው ነገር አለን?” ከዚያም በእጆቹ የአዛኝነት ምልክት እያሳየኝ፣ ልብ በሚነካና በአፅንኦት እንዲህ አለ፡-

“አሁን ተጠናቀቀ፣ ተጠናቀቀ! ” አለ

እነዚህ ጉልህ ቃላት ነፍሴ ውስጥ ዘልቀው ገቡ፡፡ እነዚህን ቃላቶች በተናገረ ቁጥር ልቤ በቢላ እንደተወጋ ያህል ይሰማኛል፡፡ ትርጉሙን ተረድቻለሁ፣ ሆኖም ግን ፍጻሜው እንዲህ በጣም ቀርቧል ብዬ አልገመትኩም ነበር፡፡ ’

ለሠላሳ ዓመታት ገደማ የአብዱል-ባሃ አትክልተኛ የነበረው እስማኢል-አቃ፣ አብዱል-ባሃ ከሞተ ሳምንት በኋላ፣ ተስፋ ቢስ በሆነ ሀዘን ተቆራምዶ፣ ሁሉንም ንብረቶቹን ማንም ሳያውቅ አስወግዶ፣ ፈቃዱን ለማድረግ፣ ወደ አብዱል-ባሃ እህት በመሄድ ለሰራው ማናቸውም በደል ምህረትዋን ጠየቀ፤ ከዚያም የሚንከባከበውን የአትክልት ሥፍራ ቁልፍ ለቤተሰቡ ታማኝ አገልጋይ ሰጠ፣ እራሱን ሊያጠፋበት የሚችል ነገር ይዞ ወደ ተወዳጁ ጌታው መቃብር ወደ ተራራው ቅዱስ ቦታ በመሄድ፣ ቦታውን ሦስት ጊዜ ከዞረው በኋላ ሕይወቱን ለማጥፋት ሞከረ ሆኖም ግን አንድ ወዳጅ እንደአጋጠሚ ስፍራው ላይ ደረሰና ያቀደውን አስደንጋጭ ተግባር እንዳይፈጽም አገደው፡፡

[ወደ ታሪኩ ስንመለስ] ዓርብ አመሻሹ ላይ አብዱል-ባሃ በዚያን ቀን ጋብቻቸውን የፈጸሙትን ሙሽሪትንና ሙሽራ ውን ባረካቸው፡፡ በሚያስደንቅ ሁኔታም ተናገረ፡፡ እንዲህ አለ "ኩህስሩዉ አንተ ልጅነትህንና ወጣትነትህን ይህን ቤት በማገልገል አሳልፈሃል፤ በዚህ ቤት ውስጥ እድሜህን ታሳልፍ ዘንድ፣ ሁልጊዜ እና እስከመቼውም አምላክን ታገለግል ዘንድ ተስፋዬ ነው፡፡" ከዚያም ምሽት ላይ በእራሱ ቤት ውስጥ በሚካሄደው በተለመደው የወዳጆች ስብሰባ ላይ ተገኘ፡፡

ቅዳሜ ኖቬምበር 26 ቀን ማለዳ ላይ ቀደም ብሎ ተነስቶ ወደ ሻይ ክፍሉ መጥቶ ሻይ ጠጣ፡፡ የባሃኡላህ ንብረት የሆነውን ፀጉራሙን ሱፍ ካፖርት እንዲያመጡለት ጠየቀ፡፡ ብዙ ጊዜ ይህን ካፖርት የሚያደርገው ሲበርደው ወይንም ጤንነት ሳይሰማው ሲቀር ነው፣ በጣም የሚወደው ካፖርት ነው፡፡ ከዛም ወደ ክፍሉ ሄደ፣ አልጋውም ላይ ተኛና እንዲህ አለ "አልብሱኝ በርዶኛል፡፡ ትናንትና ማታ በደንብ አልተኛሁም፣ በርዶኝ ነበር፡፡ ይህ ከባድ ነገር ነው፣ መጀመሩ ነው ማለት ነው" አለ፡፡

ተጨማሪ ብርድ ልብስ ከለበሰ በኋላም ቀድሞ ለብሶት የነበረው ፀጉራማ ሱፍ ካፖርት እንዲደረብለት ጠየቀ፡፡ ትኩሳትም ይዞት ነበር፡፡ እየመሸ ሲሄድም ትኩሳቱ ጨመረ [40 ሴንቲግሬድ] ደረሰ፣ ሌሊት ላይ ግን ትኩሳቱ ለቀቀው፡፡

እሁድ ጠዋት ኖቬምበር 27 እንዲህ አለ፡- "እኔ ደህና ነኝ እና እንደተለመደው ተነስቼ ሻይ አብሪያችሁ እጠጣለሁ" አለ፡፡ ልብሱን ከለበሰ በኋላ በክፍሉ ውስጥ ባለው ሶፋ ላይ ቆየ፡፡

ከሰዓት በኋላ ወዳጆችን በሙሉ ወደ ባብ መካነ-መቃብር ላከ፣ የቃል-ኪዳን ቀን ክብረ-በዓልን በማስመልከት በቅርቡ ከሕንድ በመጣ ፋርሳዊ መንፈሳዊ ጎብኚ አማካይነት ግብዣ ተደረገ፡፡

ከሰዓት በኋላ አሥር ሰዓት ላይ በክፍሉ ውስጥ ባለው ሶፋ ላይ ሆኖ፡- “ እህቴ እና መላው ቤተሰብ መጥተው ከእኔ ጋር ሻይ እንዲጠጡ” ሲል ጠየቀ፡፡

ከሻይ በኋላ የሐይፋው ሙፍቲ (የእስልምና ሊቅ)፣ የማዘጋጃ ቤቱ ኃላፊና ሌሎችም ሰዎች ሊጎበኙት መጡ፡፡ ለአንድ ሰዓት ያህል ቆዩ፡፡ ከሁለተኛ ሕልሙ ጋር በተያያዘ ስለባሃኡላህ ነገራቸው፣ ከተለመደው በበለጠ ደግነትና ትህትና አሳያቸው፡፡ ከዚያም ማረፍ አለብህ ብለው ቢማጸኑትም ሊሸኛቸው ወደ ውጭ በሩ ድረስ ሄደ፡፡ ከዚያ ደግሞ እንግሊዛዊው የፖሊስ ኃላፊው ሊጎበኘው መጣ፣ እርሱም ከአብዱል-ባሃ የተትረፈረፈ ደግነት ድርሻውን ተቀበለ፡፡ ከሐር የተሰራ የፐርሺያ መሃረብም ሰጠው፣ እጅግ ምስጋናውን ገለጸ፡፡

አራቱ አማቾቹና ሩሂ ኤፈንዲ የባብ መካነ መቃበር ተራራው ላይ በነበረው ስብሰባ ላይ ከተገኙ በኋላ ወደ አብዱል-ባሃ መጡ፡፡ እንዲህም አሉት “አንተ ባለመገኘትህ በዓሉን ያስከበረው ሰው ደስተኛ አልነበረም፡፡” እርሱም እንዲህ አላቸው፡- “እኔ ግን አካሌ ባይኖርም እዚያ ነበርኩ፣ መንፈሴ በመካከላችሁ ነበር፡፡ በመካነ መቃብሩ ከወዳጆች ጋር አብሬ ነበርኩ፡፡ ወዳጆች በአካል ካለመኖሬ ጋር መያያዝ የለባቸውም፡፡ እኔ ሩቅ ብሆንም በመንፈስ ከወዳጆች ጋር ነኝ፣ ሁል ጊዜም እሆናለሁ፡፡”

በዚያው ቀን ምሽት ላይ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባልን፣ የመንፈሳዊ ጎብኚዎችንና በሐይፋ ያሉ ወዳጆችን ጤንነት ጠየቀ። ሁሉም ደህና መሆናቸው ሲነገረው "በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ" አለ። ይህ ወዳጆችን በተመለከተ የመጨረሻ ቃሉ ነበር።

ከምሽቱ 2 ሰዓት ላይ 'እኔ ደህና ነኝ' ብሎ ትንሽ ምግብ ከበላ በኋላ ወደ አልጋው ሄደ።

ለሁሉም ቤተሰቦቹ እንዲተኙ ነገራቸው። ሁለቱ ሴት ልጆቹ ግን ከእሱ ጋር ቆዩ። በዚያች ምሽት አብዱል-ባሃ ትኩሳት ሳይኖረው በጣም ተረጋግቶ ተኛ። ከሌሊቱ 7 ሰዓት ላይ ነቃ፣ ከአልጋው ወረደና ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ውኃ ጠጣ። 'በጣም ሞቆኛል' በማለት የሌሊት ልብሱን የላይኛውን አወለቀ። ተመልሶ ተኛ፣ በኋላ ላይ ሴት ልጁ ሩሃ ካህኑም አልጋው ጋር ተጠግታ ስታየው በሰላም ተኝቶ አገኘችው፣ ቀና ብሎ አያትና የአልጋውን መጋረጃ እንድትገልጥለት እንዲህ አላት፡-

'ለመተንፈስ ተቸግሬያለሁ፣ የበለጠ አየር ላግኝ።' እንዲጠጣ ጥቂት የጽጌሬዳ ውሃ አመጡለት፣ ለመጠጣትም ማንም ሳይረዳው አልጋው ላይ እንዳለ ቀና አለ። ተመልሶ ከተኛ በኋላም ትንሽ ምግብ አመጡለት፣ ጥርት ባለና ጉልህ በሆነ ድምጽ እንዲህ አላቸው፡-

> 'እየሄድኩ እያለሁ ምግብ እንድበላ ትፈልጋላችሁን?' ደስ በሚል ሁኔታም አያቸው። ፊቱ ላይ እርጋታ አለ፣ ገጽታውም የረጋ ነው፣ እነርሱም የተኛ መስሏቸው ነበር.... ረጅሙ የመስዕዋትነት ዘመኑ አበቃ!

ዶ/ር ፍሎሪያን ክሩግ በፍጥነት ተጠርቶ በችኮላ ደረሰ፣ ሆኖም ግን አብዱል-ባሃ ከሚወዳቸው ሰዎች እይታ ርቆ ሄዷል።

ግሬስ እና ፍሎሪያን ክሩግ፣ ሉዊዝ እና ጆን ቦሽ ከካሊፎርኒያ፣ ኤቴል ሮዘንበርግ ከለንደን፣ እና ፍሉሊን ዮሃና ሀውፍ ከስቱትጋርት በዚያ አስጨናቂ ሰዓት በሐይፋ የተገኙ ምዕራባዊያን መንፈሳዊ ጎብኚዎች ነበሩ፤ እንዲሁም የባብ መካነ-መቃበር ሕንፃ ውስጥ የኤሌክትሪክ ገመድ ለመዘርጋት ሐይፋ የነበረው አሜሪካዊው ከርቲስ ኬልሲም ነበር።

አብዱል-ባሃ ከዚህ ዓለም እንደተለየ ብዙም ሳይቆይ ምዕራባውያን ምዕመናን አስከሬኑ ወዳለበት ክፍል እንዲገቡ ተፈቀደላቸው። ሉዊዝ ቦሽ ዲሴምበር 5 ለኤላ ኩፐር እንዲህ በማለት ጽፋለች፡-

> መጀመሪያ ላይ ዲዳዎች ሆነን ፈዝዘን፣ ግራ ተጋብተን ነበር። ከአልጋው ፊት ቆመንና ተንበርክከን ነበር። ፊቱን አየን ዓይኖቻችንን ማመን አቃተን። በመጨረሻ ግራ መጋባቱ ቀነሰና እውነታው ተተካ። በእውነት ዓይኖቹ ከእንግዲህ ወዲያ አይከፈቱምን? እኛን ለማየት ዓይኖቹ አይገለጡምን? አልሞትኩም ለማለት አንደበቱ አይናገርምን? በወቅቱ ሌሎች ሐኪሞችም ተጠርተው ስለነበር እርግጥ መሞቱን ለማረጋገጥ ሐኪሞቹን ጠየቅናቸው። እነሱም አዎን፣ ልቡ መምታቱን አቁሟል፤ እንደገና ልቡ እንዲመታ ለማድረግ መሞከርም አይቻልም አሉ። ከዛም፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአልጋው ዙሪያ የወባ መከላከያ የሚመስል ስስ መጋረጃ ተደረገ፣ ይህም የጌታችንን

ምድራዊ ቅሪተ-አካል ከዓይናችን ሸፈነው፡፡ ከዛም ተነስተን በአቅራቢያው ወዳለው ክፍል ገባን፣ የእርሱ ክፍል በርም ተዘጋ፡፡

የሃዘን ቁስሎች እንደደም መፍሰስ ጀመሩ፣ በእያንዳንዱ ደቂቃ ለቅሶ፣ ዋይታ እየጨመረ መጣ፡፡ እኛ አምስታችን አውሮፓዊ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ከቅዱሳን ቤተሰቦቹና ከቅዱስ ባለቤቱ ጋር አንድ ክፍል ውስጥ አብረን ነበርን፣ እኔ የባለቤቴን እጅ ይዣለሁ፣ ታላቋ ቅድስት ቅጠል ደግሞ የእኔን እጅ ይዛለች፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቅዱሳን ቤተሰቦችን በነበርንበት ክፍል ውስጥ ትተናቸው እኛ ወደ መንፈሳዊ ጎብኚዎች ማረፊያ ቤት ሄድን፡፡ ሌሊት ነበር፣ ጨረቃም አልነበረችም፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላም ከዚያ ከማይረሳ ምሽት በኋላ ማለዳ ወገግ አለ፣ ፀሐይም በታላቅ ግርማዋ መውጣት ጀመረች…

የሾጊ ኤፌንዲ እና የሌዲ ብሎምፊልድ ቃላት ደግሞ፡-

ወዳጆችንም ሆነ ጠላቶችን ለሰብዓዊ ፍጡር በሚሆን በፍቅራዊ ደግነት የሚመለከቱ ዓይኖቹ አሁን ተከድነዋል፡፡ ለድሆች እና ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡት፣ ለተሰበሩና ለጉዳተኞች፣ ለዓይነ ስውራን፣ ለወላጅ አልባዎችና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ምጽዋት ለመስጠት የተዘረጉ እጆች አሁን በድካም የተሞላ ሥራቸውን አጠናቅቀዋል፡፡ ሳያቋርጡ ይጓዙ የነበሩት፣ የሩሁሩሀ ጌታ ተልዕኮዎች የነበራቸው የማይደክሙት እግሮቹ አሁን አርፈዋል፡፡ በመከራ ውስጥ ለሚገኙት የሰው ልጆች መንስኤ በአንደበተ-ርቱዕነት ይናገር የነበረው አንደበቱ አሁን በዝምታ ተውጠዋል፡፡ ለአምላክ

> ፍጡር ለሆኑ ለሰው ልጆች የሚያስደንቅ እጅግ ኃያል ፍቅር የሚያሳይ የነበረው ልብ አሁን ጸጥ ብሏል። ከጽድቅ ጠላቶች ጭቆናና ለሌላው መልካም ለማድረግ ወደ ሰማንያ ዓመት ለሚጠጋ በማዕበል እና በውጥረት ውስጥ ያደረገው ድካም አልፎ የከበረ መንፈሱ ምድራዊ ሕይወትን ተሸጋገረ።

ሀዘን እና ጭንቀት በጣም እያየለ መጣ። ሆኖም ግን ዝግጅት መደረግ ስለነበረበት ውሳኔዎች መወሰድ ነበረ ባቸው። በመጀመሪያ የአብዱል-ባሃ ቅሪተ-አካል የት ይረፍ የሚለው ነበር? የባብ ቅሪተ-አካል ካረፈበት ከመሬት በታች ከተገነባው ሳጥን መሰል ግንባታ አጠገብ ሌላ ተመሳሳይ ግንባታ እንዳለ ስላስታወሱ፣ ታላቋ ቅድስት ቅጠል የአብዱል-ባሃ መቃብር እዚያ እንዲሆን ወሰነች። ተገቢ የሆነ የሬሳ ሣጥን ወዲያው ተገኘ፣ የአብዱል- ባሃ አማችና ጆን ቦሽ ቅሪተ-አካሉን በሬሳ ሣጥን ውስጥ ተረዳድተው አስገቡ።

የአብዱል-ባሃ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በቅድስት አገር ታይቶ የማይታወቅ ነበር፦

> የፍልስጤም ከፍተኛ ኮሚሽነር ክቡር ኸርበርት ሳሙኤል፣ የኢየሩሳሌም ገዥ፣ ፎኒሲያ (ምስራቃዊ ሜዲትራኒያን፣ በዋነኝነት የአሁኑ ሊባኖስና አካባቢው) ገዥ፣ የመንግሥት ዋና ባለሥልጣናት፣ የተለያዩ አገር ቆንስላዎች፣ የሐይፋ ነዋሪዎች፣ የተለያዩ የሃይማኖት ማህበረሰብ መሪዎች፣ የፍልስጤም ታዋቂ ሰዎች፣ አይሁዶች፣ ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞች፣ ድሩዞዎች፣ ግብፃውያን፣ ግሪኮች፣ ቱርኮች፣ ኩርዶች እና የአሜሪካና የአውሮፓ ምዕመናኖች፣ ወንዶች፣

ሴቶች እና ልጆች፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሁሉም ከፍተኛና ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎች፣ የሚወዱትን ሰው በሞት በማጣታቸው አዘኑ።

ይህ አስደናቂ፣ የሰልፍ ሽኝት የከተማውን የፖሊስ ሠራዊት ያካተተ በክቡር ዘበኛ የሚመራ ሲሆን፣ የሙስሊምና የክርስቲያን ማህበረሰብ ወጣት ሰልፈኞችን፣ ከቁርዓን ጥቅሶች የሚያዜሙ የሙስሊም መዘምራንን፣ በሙፍቲው የሚመራ የሙስሊም ማህበረሰብ አለቆችንና በርካታ የክርስትና ካህናትን፣ ላቲኖችን፣ ግሪኮችንና አንግሊካኖችን የጨመረ ነበር። ሁሉም በተወዳጆቹ ትከሻ ላይ ያረፈውን ቅዱስ የሬሳ ሣጥን አጀቡ። ከአጃቢዎቹ ቀጥሎ የቤተሰቡ አባላት ተከተሉ፣ ከእነሱ ጋር የእንግሊዝ ከፍተኛ ኮሚሽነር፣ የኢየሩሳሌምና የፎኒሲያ ገዥ አብረው ነበሩ። ከእነሱ በኋላም ቆንስሎች እና የአገሪቱ መኳንንት ተከተሉ፣ እርሱን የሚያከብሩትና የሚወዱት እጅግ ብዙ ሕዝቦችም አጀቡት።

ከእስልምና ለስላሳ ዜማዊ የጸሎት ጥሪ እና እነዚያ አቅመ ደካሞች በተወዳጃቸው ሞት ምክንያት ከሚያሰሙት የለቅሶ ጩኸት በስተቀር በከተማውና በዙሪያው ባለው መንድር ሁሉ ድምፅ አልነበረም፣ …

ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ልብ እንዲህ ሲል አለቀሰ 'አምላኬ አምላኬ ሆይ! አባታችን ጥሎን ሄደ፣ አባታችን ጥሎን ሄደ!'

አቤት የዚያ የተሰበሰበ ብዙ ሕዝብ ትንግርት! በአብዱል-ባሃ የሕይወት ዘመን አገልግሎት ክስተት ምክንያት የእያንዳንዱ ሃይማኖት እና የእያንዳንዱ ዘርና ቀለም ሕዝቦች ከልብ ተዋሃዱ!

የእግዚአብሔር የወይን እርሻ ወደ ሆነው ወደ ቀርሜሎስ ተራራ በእርጋታ ሲጓዙ፣ ሣጥኑ በማይታይ እጆች እንደተያዘ ያህል ከርቀት፣ ከሕዝቡ ራስ በላይ ከፍ ብሎ ይታያል፡፡ ከሁለት ሰዓታት የእግር ጉዞ በኂላ የባብ መካነ- መቃ ብር የአትክልት ስፍራ ደረሱ፡፡ በተስተካከለ ነጭ ሐር ጨርቅ በተሸፈነ ጠረጴዛ ላይ የተቀደሰ የሬሳ ሣጥኑም በጥንቃቄ ተቀመጠ፡፡ ሰፊው ታዳሚ በቅሪተ-አካሉ ዙሪያ ተሰበሰቡ፣ ከዚያም የባብ ቅሪተ-አካል ካለበት ጎን ከመሬት በታች ባለው የማረፊያ ቦታው ውስጥ እስኪያርፍ ድረስ የተለያዩ ቤተ-እምነቶች፣ የሙስሊሞች፣ የክርስቲያኖች እና የአይሁድ ተወካዮች፣ ሁሉም ልቦች በአብዱል-ባሃ ጥልቅ ፍቅር ተቃጥለው፣ አንዳንዶች በሁኔታው ተነሳስተው፣ ሌሎች ቀድመውም ተዘጋጅተው ስለነበር ፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በጸሎት እና በፀፀት፣ ለሚወዱት ሰው የመጨረሻውን የስንብት ክብር ሰጡ፡፡

ቀጥሎ የተወሰዱት በዚያ የማይረሳ ሥነ-ሥርዓት ላይ ከተደረጉት አንዳንድ ንግግሮች ውስጥ ነው፡፡

የመጀመሪያው ተናጋሪ ፣ ታዋቂው ሙስሊም ዩሱፍ አል-ከቲብ ነበር፡-

የአረብንና የፋርስ ታዳሚዎች ሆይ! አሁን የምታለቅሱለት ለማን ነው? ትናንት በሕይወቱ ታላቅ የነበረና ዛሬም በሞቱ የበለጠ ታላቅ ስለሆነው አይደል? ወደ ዘለዓለማዊው ዓለም ለሄደ ሰው እንባን አታፍስሱ ፣ ነገር ግን በኀነት እና ጥበብ ፣ ዕውቀት እና ለጋስነት በመቅረቱ አልቅሱ። ለራሳችሁ አልቅሱ፣ ያጣችሁት እናንተ ናችሁና፣ እሱ ያጣችሁት ከሟች ዓለም ወደ ዘላለማዊ ቤት የሚሄድ የተከበረ መንገደኛ ነው። ስለ እርሱ ስትሉ አንድ ሰዓት አልቅሱ፣ እርሱ ወደ ሰማንያ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ ያህል አል ቅሶላችኋልና! ምን ያህል ክብርና ታላቅነት እንደጠፋ ወደ ቀኝ ተመልከቱ ፣ ወደ ግራ ተመልከቱ ፣ ወደ ምሥራቅ እዩ እና ወደ ምዕራብም እዩ! እንዴት ያለ የሰላም ዓምድ ፈረሰ! እንዴት ያሉ አንደበተ ርቱዕ ከንፈሮች ጸጥ አሉ! ያሳዝናል! በዚህ መከራ ውስጥ በጭንቀት ያልታመመ ልብ የለም ፣ በእንባ ያልተሞላ ዓይንም የለም። ለድሆች ወዮላቸው! መልካምነት ከአጠገባቸው ጠፋ፣ ወላጅ አልባ ለሆኑት ወየውላቸው! አፍቃሪ አባታቸው ተለያቸው። በብዙ ውድ ነፍሶች መስዋዕትነት የአብዱል-ባሃ አባስ ሕይወት ሊተካ ይችል ነበር? እነሱ በእርግጠኝነት ሕይወታቸውን ለሕይወቱ ይሰጡ ነበር። ነገር ግን ዕጣ ፈንታ በሌላ መንገድ ደንግጓል። እያንዳንዱ ዕጣ ፈንታ አስቀድሞ ተወስኗል እናም ማንም መለኮታዊውን ድንጋጌ መለወጥ አይችልም። የዚህን የሰው ልጅ መሪ ስኬቶች ለመዘርዘር እኔ ማን ነኝ? ከሙገሳ በላይ ናቸው፣ ለመዘርዘርም ብዙ ናቸው። እሱ በልቦች ውስጥ እጅግ ጥልቅ ስሜቶችን፣

> በሁሉም አንደበቶች ውስጥ እጅግ አስደናቂ ውዳሴዎችን ትቶ አልፏል ማለቱ ይበቃል። የሚወደድ ትዝታ ትቷል፣ እርሱ በእውነቱ የማይጠፋ ነው፤ አልሞተም። የባሃ ሕዝቦች ሆይ ተጽናኑ! ቻሉ፣ ታገሱ፤ ማንም የምሥራቅ ወይም የምዕራብ ሰው ሊያጽናናችሁ አይችልም፣ እነሱ እራሳቸው የበለጠ አጽናኝ ይፈልጋሉ።

በእርግጥ ያዘኑት ድሆች አንዳቸው ለአንዳቸው እንዲህ ተባባሉ፡- 'እኛ ከአሁን በኋላ ምን እንሆናለን? ማን ይንከባከበናል? እኛ ተንከባካቢ አልባ ሆንን። ከመሞት በስተቀር ምን ማድረግ እንችላለን'

ቀጣዩ ተናጋሪ የተከበረው የክርስቲያን ጸሐፊ አብራሃም ናስር ሲሆን እንዲህ አለ፡-

> ጌታዬ ስለሞተ ለዓለም አለቅሳለሁ፤ ሌሎችም እንደ እኔ በጌታቸው ሞት የሚያለቅሱ አሉ።..በዚህ ልብ በሚነካ እጦት ምክንያት የተፈጠረው ጭንቀት መራራ ነው! የአገራችን ኪሳራ ብቻ ሳይሆን የዓለም መከራ ነው።...የአምላክ መልእክተኞችንና ሐዋርያ ቶችን ሕይወት ለሰማንያ ዓመታት ያህል ኖሮታል። እርሱ የሰዎችን ነፍስ አስተምሯል፣ ለእነሱ ቸር ሆኖላቸዋል፣ ወደ እውነት መንገድ መርቷቸዋል። ስለዚህ ሕዝቡን ወደ ክብር ጫፍ ከፍ አድርጓል፣ በአምላክ ዘንድ የጻድቃን ዋጋ ታላቅ ነው። ስሙኝ ሰዎች ሆይ! አባስ አልሞተም፣ የባሃ ብርሃንም አልጠፋም! ይህ ብርሃን በዘላለማዊ ግርማ ያበራል። የባሃ ብርሃን፣ አባስ(አብዱል-ባሃ) ጥሩ ሕይወት ኖሯል፣ እውነተኛ የመንፈስ ሕይወትን በራሱ ውስጥ ከስቷል። ንፁህ መልአክ የሆነው፣ በበጎ

> ተግባሮች የበለፀገው ፣ በክቡር ባሕሪያቱ የተከበረው አሁን ወደ ክብር ተሰብስቧል። የክርስትና እምነት ተከታዮች ሆይ! በእውነት የዚህን የተለቀሰለትን ሰው ሟች ቀሪተ-አካል እስከ መጨረሻው ማረፊያው ድረስ ተሸክማችኋል፣ አባስ በድርጊቶቹ፣ በቃላቱ፣ በበጎነቱና በሁሉም የሕይወቱ ይዘት በመካከላችሁ በመንፈስ ለዘላለም እንደሚኖር በእርግጠኝነት እወቁ። እኛ የአባስን ቁሳዊ አካል እንሰናበታለን፣ ቁሳዊ አካሉ ከእይታችን ጠፍቷል፣ ግን እውነተኛው፣ የእኛ መንፈሳዊ አባስ፣ ከአእምሯችን፣ ከሀሳባችን፣ ከልባችን፣ ከአንደበታችን በጭራሽ አይጠፋም።

ሌላው ታዋቂ ሙስሊም አብዱላህ ሙክሊስ የሐይፋን ሙፍቲ ተከትሎ እንዲህ አለ፡-

> …የዕውቀት ፀሐይ ጠለቀች፤ የመልካምነት ጨረቃ ጠፋች፤ የክብር ዙፋን ፈረሰ፣ ይህ ቸር ሰው ከሟች ዓለም ወደማይሞትው ዓለም በመሄዱ የደግነት ተራራ ዝቅ አለ። ያጣነውን የታላቁን ልዕልና መገለጽ ወይንም ታላላቅ ባሕርያቱን መዘርዘር አያስፈልገኝም፣ ፍትሃዊ የሆናችሁ ሁሉ ምስክሮች ናችሁ እናም ስለግል ውበቱ ማለትም የባህሪው ውበት፣ የልቡ ታላቅነት ፣ የእውቀቱ እና የለጋስነቱ ባህር ስፋት መመስከር ትችላላችሁ… ታማኝነትን በተመለከተ ግዴታዬን ባለመወጣቴ ወይንም ለተለየን ሰው የሚገባውን ከፍ ያለ ምስጋና ማቅረብ ካልቻልኩ ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ምክንያቱም አንደበቴ የሚናገረው ከልብ ትውስታና ከተሰበረ ልብ የመነጨ ነው። በእርግጥ እነዚህ ቁስሎች እንጂ

> ቃላት አይደሉም፤ እንባዎች እንጂ የቃላት ሐረጎች አይደሉም። ‘ይህ ቅስፈተ-አደጋ ከዚህ በፊት የነበሩት ቅስፈቶች ሁሉ እንዲረሱ አድርጓቸዋል። ይህ ቅስፈተ-አደጋ ግን መቼም አይረሳም። ’

በመቀጠል ሼክ ዩኑስ አል-ከቲብ ፣ የሙስሊም ባለቅኔና ገጣሚ ያቀናበረውን ግጥም አነበበ፤ በመቀጠልም በተለይ በአብዱል-ባሃ የሰብአዊነት ሥራዎች ፣ ለድሆች ባለው ልግስና፣ በመስህቡ እና ግርማ ሞገስ ላይ ያተኮሩት የሐይፋ የግሪክ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ኃላፊ የሆኑት ጳጳስ ባሲሊሲ ተከተሉት። ከዚያም የወጣቱ ተራ ደረሰና አክብሮቱንና አድናቆቱን ለመክፈል መጣ። ዋዲ ’ቡስታኒ የተባለ ወጣት ክርስቲያን ግጥም አቀረበ።…

ስምንተኛው ተናጋሪ የሐይፋ የአይሁድ ማሕበረሰብ ግንባር ቀደም ሰው ከሆኑት አንዱ ሰሎሞን ቡዛግሎ ሲሆኑ በፈረንሣይኛ በአንደበተ ርቱዕነት ተናገሩ ።

የንግግራቸው ትርጉም፡-

> በከባድ ፍቅረ ንዋይ እና በእምነት ማነስ ዘመን እኛ አሁን እያዘንን ያለነው እሱ ታላቁ ፈላስፋ አብዱል-ባሃ አባስ መከሰቱ በእርግጥ እንግዳ ነገር ነው። ለልባችንና፣ ለህሊናችን ተናግሯል። የተጠማውን ነፍሳችንንም የሃይማኖትና የሞራል ሁሉ መሠረት በሆኑ ትምህርቶቹና መርሆዎቹ አርክቶልናል። በጽሑፎቹ፣ በአደባባይ ንግግሮቹ እና በግል ውይይቶቹ ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ የተማረውንና እጅግ አክራሪውን ማሳመን ይችላል። ከራስ ይልቅ የሌሎችን መልካም ነገር በመምረጡ ሕይወቱ

የራስን ጥቅም መስዕዋት የማድረግ ሕያው ምሳሌ ነበር።

የአብዱል-ባሃ ፍልስፍና ቀላልና ግልጽ ነው። ከሰው ባህሪይ ጋር ይስማማል። የእሱ በጎነቶች ጭፍን ጥላቻንና አጉል እምነትን ያሸንፋሉ… አባስ ነቢያት በሚከሰቱበት ቅድስት ምድር በሐይፋ ፍልስጤም ውስጥ አረፈ። የዚህች ምድር ጥንታዊው ክብር ተመልሷል። ስለ እርሱ የምናለቅሰው እኛ በእርሱ የምንኮራው ብቻ አይደለንም። በአውሮፓ፣ በአሜሪካ በየአገሩ፣ ለማህበራዊ ፍትህ እና ለወንድማማችነት የተጠሙ ሰዎችም ስለእርሱ ያለቅሳሉ። ለበርካታ አሥርተ ዓመታት በአካ ኦቶማኖች እስረኛ አድርገውታል። ባግዳድ ለእሱ እና ለአባቱ እስር ቤት ሆኖ አገልግሏል። ፋርስ የጥንታዊ መለኮታዊ ፍልስፍና መቀመጫ መርሆዎቹን በአገሯ የጠነሰሰውን ልጇን አውጥታ ጣለች። ቅድስቲቱን ምድር እንደገና የከበሩ የልጋስና መርሆዎች መገኛ እንድትሆን ማድረጉ የመለኮታዊ ፈቃድ መከሰትን ማየት አንችልምን?

ከመሐመድ ሳፋዲ ግጥም ጥቂት መስመሮች እነሆ፡-

እሁድ ምሽት ሰማይ ተከፈተ እና የአብዱል-ባሃ መንፈስ ከነክብሩ አረገ።

ነቢያቶች አቀባበል አድርገውለት አስተናገዱት።…

የቀርሜሎስ ተራራ ሆይ ፣ አሁን ከሰማይ ይልቅ ኩሩ ሆንሽ ፣

አንቺ ቅዱስ ተራራ ሆነሻልና። …

በሕይወት እስካለሁ ድረስ ለአንቺ አለቅሳለሁ ፤

ስንት ጊዜ በእጆችሽ እንባቸውን ጠረግሽላቸው።…

የቀብር ሥነ ሥርዓት ንግግሮች ተደረጉ ፣ ሌሎቹን ባለሥልጣናት ተከተሎ ከፍተኛ ኮሚሽነሩም አክብሮቱን ገለጸ፡፡

…ከዚያ የአፍቃሪነት ዕንቁ ከያዘው የሬሳ ሣጥን በዝግታ እና ግርማ ወደ ተቀደሰው የእረፍት ቦታው ሄደ፡፡

ወሰን የለሽ አዛኞች ሆይ! የተወዳጁ እግሮች ከእንግዲህ ወዲያ በዚህች ምድር ላይ አይራመዱም! እንዲህ ዓይነቱን አምልኮ እና አክብሮት ያነሳሳው መገኘቱ አበቃ!

ሾጊ ኤፌንዲ እና ሌዲ ብሎምፊልድ እንዲህ ጽፈዋል፡-

በመላው ምስራቅ እና ምዕራብ ስለዚህ ታላቅ ክስተት በመጽሔቶቻቸው ገጾች ውስጥ ከሰጡት ብዙ እና የተለያዩ ዘገባዎች ውስጥ የሚከተለው ቀዳሚ ነው፡፡

Le Temps ፣ የሚባለው የፈረንሣይ ዋና ጋዜጣ በዲሴምበር 19 ቀን 1921 እትሙ፣ ሰላም ፈጣሪ በሚለው ርዕሱ ስር፣ የአብዱል-ባሃን ሕይወት በሚዳሰስ መልኩ ገልጿል፡፡

የእንግሊዙ እለታዊ ጋዜጣ፣ አብዱል-ባሃ ከአረፈ ከሁለት ቀናት በኋላ፣ ልዩ ዘገባ ከሰጡት ጋዜጦች መካከል አንዱ ነው፣ ዘገባውን ያጠቃለለውም በእነዚህ ቃላቶች ነበር፡-

የተከበረው ባሃኡላህ በ1892 አረፈ፣ የሃይማኖቱ ኃላፊነት በልጁ በአብዱል-ባሃ እጅ ላይ ወደቀ፣ ከአርባ ዓመታት የእስራት ሕይወት በኋላ የቱርክ መንግሥት ሲለወጥ እንግሊዝን፣ ፈረንሣይን እና አሜሪካን እንዲጎበኝ ፈቀዱለት። የሰው ልጅ አመጣጡ መለኮታዊ ምንጭነት እንዳለውና አንድ እንደሆነ የሚገልጹት የማያቋርጥ መልእክቶቹ እንደ እራሱ እንደመልዕክተኛው (እንደባሃኡላህ) አስደናቂ ነበሩ። እሱ ልዩ የሆነ ጨዋነት ነበረው። በጠረጴዛው ዙሪያ ቡድሂስት እና ሙስሊም፣ ሂንዱ እና ዞሮአስትሪያን አይሁድ እና ክርስቲያን፣ በፍቅር ይቀመጣሉ። "በሰላም እና በፍቅር ይኑሩ ዘንድ ፍጥረታት በፍቅር ተፈጥረዋል።" ይላል

"የኒውዮርክ ዓለም" የሚባለው ጋዜጣ ዲሴምበር 1921 የሚከተለውን አትሟል፡-

"ከአብዱል-ባሃ በቀር ከዚህ በፊት የምስራቃዊያን ሃይማኖታዊ ንቅናቄ መሪ አሜሪካንን ጎብኝቶ አያውቅም... በዚያው ዓመት ጁን ወር ላይ አንድ ልዩ ዘጋቢ ሲገልጸው፡- " አንዴ አብዱል-ባሃን ከተመለከ ትን ፣ ስብዕናው በአእምሮ ውስጥ ዘልቆ ይገባል፤ ግርማ ሞገስ የተላበሰው የተከበረ ገጽታው በካባው ውስጥ ተሸፍኗል፣ እራሱ ላይ ያለው ጥምጣም እንደ ፀጉሩ ነጭ ነው፤ ጠልቀው የሚያዩት ዓይኖቹ ልብን ያናውጣሉ፤ ጣፋጭ ፈገግታው ከሁሉም አቅጣጫ ይፈሳል።"

'በሕይወቱ ማብቂያ ላይ እንኳን' አብዱል-ባሃ በዓለም ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ ነበር ። ጄኔራል አለንቢ በግብፅ በኩል አድርጎ ወደ ሐይፋ እስራኤል

ሲገባ መጀመሪያ ለመማከር ወደ አብዱል-ባሃ ሄዶ ነበር። ጽዮናውያን ወደ ተስፋይቱ ምድራቸው እስራዔል ሲገቡ የአብዱል-ባሃን ምክር ጠይቀው ነበር ። እርሱ ለፍልስጤም ብሩህ ተስፋ ነበረው። “የሰው ልጅ ዓለም ወንድና ሴት የሆኑ ሁለት ክንፎች አሉት፣ አንዱ ክንፍ ደካማ ከሆነ ወፏ መብረር አትችልም” በማለት የወንዶችን እና የሴትቶችን እኩልነት አስተምሯል።

የሕንድ ጋዜጣ በጃንዋሪ 1922 እትሙ እንደሚከተለው ዘግቧል፡-

የአብዱል-ባሃ ህልፈት በቦምቤይ በባሃኢ ኮንፈረንስ ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ ባይነገር ኖሮ፣ የባሃኢ ወንድማማችነት አባል ባልሆኑ ብዙ ሰዎች ዘንድ ስሜትን በቀሰቀሰና ለመርሆዎቹ የድጋፍ ስሜት ባሳዩና የመሥራቾቹንም ሕይወት በዘከሩ ነበር። እኛ የዚህ ታላቅ ሃይማኖት መሪ ሞትን በአጋጣሚ ሰምተናል፣ የፖለቲካና የዘመኑ ክስተቶች ሁከት ወደ ኋላ ከመመለስ ሳያግደን ይህ ሰው ያደረገውንና ትኩረት የሰጠውን አጢነናል።

የእንቅስቃሴውን ታሪክ ዘገባ በአጭሩ በመዳሰስ እንደሚከተለው ይደመድማል፡-

’ታላቁ መሪያቸው ከአለፈ በኋላ ንፁህነቱን፣ መንፈሳዊ ምስጢሩንና ከፍ ያለ የባሃይዝም ሀሳቦቹን ሳይለወጥ ይቀ ጥል እንደሆነ ለመፍረድ ለእኛ አሁን የሚገባ አይደለም ወይንም ባሃኢዝም አንድ ቀን በዓለም ውስጥ እንደክርስትና ወይም እንደእስልምና ታላቅ ይሆናል የሚል ግምት ለመገመት አይደለም፤

ሆኖም ግን መልካም ሰፊ ተጽዕኖ ለነበረው ሰው መታሰቢያውን ለመዘከር ነው፣… ’

ወደ ሜጀር ቴዎዶር ፖል ማስታወሻ ስንመለስ፡-

መጻፍ ስጀምር አንዳንድ ትዝታዎች በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ እኔ ይመጣሉ። ለንደን ከተማ ባለ ቤተ-መቅደስ መድረክ ላይ ከአብዱል-ባሃ አጠገብ ቆሜ ፣ ከአምስት ሺህ (5000) በላይ ሰዎች ደምጽ ሳያሰሙ ቁጭ ብለው የአብዱል-ባሃን፣ ሕይወት ያላቸውን መንፈሳዊ ቃላቶችን ሲያዳምጡና ፈገግታውንና እንቅስቃሴውን ሲያዩ ትዝ ይለኛል።

እ.ኤ.አ. በ1911 ክሊፍተን በሚባል እንግሊዝ አገር ውስጥ ባለ ጫካ ከእርሱ ጋር በእግራችን እየተጓዝን ሳለ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መንፈሳዊ ህዳሴ ስለመምጣቱ ሲናገር አስታውሳለሁ፤ በተጨማሪም በ 1913 ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል በፈረንሳይ ሴይን ወንዝ ዳር እየተረማመደ፣ ስለሚመጣው ታላቁ ጦር ነትና ከዚያም ስለሚመሰረተው ሰላም ሲናገር ትዝ ይለኛል።

ራምሌህ እስክንድርያ በዘንባባው ጥላ ሥር ከእሱ አጠገብ ተቀምጬ፣ ስለሰው ልጅ አንድነት መሠረታዊ አስፈላጊነት ሲናገር አስታውሳለሁ። በዚያ አጋጣሚ ክርስቲያኖች፣ አይሁዶች፣ ሙስሊሞች፣ ፋርሲዎች፣ ሂንዱዎች እና ነፃ አስተሳሰብ አራማጆች በዙሪያው ተቀምጠው ነበር፣ ሁሉም በአንድ እምነት እና አመለካከት አንድ ሆነው ነበር።

በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ከአብዱል-ባሃ ጋር ብቻዬን ስሄድ፣ በሀይፋ ቤቱ ውስጥ መጠነኛ የሆኑ ምግቦቹን አብሬ ስካፈል ፣ በመቃብር ዙሪያ ባለው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ዜማውን ሳዳምጥ፣ አካ በሚገኘው የባሃኡላህ ቤት ውስጥ ከቤተሰቡ አንዱ ሆኜ ስኖር ትዝ ይለኛል።

እነዚህን ቃላት የሚያነቡ ወዳጆች በራሳቸው ተሞክሮ ውስጥ ብዙ ተመሳሳይ ትዕይንቶችን ወደ ትውስታ ያመጣሉ፣ እንደዚህ ላሉት ትዝታዎች ሁል ጊዜ አመስጋኝ ሆነው ይኖራሉ።

ሞት የለም። አብዱል-ባሃ በአጠገባችን ይኖራል፣ ለሰው ልጅ ቤዛነት የሚሆነው ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ ያለማቋረጥ ወደፊት ይገሰግሳል።

ምንም እንኳን የአሁኑ ሰዓት የዓለም መከራዎች ቢኖሩም፣ የአዲስ ቀን ጎህ ተቃርቧል፣ ለዓለም ሰላም እና ለእውነተኛ ሰብአዊ ወንድማማችነት ባለመረበሽ እና በጽናት የመሥራት የእያንዳንዱ ወንድ እና ሴት የዕለት ተዕለት መብት(ዕድል) ነው።

የባብ፣ የባሃኡላህ እና የአብዱል-ባሃ፣ እናም የሁሉም የከፍተኛው ጉባኤ መንፈሳዊ ሠራዊት በረከት አሁንም፣ሁልጊዜም በእኛ ላይ ይኑር።

የሾጊ ኤፈንዲ እና የሌዲ ብሎሚፊልድ ገለጻ ሲቀጥል፡-

አብዱል-ባሃ ካለፈ በኋላ በሰባተኛው ቀን፣ እርሱ ሁል ጊዜ ወዳጃቸውና ጠባቂያቸው ለሆኑት፣ በሺህ ለሚቆጠሩ የሐይፋ ድሆች ፣ ዘር ወይም ሃይማኖት ሳይለይ በስሙ በቆሎ ተከፋፈለ። 'የድሆች አባት'

የሆነውን በማጣታቸው ሐዘናቸው እጅግ ጥልቅ ነበር። በመጀመሪያዎቹ ሰባት ቀናት ውስጥ ከሃምሳ እስከ መቶ ድሆች በየቀኑ በአብዱል-ባሃ ቤት ይመገቡ ነበር ፣…

በአርባኛው ቀን ለሐይፋ ፣ለአካ ሰዎች እና በዙሪያው ላሉ የፍልስጤም፣ የሶሪያ ሰዎች፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ ዘር እና ቀለም ላላቸው ከስድስት መቶ ለሚበልጡ ሰዎች የዝክር ግብዣ ተደረገ። በተጨማሪም ከመቶ በላይ የሚሆኑ ድሆችም በዚሁ ቀን ተመግበዋል። የፎኒሺያ ገዥ፣ ሌሎች ብዙ ባለሥልጣናት እና አንዳንድ አውሮፓውያን ተገኝተው ነበር።

ግብዣው ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀው በአብዱል-ባሃ ቤተሰብ አባላት ነበር። ረጃጅሞቹን ጠረጴዛዎች በቦጋንቪል ሐርግ አበቦችና ቅርንጫፎች አስጌጡት፣ በጣም የሚያምር የቦጋንቪል ሐምራዊ አበባ ከነጭ ዳቮዲል ከሚባል አበባ ጋር ተዋህዶ አስዋበው፣ ከተወዳጁ መምህር(አብዱል-ባሃ) የአትክልት ስፍራ ውስጥ ከተቀጠፉት ወርቃማ ብርቱካኖች ጋር ሲዋሃድ በዚያ ሰፊ ክፍል ውስጥ የፍቅርን ምስል ሠሩ፣ ሌላው ክፍሉን ያስዋበው፣ ብርቅየው በተለያዩ ቀለማት ያማረው የፋርስ ምንጣፍ ነበር።

በአብዱል-ባሃ ቤት ሁልጊዜም እንደሚደረገው አንዱን ከአንዱ ሳያበላልጡ፣ እንግዶቻቸውን ሁሉንም በአንድ ዓይነት ክብር ተቀበሏቸው።

የፎኒሺያ ገዥ፣ የሚከተለውን ተናገረ፡-… ’ብዙዎቻችን ስለ ሰር አብዱል-ባሃ አባስ ግልፅ እይታ

> ያለን ይመስለኛል ፣ ክብር በተመላው ሁኔታ በጎደናዎች ላይ ሲራመድ፣ ጨዋነት እና ለጋስነት የተሞላበት ደግነቱ፣ ለትንንሽ ልጆች ያለው ፍቅር፣ ለድሆች ያለው ለጋስነት እና እንክብካቤ፣ በጣም ጨዋ፣ በጣም ትሁት ከመሆኑም የተነሳ የትኛውም ሰው በእርሱ ፊት እራሱን ይረሳል ማለት ይቻላል። እርሱ ታላቅ አስተማሪ ነበር፣ ጽሑፎቹ እና ንግግሮቹ በምስራቅና በምዕራብ ለሚገኙ በመቶዎች እና በሺህዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች መጽናኛ እና መነቃቂያ ናቸው።…'
>
> ሌሎችም በተከታታይ ስለአብዱል-ባሃ ሥራ እና ሕይወት በማድነቅ ተናገሩ።

ለሾጌ ኤፊንዲ በአደራ በታሸገ ፖስታ ውስጥ የተቀመጠው የአብዱል-ባሃ ኑዛዜ እና ቃል-ኪዳን በታላቋ ቅድስት ቅጠል እጅ ነበር። ሾጊ ኤፊንዲ ሐይፋ እስኪደርስ ድረስ ሳይከፈት ቆይቷል። ከዚያም ታላቋ ቅድስት ቅጠል እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 16 ቀን ለመላው ባሃኢ ዓለም የሚከተለውን ቴሌግራም ላከች፦

> በኑዛዜው መሠረት፣ ሾጊ ኤፌንዲ የእምነቱ ሞግዚት እና የቤተ-ፍትህ ኃላፊ ሆኖ ተሹሟል።

ከመሞቱ ጥቂት ዓመታት በፊት ይህንን መቅድም የያዘውን ጸሎት አብዱል-ባሃ ገልጾ ነበር።

ይህን ፀሎት በትህትናና በጋለ ስሜት የሚያደርግ ማንም ሰው፣ ለዚህ አገልጋይ ልብ ደስታንና ሐሴትን ያስገኛል፤ እንዲያውም እርሱን ፊት ለፊት እንደማግኘት ይቆጠራል።

# እርሱ ንዑዱ ነው!

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ዝቅተኛውና እንባዬን በማፍሰስ ላይ የምገኘው አገልጋይህ፣ ተማፃኝ እጆቼን ወዳንተ በማንሳት ከምሁራን ዕውቀትና ከአወዳሾችህ ውዳሴ ሁሉ በላቀው ደጀሰላምህ አፃራ ላይ ግንባሬን እደፋለሁ፤ በችሮታህ፣ ይህን በደጃፍህ ዝቅተኛ የሆነውን አገልጋይህን በምሕረትህ አይን ተመልከተው በዘለዓለማዊውም ፀጋህ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥመው፤

ጌታ ሆይ እርሱ ምስኪንና ዝቅተኛ አገልጋይህ ነው፤ ተመስጦና አንተን እየተማፀነ፣ በእጅህ ውስጥ ያለ ምርኮኛ፣ ወዳንተ በጥልቅ ስሜት እየፀለየ እምነቱን ባንተ ላይ በመጣል፣ በፊትህ እንባውን እያፈሰሰ፣ ወዳንተ እየተጣራ እንዲህ በማለት ይማፀንሃል፤

ጌታ አምላኬ ሆይ! ተወዳጆችህን አገለግል ዘንድ ፀጋህን ስጠኝ ለአንተ አገልጋይ እንድሆን አበርታኝ፣ በቅድስና መንበርህ አንተን በማምለክና ለታላቅነት መንግሥትህ በመፀለይ ብርሃን ግንባሬን አብራው፤ በመንግስተ ሰማያዊ መግቢያ በርህ ላይ እራሴን ከመወደድ የነፃሁ፣ በቅዱስ ክልልህም ውስጥ ከሁሉ ነገሮች የተላቀቅሁ እንድሆን እርዳኝ፤ ጌታ ሆይ! ከራስ ወዳድነት ከመራቅ ጽዋ እጠጣ ዘንድ ስጠኝ፣ በካባውም አልብሰኝ፣ በውቅያኖሱም ውስጥ አስጥመኝ፤ የፍጹም ክብር ጌታ ሆይ በተወዳጆችህ መንገድ ላይ እንዳለው አፃራ አድርገኝ፤ በመንገድህ በምርጦችህ እርምጃዎች ለተቀደሰው አፈር ነፍሴን እንድሰዋ ፈቃድ ይሁን፤

አገልጋይህ በማለዳና በውድቅት በዚህ ፀሎት ይጠራሃል፣ ጌታ ሆይ የልቡን ምኞት አሟላለት እምነትህንና አገልግዮችህን ያገለግል ዘንድ፣ ልቦናውን አብራለት፣ ልቡን አስደስትለት፣ ብርሃኑንም አቀጣጥልለት፤

አንተ ሰጪው አዛኙ፣ ከሁሉም በላይ ለጋሱ ፀጋ የተመላው መሐሪው ሩኅሩኅ ነህና!

# ክፍል አራት

## የአብዱል-ባሃ የሕይወት ገጽታ

(*Vignettes from the Life of Ahdu'l-Baha) ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ*

### መግቢያ

ይህ የአብዱል-ባሃ የሕይወት ገጽታ መጽሐፍ ሙሉ የሕይወት ታሪኩን የሚገልጽ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን የአንድ ባሃኢ ሕይወት ምን መሆን እንዳለበት ከአብዱል-ባሃ የቀን ተቀን ሕይወት እንዲማር የሚጠቅም ይሆናል፡፡ የሚናገረውና የሚተገብረው ሕይወቱ የተሰናሰለ ሲሆን የሚያበረታታንና የሚያጠነክረን ነው፡፡ በዚህ ሕይወቱ አማካይነት ነው የሰው ዘርን እንድናስተምር እኛን የሚጠራን፡፡ ስለሆነም የአብዱል-ባሃን ፈለግ እንከተል!

ይህን የአብዱል-ባሃን የሕይወት ገጽታ ለማዘጋጀት ከአነሳሱኝ ዋና ዋና ሃሳቦች አንዱ ልንጨብጠውና ልንዳስሰው የምንችል የአብዱል-ባሃ ማንነትን ለማሳየት ስለፈለኩ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የየቀን ሕይወቱን ማሳየቱ ዋና ነው፡፡ ለምሳሌ አብዱል-ባሃ ለጋስ ነው ከምንል ለጋስ የሆነበትን ሁኔታዎች ማሳየት፡፡ መንፈሳዊነት በተግባር ሕይወት ላይ ሲተገበር ስናይ እኛም በሕይወታችን እንድንተገብረው ይረዳናል፡፡ የአብዱል-ባሃን ሕይወት በተጨባጭነት ማወቅ ከቻልን እኛም በሕይወታችን ለመተግበር እንጣጣራለን፡፡ ደግሞም ሁላችን ለሕይወታችን እንደምሳሌ የሚሆነን ቅዱስ ሰብዕና ያስፈልገናል፣ ለዚህም አብዱል-ባሃ ወደር የማይገኝለት በአምላክ የተለገሰን ስብዕና ነው፡፡

የባሃኢ እምነት ሞግዚት ሾጊ ኤፌንዲ እንዳለው፡- ያለፍራቻና በቆራጥነት የአብዱል-ባሃን ፈለግ መከተልን በአንክሮ ያስቡበት፡፡ ጀግንነቱን፣ ከልብ የመነጨ እውነተኛ ፍቅሩን፣ ምንም የማይገድበውና ማንንም የማይለይ

የወንድማማችነት አጋርነቱን፣ ለሂሳዊ ነቀፌታ አይበገሬነቱን ፣ በብልሃትና በጥበብ መካኑን ያጢኑበት፡፡ ...ለፍትህ ያለውን መቆርቆር ያሳየበትን፣ ለተጎዱት ፈጣን ምላሽ መስጠቱን፣ ዘላቂ ቋሚ ለሆነው የሰው ዘር አንድነት ስሜቱን፣ ለሰውም ሁሉ ያለው የሚያጥለቀልቅ ፍቅሩን እናም ይህን ምኞቱን ለማፍረስ፣ ይህን ዘዴኛነቱን ለመገደብ፣ መርሆውን ለመፎካከር ወይንም ምግባሩን ለማጣጣል ለሚሹት ያለው ምክንያታዊ ቁጣውን ሁሉ ያጢኑ፣ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ይነሱ፡፡”

ዓለም አቀፍ ቤተ-ፍትህም እ.ኤ.አ. በ1966 መልዕክታቸው ወጣቶችን በዋነኛነት ባሕሪያቸውን በአብዱል-ባሃ አርያነት መሠረት እንዲቀርጹ ጠይቀዋል፡፡ ለመላው የባሃኢ ዓለም በላኩት መልዕክት ደግሞ “የአብዱል-ባሃን የመለኮታዊ ተምሳሌነት... በአንክሮ ስናጤን ሕይወቱና ምግባሩ የተሰናሰሉ መሆናቸው የተግባር መስፈርት ብቻ ሳይሆኑ የተተ ገበሩ፣ የውስጣዊ ማንነቱ ተፈጥሮአዊና አይቀሬ መገለጫ ዎች ናቸው፡፡ እኛም የእሱን አርአያነት ለመከተል የምን ችለው ውስጣዊ መንፈሳችን በፀሎት ሲተጋ፣ ትምህርቱን የመተግበር አቅማችን ሲጎለብትና ሲዳብር ሲሆን የባህሪ ያችንና የምግባራችን መገለጫ ምንጭ ይሆናል፡፡”

የአብዱል-ባሃን አርአያነትን ወይንም የባሃኢነት መገለጫ መሆኑን በመረዳት ከተቻሉ ሕፃናትም ይሁን አዋቂዎች የባሃኢ ሕግጋትን ለማክበር ውስጣዊ አቅማቸውን ለማጎልበት ይረዳቸዋል፡፡ በአንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስንሆንና ምን ማድረግ እንዳለብን ማሰላሰል ስንፈልግ “አብዱል-ባሃ ቢሆን ይህን ሁኔታ እንዴት ያልፈው ወይም ይወጣው ነበር” በማለት እራሳችንን መጠየቅ እንችላለን፡፡

የዚህ መጽሐፍ የድርጊት ትረካዎች ጥቅማቸው በደንብ የተቀናበሩና ፍሰት ያላቸው መሆናቸው ናቸው፡፡

በተጨማሪም የታሪኩ መንፈስም እምብዛም ስህተት አይኖረውም። ስህተት እንኳ ቢኖር የትረካው ዋና ጉዳይ ላይ ሳይሆን ከትረካው ዋና ሃሳብ ጋር የተያያዙ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ይሆናል። ሆኖም ግን በእርግጠኝነት ታሪኩ በትክክል ተዘግቧል ማለት አንችልም። ምክንያቱም አንድን ትክክለኛ ሁኔታን ሁለት ሰዎች እንኳን ዘግቡ ቢባሉ ሁለቱም አንድ አይነት ዘገባን አይጽፉም። ይህ መጠነኛ የሆነ የአብዱል-ባሃን የሕይወት ገጽታ የሚያሳይ ጽሑፍ መለኮታዊ መዓዛን የሚያሰራጭ እንዲሆን ምኞቴ ነው። በቀላሉ ልናነበውና አብዱል-ባሃን ልንወደው የሚያስችለን ነው። ደግሞም በጥልቀት የአብዱል-ባሃን ሕይወት ለመመርመር ለሚፈልጉ ደግሞ መነሻ ይሆናቸዋል። በዋናነት ደግሞ ሁላችንም በአንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስን ሆንና ምን ማድረግ እንዳለብን ማሰላሰል ስንፈልግ “አብዱል-ባሃ ቢሆን ይህን ሁኔታ እንዴት ያልፈው ወይንም ይወጣው ነበር” በማለት ለራሳችንን ምላሽ የምናገኝበት ይሆነናል። ይህ ከሆነ “የአብዱል-ባሃ የሕይወት ገጽታ” የሚለው መጽሐፍ ዓላማውን አሳክቷል ማለት ነው።

ለአብዱል-ባሃ ያለኝ ፍቅር እጅግ ጥልቅ ነው። ወላጆቻችን ለመንፈሳዊ ጉብኝት እ.ኤ.አ 1921 ሐይፋ የሄዱ ጊዜ ለእኔና ለእህቴ ፀሎት ገልጾልናል። እንደእንቁ በሆነው በባሃኢ ትምህርት መሠረት እንድናድግ ተመኝቶልናል። ይህ ትምህርትም ደስታንና የሕይወት ትርጉምንም አረጋ ግጦልናል።…

አናማሪያ ሆኖልድ<br>አሜሪካ

## ንጹሕ ልብ

“በዛሬው ጊዜ በጣም አንገብጋቢዊ ጉዳይ ፀባያችንን የማንጻት ስነ-ምግባራችንን የማነጽ፣ የእርስ በእርስ ግንኙነትን የማስተካከል ነው፡፡”

“ልበ-ንጹህ  ማለት ከእኔነት ሙሉ በሙሉ እራሱን ያጸዳ ማለት ነው፡፡ እኔነት የሌለው ማለት ንጹሕ መሆን ማለት ነው” ከአብዱል-ባሃ ንግግሮች የተወሰደ

## ከእኔነት ከእራስ ወዳድነት የነፃ

አብዱል-ባሃ እንግሊዝ አገር ያለ አንድን እስር ቤት ሲጎበኝ በጎብኚ መዝገብ ላይ የፃፈው “ ትልቁ እስር ቤት የእኔነት እስር ቤት ነው” ብሏል፡፡

***

አብዱል-ባሃ ሰዎች ከእስር ነፃ ስለወጣ ደስታቸውን ሲገል ጹለት እንዲህ አላቸው፡-

“ነፃነት ማለት ከቦታ ጋር የተያያዘ አይደለም ነገር ግን በውስጣችን ካለው ሁኔታ ጋር እንጂ፡፡ እኔ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ ደስተኛ ነበርኩ ምክንያቱም እነዚያ ቀናት የሰውን ልጅ በማገልገል ያሳለፍኳቸው ቀናት ነበሩና፡፡

አንድ ሰው ከእኔነት እስር ከተገላገለ ያ በእውነትም ነፃነት ነው፡፡ እኔነት ታላቅ እስር ቤት ነውና፡፡

አንድ ሰው ከባድ መከራዎችን ስሜት አልባ በሆነ ይሁንታ ሳይሆን ብሩህ በሆነ ፍቃደኝነት ካልተቀበለ …ነፃነቱን አይቀዳጅም፡፡

***

በአንድ ወቅት አብዱል-ባሃን "ሰይጣን" ምንድን ነው? ተብሎ ተጠየቀ እሱም...፡- "ያ የሚጎተጉተን እኔነት" ነው ብሎ መለሰ፡፡

***

አብዱል-ባሃን ሐይፋ የጎበኘችውን የኒውዮርክ ጋዜጠኛ እንዲህ ብሏት ነበር፡- "ልትፈሩት የሚገባ ምንም ጠላት የላችሁም፣ የምትጠሉት ባላጋራም የለም፡፡ የሰው ዋና ጠላቱ እሱ እራሱ ነው፡፡ ለተከታዮቼ ይህን ንገሪያቸው፡፡"

***

አብዱል-ባሃ ስለ እራስ ወዳድነት ይህንን ብሏል፡- " እራስን መውደድ ልንገልጸው የማንችል አደጋና በዓለም ላይ ላሉ ለብዙ መልካም ነፍሶች መጥፊያ የሆነ ነው፡፡ ሰው በመልካም ባህሪያት የተሞላ ቢሆንና ግን እራሱን የሚወድ ከሆነ፣ እነዚያ ምግባራቱ ሁሉ እየደበዘዙ ይመጣሉ፣ ወይንም ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄድና በመጨረሻም የከፋ ይሆናል፡፡

***

እኔ፣ እራሴና የእኔ የሚሉት ቃላቶች አላስፈላጊ ወይንም አሳፋሪ የሚሆኑበት ቀን ይመጣል በማለት አብዱል-ባሃ ኒውዮርክ ለሚኖሩ ወዳጆች (ባሃኢዎች) ነገሯቸው ነበር፡፡

አንድ ቀን ሉዋና ጆርጅ የሚባሉ ባሃኢዎች ከአብዱል-ባሃ ጋር በመኪና እየሄዱ ነበር፡፡ አብዱል -ባሃም ለማሸለብ ዓይኑን ከደን እንዳደረግ እንቅልፍ ይዞት ሄደ፡፡ ሉዋና ጆርጅ ግን ወሬያቸውን ቀጠሉ ወሬያቸው ስለራሳቸው ጉዳዮች ነበር (እኔ፣ እራሴ እና የእኔ... የሚሉትን ቃላት

ይጠቀሙ ነበር) እናም ድንገት አብዱል-ባሃ ነቃና ሳቀ፡፡ “እኔ፣ ራሴ፣ የእኔ የሚሉት ቃላቶች የሰይጣንነት ቃላቶች” አለ፡፡

***

ሁለት መንፈሳዊ ጎብኚዎች ከአብዱል-ባሃ ጋር አብረው ገበታ ቀርበው ሳለ፣ አብዱል -ባሃ በአካ መንፈሳዊ ጉብኝታቸው እየተደሰቱ እንደሆነ ጠየቃቸው፣ እነሱም ከእርሱ ጋር በመሆናቸው ወሰን የሌለው ደሰታ ላይ እንዳሉ ገልጸው ነገር ግን ስለራሳቸው ጉድለት ሲያስቡ ግን ደስታቸው እንደሚጠፋ ገለጹ ፡፡ አብዱል-ባሃም “ ስለራሳቸሁ አታስቡ፤ ይልቁንም ስለአምላክ ፀጋ አስቡ፡፡ ይህን ስታደርጉም ሁሌ ደስተኛ ትሆናላችሁ፡፡” ከዚያም በፈገግታ ስለፒኮክ ወፍ (ጣዎስ) የአረብ ተረት ነገራቸው፡- ወፉ ሁሌም በራሱ እንደተደሰተ የሚኖር ነበር ምክንያቱም አስቀያሚ የነበሩትን እግሮቹን ፈጽሞ አይቶአቸው አይውቅምና፤ ይልቁንም የተዋበውን ላባውን ብቻ ነበር ሁሌም የሚያስበው፡፡”

***

ባሃኡላህ ለአብዱል-ባሃ የሰጠውን የማዕረግ ደረጃ በተመለከተ አብዱል-ባሃ እራሱ ሲናገር “…እኔን ተመልከቱ፣ እኔን ተከተሉ፣ እንደኔ ሁኑ፣ ስለራሳችሁና ስለኑሮችሁ አታስቡ፣ ስለመብላታችሁ ሆነ፣ ስለመተኛታችሁ፣ ስለምቾታችሁ፣ ስለጤናችሁም ሆነ ስለመታመማችሁ፣ ከጓደኞቻችሁ ሆነ ከባላጋራችሁ ጋር ስለመሆናችሁ፣ ምስጋናም ይለገሳቸሁ ወይንም ጥላቻ ይሰንዘርባችሁ ስለምንም አታስቡ ፣ ስለእነዚህ ሁኔታዎችም አትጨነቁ፡፡ እኔን ተመልከቱ እና እንደእኔ

ሁኑ፤ እንደገና እንድትወለዱና ወደ መንግስተ-ሰማያት ትገቡ ዘንድ ስለእራሳችሁና ለዓለም መሞት አለባችሁ። ሻማ ብርሃን እንዴት እንደሚሰጥ ተመልከቱ። ብርሃን መስጠት እንዲችል እራሱን እንዴት ሳያቋርጥ እንደሚያቀጣጥል።

አብዱል-ባሃ የጽሞናንና የጸጥታን ጥቅም ያውቀዋል፣ አንድ የአሜሪካ ባሃኢ ያጋጠመውን ሲናገር፡- አብዱል-ባሃ ጥያቄ ሲጠየቅ የመጀመሪያ ምላሹ ጽሞናና ፀጥታ ነው። ሁሌም የሚያበረታታው ሌሎች እንዲናገሩና እርሱ እንዲያዳምጥ ነው። ሌሎች ላይ እንደሚታየው ለጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መቸኮልና ጠያቂው ጥያቄውን ሳይጨረስ ለመናገር መጣደፍ አያሳይም። አንድ ጊዜ የክርስቲያን ምሁር የሆነ ሰው ጋዜጣ ላይ ለሚወጣ ጽሑፍ ሊጠይቀው መጣ፤ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ረጃጅም ነበሩ። አብዱል-ባሃ በጽሞና በትኩረት ያዳምጠው ጀመር እያዳመጠው እንደ ሆነ ለመግለጽ አንድ ቃል ብቻ እያሰማ አደመጠው። ከልብ እየተረዳው እንደሆነ ፍቅሩን አሳየው። እኔ ትዕግስት አጣሁ አብዱል-ባሃ ግን ታገሰው። ምክንያቱም ጎብኚው ጠያቂ ሙሉ ለሙሉ መደመጥ አለበትና። ከረጅም ቆይታ በኋላም ጥያቄውን ጨረሰ አብዱል-ባሃም በጽሞና ጸጥታ ትንሽ ቆየና "ውድ ልጄ" በማለት ፍቅርና ጥበብ የተሞላውን ምላሹን አቀረበለት። የክርስቲያን ምሁሩ ጠያቂ ወዲያው ትህትናውን አሳየ። አብዱል-ባሃም ተነስቶ አቀፈው። እስከበሩ ድረስም ሸኘው ከዚያም በሩ አጠገብ ካለ ጠረጴዛም ላይ ውብ የሆነ ጥቅል አበባ አንስቶ በፈገግታ አበረከተለት። ምሁሩ ጠያቂ ተገርሞ፣ ፈክቶ፣ ትሁት ሆኖና ተቀይሮ የሄደበትን ያችን ቀን አልረሳትም።

***

አንድ ቀን አብዱል-ባሃ ከአካ ወደ ሐይፋ በባቡር ሲጓዝ ሁሉም ሰው ወደሚቀመጥበት የባቡሩ ክፍል ሊገባ ሲል የባቡሩ ሹፌር “ክቡርነትዎ እርሶዎ ብቻ የሚቀመጡበትን የግል ክፍል ለምን አይዙም” ሲል ጠየቀ አብዱል-ባሃም እንደማይፈልግ ገለጸ፡፡ ጉዞም ተጀመረ፡፡ ሐይፋ ሲደርሱ ከባቡሩ እደወረዱ አንድ አሣ አጥማጅ ሴት ሙሉ ቀን አሣ ለማጥመድ ሞክራ ስላጣች አዝናና ተርባ ወደ ቤቷ ልትመለስ እንደሆነ ለአብዱል-ባሃ ተናገረች፡፡ አብዱል-ባሃም መጸወታትና ለባቡሩ ሹፌር “አየህ ለምን አንደኛ ደረጃ የባቡር ክፍል እንደማልፈልግ፤ ሰዎች እየተራቡ እኔ ለምን የግል ምቾቴን እፈልጋለሁ?”

## ትህትናና ዝቅተኝነት

አብዱል-ባሃ ትሁት መሆኑ በብዙ መንገድ ይታያል፡፡ አብዱል-ባሃ (የባሃ አገልጋይ) ከሚለው ሌላ ምንም ዓይነት ማዕረግና ስልጣን አይፈልግም፡፡ ለመንፈሳዊ ጉብኝት እርሱ ጋር የሚመጡት ጎብኝዎች እግሩ ሥር እንዲወድቁ አይሻም፡፡ በቀድሞ ጊዜ ለጉብኝት ለሚመጡ ሁሉ እራሱ ምግብ ያዘጋጅ ነበር፡፡ ማዕድ ሲቀርቡም እራሱ ያስተናገዳል፡፡ ሌሎችም እንግዶቻቸውን እንዲህ እንዲያስተናግዱ ይመክራል፡፡

***

ባሃኡላህ ባህጂ (ከአካ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ቦታ) ይኖር በነበረበት ወቅት አብዱል-ባሃ እርሱን ለመጎብኘት በሣምንት አንድ ጊዜ ከአካ ወደ ባሃጂ ይሄድ ነበር፡፡

የሚሄደውም በበቅሎ ወይንም በፈረስ ሳይሆን በእግሩ ነበር፣ ለምን በእግሩ እንደሚሄድ ሲጠየቅ “ጌታ ክርስቶስ እንኳን በእግሩ እየሄደ እኔ ማነኝና ነው በፈረስ ወይም በበቅሎ የምሄደው?” ይል ነበር። ሆኖም ግን ባሃኡላህ በእግሩ እንዳይመጣ ስለጠየቀው እየጋለበ ወደ ባሃጂ ይሄድና ነገር ግን ሲቃረብ መጋለቡን አቁሞ ይወርድና በእግሩ መሄድ ይጀምራል። ባሃኡላህም ከሩቅ አብዱል-ባሃን ሲያይ በደስታ ተሞልቶ እንዲቀበሉት ሰዎች ይልክለታል።

***

…አንድ ልጅ አብዱል-ባሃን ለምን ወንዞች ሁሉ ወደ ውቅያኖስ እንደሚፈሱ ሲጠይቀው “ውቅያኖስ ከሁሉ ዝቅ ያለ ስለሆነ ወንዞች ሁሉ ወደ እሱ እንዲፈሱ ይስባቸዋል” ብሎ መለሰለት።

***

የባሃኢ ማሕበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት መገለጫ ስለሆነው ስለ አሥራ ዘጠነኛ ቀን በዓል አስፈላጊነት አብዱል-ባሃ ለአሜሪካ ባሃኢዎች ሲናገር “እያንዳንዳችሁ ሌሎችን እንዴት ልታስደስቱና ልታረኩት እንደምትችሉ አስቡ፣ እያንዳንዳችሁ ሌላው ከእናንት እንደሚልቅና እንሚሻልም ተገንዘቡ፣ እያንዳንዱም ከሁሉም ከተሰበሰበው እንደሚያንስ ያጢን። የእነሱ ደረጃ ከፍ ያለና የእርሱ ደረጃ ዝቅ ያለ እንደሆነ ይወቅ። ልክ በዚህ ሁኔታ ብትኖሩና ብትተገብሩ በእውነት ያ የአሥራ-ዘጠነኛው ቀን በዓል የሰማያዊው ገበታ ይሆናል። ያ ግብዣም “የጌታ እራት” ይሆናል! እኔም የእነዚያ ታዳሚዎች አገልጋይና አሳላፊ እሆናለሁ።”

***

ሐዋርድ የተባለ ባሃኢ ሲጽፍ፡- አብዱል-ባሃን በማግኘት ለማዳመጥና ለማናገር በቻልኩባቸው ጊዜያት ሁሉ እጅግ የተደመምኩበትና የተሳብኩበት ሁኔታ በማስተማሪያ ዘዴዎቹ ነው፡፡… እንደሚታወቀው መከራከር አይፈልግም፡፡ በአንድም ጉዳይ እንደጫና እንዲሆን አያደርግም፡፡ ምንም ዓይነት የበላይነትን አያሳይም፣ ይልቁንም የት ሁትነት መገለጫ ነው የሚሆነው፡፡ ሲያስተምር "ልክ ለንጉስ ገጸ-በረከት እንደሚያቀርብ ሰው ዓይነት" ነው፡፡ እያደረኩ ያለው ነገር ትክክል እንደሆነ ከመጠቆም ባሻገር ይህን አድርግ አይለኝም፡፡ ማመን ያለብህ ይሄን ነው ብሎኝም አያውቅም፡፡ እውነትንና ፍቅርን ውብና ታላቅ ስለሚያደርገው ልብ በዚህ ሁኔታ ተገዝታ እንድትቀየር ትሆናለች፡፡ በአነጋገሩ፣ በምግባሩ፣ … መሆን ያለብኝን ሁኔታ ሁሉ አስተምሮኛል…

***

ሚርዛ አብዱል-ፈድል የተባለው ታላቁ የባሃኢ ሊቅ አስተማሪን፣ አብዱል-ባሃ አሜሪካን አገር ልኮት ባሃኢዎችን በማስተማርና በማጠናከር ቆይቶ ነበር፡፡ ከተመለሰም በኋላ ብዙ የአሜሪካን አገር መንፈሳዊ ጎብኝዎች አካ አብዱል-ባሃ ጋር መጥተው ሳለ ሚርዛ አብዱል-ፋድል እንዴት እንደረዳቸው፣ እምነቱን ለብዙ ሰዎች ማስተማሩን፣ የእምነቱን ትምህርት ከሚያዛቡ ሰዎች እንዴት እንደተከላከለላቸውና ጠንካራና ጽኑ የሆነ የባሃኢ ማሕበረሰብ በአሜሪካ እንዲኖር እንዳደረገ በመናገር አሞገሱት፡፡ ሙገሳቸውን ቀጠሉ ሚርዛ አብዱል ፋድል ግን እስኪያስለቅሰው ድረስ በጣም ተጨነቀ፣ አዘነ፡፡

በሁኔታው አሜሪካውያኖቹ ግራ ገባቸው፣ በሚገባ አላመሰገነውም በማለትም አሰቡ።

አብዱል-ባሃም ሲያሞግሱት እየጎዱት እንደሆነ ነገረቸው፣ ምክንያቱም እሱ በዚህ ታላቅ እምነት ውስጥ ራሱን እንደሌለ ነገር ስለሚቆጥርና ምንም ዓይነት ሙገሳ እንደማይገባው በጽኑነት ስለሚያምን ነው አላቸው።

***

ኢራን የሚገኙ ባሃኢ ባለቅኔዎችና ጸሐፊዎች አብዱል-ባሃን በማሞገስ ይጽፉ ነበር። የአካ ባሃኢዎች ግን አብዱል-ባሃ ይህን እንደማይወድ ስለሚያውቁ ይጠነቀቁ ነበር። ብዙዎቹንም እርሱን እያሞግሱ ከሚጽፉ ይልቅ ሳያሞግሱት ቢጽፉ ጥሩ እንደሚሆን መክሯቸዋል።

ለብዙ ዓመት ጸሐፊው የነበሩት ዩኑስ ካሃን ሲያስታውሱ፣ አንድ ቀን አብዱል-ባሃን የሚያሞግስ ደብዳቤ ደረሰን። እኔም አካ ከሚገኘው ቤቱ ከላይኛው ክፍል ወደታች እየወረደ ሳለ አገኘሁትና አሁን ደብዳቤውን ቢያየው ጥሩ ይሆናል በማለት ሰጠሁት። አንድ ሁለት መስመር ካነበበም በኋላ ወደ እኔ ዞሮ በሃዘኔታና በመቆጨት “አንተም እንደዚህ ዓይነት ደብዳቤ ሲመጣ ታቀብለኝ ጀመር! እንዴት እንደማዝንና እንደምጎዳ አታውቅም፣ እኔን እንደዚህ ክበውና አልቀው ሲያሞግሱኝ? አንተ እንኳን አልተረዳኸኝም ማለት ነው!... እኔ እራሴን የተባረከው ውበት (የባሃኡላህ) ተወዳጆች ከሆኑት ከእያንዳንዳቸውና ከሁላቸው በታች ማድረግ እንደምፈልግ አታውቅምእን።”

በቁጣና በስሜት ተሞልቶ ስለተናገረ ልቤ ቆመች። ሰውነቴ ሁሉ ተዝለፈለፈ። አብዱል-ባሃ እንዲህ ሲያዝን

ከማየት መሬት ተከፍታ ብትውጠኝ ተመኘሁ።... አብዱል-ባሃን በማሳዘኔ ተጨነቅሁ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሁሉ ጠፋኝ። በዚህ ሁኔታ ሳለሁ አብዱል-ባሃ “ይሁንና የወዳጆቻችንን ጥፋት እንዳልሆነ አውቃለሁ የሚያሞግሱኝ ጽናታቸውን፣ ፍቅራቸውንና ታማኝነታቸውን ለመግለጽ ነው” አለና “አንተ የእኔ ቅርብና አጋር እንደሆንክ እኮ አውቃለሁ” አለኝ። ማንንም ነፍስ መጉዳት እንደማይፈልግ ወዲያው ተረዳሁ መጽናናትና ብርታትንም አገኘሁ። ሀዘኔም ጠፋ። በደስታና በፍስሃ ተሞላሁ የገነት በር ተከስቶ ባርግም ብዬ ተመኘሁ።

***

አብዱል-ባሃ በዚህ ምድር ላይ ሳለ በመጨረሻ ከጎበኙት ምዕመናኖች መካከል አንዷ ስዊዘርላንድ የምትኖረው አና ኩንዝ ናት። ስለአብዱል-ባሃ ስትናገረም፡- “እሱን ሳስታውስ በቀዳሚነት ወደአእምሮዬ የሚመጣው ቀለል ያለ ሰብዕናውን፣ የሚገርም እራሱን ዝቅ የማድረግ የዋህነቱን፣ እናም ገደብ የለሽ ፍቅሩን ነው።”

## ታጋሽነትና ቻይነት

አብዱል-ባሃ ባሃኢዎች መንፈሳዊ ባሕሪያትን እንዲያዳብሩ በጉጉት ሆኖም ግን በትእግስት እንደሚጠባበቅ ሲናገር፡ “ወዳጆች! ከእናንተ ጋር በአካል የማልኖርበት ጊዜ እየተቃረበ ነው። ሊደረግ የሚቻለውን ሁሉ አድርጌያለሁ፤ የባሃኡላህን እምነት እስከምችለው ድረስ አገልግያለሁ። በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ቀንና ለሊት ለፍቻለሁ። ተወዳጆች የእምነቱን ሃላፊነት

የሚውስዱበትን ቀን ለማየት እጓጓለሁ! አሁን የአብሃ መንግሥትን የማወጅ ጊዜ ነው፡፡ አሁን የፍቅርና የሕብረት ወቅት ነው!

አማኞች የጽኑነትና የእውነትኝነት መገለጫ፣ የፍቅርና የወዳጅነት ሕልውና፣ የአንድነትና የስምምነት ተምሳሌ የሚሆኑበትን አስደሳች ብስራት የምሰማበትን ጊዜ አቤት እንዴት እየተጠበኩ፣ እየተጠባበኩ ነው፡፡ ልቤን አያስደስቱልኝም እንዴ? ፍላጎቴን አያሟሉልኝም እንዴ? የምኞቴ መገለጫ አይሆኑም እንዴ? የልቤን ፍላጎት አያሟሉም እንዴ? ለጥሪዬ ጆሮዋቸውን አያቀኑም እንዴ? እየጠበኩ፣ በትእግስትም እየተጠባበኩ ነው፡፡

***

ሐይፋ ከተማ ውስጥ አብዱል-ባሃን የሚጠላ አንድ ሰው ነበር፡፡ አብዱል-ባሃን ባየ ቁጥር እሱን ላለማግኘት ሲል መንገድ ለውጦ ይሄድ ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን አብዱል-ባሃን አገኘውና፡- “አንተ የአምላክ አገልጋይ ነህ” አለው፡፡ “አዎ! ስሜም ነው” ሲል አብዱል-ባሃም መለሰ ፡፡

ሰውየው “እኔም እንግዲህ ሙሴ ነኝ” አለ በኩራት፡፡

“በል እንግዲህ ሙሴ ጠዋት በአንድ ሰዓት እዚህ ጋር ጠብቀኝ አብረን ሆነን ልክ ታላቁ ሙሴ እንዳደረገው ሰዎችን እየዞርን እናገለግላለን” አለው አብዱል-ባሃ፡፡ ሰውየውም ተስማማና በነገታው በተቀጣጠሩበት ቦታ ተገናኙ፣ አብዱል-ባሃም የተለመደውን ሰዎችን የማገልገል እንቅስቃሴውን ማለትም ጎስቋሎችን ማገዝ፣ ደሆችንና ችግረኞችንም መርዳት፣ ከሰዎች ጋር መወያየትና መምከርን ተያያዙት፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ውለው ማታ ላይ ሰውየው በድካም ዝሎ ነበር፡፡ አብዱል-

ባሃም "በል ሙሴ እንግዲህ ነገ ጠዋትም በተለመደው ሰዓት እንገናኝ እዚህ እጠብቅሃለሁ" አለው፡፡ በነገታውም በተቀጣጠሩት መሠረት ተገናኙ፡፡ እንደተለመደውም አብዱል-ባሃ የዕለት ተዕለት ተግባሩን አብረው እንዲያከናውኑ አደረገ፡፡ ማታ ሲደርስም ሰውየው በጣም ደክሞ ነበር፡፡ ልክ ሊለያዩ ሲሉ ሰውየው "አብዱል-ባሃ ነገ እኔ ሙሴ መሆኔን እተዋለሁ" አለው፡፡

## ጠንካራነቱ

ባሃኡላህና ተከታዮቹ በአካ/አቆር እስር ቤት ለሁለት ዓመት ከሁለት ወር እና ከአምስት ቀን ከታሰሩ በኂላ ተለቀቁ፡፡ ብዙዎች የባሃኡላህ ተከታዮችም ለመኖር አስቸጋሪ የሆኑ ክፍሎችን ተከራዩ፡፡

የሚኖሩበት ክፍሎች በጣም ያራጁ የታመጉና ሽታ ያላቸው ነበሩ፡፡ አብዱል-ባሃም ባግዳድ ሳሉ ስጦታ የተሰጠውን እቃ ሽጦ የባሃኡላህ ተከታዮች የተከራዩትን ክፍሎች አሳደሰ፡፡ የእርሱን ክፍል ግን ለማሳደስ ገንዘብ ስላጠረው ጣራው የሚያፈስ፣ ግድግዳዎቹ የሚከረፋ ሽታ ያላቸውና ወለሉ በአቧራ ሽታ የታመገ ነበር፡፡ እርሱ ግን በእዚያ ክፍል ውስጥ መኖሩን ቀጠለ፡፡ የሚተኛው ሰሌን ላይ የሚለብሰው ደግሞ ድብዳብ ነበር፡፡ ክፍሉ በቢንቢና ትንኝ የተሞላ ስለነበር ሌሊት ላይ እየበሉት አላስተኛ ይሉታል፣ እየነቃ ድብዳቡን እያራገፈ እንደገና ይተኛል በተደጋጋሚ ይህን ማድረግም ነበረበት በሌሊት ውስጥ ቢያንስ አሥር ጊዜ ያህል ይነሳ ነበር፡፡

***

እ.ኤ.አ በ1904 አንዲት የእንግሊዝ አገር ባሃኢ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት ወደ አካ/እስራኤል ለሁለተኛ ጊዜ ሄዳ ሳላ በወቅቱ አብዱል-ባሃና ቤተሰቦቹ በእስር ከተማው አካ ውስጥ እየኖሩ ነበር። ለስምንት ወርም ከእነርሱ ጋር በእንግድነት ቆየች። ስለ ቆይታዋም ስትጽፍ፡- "ከአብዱል-ባሃ ጋር በአንድ ገበታ ዙሪያ እስላሙም ክርስቲያኑም አይሁዱም እናም ሌላውም ተቀምጠው የወንድማማችነትን መንፈስ ሲተነፍሱ ማየት መታደልና የማይረሳም ትውስታ ነበር።

በቆይታዋም የእምነቱ ጠላቶች አብዱል-ባሃንና ጽኑ አማኞችን ከፍተኛ ችግር ሲፈጥሩባቸውና ለመገመት ከሚቻል በላይ ሃዘን ላይ ሲጥሏቸው ተመለከተች። በዚህም በጣም አዝና አብዱል-ባሃን፡- "አንተ እንዲህ በፍጹም ንጽሕና እያለህ ይህ ሁሉ መከራን ለምን ትቀበላለህ" ብላ ጠየቀችው። አብዱል-ባሃም፡- "እነዛ የአምላክ አስተማሪዎች፣ ሰዎችን ሲያስተምሩና ሲመሩ እነርሱ እራሳቸው እያንዳንዱ ሰው የሚደርስበትን ፈተናንና መከራን መቀበልና ማለፍ አለባቸው።" አላት

***

ከቀደምቶቹ የአሜሪካን ባሃኢ መካከል ጁሊየት የምትባል ነበረች። እናቷ ባሃኢ በመሆኗ በጣም ይናደዱ ነበር፣ በተጨማሪም ደግሞ እጮኛዋም እንዲሁ ከእምነቱ ጋር ያላትን ቁርኝት አይፈልግም ነበር። ይህም የጁሊየትን እናት አናዷቸዋል በዚህ ሁኔታ እያሉ አብዱል-ባሃ አሜሪካን አገር ስለነበር እንዲጎበኙት ግብዣ ይደርሳቸዋል። በንዴት ተሞልተው ወደእሱ ይሄዳሉ አብዱል-ባሃ ቀኑን ሙሉ ብዙ እንግዶች አስተናግዶ እጅግ ደክሞ ነበር። እሳቸውንም በጥሩ ሁኔታ ተቀበላቸው

እንዲህም አላቸው “ሃዘነዎን ሰምቻለሁ። ላጽናናዎትም እፈልጋለሁ። በአምላክ ተማመኑ። አምላክ መልካም ነውና። አምላክ ታማኝ ነውና። አምላክ አይረሳዎትምና። ሌሎች ሰዎች ክፉ ቢሆኑ አምላክ ክፉ ስላልሆነ ምንም ለውጥ አያመጣም… አምላክ ከጎንዎ ከሆነ ሰዎች የፈለጉትን ቢያደርግብዎትም ምንም ሊደርስብዎት አይችልም።”

እናትየው በነገታው “ያ ሁሉ ጥላቻዬ ጠፋ” በማለት ለልጃቸው ለጁሊየት ነገሯት። ሁኔታውንም እንደተአምር ቆጠሩት።

## ሃቀኝነቱ

ከምዕራቡ ዓለም አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት አካ እስራኤል የሄደ ምዕመን ሲናገር፡- “አብዱል-ባሃ ባሃኢ ባልሆኑ ሰዎች እንኳ የተለየ እውቅናና ክብር አግኝቶ ነበር። የአብዱል-ባሃ መኖሪያ ግቢ ውስጥ መጠነኛ አጸድ (የአትክልት ሥፍራ)፣ የውሃ ገንዳ ፏፏቴና አብዱል-ባሃ እንግዶቹን የሚቀበልበት ድንኳን አለ። በተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ከፍተኛ ጥላቻና አክራሪነት ስለነበረ ማንም ሰው በነፃነት መናገር አይችልም፣ ሆኖም ግን አብዱል-ባሃ በሁሉም የተከበረና በጥበቡ የታወቀ ስለነበር እርሱ ጋር ሲመጡ በሃይማኖት ጽሑፎቻቸው ውስጥ ያለውን ሁኔታ ማብራሪያ ያቅርብላቸዋል፣ በንግድ ምክንያት በመካከላቸው ያለውን ጠብ ያረግብላቸዋል፣ የቤተሰብ ችግሮቻችውን ሳይቀር ይፈታላቸዋል። ሁሉም ስለ አብዱል-ባሃ ሲናገሩ በመካከላቸው ምንም ልዩነት ሳያደርግ ክርስቲያኑንም፣ አይሁዱንም፣ ሙስሊሙንም

እኩል ይረዳል። የአካ ከንቲባ እንኳን ልጁ መልካም አስተ ዳደርና ፍትህን እንዲማር አብዱል-ባሃ ዘንድ ይልከው ነበር።”

## ቅንነቱ

አንድ ምዕመን መንፈሳዊ ጉብኝት ለማድረግ አብዱል-ባሃ ጋር ሄዶ ሳላ የነገረውን ታሪክ ሲናገር፡- “…አብዱል-ባሃ በጋሪ ከብዙ ሰዎች ጋር መንገድ እየሄደ ሳለ አብረውት ከሚሄዱት ሰዎች መካከል አንዱ ነጋዴ ነበር። ጋሪው በየመንደሩ ሲቆም ብዙ ሰዎች አብዱል-ባሃ ጋር ይሰበሰባሉ። ይህ ሁኔታ በየመንደሩ ሲደጋገም የየመንደሩ ነዋሪዎች ፍቅርና አክብሮት ለአብዱል-ባሃ እንዳላቸው ነጋዴው ሰውዬ ተገነዘበ። ከዚያም አብዱል-ባሃን ባሃኢ መሆን እንደሚፈልግ ነገረው። አብዱል-ባሃም ለምን ባሃኢ መሆን እንደሚፈልግ ሲጠይቀው “አንተ ባሃኢ ነህ የትም ቦታ ስትሄድ ብዙ ሰዎች አንተ ጋር ይሰበሰባሉ። እኔን ለማግኘት ግን ማንም አይመጣም ስለዚህ ባሃኢ መሆን የምፈልገው ለዚህ ነው አለ። አብዱል-ባሃም የበለጠ ሁኔታውን ለማጣራት በማለት “ባሃኢ ለመሆን እውነተኛ ምክንያትህ ምንድን ነው” አለው። ነጋዴው በየዋህነት “ብዙ ሰዎች እኔ ጋር የሚሰበሰቡ ከሆነ ለንግዴም ይረዳኛል” አለ። አብዱል-ባሃም “ለዚህ ብለህ ባሃኢ ባትሆን ይሻልሃል” በማለት በግልጽ እቅጩን ነገረው።

## የመንፈስና የልብ ንጽሕና

ለአንድ ምዕመን አብዱል-ባሃ ሲጽፍ፡- “የሚያንጸባርቀው የእውነት ፀሐይ ጨረሮች አንቺ ላይ ያርፍና በዙሪያሽ ያለ

ውን ሁሉ እንዲያጥለቀልቅ እስከምትችዪው ደረጃ ድረስ ልክ እንደመስታወት ንጹሕና የነጻሽ፣ ከማንኛውም አቧራ ከሚሆንብሽ ነገር የጸዳሽና የጠራሽ ለመሆን ተጣጣሪ።"

**ሩህሩህነቱ**

አብዱል-ባሃ አሜሪካን ያሉ ባሃኢዎችን ለማጠናከር በጎበኛቸው ጊዜ አንድ ቀን ፍሬድ የተባለ ወጣት ጎልማሳ እሱን ለመጠየቅ ከእሩቅ የአሜሪካ ግዛት አብዱል-ባሃ ወዳረፈበት ቦታ መጣ። ከብዙ ጊዜ በኋላ አብዱል-ባሃን ስለመጎብኘቱ ሲጽፍ፡- እኔ ያደግሁበት ሰፈር በጣም አደገኛ የሚባል ስርቆሽ፣ ድብድብ፣ ዝርፊያ ያለበትና ሁሉም ዓይነት የዱርዬና የዘራፊ ቡድን የሚበዛበት ነበር። እኔም የአንዱ ቡድን አባል ነበርኩ። ከእስር ቤት አምልጬ የምኖረውም እየተሸሸግኩ ነበር ። አንድ ጊዜ ፖሊስ የሆነን ሰው ሊይዝ ሲሞክር ተከላከልኩ፣ በዚህ ግብግብም ከትልቅ ግንብ ላይ ስዘል እግሬ ተሰበረ። ከዚያም ታሰርኩ፣ በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለሁም ጠበቃዬ ረድቶኝ እንድፈታ ሆነ። ጠበቃዬ ታዲያ ስለባሃኢ ሃይማኖት ነገረኝ መጀመሪያ ላይ ሃይማኖቱ ግር ቢለኝም ቀስ በቀስ እየሳበኝ መጣ፣ ሕይወቴንም ቀየረው። የአምላክ ቃላቶች አዲስ ሕይወት ሰጡኝ።

አብዱል-ባሃ አሜሪካ እ.ኤ.አ በ1912 ሲመጣ እሱን የመጎብኘት መንፈስ ገፋፋኝ። ሌላ የምሳተፍበት ኮንፍረንስ ቢኖርም መንፈሴ ግን እረፍት አሳጣኝ ሂድ ሂድ አለኝ። ከመሄዴ አንድ ቀን በፊት በሕልሜ "የአብዱል-ባሃ እንግዳ ሆኜ በረጅም ጠረጴዛ ላይ ከብዙ ሰዎች ጋር ተቀምጬ አየሁ። አብዱል-ባሃም በጠረጴዛው ዙሪያ እየተንጎራደደ

ታሪክ ይነግረናል ያብራራልናል፡፡" በሚገርም ሁኔታ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት ከበቃሁ በኋላ ህልሙ እውን ሆነ፡፡

በባቡር ለመጓዝ ገንዘብ ስላልነበረኝ እባቡር ላይ የጉልበት ሥራ የመስራት ግዴታ ነበረብኝ፡፡ ከአንዱ ባቡር ሌላ ባቡር እየቀየርኩ የጉልበት ሥራ እየሰራሁ ወደ አብዱል-ባሃ ጉዞዬን ተያያዝኩት፡፡ የባቡሩ ጉዞ ሲያልቅ የመኪና ጉዞ ደግሞ ተጀመረ ከዚያ ደግሞ በታንኳም ተጓዝኩ፣ በዚህ ሁሉ ጉዞዬ ውስጥ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም ልቤ በጣም ነበር የምትመታው፡፡ ደክሜአለሁ፣ ቆሽሼአለሁ ተንከራትቻለሁ ግን ደስተኛ ነበርኩ፡፡

አብዱል-ባሃ ያለበት ቦታ ስደርስ ብዙ ሰዎች እርሱን ለማግኘት ተሰብስበዋል፡፡ መሽቶ ስለነበር በነገታው አብዱል-ባሃን ለማግኘት እንደምችል ተነገረኝ፡፡ በሚቀጥለውም ቀን አብዱል-ባሃን ለማግኘት እየተጠባበቅሁ ሳለ፣ ልክ ሐኪም ጋር እንደሚገባ ሰው ሆኜ ነበር፡፡ ተራዬ ደርሶ አብዱል-ባሃ ጋር ገባሁ፡፡ አብዱል-ባሃ በፍስሃና በፈገግታ ተቀበለኝ፡፡ እንድቀመጥም ጋበዘኝ፡፡ በተደጋጋሚ እንኳን ደህና መጣህ እንኳን ደህና መጣህ አለኝ፡፡ ከዚያም ደስተኛ ነህን ሲል ደጋግሞ ጠየቀኝ፡፡ ጉዞህ እንዴት ነበር አለኝ፡፡

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከብዶኝ ወደ መሬት አዘቀዘቅሁ፡፡ ደግሞ ጠየቀኝ፡፡ ቀና አልኩ ዓይኖቹ ሰማያዊና የሚያንጸባርቁ ናቸው ውስጣ ውስጤን ሁሉ ጠልቀው እንደሚያዩና እንደሚያውቁኝም ገባኝ፡፡ እናም ልነግረው ወሰንኩ እኔ የመጣሁት አንተን ለማየት እንደሚመጡት ሰዎች በተለመደው የጉዞ ሁኔታ አይደለም አልኩ፡፡

እንዴት ነው የመጣኸው አለኝ

ከባቡሩ ከታችኛው ከፉርጎው ስር በመሆን ነው አልኩት

እስቲ በደንብ አስረዳኝ

አሁን የአብዱል-ባሃ ዓይኖች ተቀየሩ ልዩ የሆነ ጨረር የሚፈነጥቁ ሆኑ፡፡ የፍቅር ብርሃን ነበሩ፤ ታላቅ እረፍት ተሰማኝ፣ ደስም አለኝ፡፡ እንዴት እንደተጓዝኩም አብራራሁለት፡፡ ከዚያም ጉንጮቼን ሳማቸው፤ ብዙ ፍራፍሬ ሰጠኝ፤ የቆሸሸና ያደፈ ባርኔጣዬንም ሳመው፡፡

ከዚያም እኔም ጉብኝቴን ጨርሼ ልመለስ ስል፣ አብዱል-ባሃም ወደሌላ የአሜሪካ ክ/ሃገር ሊሄድ እየተዘጋጀ ነበር፣ የሚያስገርም ግብዣ አቀረበልኝ፣ ከእሱ ጋር አብሬው እንድጓዝ ጠየቀኝ፣ እናም አብሬው ተጉዤ ለሳምንት ከእርሱ ጋር ቆየሁ፡፡ እነዚያ ከእርሱ ጋር ባደረኳቸው ቆይታዎች እያንዳንዷ ቅጽበት የማትረሳ ስለነበረች በልቤ ላይ ተቀረጸ፡፡ የባሃኡላህ ቃላት ምግቤ፣ መጠጤና ሕይወቴ ሆኑ፡፡ በመንገዱ አገልጋይ ከመሆንና ለቃል ኪዳኑም ከመታዘዝ ሌላ ምንም ዓላማ የለኝም፡፡

***

የአብዱል-ባሃ ለሕሙማን የሚያሳየው ልበ-ሩህሩህነት ላቅ ያለ ነው፡፡ ሕመማቸውንና ምቾት አልባነታቸውን ይቀርፍ ላቸዋል፡፡ በአካ ሳለ የታመሙ ሰዎችን ሁኔታ ለማጣራት ሠራተኛውን ይልክ ነበር፤ በዚያን ወቅት አካ ከተማ ውስጥ ሆስፒታል ስላልነበረ ለሐኪም ደሞዝ እየከፈለ ደሃ ሕመምተኞችን እየዞረ እንዲያክም ያደርግ ነበር፡፡ በከተማው ውስጥ በጠና የታመሙ ባልና ሚስቶችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሃያ ጊዜ እየተመላለሰ

አስተምሟቸው ያውቃል፡፡ አንድ አካለ ጎዶሎ የሆነች ሴት በኩፍኝ ወረርሽኝ ታማ በሕዝቡ ተገልላ እንዳለች ሲሰማ ወዲያውኑ ደርሶላት አንድ ክፍል ቤት ተከራይቶላት የራሱን ፍራሽና ብርድ ልብስ ወስዶላት፣ ምግብ እየላከላት፣ ሐኪምም መድቦላት አስታመማት፡፡ ስትሞትም የቀብር ስነ-ሥርዓቱን ወጪ ከፈለ፡፡

***

አብዱል-ባሃ የአሜሪካን ባሃኢዎችን በጎበኘበት ጊዜ ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ንግግር ሲያደርግ "ሕሙማንን መጠየቅ አለብን ፡፡ በሐዘንና በችግር ጊዜ ጓደኛ ጠያቂ ማግኘት ትልቅ እርዳታና እፎይታ ነው፡፡ ለሕሙማን ደስታ እንዲሰማቸው ማድረግ ትልቅ ፈውስ ነው፡፡ በእኛ አካባቢ በምሥራቁ ዓለም ሕሙማንን በተደጋጋሚ እየሄዱ መጠየቅ የተለመደ ነው፡፡ የምሥራቅ ሕዝቦች ለሕሙማንና ለተጎሳቆሉ ሩህሩህነትንና አሳቢነትን በእጅጉ ያሳያሉ፡፡ ይህ ሕሙማንን መጠየቅ ከመድሐኒት ባልተናነስ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሕሙማንንና የተጎዱትን ስትጠይቁ ፍቅርና መተሳሰብ በልባችሁ ውስጥ ይኑር፡፡"

ከዚያም አብዱል-ባሃ ስለ ባሃኡላህ ትምህርት ማረጋገጫ ሲሰጥ፡- ባሃኡላህ መለኮታዊው ሐኪም ነው፡፡ የሰውን ዘር በሽታ መርምሮ አስፈላጊውን ሕክምና አዟል፡፡ የሕክምና ውም ዋና መርህ የአምላክ ዕውቀትና ፍቅር፣ ከአምላክ በስተቀር ከሌላው ሁሉ መላቀቅ፣ በጽናት ወደ አምላክ መንግሥት ፊታችንን ማዞር፣ የማይናወጥ እምነት፣ ጥንካሬና ታማኝነት፣ ለሁሉም ፍጥረታት ፍቅራዊ ደግነትን ማሳየትና ለሰው ዘር ዓለም የተደነገጉትን መለኮታዊ ባሕሪያትን ማዳበር ነው፡፡ የእድገት፣

የስልጣኔ፣ የዓለማቀፋዊ ሰላምና አንድነት ዋንኛ መርሆዎች እነዚህ ናቸው። እነዚህ ዋና ዋና የባሃኡላህ ትምህርቶች፣ ለዘለ ዓለማዊ መድህን ሚስጠሮች፣ ለሰው ዘር ፈውስና መድህን ናቸው።

## ይቅር ባይነቱ

አብዱል-ባሃ አሜሪካንን በጎበኘበት ወቅት ለወዳጆች ንግግር ሲያደርግ፦ ፍጹም የሆነ ፍቅር ይኑራችሁ። አንዱ በሌላው ላይ አይቆጣ። ዓይኖቻችሁ ወደ እውነት መንግሥት እንጂ ወደ ፍጡራን ዓለም አያተኩር። ፍጡሮችን ለእነሱ ብላችሁ ሳይሆን ለአምላክ ስትሉ አፍቅሩ። ለአምላክ ብላችሁ የምታፈቅሩአቸው ከሆነ ልትቆጡ ወይንም ትእግስት ልታጡ ከቶ አትችሉም። ሰው ፍጹም አይደለም። በእያንዳንዱ ሰው ላይ ጉድለቶች አሉ። ራሳችሁን ከተመለከታችሁ ሁልጊዜ ደስታ ያጣችሁ ትሆናላችሁ። ነገር ግን አምላክን ከተመለከታችሁ ታፈቅሩዋችዋላችሁ እንዲሁም ደጎች ትሆኑላቸዋላችሁ። ምክንያቱም የአምላክ ዓለም ፍጹም የተሟላ የምህረት ዓለም ነውና። ስለዚህ የማንንም ድክመት አትመልከቱ፤ ይልቁንም በምህረት (በይቅርባይነት) ዓይን ተመልከቱ።

## አሳቢነቱ

አብዱል-ባሃ የሳንፍረንሲስኮ ከተማን ከንቲባ እንዲያገኝ ግብዣ ተዘጋጅቶ ነበር። በግብዣው ላይ የታወቁ ሰዎችና የዩኒቨርስቲ ምሁራንም ተጋብዘዋል።

የቀጠሮው ሰዓትም እየደረሰ ሲመጣ ወደ ግብዣው ቦታ የሚወስዱት ሰዎች ሰዓት መድረሱን ያሳውቁታል፡፡ እርሱም ትንሽ ጊዜ ስጡኝ ይላል፡፡

ወደ ግብዣው ቦታ የምትወስደውም ሴትዮ ትንሽ ጊዜ ልትሰጠው ወሰነች፡፡ እንደገናም ትንሽ ቆይታ እንዲዘጋጅ ልትነግረው ወደ ክፍሉ አማራች አሁንም ትንሽ ጊዜ ሰጪኝ አላት፡፡ ሴትየዋ ትእግስቷ አለቀ፣ ግብዣው ቦታም ከንቲባው እየጠበቁ እንዳይሆን ሰጋች፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ዋናው በር ተንኳኳ፡፡ አብዱል-ባሃም ካለበት ክፍል ወደ በሩ መምጣት ጀመረ በሩ ሲከፈት አንድ ማንም የማያውቀው አቧራ በአቧራ የሆነና የተጎሳቆለ ሰውዬ በሩ ላይ ቆሟል፤ አብዱል-ባሃም ሰውዬውን ልክ ከዚህ በፊት እንደሚያውቀው ያህል አቀፈው፡፡

ሰውዬው ስለአብዱል-ባሃ ያወቀው ጋዜጣ ሲያነብ ነበር፡፡ እናም ሊያገኘው ወሰነ ነገር ግን እሱ ያለበት ቦታ ለመሄድ የመጓጓዣ ብር ስላልነበረው በእግሩ 22 ኪ.ሜትር መጓዝ ነበረበት፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ ግብዣው ቦታ በተወሰነው ሰዓት ሄዶ ቢሆን ኖሮ ሰውዬውን አያገኘውም ነበር፡፡ ነገር ግን በውስጡ ያውቅ ስለነበር ሰውዬው እስኪመጣ ጠበቀው፤ ምግብ እንዲበላና እንዲያርፍ አደረገ፡፡ ከዚያም ለሚወስዱት ሰዎች አሁን መሄድ እንችላለን አለ፡፡ ሰውዬውንም እዚህ ከጠበቀኝ ስመለስ በደንብ እንጫወታለን አለው፡፡

***

ባሃኡላህ በሕቡዓተ-ቃላት ውስጥ "አሳላፊ የያዘውን ዋንጫ ፈላጊ እስኪያገኝ እንደማያቀርብ ሁሉ ሰሚ ካላገኙ የማይናገሩ ብልሆች ናቸው፡፡" ይላል፡፡ ከዚህ ጽሑፍ ጋር

የሚስማማ አንድ ታሪክ አካ ከተማ አብዱል-ባሃ ቤት ውስጥ ተከስቷል፡፡ አንዲት ከዝቅጠኛ ቤተሰብ የተወለደች ነዋሪነቷም ሐይፋ የነበረ ካቶሊክ ወጣት ሴት አብዱል-ባሃ ቤት አካ ከተማ መጥታ ልጆቹን ፈረንሳይኛ ቋንቋ ታስተምርለት ነበር፡፡ እዚያ ያሉ የካቶሊክ ሴት መነኮሳትም ይንከባከቧታል፡፡

አንድ ቀን የፈረንሳይ ባሃኢዎች መንፈሳዊ ጉብኝት ለማድረግ አብዱል-ባሃ ጋር መጡ፤ ማንም ፈረንሳይኛ የሚያውቅ ስላልተገኘ እርሷ እንድታስተረጉም ተጠራች፡፡ በዚህም በጣም አዘነች ለሴቶቹ መነኮሳትም ሄዳ ተናዘዘች፤ ለብዙ ቀናትም ጭምት አለች፡፡ አብዱል-ባሃም ይህን ሁኔታዋን አይቶ አስጠራትና ፡- “ለካቶሊኮቹ መነኮሳት አንቺን ለማስተማር ብዬ አስተርጓሚ ያደረኩሽ እንዳይመስላቸው አጥብቀሽ አስረጂያቸው፡፡ ትምህርታችንን የምንለግሰው የእኛን ምክራችንንና መመሪያችንን በመማጸንና በጉጉት ለሚጠብቁ ብዙ ባሃኢዎች ነው፡፡ አንቺ እንድናስተምርሽ ከፈለግሽ እኛን ከልብሽ መማጸን አለብሽ፡፡ እኔም ምን አልባት አስተምርሽ ይሆናል፤ ትምህርቱ ፈላጊ ሳይገኝ ዝም ብሎ እንደርካሽ ነገር የሚሰጥ አይደለም፡፡

ከፈልግሽ እኛ ጋር መኖሩን መቀጠል ትችያለሽ፡፡ ደስተኛ ካልሆንሽ ግን ሂጂ፡፡ እዚህ መኖር ከፈለግሽ እኛ በጣም ደስተኞች ነን፤ ልብሽ ውስጥ ካለው “ባሃኢ ያደርጉኛል” ከሚል ፍራቻ በሙሉ ነፃ ሁኚ” አላት፡፡

ማበረታቻው

ሁሉም ሰው በአቅሙ ማስተማር እንዲችል አብዱል-ባሃ ያበረታታ ነበር፡፡ ሁላችሁም ይህንን ታላቅ እምነት

በምትችሉት ሁኔታ ሁሉ አስተምሩ ይላል፡፡ ለመኖር ከአውሮፓ ወደ አሜሪካ የሄደ አንድ ባሃኢ፣ እምነቱን በደንብ በማስረዳት ለማስተማር የማይችል ስለመሰለው አጭር የመግቢያ ጽሁፎችንና መጽሐፎችን ለሰዎች ማደል ብቻ ያደርግ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃም ሲያበረታታው፡ - አንተ ጥሩ እያደረክ ነው፤ ከመናገር የበለጠ ተግብረሃል፡፡ መናገርህና ማስረዳትህ ብቻ ሳይሆን እያስተማረ ያለው ልብህ ነው፡፡ ዝምታህ ይናገራል፡፡ ያንጸባርቃልም፡፡

***

ጁሊየት ቶምሰን የተባለች ጠንካራ ባሃኢን አብዱል-ባሃ ሲያበረታታት፡- አንቺ በግልጽነትና በፍቅር ይህንን እምነት እያስተማርሽ ነው፡፡ በአንች የተሳቡ ብዙ ሰዎችን አግኝቻለሁ፡፡ …እንደበተ-ርዕቱነትሽ ወይንም በደንብ ማስረዳትሽ ሳይሆን  እያስተማረ ያለው ልብሽ ነው፡፡ የምታስተምሪው ከልብ በስሜት ተሞልተሽ ነው፣ ይህ በስሜት ከልብ ማስተማርሽ ሰዎች “ምንድን ነው እንዲህ ሊያደርጋት የቻለው” ብለው እንዲጠይቁ ያደርጋቸዋል፡፡

***

ባሃኡላህ የእስር ቤት ቆይታው እንዲያበቃ ተወሰነ፣ ነገር ግን ከከተማ ማለትም ከአቆር መውጣት አይችልም ነበር፤ በዚህ ጊዜ ታዲያ አንድ በባሃኡላህ አዲስ ግልጸት ልቡ የተቀጣጠለ ግብፃዊ ነጋዴ ባሃኢ ባሃኡላህን አካ ደረስ ሄዶ መጎብኘት ፈለገ፡፡ እንዲፈቀድለትም ደብዳቤ ጻፈ፡፡ ምላሹ ግን አስገራሚ ነበር፡- የተሰጠው ምላሽ፣ መንፈሳዊ ጉብኝት ለማድረግ እኛ ጋር ከመምጣትህ በፊት ያለብህን እዳ ሁሉ ክፈል የሚል ነበር፡፡

በንግድ ዓለም ብዙ የቆየ ሰው ነበረ የንግድ አጋሰሶቹ ብዙ ውድ እቃ ጭነው ከአገር አገር ይጓጓዛሉ። በዚህ ምክንያት የበለጠ ንግዱን ማስፋፋት ይችል ነበር፣ ሆኖም ግን የእርሱ ዋና ዓላማ እዳውን መክፈል ሆነ። ከንግድ ግብይቱ ክፍያ ባገኘ ቁጥር እዳውን መክፈሉን ተያያዘው። ለ5 ዓመታት በዚሁ ቀጠለ። ከዚያም ከእዳው ነፃ ሆነ።

ንግዱ ግን ቀነሰ። ከንግድ ፍቅርም ተላቀቀ። እዳውን ሁሉ ከከፈለ በኋላ የቀረው ቤተሰቡን ለተወሰነ ጊዜ የሚያኖርና ወደ ሐይፋና አካ የሚያስኬደው ብቻ ሆነ። ቀድሞ በሃብታምነቱ ጊዜ በመርከብ ሲጓዝ የመጀመሪያ ደረጃ ክፍል ይይዝ የነበረው አሁን ግን መተኛ የሌለውና የማይሞቅ ክፍል ውስጥ ሆነ። እርሱ ግን ባሃኡላህን ሊጎበኝ ስለሆነ የሚሄደው ስለምንም ነገር ደንታ አልነበረውም። ጭራሽ ወደ መርከቡ ሲገባ ንፋስ የለበሰውን ሸማ ወስዶ ውቅያኖስ ውስጥ ጣለው። ጉዞው ተጀምሮ አመሻሽ ላይ አየሩ በጣም ይቀዘቅዝ ነበር እርሱ ግን ልቡ በደስታ ግሎ በፀሎት ተሞልቶ ነበር።

ባሃኡላህ ለቤተሰቦቹ የተከበረ እንግዳ እንደሚመጣ ነገራቸው። ከመርከብ መንፈሳዊ ጎብኝ ነጋዴውን ለመቀበልም ወደ ሐይፋ የፈረስ ጋሪ አስላከ። ባለጋሪው የሚቀበለውን ሰው ማንነት የሚገልጽ ምልክት ስላልተሰጠው ከመርከብ የሚወርዱትን ሰዎች ዝም ብሎ ሲቃኝ ቆየና ሰውዬውን መለየት ስላልቻለ ወደ አካ ተመለሰ እንግዳውም እንዳልመጣ ተናገረ።

ነጋዴው መንፈሳዊ ጎብኝ ግን መጥቶ ነበር ። ከሐይፋ ወደ አካ ለመሄድ ጋሪ ለመከራየት በቂ ገንዘብ ስላልነበረው አዝኖና ተክዞ ብቻውን ቁጭ አለ። የተላከው ባለጋሪ ሰውዬውን መለየት አዳገተው እንጂ ባሃኡላህ ጎብኘው

መምጣቱን ግን አውቋል፡፡ ስለዚህም እንደገና ሰው መላክ ነበረበት በዚህ ጊዜ ግን አብዱል-ባሃን ላከ፡፡ አብዱል-ባሃ አመሻሽ ላይ ሐይፋ መርከቡ ዳርቻ እንደደረሰም ነጋዴውን ሰውዬ ወዲያው ለይቶ አወቀው፣ አዝኖ ብቻውን ቁጭ ብሎ አገኘው፡፡ አብዱል-ባሃ ወዲያው እራሱን አስተዋወቀና የተፈጠረውን ሁኔታ ሁሉ ነገረው፡፡ ከዛም አሁኑኑ ወይንስ በነገታው ወደ አካ መሄድ እንዲሚፈልግ ጠየቀው፡፡ ሰውዬው ባሃኡላህን ከማግኘቱ በፊት ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ብዙ ሰዓታትን በፀሎት አሳልፎ ነበር ሆኖም ግን በተፈጠረው ችግር ምክንያት ምሬት ተሰምቶታል፡፡ የባሃኡላህ ደረጃም ምን እንደሆነ ማውጠንጠን ጀመረ፡፡ በመንፈሳዊ ስቃይም ውስጥ ሆነ፡፡ ሆኖም ግን ይህ የተከበረ ሰው (አብዱል-ባሃ) ያደረገለት አቀባበል ጥርጣሬውንና ግራ መጋባቱን ከነፍሱ ውስጥ ቀረፈለት፤ መንፈሳዊነት እንዲሰማው እንደገና በፀሎት ጊዜውን ለማሳለፍ ፈለገ፡፡

አብዱል-ባሃም ይህ ሰው በነገታው ወደ አካ እስኪሄዱ ድረስ ለማረፊያ የሚሆን ሆቴል እንደማይፈልግ ስለታወቀው ሰፊ ካባውን ዘርግቶ ሁለታቸውንም አለበሰና ለሊቱን ሙሉ በፀሎትና ምሕላ ሐሴት ውስጥ አሳለፉ፡፡ በነገታውም ወደ አካ ተጓዙ ይህ ግብጻዊ ሰውዬም ባሃኡላህ ፊት ከአምስት ዓመት ፈተና በኋላ በሚያበራ ልብ ለመቅረብ ቻለ፡፡

## የግልጋሎት ቁርጠኝነት

ሉዋ ጌትሲንገር የምትባለዋ አሜሪካዊ ባሃኢ አብዱል-ባሃን ለማግኘት አካ ሄዳ ሳለ አንድ ቀን አብዱል-ባሃ እንዲህ አላት፡- “ዛሬ እኔ ሥራ ስለበዛብኝ የታመመውን ደሃ ወዳጄን መጎብኘት አልቻልኩም አንቺ ሄደሽ ጎብኚው፡፡

ልክ እኔ እንደማደርገው ምግብ ይዘሽለት ሂጂ ተንከባከቢው አላት”፡፡ የት እንደሚኖርም አመላከታት፡፡ እሷም አብዱል-ባሃ ለእንደዚህ ያለ ተግባር ስላጫት ተደስታ ወደ ሰውየው ቤት ሄደች፡፡

ሆኖም ግን ወዲያው ተመለሰች በድንጋጤም “በጣም አስቸጋሪ ቦታ እኮ ነው የላከኝ፡፡ ከቦታው ሽታ የተነሳ እራሴን ልስት ነበር፣ የመኖሪያ ክፍሎቹ ገምተዋል፣ ሰውየው አስከፊ ሁኔታ ላይ ነው ያለው፡፡ እኔም ተስቦ በሽታ እንዳይዘኝ በማለት በፍጥነት ወጣሁ፡፡” አለች

አብዱል-ባሃም አዝኖና ተቆጥቶ እንዲህ አላት “አምላክን ማገልግል ከፈለክሽ፣ መሰል የሰው ዘርን አገልግይ፤ በእነሱ ውስጥ የአምላክን መልዕክትና ገጽታ ታይ ዘንድ” ከዚያም ተመልሳ ወደ ሰውየው ቤት እንደትሄድ ነገራት፡፡ “የሚሸት ከሆነ አጽጂ፣ ከቆሸሸም እጠቢ፣ ከተራበም አብይው፡፡ ይህን ሁሉ ካላከናወንሽ እንዳትመለሺ” አላት፡፡

***

አንድ የአሜሪካን ባሃኢ ለባሃኢ መጽሔት አዘጋጅ እንደተናገረችው፡- “አብዱል-ባሃ በኒዮርክ ከተማ የመጨረሻ ቆይታው ጊዜ አብሮ መሆን መቻል ትልቅ ዕድል ነበር፡፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቀው በጣም እፈልግ ነበር ነገር ግን የሚመልስልኝ መልስ ከባድ ይሆናል በማለት ለመጠየቅ ሰጋሁ፡፡ ሆኖም ግን በመጨረሻ ቀን ከመጠየቅ መቆጠብ እፍረት መስሎ ተሰማኝ ፡፡ ወደ እርሱም ሄድኩ፣ እርሱም “ጥያቄ አለሽ ወይ አለኝ” እኔም ወዲያውኑ እንዲህ ብዬ ጠየቅኩ “የባሃኢ እምነትን ለማስተላለፍ የትኛው መንገድ ነው ጥሩ” አልኩት፡፡ በዚህ ጊዜ አብዱል-ባሃ ኮስተር አለ፣ መልስ መመለስ

ሲጀምርም ድምጹን ጎላ አደረገና፡- “የመጀመሪያው ነገር ለመንፈሳዊነት ብርቱ ፍላጎት እንዲኖረን ማድረግ ነው፣ ከዚያም የባሃኢን ኑሮ መኖር ነው፣ ኑሮውን ኑሩት! ጠንካራ የመንፈሳዊነትን ፍላጎት ማዳበር የሚቻለው ሰለመጪው ሕይወታችን ማሰላሰል ስንጀመር ነው፡፡ ቅዱሳን ጽሑፎችን ደግሞ ማጥናት፣ ማንበብ…፣ በዋናነት ከአንደበቱ የፈለቁትን የባሃኡላህን ቅዱሳን ጽሑፎች ማጥናት፣ ፀሎት ማድረግ ማሳላሰል፣ ለእነዚህ ለሁለቱ በደንብ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም ታላቅ የሆነ የመንፈሳዊነት ጥማት ያድርብሻል የባሃኢ ኑሮም መኖር የምትጀምሪው ከዚያ በኋላ ነው፡፡

“የባሃኢ ሕይወትን ለመኖር እጅግ በጣም ደግ፣ ንጽሁ፣ እውነተኛ ሰው መሆን ያስፈልጋል፣ እናም ትክክለኛ የሰመረ ኑሮ መኖር”

“ጎረቤቶችሽን መጎብኘት፣ ለችግሮቻቸው ደራሽ መሆን፣ እነርሱንም ለማገልገል ጥልቅ ምኞት እንዳለሽም አሳያቸው፡፡”

“የተራቡትን መግቢ፣ ያለሽን አካፍዪ፡፡ አምላክ በሰጠሽ እርኪ፤ አምላክ እንድትንከባከቢያቸው በአደራ የሰጠሽን ታማኝ ሁኚላቸው በዚህ ጉዳይ በምንም ሁኔታ እንዳታወላውዪ፤ በአኗኗርሽ ልዩ የሆነ ነገር እንዳለሽ አሳዩ፣ በዚህም ሁሉም ይህን ተገንዝቦ ፡- “ይህ ሰው እኔ የሌለኝ ምን አለው ማለት ነው” እንዲል ይሁን፡፡”

“ዓለም በከፍተኛ ችግር፣ ድህነትና በሽታ ላይ ብትሆንም አንቺ ግን ጥንካሬ፣ ደህንነትና ሰላም የሚሰጥሽ ነገር እንዳለሽና ደስተኛ፣ የተረጋጋሽና እርካታን ያገኘሽ እንደሆነሽ አሳያቸው፡፡

“ከዚያም እነርሱ አንቺ ያለሽን እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፣ አንቺም ምን እንዳለሽ ስትነግሪያቸው ተጨማሪ ማብራሪያ አይፈልጉም፡፡”

***

አንድ ቀን አብዱል-ባሃ አሜሪካን አገር እያለ ከዋሽንግተን ከተማ ወደ ሌላ ከተማ አሥራ ሁለት ሰዓት የሚፈጅ የባቡር ጉዞ ያደርግ ነበር፤ አብሮት ይጓዝ የነበረው ሰው ለአብዱል-ባሃ ምቾት በማሰብ የተደላደለና የሚያዝናና ክፍሎች ያሉትን የባቡሩን የመጀመሪያ ደረጃ ክፍል እንዲይዝ ይለምነዋ፡፡ አብዱል-ባሃም፡- “እኔ ተጨማሪ ገንዘብ የማወጣው ሰዎችን ለመርዳትና የአምላክን እምነት ለማገልገል ብቻ ነው፤ ከልጅነቴ ጀምሮ ክብርና ዝናን አልሻም” በማለት አብሮት ለሚጓዘው ሰው ነገረው፡፡

***

የመጀመሪያ እንግሊዛዊ ባሃኢ ቶማስ ብሬክ ዌል፣ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት አካ ሄደ፡፡ ከአብዱል-ባሃ ጋር በቆየበትም ጊዜ ስለሥራው ሲያወራም አሜሪካን አገር ያለ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ እንደሚሰረና ፋብሪካውም የሕጻናትን ጉልበት እንደሚጠቀም ይነግረዋል፡፡ አብዱል-ባሃም አንክሮና በማዘን ትኩር ብሎ አየውና “አሁኑኑ የሥራ መልቀቂያህን በቴሌግራም ላክ” አለው፡፡ ቶማስ ብሬክዌልም በደስታ በእፎይታ ትእዛዙን ፈጸመ፡፡

***

አብዱል-ባሃ ጥቃቅን በሆኑ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ፍትኸኝነትን ያሳይ ነበር፡፡ አንድ ቀን ግብፅ አገር ለመጎብኘት ሄዶ ሳለ ታዋቂ ባለስለጣናትና ምሳ

ይጋብዘዋል፤ ወደ እሱም ለመሄድ የፈረስ ጋሪ ይከራያል፤ ባለጋሪውም እቦታው ካደረሰው በኋላ ከአግባብ ውጪ የሆነ ዋጋ ይጠይቀዋል፡፡ አብዱል-ባሃም ከሚገባው በላይ እንደተጠየቀ ስለገባው አልከፍልም ይላል፡፡ ባለጋሪው ግዙፍና መጥፎ ጠባይ የነበረው ሰው ስለሆነ አብዱል-ባሃን ጭምቅ አድርጎ ይዞ እየወዘወዘ የጠየቀውን ዋጋ እንዲከፍለው ያስፈራራው ጀመር፡፡ አብዱል-ባሃ ግን በውሳኔው ፍንክች ሳይል ቀረ፣ ሰውየውም ተስፋ ቆርጦ አብዱል-ባሃን ለቀቀው፡፡ አብዱል-ባሃም የሚገባውን ዋጋ ከፈለውና አጭበርባሪ ባይሆን ኖሮ ጠቀም ያለ ተጨማሪ ገንዘብ ይሰጠው እንደ ነበር ነገረውና ወደ ግብዣው ቦታ ሄደ፡፡

ይህ ሲሆን ሾጊ ኤፌንዲም አብሮት ነበር፡፡ እርሱም ከጊዜ በኋላ ስለሁኔታው ሲናገር በጣም አፍሮና ደንግጦ እንደ ነበርና ሁኔታውም ሲካሄድ ምሳ ጋብዞት የነበረው ታዋቂው ባለሥልጣን እያየ እንደነበረ ተናግሯል፡፡ አብዱል-ባሃ ግን በሁኔታው ምንም ሳይደናገጥና ሳይፈራ ላለመታለል ቁርጠኛ ሆኖ ነበር፡፡

## ለእኩልነት መቆሙ

አብዱል-ባሃ አሜሪካን በቆየበት ጊዜ ዋሽንግተን ከተማ ውስጥ ለእርሱ ክብር ሲባል የኢራን አምባሳደር ግብዣ አዘጋጀ፡፡ ታዋቂ ሰዎችን፣ ባለስልጣኖችንና ባሃኢዎችንም ጭምር ጋበዘ፡፡ በወቅቱ የተወሰኑ ጥቁር ሰዎች ብቻ የከፍተኛ ትምህርት የተማሩበት የነበረበት ወቅት ስለነበር ሉዊስ ግሪጎሪ የሚባል የተማረና የመንግሥት ሠራተኛ የነበረው በኋላም እደ-ሃይማኖት የሆነው ጥቁር ባሃኢ

ግብዣው ላይ ተጠርቶ ነበር። እርሱም በዘመኑ የነበረው የጥቁርና የነጭ ጥላቻ ይህን የግብዣ ሁኔታ ተፈታታኝ እንደሚያደረገው ቢያውቅም ወደግብዣው ቦታ በሰዓቱ ደረሰ። ከምሳው ግብዣ በፊት የሚደረገውም ንግግርና ውይይትም ቀጠለ።

ከዚያም የምሳው ሰዓት ደረሰና ሁሉም ወደ አዳራሹ መግባት ጀመሩ አብዱል-ባሃም ተከተላቸው። ሉዊስ ግሪጎሪም ግራ መጋባት ውስጥ ሆነ። ወጥቼ ልሂድ ወይንስ አብዱል-ባሃን ልጠበቅ ሲል አሰበ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የግብዣው አዳራሽ ውስጥ ተጋባዦቹ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠው ነበር። በደግነት አብዱል-ባሃ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ "የት አለ ወዳጄ ሉዊስ ግሪጎሪ ከእኔ ጋር አብሮ ምሳ መብላት አለበት" ሲል ጠየቀ። ጋባዦቹ ጥቁርና ነጭ አብሮ መብላት የማይቻልበት ስለሆነ ግብዣው ላይ እርሱን አላሳተፉትም ነበር። ሆኖም ግን ወዲያው አምባሳደሩ ሁኔታውን አመቻቸ። አብዱል-ባሃም አጠገቡ የክብር ወንበር የተባለውን ለሉዊስ አዘጋጀ አብረውም ተቀምጠው ግብዣውን ተስተናገዱ።

## ደስታ

አንድ ሴት አብዱል-ባሃን ሐይፋ ትጎበኛለች። ከጊዜ በኋላ ስለጉብኝቷ ስትናገር "ሲያናግረኝ በደግነቱና በጥሩነቱ ልቤ ተንሰፈሰፈ፤ እምባዬም ፈሰሰ። ደስተኛና ደህና እንደሆንኩ ጠየቀኝ ። እኔም ብዙ ሃዘን እንዳለብኝ ተናገርኩ። እሱም ሲመልስልኝ "ሃዘንሽን እርሻቸው! ልብሽ በአምለክ ፍቅር ከተሞላ ለሐዘን ቦታ አይኖርሽም፤ የሚኖርሽ ፍቅርና ደስታ ብቻ ይሆናል።" እነዚህን ጥዑምና የሚያጽናኑ

ቃላቶችን ሲነግረኝ የድምጹን ጣፋጭነት ልነግራችሁ ያዳግተኛል፡፡

ደስታን በተመለከተ የአብዱል-ባሃን ጽሑፎች ማንበብ፣ መንፈሳዊ ትርጉማቸውንም መገንዘብና በሚሰጡት ሙቀት መጋጋል፣ ጥልቅ የሆነ የውስጥ ደስታንና መነቃቃት ይሰጣል፡፡ ስለ ደስታ ሲናገርም፡- “ደስታ ክንፍ ይሰጠናል! በደስታ ጊዜ ጥንካሬያችን ይጎለብታል፣ አእምሯችን የሰላ፣ ግንዛቤያችን የበራ ይሆናል፡፡ ከዓለም ጋር ያለን ግንኙነትም የሰመረና ጠቃሚም እንሆናለን፡፡ ሆኖም ግን ሃዘን ሲጎበኘን ደካማ እንሆናለን፣ ጉልበታችን ይከዳናል፣ ግንዛቤያችንም ይጨልማል፣ አእምሮችን ይጋረዳል፡፡ የሕይወት ዓላማ ከእጃችን ያመልጠናል፣ የመንፈስ ዓይናችን የተከበሩ ምስጢራዊ እውነታዎችን ፈልጎ ከማግኘት ይሰናከላል፣ እንደሞተ ሰው እንሆናለን፡፡ ያዘናችሁ (የተጨነቃችሁ) አትሁኑ፡፡”

አብዱል-ባሃ ማንም ሰው ሲጎዳ ማየት አይሻም፣… ሰው ሊሰጠው ከሚችለው ስጦታ ሁሉ የበለጠው ስጦታ ሌሎችን ማስደሰት ነው፡፡

መንፈሳዊ ደስታ፣ የሰው ሕይወት እውነተኛ መሠረት ነው፤ ሕይወት የተፈጠረው ለሃዘን ሳይሆን ለደስታ ነው፤ ለደስታ እንጂ ለችግር አይደለም፡፡ መደሰት ሕይወት ነው፤ ማዘን ሞት ነው፡፡ መንፈሳዊ ደስታ የዘላለማዊነት ሕይወት ነው፡፡ ይህም ጨለማ የማይከተለው ብርሃን ነው… ይህ ታላቅ የሆነ ፀጋና ውድ የሆነ ስጦታ የሚገኘው በአምላክ መመሪያ ውስጥ ነው፡፡ ይህ ደስታ የአምላክ ፍቅር ነው፡፡

ሁሉም ሰው ወደ እናንተ እየጠቆመ፡- “እነዚህ ሰዎች ለምንድን ነው እንዲህ ደስተኛ የሆኑት” ብሎ እንዲጠይቅ ይሁን፡፡ ሌሎች እናንተን አይተው እንዲደሰቱ ደስተኛ፣ በፈገግታ የተሞላችሁ፣ የምትስቁና የምትደሰቱ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ ፡፡

አብዱል-ባሃ ሌሎች እንዲደሰቱ፣ ከጭንቀት፣ ከግራ መጋባት ነፃ እንዲሆኑ፣ ካለው ታላቅ ፍላጎት የተነሳ ብዙ ጸሎቶችን ሰጥቶናል፡-

> “አምላኬ ሆይ! መንፈሴን አድስልኝ፣ አስደስትልኝም፡፡ ልቤን አንጻልኝ፡፡ አእምሮዬን አብራልኝ፡፡ ጉዳዮቼን ሁሉ በአንተ ላይ ጥያለሁ፡፡ አንተ መሪዬና መሸሻዬ ነህ፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ የተከፋሁና ሃዘንተኛ አልሆንም፣ ደስተኛና በሃሴት የተሞላሁ እሆናለሁ፡፡ አምላኬ ሆይ ከእንግዲህ ወዲያ በሥጋት ውስጥ አልኖርም፡፡ ችግርም እንዲያስጨንቀኝ መንገድ አልሰጥም፤ደስ በማያሰኝ የህይወት ነገር ውስጥ አልኖርም፡፡ አምላኬ ሆይ አንተ ከእራሴ ይልቅ ለእኔ ትራራልኛለህ፡፡ ጌታዬ ሆይ እራሴን ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁ፡፡”

***

አንዲት ሴትዮ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት ከአሜሪካን አገር አካ ትሄዳለች፡፡ አኗኗሯም ዘመናዊነት የተላበሰ ነበር፡፡ ሆኖም ግን እርካታ የላትም ነበር፡፡ ጽኑ ክርስቲያን ብትሆንም ሃይማኖቷ እምብዛም አልተስማማትም፡፡ በዚህም ምክንያት አዝናለች፡፡ ስለአብዱል-ባሃ የሰማችው ከአገሯ ውጪ ለጉብኝት በምትጓዝበት ወቅት ነበር፡፡ በትምህርቱም ተስባ ወዲያውኑ ወደ አካ አመራች፡፡ እዚያም ስትደርስ በአብዱል-ባሃ ሁኔታ እጅግ ተማረከች

ተደነቀች፡፡ ሆኖም ግን አብዱል-ባሃ ሰላምታውን በለገሳት ቁጥር “ደስተኛ ሁኚ” ይላት ነበር፡፡ ሌሎቹን ጎብኚዎች ግን ይህን ስለማይላቸው ይህ ጉዳይ እሷን አሳሰባት፡፡ ከዚያም ለምን በዚህ ሁኔታ ሰላም እንደሚላት እንዲጠይቁላት አደረገች፡፡ አብዱል-ባሃም ሲመልስ በሚያበራ ሁኔታ ፈገግ እያለ “ደስተኛ ካልሆንን መንፈሳዊ ሕይወትን ልንገነዘበው አንችልም” አላት፡፡

## መንፈሳዊነት

አብዱል-ባሃ እንግሊዝ አገር ካደረጋቸው ንግግሮች አንዱ በአምላክ ነብያቶች (መልዕክተኞች) እና በሰው መካካል ስለሚደረግ ምናባዊ ውይይት ትምህርት የሚሰጥ ነበር፡፡ በውይይቱም ሰው የአምላክ ነብያቶችን (መልዕክተኞችን) የሚከተሉትን ጥያቄያዊ ሃሳቦች በማቅረብ ይሞግቷቸ ዋል፡- “እንደእሾታችን እንደሰታለን፣ እንደምኞታችንና እንደፍላጎታችን እንኖራለን፡፡... አምላክን አንፈራም ገነት ንም አንመኝም፤ እዚህ ምድር በምናደርገው ብቻ እንደሰታለን፡፡ እንደፈለግነው እንሆናለን፡፡ እናንተ (ነብያቶችና መልዕክተኞች) ትመጡና ፍላጎታችንን ደስታችንን ትወስዱብናላችሁ፡፡ ከዚያም ስለአምላክ ቁጣ፣ ስለቅጣትና ሽልማት ታስተምሩናላችሁ፡፡ ተስማሚያችን የነበረውን አኗኗራችንን ታዛቡብናላችሁ፡፡”

የአምላክ ነብያቶች (መልዕክተኞች) የሚሰጡት መልስ ደግሞ፡- “ሰዎች በአኗኗራቸው የእንስሳት ዓለም ፍላጎት ውስጥ መኖር ይፈልጋሉ፤ እኛ ደግሞ ወደ ሰው ዓለም እንዲመጡና ሰብዓዊ ፍጡር እንዲሆኑ እንፈልጋለን፡፡ ጨለማ ውስጥ ነበራችሁ እኛ ወደ ብርሃን እንጠራችኋለን፤ ሙት ነበራችሁ ሕይወት እንዲኖራችሁ

እንፈልጋለን፡፡ ምድራዊ ነበራችሁ መንግስተ-ሰማያዊ እንደትሆኑ እንሻለን፡፡”

***

አብዱል-ባሃ አሜሪካ አገር በነበረው ቆይታ አንድ ቀን ብሔራዊ ቤተ-መዘክርን(ሚዩዚየም) ይጎበኛል፡፡ ትንሽ አረፍ ለማለትም ወደ ውጭ ወጥቶ አንድ ዛፍ ጥላ ስር አረፍ ይላል፡፡ የቤተ-መዘክሩ አስተናጋጅም ወደ አብዱል-ባሃ ጠጋ ብሎ “እረፍት ካደረጉ በኋላ እንደገና ገብተው ተጨማሪ ጉብኝት ማድረግ ይፈልጋሉን? ሲል ጠየቀው፡፡ አብዱል-ባሃም ፈገግ እያለ “ የዚህን ዓለም ሁኔታዎችና ክንዋኔዎች ማየት ደክሞኛል፡፡ እኔ የምፈልገው ወደ ላይኛው ወደ ሚቀጥለው ዓለም መሄድና መንፈሳዊውን ዓለምን መጎብኘት ነው፡፡ ስለዚህ ሁኔታ ምን ሀሳብ አለህ?” አለው፡፡ ሰውየውም ግራ ገባው ፡፡ አብዱል-ባሃም እንደ ገና እንዲህ ሲል ጠየቀው “ የትኛውን ዓለም የበለጠ ትፈልገዋልህ ይህን ቁሳዊውን ዓለም ወይንስ መንፈሳዊውን ዓለም?” ሰውየውም “እንደእኔ ከሆነ ይህ ቁሳዊው ዓለም ይሻለኛል” አለ፡፡ አብዱል-ባሃም “ወደ መንፈሳዊው ዓለም ስትሄድ ቁሳዊው ዓለም አብሮህ ይሆናል፤ ልክ አንደ ፎቅ ቤት ውስጥ ሆነህ ወደላይኛው ክፍሎች ፎቁን ወጥተህ እንደመግባት ነው ወደላይኛው ክፍል በመሄድህ ቤቱን ጥለህ ሄድክ ማለት አይደለም፡፡” በዚህ ጊዜ ሰውየው ሁኔታው እንደብርሃን ፍንትው አለለት፡፡

***

ሉዋ የተባላችው ታላቋ የአሜሪካን አገር ባሃኢ ለመጀመሪያ ጊዜ አብዱል-ባሃን ለመጎበኘት ከምዕራቡ ዓለም ከሄዱት ምዕመናኖች ውስጥ ዋናዋ ናት፡፡ ከዚያም

ጊዜ በኋላ ለቀጣዮቹ አሥራ ስምንት ዓመታት ሐይፋና አካ አብዱል-ባሃን ለመጎብኘት ተጉዛለች፡፡ አብዱል-ባሃም እምነቱን የማስተማር ሃላፊነቶች በተደጋጋሚ ይሰጣት ነበር፡፡

አብዱል-ባሃም ሲመክራት፡- "በዓላማሽ ጽኑና ጠንካራ መሆን አለብሽ፡፡ በምንም ዓይነት ውጫዊ (የግልም ሆነ የዓለም) ጉዳዮችና ነገሮች ሊያሳስቡሽ አይገባም፡፡ እርግጠኛ የሆነ ውጤት እንድታመጪ ወደ ሕንድ አገር እልክሻለሁ፤ ወደ እዚያ አገር ስትገቢ ግልጋሎትሽ የተሳካ እንዲሆንልሽ ብርታት የተሞላው መንፈሳዊነት፣ ብሩህ እምነት፣ የማያልቅ ጉልበት፣ የማይዳፈን እሳት፣ ጽኑ ትጋት ይኑርሽ፡፡ ልብሽ አይሸበር፡፡ እንደዚህ ባለ በማይናወጥ ጽኑ ሁኔታ ከሄድሽ የስኬት በሮች ወለል ብለው ሲከፈቱልሽ ታያለሽ፣ ሕይወትሽም በመንግሰተ ሰማያዊ ጽጌሬዳ ያጌጣል፣ ታላቅ ድልም ትጎናጸፊያለሽ፡፡

ይህን የላቀ ደረጃ እንድትቀዳጂ በቀንም በማታም ጥረት አድርጊ፡፡ እኔን ተመልከቺ! በሺህ የሚቆጠሩ አስቸጋሪ ነገ ሮችና መሰነናክሎች በየቀኑ ይገጥሙኛል፡፡ እኔ ግን ትኩረት አልሰጣቸውም፤ በተመረጠልኝ የአገልግሎት ጎዳና መጓዜን እቀጥላለሁ፡፡

ሉዋ በቅጽበት መንፈሳዊነትን መቀዳጀትና አብዱል-ባሃን ማገልገል ፈለገች፡፡ በዚህም ምክንያት እረፍት አጣች ትእግስቷ አለቀ፡፡ አብዱል-ባሃ ፈጣን እድገትን ልትቋቋመው እንደማትችል ነገራት የፍጹምነት ደረጃ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ሂደት ነው አላት፡፡

ለእምነቱና ለአብዱል-ባሃ ያላት ፍቅር ወሰን የለውም ነበር፡፡ በመንፈሳዊነት እየጎለበተች ስትመጣ ይህ ዓለም

ለእሷ እምብዛም የማያሳስባት ሆነ፡፡ አለባበሷ እንኳን ሳይቀር ተቀየረ የዘመኑን አለባበስ ተወች፡፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመኗም እጅግ ከፍተኛ የመንፈሳዊነትን ሕይወትም ኖረች፡፡

***

አንድ ሰው ስለሞት ምን ዓይነት እይታ ሊኖረው እንደሚገባ አብዱል-ባሃ ተጠይቆ ሲመልስ፡-

“አንድ ሰው ወደ አንድ ቦታ ሲጓዝ የጉዞውን መድረሻ (ማብቂያ) እንዴት ነው የሚጠባበቀው? በተስፋና በጉጉት አይደለምን! የምድራዊውን ሕይወት ጉዞ ማብቂያ እንዲሁ በተስፋና በጉጉት መጠበቅ አለብን፡፡ በሚቀጥለው ዓለም፣ ሰው በዚህ ዓለም እንቅፋት ከሆኑትና ከሚያሰቃዩት ነገ ሮች ሁሉ ይላቀቃል፡፡ የሚቀጥለው ዓለም በጊዜና በቦታ የማይወሰን ነው፡፡ በእዚህ ምድራዊ ዓለም፣ ጊዜ የሚቆጠረው ፀሐይ ስትወጣና ስትጠልቅ ነው፡፡ ወደሚቀጥው ዓለም የተሸጋገሩ ሰዎች እዚህ ካሉት ሰዎች የተለየ ባሕሪይና ሁኔታ ይኖራቸዋል፤... ሆኖም ግን በፀሎት ልንገናኝ የምንችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ለእነርሱ እንደምንጸልይ ሁሉ እነርሱም ለእኛ ይጸልዩልናል፡፡”

## ድፍረት

ባሃኡላህና ተከታዮቹ አካ ከገቡ ከሶስት ቀናት በኋላ የሱልጣኑ በእድሜ ልክ እስራት የሚያወግዘው አዋጅ በመስጊዱ ውስጥ ተነበበ ፡፡ እስረኞቹ የሕዝቡን ሥነ ምግባር ያበላሹ ወንጀለኞች እንደሆኑ ተነገረ ፡፡ እነርሱም

በእስር ቤት ውስጥ ብቻ እንዲወሰኑና ከማንም ጋር መገናኘት እንዳልተፈቀደላቸው ተገለጸ፡፡

አብዱል-ባሃ የትእዛዙን ይዘት እንዲያውቅ በአካ አስተዳዳሪ ተጠርቶ ነበር፡፡ ለዘለዓለም በእስር እንደሚቆዩ በተነበበለት ጊዜ አብዱል-ባሃ የአዋጁ ይዘቶች ትርጉም የለሽ እና መሠረት ቢስ ነው በማለት ምላሽ ሰጠ፡፡ አገረ-ገዥው ይህንን አስተያየት ከሰማ በኋላ ተቆጥቶ አዋጁ ከሱልጣኑ ነው ሲል አፀፋውን ገለጸ፣ እናም እንዴት ትርጉም የለሽ መሆኑን ለማወቅ ፈለገ፡፡ አብዱል-ባሃ አስተያየቱን በድጋሚ በመጥቀስ ሰው በዚህ ዓለም ውስጥ የሚኖረው ለአጭር ጊዜ ብቻ በመሆኑ እስር ቤታቸው ለዘለዓለም የሚቆይ ነው ብሎ መግለፅ ትርጉም እንደሌለው፣ እናም አሁን ወይም ከጊዜ በኋላ እስረኞቹ ይህን እስር ቤት ሞተው ወይም በሕይወት እያሉ ለቀው ይወጣሉ በማለት አስረዳ፡፡ አገረ-ገዥው እና ባለስልጣኖቹ በአብዱል-ባሃ አርቆ አስታዋይነት ተደነቁ እናም የመረጋጋት ስሜት ተሰማቸው፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አብዱል-ባሃ በአካ እና በአጎራባች አገሮች ውስጥ በጣም ታዋቂ እና በጣም የተወደደ ሰው ሆነ ፣ ሁሉም የአካ ሰዎች ፣ ከፍተኞቹም ሆኑ ዝቅተኞቹ ለእርዳታ ወደ እርሱ ዞሩ፤ አገረ ገዥዎች እና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ምክሩን ሲፈልጉ የዕውቀት ብርሃኑን ለመቀበል በእግሩ አጠገብ ተቀመጡ፤ ከዚያም የባሃኡላህ እና የተከታዮቹ መታሰርን አስመልክቶ የሱልጣኑ አዋጅና ሌሎች ሰነዶች ከመንግሥት ፋይሎች ተወገዱ፡፡

## ስክነት እና መረጋጋት

በትውልድ አገሯ የባሃኢን እምነት የተቀበለች የመጀመሪያዋ እንግሊዛዊት ሴት የሆነችው ኤቴል ሮዘንበርግ ቅድስት አገር እየጎበኘች ሳለ 'አብዱል-ባሃ እንዲህ አላት "መጥፎ ባሕርያችንን ወደ ጥሩ ለመለወጥ መጣር አለብን፤ ፈጣን ቁጣን ወደ መረጋጋት፣ ኩራትን ወደ ትህትና፣ ሐሰትን ወደ እውነት፣ ማታለልን ወደ ግልፅነት፣ ስንፍናን ወደ ተግባር መለወጥ አለበት።

## በአምላክ መተማመን

በአንድ ወቅት ጁሊየት ቶምሰን የተባለች አሜሪካዊት ባሃኢ አብዱል-ባሃን በጣም ስለታመመችው ሴት ልጁ ሩሃ ካኑም ደህንነት ጠየቀችው። አብዱል-ባሃም ሲመልስ "ለተባረከው ለፍጹሙ እጅ አሳልፌ ሰጥቻታለሁ፣ ከዚህ በኋላ ምንም የሚያሳስበኝ ነገር የለም" አለ።

***

ወንድ ልጇን ያጣች ሴትን አብዱል-ባሃ ሲያጽናና እንዲህ አላት " እኔ የአራት ዓመት ወንድ ልጅ ነበረኝ ልጄ ሲሞት አመላካከቴና ባሕሪዬ አል ተቀየረም ምክንያቱም ልጄን በአደራ ለአምላክ እንደሰጠሁ ነው የምቆጥረው በመሞቱም አላዝንም" አላት።

***

አንዲት ምዕመን አካ አብዱል-ባሃንና ቤተሰቦቹን ጎብኝታ መመለሻዋ የደረሰ ቀን ልትሄድ ስትል አብዱል-ባሃ ወደ ክፍሏ ሊሰናበታት ይመጣል፣ በመስኮቱ አጠገብ ተቀምጦ

ለረጅም ጊዜ በዝምታ ወደ ባሕሩን አሻግሮ ይመለከታል። እሷ መኖሯን የረሳት መስሏታል።

ከዚያም ከብዙ ቆይታ በኋላ ወደ እርሷ ይዞርና ያ በሚታወቅበት አነቃቂ ንግግሩ እንዲህ ይላታል፡- "ወደ ኒውዮርክ ስትመለሺ ሰዎችን ስለአምላክ ፍቅር ማናገር አለብሽ። የዓለም ሕዝቦች ስለአምላክ በበቂ ሁኔታ አይነጋገሩም። ውይይታቸው ጥቃቅን በሆኑ ነገሮች ተሞልቷል፣ እናም በጣም አስፈላጊ ርዕሰ ጉዳዮችን ይረሳሉ። ስለአምላክ ብትነግሪያቸው ደስተኞች ይሆናሉ፣ ልባቸው ንም ይከፍቱልሻል። ብዙውን ጊዜ ይህንን ክቡር ግልጸት መጥቀስ አትችይ ይሆናል። ምክንያቱም፣ ጭፍን ጥላቻ ቸው ጣልቃ ስለሚገባ አይሰሙም። ሆኖም ሁልጊዜ ስለአምላክ ፍቅር የምታወሪበት መንገድ ታገኝያለሽ።

ይህን ነግሯት ሄደ እሷም በክፍሏ ውስጥ እስኪጨልም ድረስ ቁጭ ብላ ቆየች። የጨለማው ድባብ እነዚህን የአብዱል-ባሃን የመጨረሻ ቃላት የሚያስተጋቡ ይመስላሉ "ሆኖም ሁልጊዜ ስለአምላክ ፍቅር የምታወሪበት መንገድ ታገኚያለሽ።"

## መርካት መቻል

የወህኒ ቤቱ ግድግዳዎች እራሳቸው በአብዱል-ባሃ ልብ ውስጥ ያለውን ደስታ አላደበዘዙትም። እስር ቤት ሆኖ ሲጽፍ፡- "በእስራቴ እና በመከራዬ ምክንያት አትዘኑ፣ ይህ እስር ቤት ለእኔ ውብ የአትክልት ስፍራዬ፣ ገነታዊ ቤቴ እና በሰው ልጆች መካከል የግዛት ዙፋኔ ነው። በእስር ቤት ውስጥ የደረሰብኝ መከራ በጻድቃን መካከል የምመካበት የእኔ ዘውድ ነው።"

በሌላ ጊዜ ደግሞ ሲጽፍ "ማንኛውም ሰው በምቾት፣ በድሎት፣ በጤንነት፣ በስኬት፣ በመዝናናትና በፈንጠዝያ ሁኔታ ውስጥ ደስተኛ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አንድ ሰው በችግር ፣ በመከራ እና በተንሰራፋ በሽታ ጊዜ ደስተኛ እና የተረጋጋ ከሆነ የክቡርነቱ ማረጋገጫ ነው።"

የሕይወት ተሞክሮዎች (ውጣ ውረዶች) የአብዱል-ባሃን አመለካከት አለመመረዛቸውንና አለመበጥበጣቸውን ማወቅ እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው። የሳምባ ነቀርሳ በሽታ በሰባት አመቱ አሰቃየው፣ ከዚያም ድህነት ፣ ከባሃኡላህ መለየት፣ ግዞት፣ እስራት፣ የወንድ ልጁ በሕፃንነት መሞት፤ እነዚህን ሁሉ ተቋቁሞ ለሕይወት ብሩህ እና ደስተኛ ነው። በመከራ ውስጥ በክብር ተራምዷል።

***

አብዱል-ባሃ በልዩ አደጋ እና ችግር ውስጥ በነበረበት ወቅት በጻፈው 'ቃል-ኪዳን ኑዛዜ' ውስጥ በጸሎት ወደ አምላክ በመዞር፦ "በታላቅ የመከራ ባሕር ውስጥ ተጠምቄ፣ ለጥልቀቱ መጨረሻ የሌለው ገደል ውስጥ ሰጥሜ ልባቸውን ወደዚህ ወደ ተበደለው እንዲመልሱ በጠንካራ ቃል-ኪዳንህ እና ኑዛዜህ ዘመዶቼን ብታዝም እነርሱ ባቀጣጠሉት የጥላቻቸው ነበልባል ተቃጥዬ ታያኛለህ…"

እንዲህ ሆኖ እያለም በተጨማሪ በሚያደርገው ጸሎት "በዝቅተኛነት፣ በመማጸን እና በግምባሬ ተደፍቼ፣ የጎዳኙን ሁሉ ይቅር እንድትልልኝ ጥልቅ በሆነ ልመና እማጸንሃለሁ፣ በእኔ ላይ ያሴረውንና የጎዳኝን ይቅር በለው፤ በኔ ላይ ግፍ የሰሩብኝን ኃጢአታቸውን እጠብ።

መልካም ስጦታህን ለእነርሱ ለግሳቸው፣ ደስታም ስጣቸው…”

አብዱል-ባሃ ወዳጆችን አበክሮ ሊነግራቸው የሚፈልገው፡- “ሌሎች ሕይወታችሁን ቢመርዙ ነፍሳቸውን አጣፍጡላቸው” ብሏል ምክንያቱም እርካታ እና ደስታ ብዙውን ጊዜ ከሀዘን እና ከስቃይ ውስጥ እንደሚወለዱ ጠንቅቆ ያውቃል።

አብዱል-ባሃ በሕይወት ውስጥ ቀላል አካሄድ ባይኖርም በፀጋ ይቀበላል። ከባድ ጉስቁልናዎችን በቸርነት ይቀበላል፤ ለመፈፀም አስቸጋሪ በሆነው ነገር በጭራሽ አይበገርም። በአገልግሎት መንፈስ ሥራን ይሠራል፣ አምልኮ ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑን ያውቃል። ማማረር የእርሱ ተፈጥሮ አይደለም። በአምላክ ፈቃድ መርካት ለመንፈሱ ተፈጥሮአዊ ነበር ።

***

አብዱል-ባሃ በትከሻው ላይ የአበባ ማስቀመጫዎችን ተሸክሞ በሙቀት ሁለት ማይል በእግር ይሄድ ነበር። እርሱ ፀጉሩና ጺሙ የነጣ  አዛውንት ቢሆንም እነዚህን የአበባ ማስቀመጫዎች በአባቱ በባሃኡላህ መካነ-መቃብር አጠገብ ለመትከል ከአንደኛው የአትክልት ስፍራ ይዞ ይመጣ ነበር። በቀድሞ ዘመን በባሃኡላህ መቃብር አቅራቢያ አንድ በእጅ የሚሠራ የውኃ ፓምፕ ነበር፣ አብዱል-ባሃ ምንም እንኳን እድሜው የገፋ ቢሆንም ውኃ በእጁ ፓምፕ ያደርግ ነበር። ብዙ ከመስራቱ የተነሳ ሰውነቱ ተገትሮ ይቀር ነበር፣ ከዚያም የሚሻለው ሰዎች መጥተው ተሸክመው ወስደው ካሻሹት በኋላ ነበር። ለምንድን ነው እንዲህ ሰውነትህን የምታደክመው ብለው

ሰዎች ሲጠይቁት "ታዲያ ለባሃኡላህ ምን ላድርግ" ይል ነበር፡፡

## ሳቅና ደስታ

አብዱል-ባሃ ሳቅን ይወድ ነበር እናም የእርሱ ሳቅ ብዙውን ጊዜ የመጽናኛ ምንጭ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ጸሐፊ አብዱል-ባሃ በጣም ከልቡ ከመሳቁ የተነሳ ጥምጣሙ ሁሉ ወልቆ እንደነበረ አስተውሏል፡፡

አሜሪካን አገር ሳለ ሜይ ማክስዌል የተባለች ካናዳዊ ምዕመን ከልጇ እና ጁሊየት ቶምስን ከምትባል አሜሪካዊ ባሃኢ ጋር በመሆን ሊጠይቁት ሄዱ፡፡ ከእርሱ ጋርም አስደሳች ቆይታ አደረጉ፣ ግን በመጨረሻ ጁሊየት ተጨነቀች እና 'አድክመንህ ከሆነ መሄድ እንችላለን?' አለችው፡፡ እርሱም 'የለም አላደከማችሁኝም ቆዩ እንድስቅና እንድ ዝናና ታደርጉኛላችሁ' አላቸው፡፡

***

በአንድ ወቅት ስለ አንድ የሚያስቅ ቀልድ በማሰቡ ደስ ብሎታል፡፡ ለመናገርም በአዕምሮው ያብሰለስላል፡፡ አብረውት ያሉ ወዳጆችም እንዲነግራቸው ይለምኑታል፡፡ እርሱም 'አይ፣ አልቻልኩም፣ ለመንገር በሞከርኩ ቁጥር ስለ ምስቅ መናገር ያቅተኛል' አላቸው፡፡

***

በለንደን አብዱል-ባሃ "ዊክሊ በጀት" ከተባለ ጋዜጣ አዘጋጅ ተወካይ ጋር ቃለ ምልልስ አደረገ፡፡ በአካ ከተማ ስላሳለፉት የመጀመሪያ ክረምት ሲናገር፡- 'አካ በሽታ የበዛባት ከተማ

ናት፡፡ በከተማው ላይ ለመብረር የሚሞክር ወፍ በድንገት ወድቆ ይሞታል ይባል ነበር፡፡ ምግቡ የማይረባና በቂም አልነበረም፣ ውሃው ከተበከለ የጉድጓድ ውሃ የሚቀዳ ነበር፡፡ የአየር ንብረቱና ሁኔታዎቹ እንደዚህ ነበሩ፣ የከተማው ተወላጆች እንኳን ታመው ይሞቱ ነበር፡፡ ብዙ ወታደሮች እራሳቸውን ሳቱ፣ ከአሥር ጥበቃዎች መካከል ስምንቱ ሞቱ፡፡ በከባድ ሙቀቱ የተነሳ ወባ፣ ታይፎይድና ተቅማጥ እስረኞቹን አጠቃቸው፡፡ ሁሉም ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናት በአንድ ጊዜ ታመው ነበር፡፡ ሐኪሞች አልነበሩም፣ መድኃኒት የለም፣ ተገቢ ምግብ የለም፣ እንዲሁም ምንም ዓይነት ሕክምና አልተደረገም፡፡ እኔ ለሰዎች ሾርባ እሰራ ነበር፣ ብዙ መስራት ስለተለማመድኩ ጥሩ ሾርባ እሰራ ጀመር’ በማለት ሣቀ፡፡

***

አንድ የበጋ ቀን በምሳ ሰዓት ላይ ደብሊን ከተማ ውስጥ በሚስተር ፓርሰንስ ቤት ውስጥ የምሳ ግብዣ ተካሂዶ ሃያ የሚሆኑ በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ጎልተው የሚታዩ ሰዎች አብዱል-ባሃን እንዲያገኙ ተደርጎ ነበር፡፡ ባህል፣ ሳይንስ ፣ ጥበብ፣ ሀብት፣ ፖለቲካ፣ ስኬት ሁሉም ተወክለዋል፡፡ በዚህ የምሳ ግብዣ ላይ ከተገኙት መካከል አብዛኛዎቹ ስለ አብዱል-ባሃ የሕይወት ታሪክ ጥቂት ብቻ ነበር የሚያውቁት፣ ስለሆነም ስለባሃኢ እምነት ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ይጠብቁ ነበር፡፡ ጋባዣቸው ስለዘለዓለማዊነት እንዲናገር ለአብዱል-ባሃ ሀሳብ አቀረበች፡፡ የምሳ ግብዣው እየቀጠለም ሳለ የመግቢያ ንግግር አደረገች፡፡ ከዚያም አብዱል-ባሃ ስለመንፈሳዊ ጉዳዮች ንግግር ያደርጋል ብላ አሰበች፡፡

አብዱል-ባሃ ግን አንድ ተረት ቀመስ ታሪክ እንዲነግራቸው ፍቃዳቸውን ጠየቀና ከዚያም ስለአንድ ትልቅ መጋዘን ስለነበረው ሰው ተረከላቸው፣ የምሳ ግብዣው ላይ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ከልቡ ይስቅ ጀመር፡፡

ትረካው ዝምታቸውን ሰበረላቸው፡፡ በዚህ ትረካ የተነቃቃ ሰው ሌላ ትረካ አቀረበ የአብዱል-ባሃ ገጽም በደስታ በራ ሌላ ታሪክ ነገራቸው፡፡ የእርሱ ሳቅ ቤቱን ሞላው፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ፣ መሳቅ ጥሩ ነው፡፡ ፈገግታ መንፈሳዊ መነቃቃያ ነው፡፡ እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ እና እጅግ በጣም እጦት እና ችግሮች ባሉበት ጊዜ እያንዳንዳቸው በቀኑ መገባደጃ ላይ የተከሰተውን እጅግ አሳዛኝ ክስተት በቀልድ አድርገው ይተርካሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚያስቅ ነገር ማግኘት ከባድ ነበር ግን ሁልጊዜ እንባቸው በጉንጮቻቸው ላይ እስኪፈስ ድረስ ይስቁ ነበር፡፡ ደስታ በጭራሽ በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተመካ አይደለም፣ አለበለዚያ እነዚያ ዓመታት ምን ያህል አሳዛኝ በሆኑ ነበር፡፡ እነርሱ ሁል ጊዜ በከፍተኛ ደስታ ውስጥ ነበሩ ፡፡

ስለባሃኢ ተልዕኮ ትንሽ ብቻ ቢነግራቸውም በደስታ ስላዝናናቸው የነበረው ውጤት ስለባሃኢ እምነት ሰፊ ማብራሪያ ከመስጠት የበለጠ ነበር፡፡

***

የባሃኡላህ እና የአዲሱ ዘመን ደራሲ ዶ/ር ጄ.ኢ. ኤስ ሌሞንት፣ እ.ኤ.አ በ1919 ክረምት ወቅት ላይ የአብዱ-ባሃ እንግዳ በመሆን በሐይፋ ለሁለት ወር ተኩል ቆይቶ ነበር ፡፡ በቆይታው ያስተዋለው አብዱል-ባሃ ‘በምሳም ሆነ በእራት ጊዜ በርካታ ምዕመናን እና ወዳጆችን ያዝናና ነበር፣ እንግዶቹን ያስደስታል አስቂኝ ታሪኮችም

ይነግራቸዋል እንዲሁም በብዙ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ድንቅ ንግግሮችን ያደርጋል፡፡ "ቤቴ የሳቅና የደስታ ቤት ነው" አላቸው በእውነትም የእርሱ ቤት እንደዛ ነበር፡፡ በእንግዳ ተቀባይነቱ ዙሪያ የተለያዩ ዘሮችን፣ ቀለሞችን፣ ብሄሮችንና ሃይማኖቶችን በአንድነት እና በወዳጅነት በመሰብሰብ ይደሰታል፡፡ "እዚህ ቤት የሚገባ ማንኛውም ሰው ሲወጣ ልቡ ተደስቶ መውጣት አለበት፡፡" ይል ነበር፡፡

***

አብዱል-ባሃ አካ በስደት እያለ ከአንድ ጊዜ በላይ እሱን የመጎብኘት ደስታ ያገኘች አንዲት አሜሪካዊት ምዕመን፣ አብዱል-ባሃ ቤት ተሰብስበው ስለአየችው ስትናገር፤ እኔ ከተቀመጥኩበት አጠገብ ያሉ ሰዎች የተለያየ ዘር ያላቸው ሰዎች ነበሩ፣ አንዳንዶቹ ዘሮቻቸው ከጥንት ጀምሮ ጠላት የሆኑ ነበሩ፣ እዚህ ግን እነርሱ እርስ በእርሳቸው እጅግ በጣም ይዋደዳሉ፡፡ የፍቅራቸው እውነታ ቀስ በቀስ ለእርሷ ግልጽ እየሆነ ሲመጣ፣ ከዚህ ባሻገር ባለው ዓለም ውስጥ ያለው የአንድነት ቅርበት የዕውቀት ጨረር ፍንትው አለላት፡፡ ምግብ በልተው ሲጨርሱም አብዱል-ባሃ ስለ ዘለዓለማዊው ዓለም ተናገረ፡፡ የተናገራቸውም ቃላት "ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ አብረን ተቀምጠናል፣ በመንፈሳዊ ግዛቱም ውስጥ እንዲሁ ብዙ ጊዜ አብረን እንሆናል፡፡ በእነዚያ ጊዜያት አብረን በደንብ እንስቃለን እናም በአምላክ መንገድ ስላጋጠመን ነገር እናወጋለን፡፡ በእያንዳንዱ የአምላክ ዓለማት ውስጥ ለታማኞች አዲስ የጌታ እራት ተዘጋጅቶላቸዋል" አለ፡፡

***

አብዱል-ባሃ አሜሪካን አገር ኒውዮርክ ከተማ ጉብኝት ላይ እያለ፣ የመሬት ግብር እንዲሻሻል የሚጥር ሰውዬ ይጎበኘዋል እናም "ለጓደኞቼ ምን መልዕክት ልውሰድላቸው" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ አብዱል-ባሃም "ወደ አምላክ መንግሥት እንዲገቡ ንገራቸው እዚያ ብዙ መሬት ያገኛሉ ግብርም የለባቸውም" ሲል ከመለሰለት በኋላ ከት ብሎ ሳቀ፡፡

***

በኤድንበርግ ከተማ ውስጥ አብዱል-ባሃ ለእስፔራንቶ ቋንቋ ተናጋሪዎች ንግግር አድርጓል፡፡ በሰዎች መካከል ትክክለኛ የቋንቋ ግንኙነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አፅንዖት በመስጠት ሲናገር፡- "በባግዳድ ውስጥ የተከሰተ አንድ ክስተት አስታውሳለሁ፡፡ አንዳቸው የሌላውን ቋንቋ የማያውቁ ሁለት የሚተዋወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ አንደኛው ታመመ ፣ ሌላኛው ሊጠይቀው ሄደ ፣ ነገር ግን ስሜቱን በቃላት መግለጽ ባለመቻሉ "እንዴት ይሰማሃል?" ለማለት የምልክት ቋንቋ አሳየው፤ ታማሚውም "እኔ በቅርቡ እሞታለሁ" ሲል በምልክት መለሰ፡፡ እሱም ያሳየው የምልክት ቋንቋ እየተሻለኝ ነው የሚል መስሎት "አምላክ የተመሰገነ ይሁን" ብሎት ሄደ፡፡

***

አብዱል-ባሃ አንድ የጋራ ቋንቋ አስፈላጊነትን የሚጠቁም ሌላ ታሪክ ነገራቸው "በከተማዋ በር ላይ አራት ተጓዦች ተቀምጠዋል፣ ፋርሳዊ፣ ቱርካዊ፣ አረብና ግሪካዊ ናቸው፤ ተርበው ስለነበር መብላት ፈለጉ፡፡ ከማሃከላቸው አንዱ ሄዶ የሚበሉትን እንዲገዛ ተስማሙ፡፡ ምን እንደሚገዛ መስማማት ግን አልቻሉም፡፡ ፋርሳዊው አንጎር፣ ቱርክ

ኡዙም፣ አረቡ አይነብ፣ ግሪካዊው ስቴፋይልዮን አረንጓዴ እና ጥቁር እንደሚፈልጉ ይናገራሉ። የእያንዳንዳቸው ልዩ ፍላጎት ትክክለኛ ምግብ መሆኑን ለማረጋገጥ በመሞከር ተጣሉ፣ ተጨቃጨቁ እናም ለመደባደብ ተቃረቡ። በድንገት ወይን የተሸከመች አህያ ባጠገባቸው አለፈች። ከተቀመጡበት በፍጥነት ተነስተው በጉጉት በተሞላ እጆች "ኡዙምን ተመልከት!" አለ ቱርኩ። "አይነብ ተመልከት!" አለ አረቡ። "አንጎር ተመልከት!" አለ ፋርሳዊው፣ ግሪኩም ስቴፋይልዮን አለ። ከዚያ ወይናቸውን ገዙና ሰላማቸውን አገኙ።

## የአብዱል-ባሃ ቃላቶች እና ተግባሮች ውጤት

አንድ ጸሐፊ እንደዘገበው አብዱል-ባሃ በአንድ ወቅት የባሃኢ እምነትን ከአትክልት ሥፍራ ጋር አነፃፅሮታል። ሲናገርም፡- "አንዳንዶች በአትክልት ሥፍራው በር ላይ ቆመው ወደ ውስጥ ይመለከታሉ፣ ለመግባት ግን አይፈልጉም። ሌሎቹ ደግሞ ወደ ውስጥ ይገባሉ፣ ውበቱን ይመለከታሉ ነገር ግን አይቆዩም። ሌሎቹ ደግሞ በአትክልት ስፍራ ውስጥ ይንሸራሸራሉ የአበቦቹን መዓዛ ያሸታሉ፣ በውበቱ ይደሰታሉ ከዚያም በገቡበት በር ተመልሰው ይወጣሉ። አንዳንዶች ደግሞ፣ ይገባሉ፣ በሚያዩት የአትክልት ሥፍራ ድምቀት ሰክረው ለመንከባከብ ሕይወታቸውን ይሰጣሉ።"

አብዱል-ባሃ የአምላክን የአትክልት ስፍራ በር ከፈተ፣ መከተል ለሚፈልጉ ሁሉ መንገዱን መራ። በእርግጥ በባሃኢዎችም ሆነ በወዳጆች ላይ እናም በጠላቶቹ ላይ የአብዱል-ባሃ ምሳሌያዊ ሕይወት በአጠቃላይ በብዙዎች

ላይ የሚደርሰውን ውጤት ማንም ሰው መቼም ቢሆን ሊገምት አይችልም፡፡

***

በአንድ ወቅት ባሃኡላህ እራሱ ቫርቃ ለሚባል አማኝ ሲናገር፣ አብዱል-ባሃን ተመልከት ፣ የእርሱ ተግባራትና ቃላቶች በዓለም ላይ ምን ያህል አስደናቂ ውጤት እንደሚኖራቸው፣ ሁሉንም ችግሮች እንዴት በደግነት እና በትዕግሥት እንደሚቋቋም አስተውል ብሎት ነበር፡፡

***

አብዱል-ባሃን የሚያከብሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዷ ጁሊየት ቶምሰን የምትባል አሜሪካዊት ጠንካራ ባሃኢ ስትሆን ስለ እርሱ ስትጽፍም “እርሱ ዘላለማዊው የሆነው በማይጠፋው ውበቱ፣ በብርሃናማ ኃይሉ፣ በሚያስደንቅና ባልተለመደ ግርማው፣ በሰብዓዊው ዓለም በሰዎች መካከል ሲራመድ፣ የሚደነቁ ዓይኖች ሁሉ ይከተሉታል፡፡”

***

ባለቅኔው ካህሊል ጊብራን ሲጽፍ “ለመጀመሪያ ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሚሆን ክቡር ገጽታ አየሁ!” ብሏል

***

አንድ አምላክ የለም ብሎ የሚያምን ሰው አብዱል-ባሃ ሲናገር ለመስማት ወደ አንድ ቤተክርስቲያን ሄደ፣ ከዚያም “ስለአብዱል-ባሃ ምን ይሰማሃል” ተብሎ ሲጠየቅ

በንዴት ሆኖም ግን በአግራሞት “የናያጋራን ፏፏቴ ታላቅነት ያህል ተሰምቶኛል?” በማለት መለሰ፡፡

***

እርሱን ያገኙት ሰዎች ሁሉ የሚረዱት እንደአቅማቸው ነበር፡፡ አንዲት የማሕበራዊ ተቋም አባል ሴት ስትናገር፡- “እንደዚህ ዓይነት የጥንካሬ ውበት እና እንደዚህ ዓይነት ማራኪነት! እርሱ የዓለም ፍጹሙ ሰው ነው! ” ሌላ እርሱን ያነጋገረች የማሕበራዊ ተቋም አባል የሆነች ሴት ደግሞ “ከእርሱ ምንም ነገር መደበቅ አይቻልም! የልቤን ውስጥ አየው ምስጢሮቼን ሁሉ ተገነዘባቸው” ብላለች፡፡

***

አሰቃቂ ሕይወት በማሳለፏ ሃዘን ላይ ያለች አንዲት ሴት ስለ አብዱል-ባሃ ስትናገር “ሁሉንም ምሬት ከልቤ አወጣው” ብላለች፤ አንድ ታዋቂ ጸሐፊ ተውኔት አብዱል-ባሃ ያለበት ክፍል ገብቶ ሲወጣ ስለቆይታው ሲመሰክር “በአምላክ ፊት ነበርኩ መሰለኝ!” ብሏል፡፡ በወቅቱ የአሜሪካ ግምጃ ቤት ሃላፊ የነበረው ከአብዱል-ባሃ ጋር ከተገናኘ በኋላ ልምዱን ለመግለፅ ቃላት ሲፈልግ “በታላቁ ነቢይ - ኢሳይያስ - ኤልያስ ፊት ያለሁ ያህል ሆኖ የተሰማኝ መሰለኝ ነገር ግን አይደለም፤ ክርስቶስ ዘንድ ያለሁም ሆኖ ተሰማኝ፣ ሆኖም ግን አይደለም፡፡ የተሰማኝ በመለኮታዊ አባቴ ፊት እንዳለሁ ነበር፡፡”

***

‘የቱርክ አምባሳደር ዚያ ፓሻ ፣ ሙሐመዳን የሚባል የእስልምና ቅርንጫፍ ጽኑ አማኝ ሲሆን ስለባሃኡላህ መምጣት ሲነገረው ተሳልቆ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ አብዱል-

ባሃ በዋሽንግተን እያለ ዚያ ፓሻ በክቡር አሊ-ኩሊ ካን አማካይነት የፋርስ ኤምባሲ ተጋብዞ አብዱል-ባሃን አገኘው፡፡ በዚህ እራት ግብዣ ላይ ተነስቶ አብዱል-ባሃን እንባ እየተናነቀው “ክብርና ፍጹምነትን በመካከላችን ሊያሰራጭ የመጣው የዘመኑ ብርሃን” ብሎታል፡፡

***

ሰዓሊዋ ጁሊየት ቶምፕሰን እሱን ያየችበትን ጥርት ያለ የቃላት ምስሎችን ስትገልጽ፡- አብዱል-ባሃ፣ እረፍት በሌለው፣ ውስብስብ በሆነው፣ በብልጭልጩ እና በጥርጣሬ በተሞላው በምዕራቡ ዓለም ውስጥ በተረጋጋ ኃይሉ፣ በከበረው እና በደማቅ ውበቱ፤ በዚህ ሁሉ የእኛ አለመጎልበት ውስጥ የእሱ ሙሉነት በኃያልነት ይታያል፡፡

ያ የበራ ውበት ያ ክብር፣ የዚህ ዓለም ክብር አይደለም፤ በሰው መካከል ንጉሥ ሆኖ የሚያመለክተው ያ የመንፈስ ልዕልና ሳይደመጥ አልቀረም፤ ባለፈበት ሁሉ ዓይኖች ይከተሉት ነበር፣ ሕዝቡም ሳይጠየቅ አክብሮቱን ቆም በማለት ይገልጽ ነበር ፡፡

***

ሌቦች እንኳን ሳይቀሩ በአብዱል-ባሃ መስህብ ተጽዕኖ አድሮባቸው ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በ1919 ሚስተር አቭሮን የተባለ ምዕራባዊ ምዕመን ለመንፈሳዊ ጉብኝት ሄዶ ነበር፡፡ አንደኛው የዓለም ጦርነት ከቆመ በኋላ እንዲመጡ ከተጋበዙት የመጀመሪያው መንፈሳዊ ጎብኚ ቡድን ውስጥ አንዱ ነበር፤ ከቴህራን ጀምረው የተጓዙት ጉዞ በባቡር እና በጀልባ በመጨረሻም በሠረገላ ሲሆን ሦስት ወር ወሰደባቸው፡፡ ኢስታንቡል ሲደርሱ ባሃኢዎቹ ለአብዱል-

ባሃ የሚሰጥ የብር ጌጣጌጦች ሰጧቸው፣ ሆኖም ግን አካ ሲደርሱ ሻንጣዎቻቸውን ሁሉ ቀድደው ብዙ ነገሮችን ወሰዱባቸው። የብር ጌጣጌጡን ሊወስዱ ሲሉ ሚስተር አቭሮን "እሱ የአብዱል-ባሃ ነው" አላቸው። ድንገት ሌቦቹ ዝም አሉ፤ አብዱል-ባሃማ ያለብሰናል፣ ያበላናል፣ ያኖረናል አሉ። ከዚያም የብር ጌጣጌጦቹን መለሱላቸው።

***

አንድ ተመራማሪ ዕጹብ ድንቅ አስተማሪ ከሆነው ከአብዱል-ባሃ ጋር ከተገናኘ በኋላ ሕይወቱ እንዴት እንደተለወጠ የሚያሳይ ግልጽና ውድ ታሪክ በሃዋርድ ኮልቢ አይቨስ ብዕር በኩል የደረሰን የነፃነት በር Portals to Freed የሚለው መጽሐፍ ነው። ኮልቢ አይቨስ 46 ዓመት ዕድሜ ያለው የዩኒታሪያን ክርስትና እምነት ፓስተር ሲሆን ደስታ ማጣት የሚመጣው ነፍስ አምላክን ስትሸሽ ነው ይላል። እየሱስንና ትምህርቶቹን ይወዳል። ሆኖም ግን እውነተኛ ክርስቲያኖች ጥቂት ሆኑበት። ምንም እንኳን ፓስተር ቢሆንም ደሞዙም ጥሩ ቢሆንም፣ ነገሮች ግን ሊያረኩት አልቻሉም። አንድ ቀን "የእያንዳንዱ ሰው መጽሔት" በሚለው እትም ውስጥ ስለ አብዱል-ባሃ ተጽፎ አገኘ ጽሑፉ የሚለው፦ ታላቅ እውነትን ያገኘ ሰው! የድንቆች ድንቅ! የአምላክ ሥራ ሲሰራ ገንዘብ የማይሰበስብ ይላል። አይቨስ ለሰው ልጆች አገልግሎት ለመስጠት ስለሚጓጓ በዩኒታሪያን ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመስበክ በተጨማሪ በከተማው ሌላ ቦታ ውስጥ የወንድማማችነት ቤተ-ክርስቲያንን መሥርቷል። በቤተ-ክርስቲያኑ የአስተዳዳሪዎች ቦርድ ውስጥም አንድ በጣም የተወደደ፣ ትሁት እና መልካም የሆነ ሰው ነበር። ይህ መልካም ሰው በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ከባሃኢዎች ጋር

እንዲገናኝ አደረገው፡፡ ሚስተር አይቭስ ለባሃኢ ስብሰባ ግብዣ ሲደርሰው ለጓደኛው ሲል መመርመር እንዳለበት ተሰማው፡፡ ወደ ስብሰባው ሄደ የተሰማው ስሜት ግን ሌላ ነበር፤ በስብሰባው ላይ ከተለመደው ሃይማኖታዊ ወጥመዶች ይልቅ የማይቋቋም ኃያል መንፈስን አገኘ፡፡ ከእነዚህ ከባሃኢ ተናጋሪዎቹ መካከል አንዱን ወደ ወንድማማችነት ቤተክርስቲያኑ መጋበዝ እንዳለበት ተሰማው እናም አደረገው፡፡ ሦስት ድንቅ የሆኑ ወራቶችን አሳለፈ፡፡ የበለጠ ደግሞ ያነቃቃው የባሃኡላህ ሰባቱ ሸለቆዎች የሚለው መጽሐፍ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ ወደ አሜሪካ ሲመጣ ብቻውን ያለ አስተርጓሚ ከእርሱ ጋር ቃለ-ምልልስ ማድረግ ፈለገ፡፡ በሚገረም ሁኔታም ተሳካለት፡፡ ሲገናኙ በጸጥታ ተቀመጠ፣ አብዱል-ባሃ ይመለከተው ጀመር ከዚህ በፊት ማንም ሰው እንዲህ ዓይቶት አስተውሎት አያውቅም ነበር ፡፡ የነፍስ ግንኙነት ነበር ያደረጉት፣ ጥልቅ በሆነ መግባባትና ከልብ የመነጨ ፍቅር፤ አይቭስ በእንባ ተጠመቀ፡፡ አብዱል-ባሃም እንባውን ፍቅር በተሞላው ሁኔታ ጠረገለት፡፡ ሰው ሁሌም ደስተኛ መሆን አለበት አለና ከልቡ ሳቀ፡፡ ከዛ ቀን በኋላ የአይቭስ ሕይወት ልዩ ሆነ፡፡

ታሪኩን ወደኋላ እንመልሰውና አብዱል-ባሃ አሜሪካን አገር እ.ኤ.አ በ1912 ከመጣ ከሳምንት በኋላ፣ አይቭስ አብዱል-ባሃን ልክ ንብ አበባ ወዳለበት እንደምትሂዛር ሁሉ ይከተለው ጀመር፡፡ ከጊዜ በኋላ ያንን ሁኔታ ሲያስበው፣ አብዱል-ባሃ በመለኮታዊ ጥበብ የተሞላው ይህንን መግነጢሳዊ ስብዕናውን ሲያሳይ የነበረው ግርማ አስደንቆት ነበር፡፡ በሚያበራው ስብዕናውና ሁልጊዜም ወሰን በሌለው ፍቅሩ “ወደ ከፍተኛው ኑ” ወደሚለው ለመቅረብ ይገፋፋል፡፡ አንድ ቀን ምሽት ላይ ወደ አብዱል-

ባሃ ክፍል አመራ፣ በጣም መሸቶ ነበር፣ በሩን አንኳኳ። አብዱል-ባሃ እራሱ በሩን ከፈተ። አይቨስ "እባክህን ከእኔ ጋር አብረን ፀሎት እናድርግ" ሲል ጠየቀ፣ ከዚያም "ክፍሉ ገባሁ ተንበረከኩ እጁን እራሴ ላይ ጫነና በፋርሲኛ ፀሎት አዜመ። ፀሎቱ ሦስት ደቂቃ ያህል ፈጀ፣ ሆኖም ግን እነዚያ ደቂቃዎች የሰጡኝ ሰላም ከዚህ በፊት የማላውቀው ዓይነት ነበር።"

አይቨስ አስተዋይና ቶሎ የሚገነዘብ ሰው ነበር። አብዱል-ባሃ የአሜሪካን አገር ቆይታውን ጨርሶ እ.ኤ.አ በ1912 ለመመለስ መርከብ ሲሳፈር አይቨስ ከሸኚዎች መካከል አንዱ ነበር። ሕይወቱን ሙሉ የአብዱል-ባሃ ተከታይ ሆነ። እምነቱን ስለመቀየር ያሰበ ጊዜ አብዱል-ባሃ በተደጋጋሚ "ይህ ቀን የታላላቅ ነገሮች ቀን ነው" ሲለው ተሰማው። ብዙም ሳይቆይ ፓስተርነቱንና የከፈተውን ቤተ-ክርስቲያን ትቶ ባሃኢ ሆነ። ከዚያም አንድ ቀን በእርሱ እና ባለቤቱ ማቤል ትልቅ ውሳኔ አደረጉ ። ሚስቱ ያን ዕቅዳቸውን ከጊዜ በኋላ ስታስታውስ፡- "ዕቅዳችን ብዙ ገንዘብን በፍጥነት ማግኘትና ከዚያም የተቀረውን ሕይወታችንን እራሳችንን ችለን እምነቱን ማሰራጨት ነበር። ይህ ዕቅዳችን ምኞት ብቻ እንደሆነ ተገነዘብን እየተጓዝን የማስተማር እቅዳችን ላይሳካ ሆነ።

ሌላ ነገር ማሰብ ጀመርን፣ ከዚያም እየተጓዙ እቃ የማሻሻጥ ሥራ እንደምንፈልግ አመለከትን ብዙ ምላሽ አገኘን አንዱን መረጥንና ረጅሙን የመንገድ ሕይወት ለመጀመር ተነሳን። ያለንን የቤት እቃ ሁሉ ሸጥን፤ ለሰው የሚሰጠውንም ሰጠን። የሚያስፈልገንን ነገር ብቻ በሁለት ሻንጣ አዘጋጀን። ለመጓዝ የባቡር ትኬት ከገዛን በኋላ የቀረን ገንዘብ 7 ዶላር ብቻ ነበር።

***

አብዱል-ባሃ አሜሪካን የሄደ ጊዜ ፉጂታ የሚባል የሕክምና ትምህርት ተማሪ አሜሪካን አገር ውስጥ ይማር ነበር፡፡ አጭር ስለነበር አብዱል-ባሃ በመንገዳቸው ሲያልፍ ለማየት ዛፍ ላይ ይወጣል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሉቃስ ወንጌል 19፡1-5 ላይ፡- “... እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ ባለጠጋም ነበር፡፡ ኢየሱስንም የትኛው እንደሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ...ያየው ዘንድ... ሮጦ በአንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና፦ ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው፡፡” አብዱል-ባሃም ፉጂታን እንደዋሽንት በሆነ ድምጽ “ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ፡፡” ሲለው በውስጡ ተሰማው፡፡ ፉጂታ ትምህርቱንና ኑሮውን ትቶ አብዱል-ባሃን ለማገልገል አብሮት ወደ ሐይፋ ሄደ፡፡ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ በሐይፋ ሲያገለግል ኖረ፡፡

***

እደ-ሃይማኖት ዶሬቲ ቤከር “እ.ኤ.አ በ1912 በአሥራ አራት ዓመቷ እናቷ አብዱል-ባሃን እንድታይ ይወስዷታል፡፡ በጣም አይናፋር ልጅ ነበረች፣ ትልቅ ሰው ፊት መቆየት ያስቸግራትም ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ የሚናገርበት ክፍል ስትገባ ይሰማት የነበረው ፍራቻ ጥልቅ ነበር፡፡ አብዱል-ባሃ በፈገግታ እያየት ምንም ሳይናገርም በምልክት እርሱ አጠገብ እንድትቀመጥ መቀመጫ አሳያት፡፡ መጀመሪያ ላይ ሊያናግራት መስሏት በጣም ፈርታ ነበር፤ እርሱ ግን ምንም ሳይላት ቆየ፣ እርሷም

ዘና አለች። ያን ቀን ስለ ምን ንግግር እንዳደረገ አታስታውስም፣ እርሷ ግን ባሃኢ ሆና የተወለደችበት ቀን ነበር። ከዚያን ቀን ጀምሮ እራሷን ባሃኢ አድርጋ ቆጠረች። ምንም እንኳን ያን ቀን አብዱል-ባሃን ባታነጋግርም ከዚያ ቀን ጀምሮ የምታስበው እርሱን ነበር፤ ከጊዜ በኋላ እምነቱን ማገልገል እንደምትፈልግ ደብዳቤ ጻፈችለት። እምነቱን በብቃት አገለገለች። ምርጥና ብቃት ያለው ተናጋሪም ሆነች።

***

አብዱል-ባሃ ካረፈ ከአርባ ቀን በኋላ የመታሰቢያ ዝክር ላይ አገረ ገዢው ለተሰበሰቡት እንግዶች ንግግር ሲያደርግ "ብዙዎቻችን እዚህ የተሰበሰብነው አብዱል-ባሃ በግርማ ሞገሱ ተሞልቶ በከተማችን መንገዶች ላይ ሲሄድ ፣ ግብረ -ገብነትና ቁጥብነት የተሞላው ምግባሩን፣ ሩህሩህነቱን፣ አፍቃሪነቱን፣ ለጋስነቱን፣ ድሆችንና የተቸገሩትን መንከባከቡን በደንብ እናውቃለን። በጣም ገራገርና ቀላል (simple) ስለሆነ መኖሩም ይዘነጋል፣ በጣም ታላቅ አስተማሪም ነበር፣ ጽሑፎቹና ንግግሮቹ በምስራቅም ሆነ በምዕራብ ለሚኖሩ በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች መጽናኛና መነቃቂያ ሆኗል።"

***

ሴትየዋም ሙሉነት ተሰማት። ግር የሚላትና እርካታ የሚያሳጣት በሙሉ ጠፋ። ሙሉ ቀን በመለኮታዊ ምስጢር ሁኔታ ስትጥለቀለቅና ስትደሰት ትውላለች። በእንዲህ ያለ መንፈሳዊ ሁኔታ የምትዋጥ ከሆነ ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ወደ ተግባር እደሚቀየርና ቀንዋና ማታዋም ወደ ብርሃን እንደሚቀየር ተገነዘበች።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለተሰጣት መንፈሳዊ ቡራኬ ዘንግታ አታውቅም። መንፈሳዊ ሕይወትን እየተገነዘበች መጣች።